አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ስርዓቶች

በ

ሞገስ ጀንበር

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ
የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች
ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

አማካሪ:- ሰላማዊት መካ /ረ/ፕሮፌሰር/

ሰኔ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና አምልኳዊ ስርዓቶች

በ

ሞገስ ጀንበር

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች

ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ

ፊርማ

የውስጥ ፈታኝ

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቤ.ጥ.ተ.
ቤተ መጻሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

## ማውጫ

ገፅ

ምስጋና ....... i
የአማራ ክልል እና ጥናቱ ትኩረት ያደረገበት አካባቢ ልዩ ልዩ ካርታዎች ....... ii
አጠቃሎ ....... v
1 መግቢያ ....... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ....... 2
1.2 የጥናቱ ዓላማ ....... 4
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ....... 5
1.4 የጥናቱ ወሰን ....... 6
1.5 የመረጃ አሰባሰብ እና አተናተን ዘዴ ....... 6
1.5.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ....... 6
1.5.2 የመረጃ አተናተን ዘዴ ....... 9
1.6 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....... 10
1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ....... 10
2. ክለሳ ድርሳን ....... 12
2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ....... 12
2.1.1 ሀገረሰባዊ ልማድ/Social Folk Custom/ ....... 12
2.1.2 እምነቶች /Beliefs/ ....... 16
2.1.3 ስርዓቶች /Rituals/ ....... 18
2.1.4 ተረኮች/Narratives/ ....... 20
2.1.5 ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ /functional Approach/ ....... 22
2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....... 26
2.2.1 በክፍለ ትምህርቱ የተሰሩ ጥናቶች ቅኝት ....... 26
2.2.2 ከክፍለ ትምህርቱ ውጭ የተሰሩ ጥናቶች ቅኝት ....... 28
3. የገዳም ህይወት አጀማመር እና በጣና ሐይቅ ደሴቶች ውስጥ የሚገኙ ....... 32
ገዳማት ....... 32
3.1 በኢትዮጵያ የገዳም ህይወት አጀማመር እና የገዳም ኑሮ አይነቶች ....... 32
3.2 ጥናቱ በተካሄደበት በጣና ሐይቅ ደሴቶች ውስጥ የሚገኙ ገዳማት ....... 37
3.3 የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ....... 44
4. ከዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው ....... 54
የሚነገሩ ተረኮች ትንተና ....... 54
4.1 ቅድመ ገዳም ተረክ ....... 54
4.2 ለዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መመሥረት እንደምክንያት የሚጠቀሱ ....... 62

ጉዳዮች ........ 62
4.2.1 ለመስራቹ ከኢየሩሳሌም ታቦት መምጣት ........ 62
4.2.2 ለመስራቹ ገዳሙን በርስትነት መቀበል ........ 66
4.3 የዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም ቅድስና ........ 67
4.3.1 የገነት ነፋስ የሚነፍስበት ገዳም መሆኑ ........ 68
4.3.2 ተፈጥሯዊ አቀማመጡ ትዕምርታዊነት ያለው መሆኑ ........ 70
4.3.3 የተሰወረ የመድኃኔዓለም ኃይል ስለመኖሩ ........ 73
4.3.4 ጠላትን የመደምሰሻ ሀይል የሚገለጽበት መሆኑ ........ 74
4.3.5 አጽሞች ለማረፊያነት የሚመርጡት ቦታ መሆኑ ........ 76
4.3.6 ከአጽሞች ትሩፋት የሚያገኝ ገዳም መሆኑ ........ 85
4.4 ገዳሙን መልሶ ከማጠናከር እንቅስቃሴ ጋር የሚነገሩ ተረኮች ........ 88
5. የገዳሙ አምልኳዊ ስርአቶች/Sacred Rituals/ ........ 92
5.1 በማህበር የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ........ 92
5.1.1 በጸሎተ ማዕድ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ........ 92
5.1.2 በተግባር ቤት የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ........ 100
5.1.3 በምርጫ ስዩማን የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ........ 106
5.1.3.1 በአበምኔት ምርጫ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ........ 107
5.1.3.2 በስድስቱ ስዩማን ምርጫ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ........ 112
5.1.4. ጥፋትን በማረም /ኃጢአትን በማንጻት/ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ........ 115
5.2 በግል የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ........ 118
5.2.1 አቃቤ ሰዓትና ስውሩ መድኃኔዓለም በተባሉት ስፍራዎች የሚከወኑ አምልኳዊ ........ 118
ስርዓቶች ........ 118
5.2.2. በጻድቃን ማረፊያ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ........ 120
5.2.3 በአርምሞ /በጽሞና/ የሚከወን አምልኳዊ ስርዓት ........ 123
6.ማጠቃለያ ........ 128
ዋቢ ጽሑፎች ........ 132
አባሪዎች ........ i
1.በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም የተሰበሰቡ የቶፎ ግራፍ መረጃዎች ........ i
2.የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ........ vii
3.ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች ........ viii

# ምስጋና

በቅድሚያ ይህ ጥናት አሁን ከደረሰበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ ያላቸውን ጊዜ ሁሉ ተጠቅመው ጥናታዊ ጽሁፉን በማረም፣ ለዚህ ጥናት ተገቢነት ያላቸውን መጻሕፍት በማዋስና የውጭ ባለሙያ ጋብዘው የሌክቸር ሰዓት በማመቻቸት ያልተገደበ ሙያዊ እገዛቸውንና ምክራቸውን ለሰጡኝ አማካሪዬ ለወ/ሮ ሰላማዊት መካ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለዚህ ጥናት መሳካት የቃልም ይሁን የጽሑፍ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ በዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ለሚገኙ መናንያን እግዚአብሔር ብድራችሁን ይክፈላችሁ እላለሁ። ይህንን ጥናት ማካሄድ እንድችል የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው። ግማሽ ቀን እየሰራሁ እንድማር ለፈቀደልኝ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት እና ለስራ ባልደረቦቼ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ይህንን ጥናት ከማድረጌ በፊት ሰፊ ጊዜያችሁን ሰጥታችሁ ስለጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ላወያያችሁኝ ለወንድም ገብርኤልና ለዲያቆን አሸናፊ እግዚአብሔር ብድራችሁን ይክፈላችሁ እላለሁ። የጽሑፍ ስራውን በፍቅርና በትጋት ለጻፍሽልኝ ሰላማዊት ደግፌ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረስሽ። በደንብ ሳንቀራረብ ግን በሙሉ እምነት ጭኔ ኮምፒውተርሽን ላዋስሽኝ ሰናይት ኃይሉ የምታምኘው ሁሌም ይታመንሽ እላለሁ። ይህንን ትምህርት ጀምሬ እስካጠናቅቅ ድረስ በሀሳብም በሞራልም ለደገፋችሁኝ ቤተሰቦቼ እናቴ እማሆይ ባዘቶ ለገሰና እህቶቼ ውድነሽ፣ ሻሸቱ፣ ባንቺ ከነቤተሰቦቻችሁ ከልብ አመሰግናችኋለሁ። ጓደኞቼ ሰለሞን አለም፣ ጌታቸው ተስፋ፣ ደጀን ጫካ፣ ፋሲካ ይገዙና ፋሲካ መለሰ ድጋፋችሁ ስላልተለየኝ አምላክ ሃሳባችሁን ይሙላላችሁ።

## የአማራ ክልል እና ጥናቱ ትኩረት ያደረገበት አካባቢ ልዩ ልዩ ካርታዎች




BAHIR DAR ZURIYA WEREDA MAP
Gonder Zuria
N
Lake Tana
Deq
Alafa
S.Gonder
Bahir Dar Liyu
Bahir Dar Zuriya
Legend
Town
Lake
Wereda
Source: CSA, Cartography & GIS Directorate
www.csa.gov.et
June 2011
0 5 10 20 Km
1:500,000


DEQ KEBELE MAP
N
Kota Mariyam
M/Alme
Nariga Silase
K/Mihiret
Arisema Mariyam
Jega Yohanis
Giyorigis
Dega Estifanos
Legend
Church With Cemetery
Kebele Boundary
0
1
2
4 Km
1:60,000
Source: CSA, Cartography & GIS Directorate
www.csa.gov.et
june 2011

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በህገረሰባዊ ልማድ /Social Folk Custom/ ስር እንደሚካተት በሚገለፀው ሐይማኖታዊ ፎክሎር ላይ የተመሰረተ ቢሆንም የጥናቱ ማዕከላዊ ጉዳይ ግን በእምነትና እምነታዊ ድርጊት ላይ ይሆናል። ይህንን ማዕከላዊ ጽንሰ ሀሳብ አጉልተው ሊያሳዩ በሚችሉ ተረኮች/Narritives/ እና አምልኳዊ ስርዓቶች /Sacred Rituals/ ላይ ይመሰረታል። በመሆኑም የጥናቱ ትኩረት የሆኑት የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ገዳማውያን በተረኮቻቸውና በስርዓቶቻቸው የሚያንጸባርቁት እምነትና እምነታዊ ድርጊት ለገዳማዊ ህይወታቸው ያለውን አገልግሎት/Function/ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል። በጥናቱ ከተለያዩ አብያተመጻህፍት የሚገኙ መረጃዎችን ከመሰብሰብ ጀምሮ ተረኮችንና የሚከወኑ ስርዓቶችን በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል። መረጃዎችም በመቅረፀ ድምጽ፣ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ እንዲሁም በእጅ ማስታወሻ ተይዘዋል። አጥኝው ገላጭ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል።

በጥናቱ እንደታየው በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ውስጥ የሚተረኩት ቅድመ ገዳም ተረኮቹ በሀገሪቱ ክርስትና መሰበክ ከጀመረበት ከ4ኛው ክፍለ ዘምን ጀምሮ ቤተክርስቲያን የተመሰረተበት ደሴት መሆኑን እና ክርስትናና የክርስትና ህይወት የገጠመውን ተግዳሮት የሚያሳዩ ናቸው። ክርስትናን ላልተቀበሉት የክርስትና እምነትን ለማዳረስና ክርስትናን ለተቀበሉት ደግሞ በክርስትና ህይወታቸው ጠንክረው እንዲወጡ ገዳማውያን ሰፊ የሆነ ሀላፊነት እንደነበረባቸው እና አሁንም እንዳለባቸው የሚያሳዩ ተረኮች ናቸው። ይህ ገዳም ፈጣሪ ለመስራቹ ከኢየሩሳሌም በህቡእን/ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚታዩ ስውራን ሰዎች ናቸው/ አማካይነት ታቦት በመላክና ገዳሙ ለመስራቹ የዘላለም ርስት መሆኑን ቃል ኪዳን በመስጠት በፈጣሪ እቅድ የተመሰረተ ገዳም መሆኑን ያምናሉ። እነዚህ ተረኮች ለገዳማውያን የዚህን ገዳም የት መጣነት በሚገባ አደላድለው ከገለጹ በኋላ ገዳማዊ ህይወትን የመትከልና የማጠናከር ተግባር አላቸው።

ዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም በፈጣሪ እቅድ እንደተመሰረተና የተቀደሰ ገዳም እንደሆነ ይታመናል። ለዚህም እንደማሳያ የሚጠቀሱት ተረኮች በገዳሙ ውስጥ እሁድ እሁድ ከሰዓት በኋላ የገነት ነፋስ የሚነፍስበት መሆኑን፤ የደሴቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ የመስቀል፣ የኖህ መርከብና የመሶበ ወርቅ ቅርጽ ያለው መሆኑን፤ የተሰወረ የመድኃኒዓለም ኃይል አለበት መባሉን፤ በገዳሙ ጠላቶች ላይ ጥቃት የሚያደርስ የቅዱሳኑ እርዳታ አለ ተብሎ መታመኑን፤

አጽሞች ቅድስናውን የሚመሰክሩለትና በረከት የሚያፈሱበት ገዳም ነው የሚል እምነት ያለ መሆኑን የሚያሳዩ ተረኮች ናቸው። የተቋረጠው የገዳም ህይወት በፈጣሪ እርዳታ እንደገና ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንደተደረገ የሚያሳዩ ተረኮች አሉ። እነዚህ ተረኮች የገዳማውያኑን ገዳማዊ ህይወት የመትከልና የማጽናት ተግባር አላቸው።

በገዳሙ ውስጥ በማህበር ከሚፈጸሙ ስርዓቶች መካከል የጸሎተ ማዕድ ስርዓት በገዳማውያን ላይ መንፈሳዊ ድባብን በማስረጽ የገዳሙን አጠቃላይ ማህበራዊ ህይወት/አንድነት/ የመምራት ተግባር አለው። የገዳሙም ተግባር ቤት ከሚፈፀምበት ጥብቅ አምልኳዊ ስርዓት አኳያ ፍትሀዊ የሐብት ክፍፍል/አጠቃቀም/ ያለ መሆኑን የማስረጽ ሙያ አለው። የገዳሙ የስዩማን ምርጫ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የሚከናወን እንደሆነ መታመኑ የስልጣን ሽኩቻን በማስወገድ ገዳማዊ ህይወትን የመጠበቅ ሙያ አለው። በገዳሙ የሚፈጸመው ጥፋተኛን የመቅጣት ስርዓት ጥፋትን ከማረም ጎን ለጎን ሐጢአትን በማንጻት ገዳማውያንን ወደ ተገቢው ስነምግባር የመመለስ ተግባር አለው። ቅዱስ እንደሆኑ በሚነገርላቸው በተወሰኑ ስፍራዎች አምልኳዊ ስርዓቶች/Sacred Rituals/ በመፈፀም ይገኛል ተብሎ የሚታመነው እምነት ገዳማዊ ህይወትን የመጠበቅ /የማፅናት/ ተግባር አለው።

## 1 መግቢያ

ይህ ጥናት በስድስት ምዕራፎች የተደራጀ ነው። በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱን አጠቃላይ አቅጣጫ የሚያስተዋውቁ ሰባት ንዑሳን ርዕሶች ተካትተዋል። እነዚህም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ መረጃ የመሰብሰቢያና የመተንተኛ ዘዴ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት እና ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ናቸው። በጥናቱ ዳራ ስር ይህ ጥናት ከየትኞቹ ጥናቶች የቀጠለ እንደሆነ አጠር ያለ ዳሰሳ ቀርቦበታል።

በምዕራፍ ሁለት ደግሞ የገዳም ህይወት አጀማመርና ይህ ጥናት ትኩረት ባደረገበት በጣና ሐይቅ አካባቢ ስላሉ ገዳማት ዳሰሳ ቀርቦበታል። በመሆኑም በቅድሚያ በኢትዮጵያ የገዳም ህይወት አጀማመር፣ በጣና ሐይቅ ደሴቶች ላይ ስላሉ ገዳማት አመሰራረትና የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ታሪካዊ ዳራ ምን እንደሚመስል አጠር ያሉ መግለጫዎች የቀረቡበት ምዕራፍ ነው። በምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ክለሳ ድርሳን ቅኝት ተደርጎበታል። በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያው ክፍል ስለአገረሰባዊ ልማድ/Social Folk Custom/፣ ስለሀይማኖታዊ ፎክሎር /Religious Folklore/፣ ስለእምነቶች/Beliefs/፣ ስለስርአቶች/Rituals/ እና ስለሀይማኖታዊ ተረኮች /Religious Narratives/ ምንነት ማጣቀሻ መጻህፍትን መሰረት በማድረግ ገለፃ የተደረገበት ነው። በመቀጠልም ይህንን ጥናት ለመተንተን የሚመሰረትበት ንድፈ ሀሳብ/Theory/ ምን እንደሚመስል በማሳየት ይሄ ክፍል ይጠናቀቃል። በዚሁ ምዕራፍ ሁለተኛው ክፍል ላይ ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናቶች ተቃኝተው ተካተዋል።

አራተኛው ምዕራፍ ከዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮች ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ነው። ትኩረት የተደረገው ከቅድመ ገዳሙ ተረክ ጋር፣ ከገዳሙ የመመስረቻ ምክንያት፣ ከገዳሙ ቅድስና፣ የተቋረጠውን ገዳማዊ ህይወት እንደገና ከማጠናከር ጋር ተያይዘው በሚተረኩት ተረኮች ላይ ነው። በተጠቀሱት ርዕሶች ስር የሚካተቱትን ተረኮች አቅርቦ በመተንተን እነዚህ ተረኮች ለገዳማውያኑ ገዳማዊ ህይወት ያላቸውን ፋይዳ ለማሳየት ተሞክሯል።

ምዕራፍ አምስት ደግሞ የገዳሙ አምልኳዊ ስርአቶች ትንተና የሚል ርዕስ አለው። በዚህ ምዕራፍ ስር ትንተና የቀረበባቸው ይዘቶች በሁለት ተከፍለው ቀርበዋል። በመጀመሪያው ክፍል በማህበር የሚከናወኑ አምልኳዊ ስርአቶች በሚል ርዕስ ሥር ፀሎተ ማዕድ፣ ተግባር ቤት፣ ምርጫ ስዩማን፣ ጥፋተኛን ማረም ወይም ሐጢአትን ማንጻት፣ የተሰኙት ገዳዮች

ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። በሁለተኛው ክፍል ደግሞ በግል የሚከወኑ አምልኳዊ ስርአቶች በሚል ርዕሰ ጉዳይ ስር የፃድቃን ማረፊያ፣ አቃቤ ሰዓት እና ፀጥታ /አርምሞ/፣ በተሰኙ ንዑሳን ርዕሶች የተካተቱን ይዘቶች መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቷል።

በመጨረሻም በምዕራፍ ስድስት የጥናቱ ማጠቃለያ ሃሳብ ቀርቦበታል። ከዚህ ቀጥሎ ዋቢ መጻሕፍትና የተለያዩ አባሪዎች ተካተዋል።

## 1.1 *የጥናቱ ዳራ*

የኢትዮጵያ ስነቃል ስብሰባና ጥናት እንደሌሎች የአፍሪካ ሃገራት ዘግይቶ የተጀመረ ዘርፍ ነው። ፈቃደ ሥነቃልን ሰብስቦ ማሳተም የተጀመረው በአውሮፓውያን ምሁራን አማካይነት እ.ኤ.አ በ1890ዎቹ ዓመታት አካባቢ እንደሆነ ገልፆ እነዚህ አውሮፓውያን በኢትዮጵያውያን ረዳትነት ስነቃሎችን በመሰብሰብና በተወሰነ ደረጃም በማጥናት በየሀገራቸው ቋንቋዎች (ጀርመንኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ፈረንሳይኛ) አሳትመዋል ብሏል። ከእነዚህ የአውሮፓ ተመራማሪዎች መካከል ኢግናትሲዮ ጉዪዲ፣ ካርል ዊንኪስት፣ ጃኮብ ፌይትሎቪች፣ ኤንሪኮ ቼሩሊ፣ ማርሴል ኮኽን፣ ማርቲኖ ሞሬኖ፣ ሊዊጅ ፋዜላ፣ ማርሴል ግሪያቭል እና ኢኖ ሊትማን በዋናነት ተጠቃሾች ናቸው(1996፣ 56፤1991፣ 42)። በርግጥ እነዚህ ስብስቦችና ጥናቶች ከተሰበሰቡበት ዘመን የሚመነጩ ክፍተቶች ሊኖሩባቸው ቢችሉም ለቀጣዮቹ ጥናቶች በር ከፋች መሆናቸው አይካድም።

እነዚህን የአውሮፓ ተመራማሪዎች ተከትለው ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ፎክሎሮችን በተለይ ሥነቃሎችን መሰብሰብና ማጥናት ጀምረዋል። ከእነዚህም ውስጥ የአፈወርቅ ገብረ ኢየሱስና የኅሩይ ወልደሥላሴ ስብስብና ጥናት በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ሲሆን እነዚህም ሥራዎች ለሕትመት በቅተዋል። ከእነዚህ ሌላም እነ ሃጂ የሱፍ ፣ ማህተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ አበበ አይቼህ፣ መንግሥቱ ለማ፣ ጃለታ ጃፋሮ እና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ ስነቃል ጥናትና ስብሰባ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ናቸው(ፈቃደ፣ 1996፣ 57፣ 1991፣ 41)። እነዚህ ስብስቦችና ጥናቶች ምንም እንኳ በባለሙያ ያልተሠሩ ቢሆንም ቋንቋውንና ባህሉን በሚገባ በሚያውቁት ኢትዮጵያውያን የተሰበሰቡና የተጠኑ በመሆናቸው ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው አይካድም።

በኢትዮጵያ የፎክሎር ጥናትና ስብስብ ታሪክ ላይ ከአውሮፓውያንና ፈቃደ «አማተር ኢትዮጵያውያን» ከሚላቸው ባለሙያዎች በኋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ

ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ተማሪዎችና የክፍሉ አባላት የማይናቅ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ይገልፃል። ከዚህ ሌላም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ የሥነ ቃል ጥናትና ምርምር ቡድንና የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለዚህ የጥናት ዘርፍ በተወሰነ ደረጃ የየራሳቸውን ድርሻ አበርክተዋል። እነዚህ ስብስቦችና ጥናቶች ቀደም ሲል ከነበሩት በተሻለ ሁኔታ ለጥናትና ምርምር ትኩረት ነበራቸው። እነዚህ የጥናት መረጃዎች አሁንም ገና በወጉ ያልተተነተኑ ቢሆንም ቀደም ሲል ከነበሩት በተወሰነ መልኩ የተሻለ ሙከራና ጥረት የታየባቸው ናቸው ማለት ይቻላል(ፈ.ቃደ፣ 1996፣60፤ 1991፣43-44)።

ቀደም ያሉት አብዛኛዎቹ ጥናቶችና ስብስቦች ከፎክሎር አራት ዘርፎች ውስጥ በሥነ ቃል ላይ ያተኮሩ ናቸው። EtLi 723 ለተሰኘው ኮርስ ማሟያ የሚሆን በቡድን ጥናት ባደረግንበት ጊዜ ለጥናቱ ከሰበሰብናቸው 91 መጻሕፍት መካከል በፎክሎር ዘውግ/genre/ ሲከፈሉ 91% የሚሆኑት ስነቃል ሲሆኑ የዚህን 55% የሚሆነውን የያዙት ደግሞ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ተረቶች ሆነው አግኝተናቸዋል። በአሁኑ ጊዜም የተወሰነ መሻሻል ቢኖርም እነዚህ ጥናቶችና ስብስቦች በአብዛኛው በስነቃል ዘርፎች ላይ ከመመስረቱ አባዜ ያን ያህል የተላቀቁ አይመስልም።

ቀደም ሲል እንደተጠቀመው የበፊተኞቹ ስብስቦችና ጥናቶች ከፎክሎር ዘርፎች ውስጥ በስነቃል ላይ ከመመስረታቸው ሌላ በስብስቦቻቸው ላይ በቂ የሆነ ትንተና አለማካተታቸው ሌላው መሰረታዊ ክፍተት ነው። በርግጥ የወቅቱ እንቅስቃሴ መልካም ቢሆንም የተሰበሰቡት መረጃዎች በተገቢው መንገድ አለመተንተናቸው ግን ጥናቱን የተሟላ አያደርጉትም። የተሰበሰቡትን መረጃዎች ሙያው በሚጠይቀው መንገድ ተንትኖ ለማሳየት የነበረው ክፍተት አሁንም ሙሉ በሙሉ የተቀረፈ አይመስልም። በተለይ ቀደም ሲል ሲሰበሰቡና ሲጠኑ የነበሩ ሥራዎች በእቅድ ሳይሆን በአጋጣሚ የሚሠሩ መሆናቸው(ፈ.ቃደ 1991፣ 42) አሉታዊ ተጽኖው እዚህ ዘመን ድረስ የቀጠለ አስመስሎታል።

እስካሁን የተሰበሰቡትን መረጃዎች በበቂ ስፋትና ጥልቀት መመርመርና መተንተን ባይቻል እንኳ ከዚህ በኋላ በሚሰሩት ሥራዎች ላይ መረጃ ከመሰብሰብ ባለፈ ትንተና ሊሰጥባቸው ይገባል። ይሄ ጉዳይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ መምህራን ከፍተኛ ጥረት እየተደረገበት ይገኛል። የፎክሎር ዘርፎችን በእኩል ለማጥናት አሁንም የተወሰነ የትኩረት ሚዛናዊነት ችግር ቢኖርም ቀደም ሲል በሥነ ቃል ላይ ብቻ ከተመሰረተው ጥናት በተወሰነ መልኩ ለመላቀቅ ሙከራ እየተደረገ ነው። በተለይ በአሁኑ ወቅት በዲግሪና

በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የፎክሎር ትምህርት እየተስፋፋ በመሆኑ በተገቢ የጥናት ዓላማና የጥናት ስልት መረጃ ለመሰብሰብና ተንትኖ ለማቅረብ ተስፋ ሰጪ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። የእኔ ጥናትም ቀደም ሲል የነበረውን የኢትዮጵያ የፎክሎር ስብሰባና ጥናት ተከትሎ የመጣና በትምህርት ክፍሉ እየተደረገ ያለው ጥረት አካል በመሆኑ የዚህ ዘርፍ ቀጣይ ጥናት ነው ማለት ይቻላል። መረጃዎችን በተገቢው ሁኔታ በመሰብሰብ ትንተና ለማድረግ የሚሞክረው ይሄ ጥናት እየቀጠለ ለመጣው የፎክሎር ጥናት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ።

በክፍል ትምህርቴ ወቅት ፎክሎር በአንድ ማህበረሰብ የኑሮ ስርአት ውስጥ በመዋሃድ የማህበረሰቡ የማንነት አሻራ ሆኖ ስመለከት ይሄ የፎክሎር ጉልበት በሃይማኖቶች ውስጥ ሚዛኑን እንደጠበቀ ይገኝ ይሆን ወይ የሚል ጥያቄ ይፈጥርብኝ ነበር። ይህንንም መርምሮ ለማረጋገጥ ገዳማትና ገዳማውያን ጥሩ ማሳያ ሊሆኑ ይችላሉ የሚለው ሐሳቤ ይህንን ጥናት ለማድረግ ምክንያት ሆኖኛል። የሥነ መለኮትና የታሪክ ተመራማሪዎች ብዙ ጊዜ ገዳማትን ማዕከል አድርገው ጥናትና ምርምር ሲያደርጉ ይታያሉ። የታሪክ ተመራማሪው ስለገዳማት ታሪክ ሲጽፍ ፎክሎርን እንደ መረጃ የሚጠቅስበት አጋጣሚ ሰፊ ቢሆንም የጥናቱ አስኳል ግን የርዕሰ ጉዳዩ ታሪክ ነው። የሥነ መለኮት ተመራማሪውም በገዳማት ውስጥ የሚገኙ ፎክሎራዊ ገጽታዎችን እንደ ግብአትነት የሚጠቀምባቸው ቢሆንም በዋናነት በመንፈሳዊው ጉዳይ ላይ ብቻ ይመሰረታል። ለፎክሎር ባለሙያው ግን በመንፈሳዊው እንቅስቃሴና በታሪኩ ውስጥ ተሰናስለው በሚገኙት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረቱን በማድረግ ለገዳማውያኑ ገዳማዊ ህይወት ፋይዳ አላቸው በሚል ያጠናቸዋል። ይህም ጥናት ይህንን መሠረታዊ አቅጣጫ ተከትሎ በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩት ተረኮችና አምልኳዊ ስርዓቶች ለገዳማዊ ህይወቱ ያላቸውን ተግባር ለመመርመር ይሞክራል።

## *1.2 የጥናቱ ዓላማ*

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ውስጥ ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ተያይዘው በሚነገሩ ተረኮች እና በገዳሙ ውስጥ በሚፈፀሙ አምልኳዊ ስርአቶች የገዳማውያኑ እምነት ምን እንደሚመስል መመርመርና ይህም እምነት ለገዳማዊ ህይወታቸው ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው።

ከዚህ ዋና ዓላማ የወጡ ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

1. የዴጋ እስጢፋኖስን የአንድነት ገዳም በገዳምነት ለመመስረት እንደምክንያት የሚጠቀሱትን ትረካዎች መመርመር፣
2. የገዳሙን ቅድስና አጉልተው የሚያሳዩ ተረኮች ገዳማዊ ሕይወትን ከማጽናት አንፃር ያላቸውን ዋጋ ማሳየት፣
3. በገዳሙ ውስጥ የሚፈፀሙ አምልኳዊ ስርአቶች ለገዳማውያኑ በአንድነት ፀንቶ መኖርና መንፈሳዊ ብርታት ማግኘት ያላቸውን ፋይዳ መተንተን ነው።

እነዚህን ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች ይዞ የተነሳው ይህ ጥናት በጥናቱ መጨረሻ ላይ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

1. በዴጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ውስጥ ከሚሰጠው መንፈሳዊ ትምህርት በበለጠ ተረኮችና አምልኳዊ ስርአቶች ገዳማዊ ሕይወትን ሊያፀኑ ይችላሉ?
2. በዴጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ የሚኖሩ ገዳማውያን ከብዙ መንፈሳዊና ስጋዊ ፈተናዎች ተጋድሎ በኋላ በገዳማዊ ሕይወታቸው በመጨረሻ የሚደርሱበት የቅድስና ደረጃ ምንድን ነው?
3. ለገዳማውያኑ የመንፈሳዊ ጸጋ ምንጭ የሆኑ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
4. የዴጋ እስጢፋኖስ ገዳም የተቀደሰና የረጅም ዘመን የታሪክ ባለቤት እንደሆነ ማመን ለገዳማውያኑ ገዳማዊ ህይወት ያለው ረብ ምንድን ነው?

## *1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ*

1. በተለያዩ ሃይማኖቶች ውስጥ የተለያዩ አምልኳዊ ስርአቶች ተደጋግመው በመከወናቸውና ልዩ ልዩ ተረኮች ተደጋግመው በመነገራቸው ምክንያት እንደ አስተምህሮ/Doctrine/ የሚቆጠሩበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል መገመት ይቻላል። ይሄ ጥናት በሃይማኖታዊ ፎክሎሮች ላይ ትኩረቱን የሚያደርግ በመሆኑ ፎክሎር በሐይማኖቱ አስተምህሮ ላይ ያለውን ተጽእኖ ለማጥናት ለሚሞክር የስነ መለኮት ተመራማሪ በተወሰነ ደረጃ ጠቀሜታ ይኖረዋል።
2. በሀገራችን በሃይማኖታዊ ፎክሎሮች ላይ ትኩረት በማድረግ ማጥናት በተወሰነ ደረጃ እየተለመደ የመጣ ቢሆንም ይሄ ርዕሰ ጉዳይ አሁንም ገና በስፋት ያልተጠና በመሆኑ ይሄ ጥናት መደረጉ ለአንባቢ ተጨማሪ ግንዛቤ ይፈጥራል።

3. ይሄ ጥናት በሌሎች ገዳማት የሚታዩትን ሃይማኖታዊ ፎክሎሮች ለማጥናት እንደ አነሳሽ ምክንያት ሆኖ ያገለግላል።
4. የገዳሙንና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ላለው ጉዳይ ታሪክ ለመፃፍ ለሚነሳ የታሪክ ተመራማሪ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል።

## *1.4 የጥናቱ ወሰን*

በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት በጣም ሐይቅ ዙርያ ከሰባት በላይ ገዳማት ይገኛሉ። ይህ ጥናት ትኩረቱን የሚያደርገው በዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም ላይ ይሆናል። ጥናቱ በገዳሙ አመሰራረት፣ ለመመስረቱ እንደምክንያት በሚጠቀሱ ጉዳዮች እና ከገዳሙ ቅድስና ጋር ተያይዘው በሚተረኩ ተረኮች ላይ ትኩረቱን ያደርጋል። በተጨማሪም ጥናቱ በገዳሙ ውስጥ የሚከናወኑ አምልኳዊ ስርአቶች ለገዳማዊ ህይወት ካላቸው ፋይዳ አንጻር ምርመራ ያደርጋል። ከዚህ ውጭ ገዳማውያኑ በእለት ተእለት ህይወታቸው የሚያከናውኗቸውን የስራ፣ የጸሎት፣ የስርዓት ቀብር፣ የምንኩስና እና የአለባበስ ስርአቶችን አይመለከትም። እንዲሁም የገዳሙ ንዋየ ቅድሳት የጥናቱ ትኩረት አይደለም።

## *1.5 የመረጃ አሰባሰብ እና አተናተን ዘዴ*

### 1.5.1 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ለዚህ ጥናት የሚያግዙ መጠይቆችን በማዘጋጅበት ጊዜ የተለያዩ መጻሕፍትና ጥናታዊ ሰነዶችን ለማየት የሞከርሁ ሲሆን በዚህ መስክ እውቀት አላቸው ከሚባሉ ሰዎች ጋር በመወያየት ካገኘሁት ሃሳብ በመነሳት መጠይቆችን አዘጋጅቻለሁ። ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ከገዳሙ የአስተዳደር መዋቅር አኳያ፣ ከመንፈሳዊ ማዕረጋቸው አንጻር፣ በገዳሙ ከነበራቸው ቆይታና ከመንፈሳዊ እውቀታቸው በመነሳት ከሁሉም አይነት መርጦ ለማካተት ተሞክሯል። የመረጃውን ትክክለኛነት ለመመዘንና ለማነጻጸርም ሲባል ለገዳማውያኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች ለሌሎች ሰዎች/ለሀገረ ስብከቱ ሊቃውንት/ ለማቅረብ ተሞክሯል።

የዚህ ጥናት አቢይ ትኩረት በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ውስጥ ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ተያይዘው በሚነገሩ ተረኮችና በገዳሙ ውስጥ በግልም ይሁን በጋራ በሚፈጸሙ አምልኳዊ ስርዓቶች ላይ የገዳማውያኑ እምነት ምን እንደሆነና ይህም እምነት ለገዳማዊ ህይወታቸው ያለው ፋይዳ ምን እንደሆነ መመርመር ነው። በመሆኑም ገዳማውያኑ ስለቅድመ ገዳሙ ሁኔታ ምን አይነት ተረኮች አሏቸው? ለገዳሙ መመስረት እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ ተረኮች

ምንድን ናቸው? ገዳሙን ከሌሎች ገዳሞች የሚለዩት ከቅድስናው ጋር የተያያዙ ተረኮች አሉት? እነዚህን ተረኮች እንዴት ባለ ሁኔታ ይተርኳቸዋል? በተረኮቹ ላይ ያላቸው እምነት ምን ይመስላል? ገዳማውያኑ ምን ምን አይነት አምልኳዊ ስርዓቶች አሏቸው? እነዚህን አምልኳዊ ስርዓቶች በግል፣ በተናጠል ወይስ በሁለቱም መንገዶች ይፈፅሟቸዋል? በእነዚህ አምልኳዊ ስርዓቶች ላይ ያላቸው እምነት ምንድን ነው የሚሉ ጥያቄዎችን ለማንሳት ጥረት ተደርጓል።

ወደገዳሙ ከመሄዴ በፊት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶችን አድርጌአለሁ። በቅድሚያ አዲስ አበባ ከሚገኘው ጠቅላይ ቤተ ክህነት ለባህርዳር ልዩ ዞን ቤተ ክህነት የትብብር ድብዳቤ አስጽፌ ወደ ባህር ዳር ተንቀሳቅሻለሁ። የባህር ዳር ልዩ ዞን ቤተ ክህነትም የትብብር ደብዳቤ ለባህርዳር ዙሪያ ወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በጻፈልኝ መሰረት የወረዳው ጽ/ቤት ለገዳሙ ደብዳቤ አዘጋጅቶልኝ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ወደ ገዳሙ እንዴት መሄድ እንዳለብኝ በመግለጽ አሰናብተውኛል። አጠቃላይ ዝግጅቱን ካጠናቀቅሁ በኋላ ሀሙስ መጋቢት 16 ቀን 2002 ዓ.ም ከባህር ዳር በጀልባ ለሦስት ሰዓት ያህል በመጓዝ ደቅ ደሴት ጉረር ከምትባል የገጠር መንደር ደረስኩ። ይህች መንደር በጣም አነስተኛ ብትሆንም ከባህርዳር ወደደልጊ የሚሄዱት ጀልባዎች እዚች መንደር ሲደርሱ ትንሽ ደምቃ ትታያለች። ደቅ የተባለችው ይህ ደሴት በውስጡ ከሳባት በላይ አድባራትና ገዳማት ይገኙበታል። አብዛኛው የአካባቢው ማህበረሰብም በእርሻና በንግድ የሚተዳደር ነው። የባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሰራተኞች በዚች መንደር የገዳሙ ሱቅ መኖሩን ቀድም ሲል በነገሩኝ መሰረት የተባለችውን ሱቅ አግኝቼ በዚች ሱቅ የሸንኮራ አገዳ ሲሸጡ ላገኘኋቸው መነኩሴ የመጣሁበትን ምክንያት በማስረዳት ወደገዳሙ መሄድ እንደምፈልግ ስገልጽላቸው አባ ገብረ መድህን ከተባሉ መናኝ ጋር አገናኙተውኝ አብረው እንዲወስዱኝ ይነግሯቸዋል። እሳቸውም ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልጸው መንገዳችንን በጋራ ጀመርን።

ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል በእግራችን ከተጓዝን በኋላ ሞፈር ቤት ተብሎ ከሚጠራው የገዳሙ ገበሬዎች ከሚኖሩበት ሰፈር ደረስን። ሞፈር ቤት የሚባለው የሚገኘው በደቅ ደሴት ላይ ነው። የገዳሙ እርሻ እና የእንስሳት እርባታ የሚገኘውም በዚህ ሰፈር ነው። በዚህም ሰፈር መኝታ ተሰጥቶን ካደርን በኋላ ጠዋት የሞፈር ቤቱ መጋቢ ለምን ጉዳይ እንደመጣሁ ጠየቁኝ። የመጣሁበትን ጉዳይ ስነግራቸው ለገዳሙ ሀላፊዎች ጉዳዬን አስርድተው ለመግባት ከተፈቀደኝ በቀጣዩ ቀን በጀልባ እንደሚያደርሱኝ ገልፀው ተሰናበቱኝ። ይህን ሁሉ ጉዞ ካደረግሁ በኋላ

ፈቃደኛ ባይሆኑ ምን ላደርግ ነው በሚል በጣም ተረበሽኩ። በአካል ተገኝቼ እንኳን እንዳልለምናቸው ዳጋ ደሴት የምደርስበት ጀልባ ስለማላገኝ በጣም ስጨነቅ ዋልኩ። በዚህ ምክንያት ወደ ገዳሙ ሳልገባ ሞፈር ቤት ለሁለት ቀን እንዳድር ተገደድሁ። መጋቢት 18 ቀን 2002 ዓ.ም ወደ ገዳሙ እንድገባ ስለተፈቀደልኝ በጣም ደስ አለኝ። ከሞፈር ቤቱ መጋቢ ጋር ለ45 ደቂቃ ያህል በጀልባ ተጉዘን ዳጋ ደሴት ደረስን። ከገዳሙም እንደ ደረስኩ ዋናው መጋቢ ተቀብለው ካስተናገዱኝ በኋላ የመጣሁበትን ምክንያት ጠይቀውኝ ምክንያቴን አስረድቼ፣ የተጻፉልኝን ደብዳቤዎች ሁሉ ከሰጠኋቸው በኋላ መታወቂያየን አሳይቼ በገዳሙ መቆየት እንድችልና ስራየን እንድሰራ ተፈቀደልኝ። በዚህ ሁኔታ ስራየን ስጀምር እንደተልቅ ችግር ሆኖ የገጠመኝ ገዳማውያን ከንቱ ውዳሴን በመፍራትና የገዳሙ ምስጢር እንዳይባክን በመስጋት ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነው። የገዳሙን ምስጢራት በመጠበቁ ረገድ እኔም ኃላፊነት እንዳለብኝ በማሳመንና ይህ ጥናት ቢካሄድ ለገዳሙም ሆነ ለገዳማውያኑ የተወሰነ ጠቀሜታ ሊኖረው እንደሚችል በማስረዳት የተወሰኑትን ገዳማውያን ለቃለ መጠይቁ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው በማድረግ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሞክሬያለሁ።

በዚህ ሁኔታ የመጀመሪያውን ዙር መረጃ የመሰብሰብ ስራ በ10 ቀናት ውስጥ አጠናቅቄ ተመልሻለሁ። በቀጣይነት ደግሞ የተጓደሉ መረጃዎችን ለማሟላት ሚያዚያ 7 ቀን 2003 ዓ.ም ወደ ገዳሙ በመሄድ ለሦስት ቀናት ቆይቼ ተመልሻለሁ። በዚህ ወቅት ግን እንደ መጀመሪያው ጉዞ ዓይነት አስቸጋሪ ሁኔታዎች አልገጠሙኝም። ገዳማውያኑ አብሬያቸው በቆየሁባቸው ቀናት ሁሉ መልካም መስተንግዶ አድርገውልኛል። በተለይ ቃለ መጠይቅ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑት ገዳማውያን ለጠየቅኋቸው ጥያቄዎች ሁሉ ተገቢውን የተብራራ መልስ ለመስጠት ጥሩ የሚባል ተነሳሽነት ነበራቸው ማለት ይቻላል።

በዚህ ጥናት በዋናነት ሦስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህም የታተሙ ጽሑፎች፣ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ በሚመለከት የንድፈ ሃሳብ መረጃዎች ከልዩ ልዩ የጽሑፍ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥረት አድርጌአለሁ። በተጨማሪም ከአማራ ክልል የቴሌቪዥን ፕሮግራም ክፍል የገዳሙን አመሰራረትና በውስጡ ስለያዛቸው ቅርሶች ዝርዝር የሚገልጽ በምስል የተደገፈ መረጃ ማግኘት ችያለሁ። ከዚህም ጋር በተያያዘ የዳጋ እስጢፋኖስን አንድነት ገዳም በሚመለከት ያለውን ታሪካዊ ዳራና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ከልዩ ልዩ ጽሑፋዊ መረጃዎች መሰብሰብ ቀዳሚ ተግባሬ ነበር።

ከዚህ በመቀጠልም ጥናቱ በተመሰረተበት የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም በመገኘት ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በምልከታ (Observation) ሰብስቤያለሁ። በዚህ ገዳም ውስጥ ከመጋቢት 18 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ለአስር ቀናት ቆይታ አድርጌአለሁ። በእነዚህ ቀናት የገዳሙን ቤተክርስቲያን፣ ልዩ ልዩ ቅርሶች የሚገኙበትን እቃ ቤት፣ ስውሩ መድኃኔዓለም፣ የጻድቃን ማረፊያና አቃቤ ሰዓት የተሰኙ ቦታዎችን ተመልክቻለሁ። በተጨማሪም የተግባር ቤቱንና ጸሎተ ማዕድ ቤቱን መጎብኘት ችያለሁ። የእንጨት ደወሉንና ጥፋተኛ የሚቀጣበትን ግንድም አይቻለሁ። በአጠቃላይ ምድረ ግቢውን እየተመለከትኩ አስፈላጊ የመሰሉኝን መረጃዎች ፎቶግራፍ በማንሳት፣ ቪዲዮ በመቅረጽና በማስታወሻ ደብተሬ ላይ በመመዝገብ ለመሰብሰብ ሞክሬአለሁ።

እንዲሁም የጥናቱን ማዕከላዊ ሃሳብ ፈልፍለው ለማውጣት እገዛ የሚያደርጉና ከተለያዩ አቅጣጫ ምርመራ ለማድረግ የሚረዱ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ቃለ መጠይቅ (Interview) አድርጌአለሁ። ቃለ መጠይቆቹ የቀረቡት በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ውስጥ ለሚኖሩ መነኮሳትና በገዳሙ ውስጥ በአመክሮ ላይ ለሚገኙ ገዳማውያን ነው። በዚህም መሰረት የገዳሙ አበምኔት፣ መጋቢ፣ እጓል መጋቢ፣ የእቃ ቤት ሀላፊ፣ አፈ መምህር፣ የእቃቤት ጠባቂና ሌሎች ሁለት አባቶች ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቹ ናቸው። በተጨማሪም ከሌሎች አምስት መነኮሳት መረጃ የሰበሰብኩ ሲሆን በድምሩ አስራሦስት መረጃ አቀባዮችን ተጠቅሜያለሁ። ከዚህ ውጭ ርዕሰ ጉዳዩን በሚመለከት ከተለያዩ ሰዎች ጋር ውይይት በማድረግ ሃሳብ ለመሰብሰብ ጥረት አድርጌአለሁ።

መረጃዎች የሚሰበሰቡበትን ዘዴ በመከተል ለመረጃው ውጤታማነትና ተአማኒነት የሚያግዙ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን መጠቀም ተገቢ ነው። በመሆኑም ቃለ መጠይቁ በቴፕ ተቀርጿል። እንደ አስፈላጊነቱና እንደ አመችነቱ የቪዲዮ ቀረፃ ተደርጓል። እንዲሁም ለመረጃው ጥንካሬ ይሰጣል በሚል የታመነባቸውን መረጃዎች በፎቶግራፍ ለማስደገፍ ተሞክሯል።

### 1.5.2 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ከሰበሰብኩ በኋላ ከገዳሙ ሳልወጣ መተንተን ጀምሬአለሁ። በመስክ ወቅት መረጃውን ለማደራጀትና ለመተንተን መሞከሬ በሰበሰብኩት መረጃ ላይ ያለውን ክፍተት ለመሙላት አስችሎኛል። ከዚህም በኋላ

ተጨማሪ መረጃዎችን በቃለ ምልልስ የያዝኩ ሲሆን በመቅረጸ ድምጽ የሰበሰብኳቸውንና በማስታወሻ ደብተሬ ላይ የመዘገብኳቸውን መረጃዎች ከመጻሕፍት ጋር እያገናዘብኩ ትንታኔ ሰጥቼባቸዋለሁ። ለዚህም ጥናት የተጠቀምኩት የትንተና ስልት ገላጭ /Descriptive/ የምርምር ዘዴን ነው። ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው ተረኮችና አምልኳዊ ስርዓቶች ለገዳማዊ ህይወት ያላቸውን ፋይዳ ለመመርመር ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ /Functional Approach/ ቅርበት ያለው ሆኖ ስላገኘሁት እንደተጨማሪ የመተንተኛ ዘዴ ተጠቅሜበታለሁ።

## *1.6 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት*

ለዚህ ጥናት እንደ አነሳሽ ምክንያት የምጠቅሰው ጉዳይ በክፍል ትምህርቴ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ ሐይማኖታዊ ፎክሎሮች ለጥናት ትኩረት እንዳላገኙ በተደጋጋሚ ሲጠቀሱ መስማቴ ነው። ጥናቱን በምን ክልል፣ ምን ቦታ ላይ ላድርግ እያልኩ በማስብበት ወቅት ደግሞ ዴርቶጋዳ የተሰኘው ልብወለድ መጽሐፍ በዚህ ገዳም ላይ እንድመሰረት አቅጣጫ ጠቁሞኛል ማለት እችላለሁ። ደራሲው የገዳሙን ስርዓት በሚመለከት ገዳማውያኑ ትህትናን የተላበሰ የተለየ የሰላምታ አሰጣጥ እንዳላቸው፣ ለበረከት በሚል ወደ ገዳሙ የሚመጡ እንግዶችንና ምዕመናንን ሁሉ እግራቸውን እንደሚያጥቡ፣ የተለየ የአመጋገብና የአቀጣጥ ስርዓት እንደሚከተሉ፣ ሴቶች ወደ ገዳሙ መግባት እንደማይፈቀድላቸውና ጠበቅ ያለ የጸጥታ ህግ እንዳላቸው ሳነብ በዚህ ገዳም ላይ ትኩረቴን እንዳደርግ አነሳስቶኛል።

ከዚህ ሌላም በገዳሙ የቅርስ ማስቀመጫ ቤት ውስጥ ብዙ አጽሞች እንደተቀመጡ ጠቅሶ የአጼ ዘርዐ ያዕቆብ አፅም የጥይት መከላከያ ይሆናል በሚል እንደሚታመንበት፣ በዚህም ምክንያት ከአፅሙ አካል የተወሰነ ተሰርቆ መወሰዱንና መስራቹ በሐይቅ ላይ ተጉዘውባቸዋል በሚል በቅርስነት ስለተቀመጡት የድንጋይ ታንኳዎች ሳነብ ያልተጠቀሱ በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገመት ይህንን ጥናት ለማድረግ እንድወስን ገፋፍቶኛል ማለት እችላለሁ።

## *1.7 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች*

ገዳማውያን ከንቱ ወዳሴ ይሆንብናል በሚል እምነት የሚያውቁትን እንደማያውቁ ሆነው ስለሚኖሩ ሁሉም ማለት ይቻላል ስለአኗኗር ዘይቤያቸው፣ ስለእምነታቸው፣ ለተረኮቻቸው ስላላቸው አመለካከትና ስለገዳማዊ ስርዓታቸው ግልጽና ደፋር የሆኑ አስተያየቶችን ያለ

ጉትጎታና ያለ ፈታሽ ጥያቄዎች/Cross Checking Questions/ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው እንደ ችግር የሚጠቀስ ነው። የገዳሙ ታሪክ እንዳይዛባ በሚል ስጋት የምፈልገውን ገዳማዊ ሁሉ እንዳነጋግር አለመፈቀዱና ገዳማውያኑም መጋቢው ከነገሩህ የተለየ ነገር የለንም በሚል ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ሌላው ሊነሳ የሚገባው ችግር ነው። ቃለመጠይቅ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑት ደግሞ የተቀረጹበትን ካሴቶች እንድሰጣቸው ቃል የማስገባት ሁኔታ ነበር። ከዚህ ሌላ ደግሞ ስማቸውን፣ እድሜያቸውን፣ የገዳሙን የቆይታ ጊዜያቸውን ለመግለጽ አለመፈለግና ፎቶ ለመነሳትም ሆነ ቪዲዮ ለመቀረጽ ፈቃደኛ አለመሆናቸው እንደችግር የሚጠቀስ ነው።

ለእነዚህ ችግሮች የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች በተቻለኝ አቅም ሁሉ ለገዳሙ ምስጢራትና ሊሰጠው ስለሚገባው ክብር ተቆርቋሪ መሆኔን በመግለጽ ይህ ገዳም ትልቅ ታሪክ ያለው ገዳም ሆኖ እያለ እስካሁን ድረስ በስፋት አለመታወቁ ሊያስቆጫቸው እንደሚገባ በማነሳሳት ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ እንዲሆኑልኝ ማግባባት ችያለሁ። ቃለመጠይቅ የተደረጉባቸውን ካሴቶች እንድልክላቸው ለጠየቁኝም አስገልብጬ እንደምልክላቸው ቃል በመግባት ለማግባባት ሞክሬአለሁ። በገባሁትም ቃል መሰረት 11 ካሴቶችን አስገልብጬ ልኬላቸዋለሁ። ይህም ለሁለተኛ ጊዜ ስሄድ በተወሰነ ደረጃ የመታመን እድል እንዳገኝ አመቻችቶልኛል ማለት እችላለሁ። ቃለ መጠይቅ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑት መካከል አንዳንዶቹ ቆይታየን እያራዘምኩና ወዳጅነቴን/ቅርበቴን/ እያሳደግሁ በሄድሁ ቁጥር በማስታወሻ ብቻ እየጻፍኩ እንዳናግራቸው ፈቃደኛ መሆን ችለዋል።

# 2. ክለሳ ድርሳን

የዚህ ክፍል የትኩረት ነጥብ ጥናቱ የተመሰረተበትን ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት እና ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች መቃኘት ነው። በመሆኑም በቅድሚያ ጥናቱ የተመሰረተበት ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ምን እንደሚመስል እንመልከት።

## 2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 ሀገረሰባዊ ልማድ/Social Folk Custom/

የፎክሎር ባለሙያዎች ፎክሎርን በጥቅል ከማጥናት ይልቅ በተለያዩ ፈርጆች ከፍሎ ማጥናት የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ይገልጻሉ። ሪቻርድ ዶርሰን/Richard Dorson/ ፎክሎርና ፎክ ላይፍ ጥናት በአራት ሰፋፊ ክፍሎች እንደሚመደቡ ጠቁሞ እነሱም ቃላዊ ስነጽሑፍ/Oral Literature/ ወይም ቃላዊ ጥበብ/verbal art/፣ ቁሳዊ ባህል/Material Cultur/፣ ሀገረሰባዊ ልማድ/Social Folk Custom/፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት/Performing Folk Arts/ እንደሚባሉ ይገልፃል(Dorson,1972,3)። እነዚህም የፎክሎር ክፍሎች ሰፊ እንደመሆናቸው መጠን በስራቸው ተካተው የሚጠኑ የተለያዩ ዘርፎች አሏቸው። የዚህ ጥናት ትኩረት በሀገረሰባዊ ልማድ ላይ በመሆኑ ይህንን ክፍል ቀጥለን እንመልከት።

ሀገረሰባዊ ልማድ/Social Folk Custom/ የሚባለው የፎክሎር ክፍል በተለምዶ ተደጋግሞ በሚፈጸም ድርጊትና በድርጊቱ ተለምዶአዊ የመፈጸሚያ ዘዴ ላይ ትኩረት ያደርጋል (Sims,2005,17)። ልማድ ሰዎች ሁልጊዜ አምነውና ወደው የሚፈጽሙትን ድርጊት ወይም ለማህበራዊ ህይወታቸው ዋስትና ሲሉ አጥብቀው የሚቀበሉትንና የሚይዙትን እምነት የሚያጠቃልል ነው። ዶርሰን ሀገረሰባዊ ልማድ የበለጠ ትኩረት የሚያደርገው ከግለሰቡ ጥበብና ክወና ይልቅ ቡድኑ/ማህበሩ/ በሚያሳድረው ተጽዕኖ ወይም መስተጋብር ላይ ነው(Dorson, 1972,3) ይላል። ይህ ተደጋግሞ የሚፈጸም ሀገረሰባዊ ልማድ የማህበሩን ማንነት የሚያመላክት በመሆኑ በልማዱ ውስጥ የማህበሩን ተሳትፎና እምነት ማየት ጠቃሚ ነው። ልማድ ተመሳሳይነት ያላቸው ተደጋጋሚ ባህርያት መገለጫ ሲሆን፣ የማህበረሰቡን ተሳትፎ በሚያመለክት ሁኔታ ሰዎች የሚከውኑት በድርጊቶች፣ በቃላት፣ በምልክቶች የታጠረ ተግባር(Sims,2005,17) ነው በሚል የዶርሰንን ሃሳብ ያጠናክራሉ። አንዳንድ ልማዶች ውሱንና አካባቢያዊ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመግለጽ ጥቅልና ልዩ ልማዶች በአብዛኛው አካላዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ልማዳዊ እምነቶችንና ቁሳዊ አካላትን እንደሚያካትት(Dorson,1972,3)

ይገልጻል። በአጠቃላይ ልማድ የሚባለው የአንድ ማህበር/Group/ ተደጋጋሚነትና ተመሳሳይነት/Pattern/ ያለው ድርጊት ወይም ባህርይ ሲሆን ክወና ያለውና ለክወናውም ቁሶችን፣ የተለያዩ ቃላትንና ምልክቶችን የሚጠቀም የማህበሩ እምነት፣ እሴትና ትውፊት የሚንጸባረቅበት ነው ብሎ ማጠቃለል ይችላል።

በሀገረሰባዊ ልማድ/Social Folk Custom/ ክፍል ውስጥ የሚካተቱ ንዑሳን ዘርፎች አሉ። ፊቃደ ዶርሰንን ጠቅሶ በዚህ ክፍል ይካተታሉ የሚላቸው ፌስቲቫልና ክብረበዓል (ክበራ)/Festivals and Celebrations/፣ ሀገረሰባዊ መድኃኒት /Folk Medicine/፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች/Recreations and Games/፣ እና ሀገረሰባዊ ኃይማኖት/Folk Religion/ እንደሆኑ ዘርዝሯል(1991፣13)። እነዚህ የሀገረሰባዊ ልማድ ዘሮች ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ዘርፎች በመሆናቸው በተናጠል ሊጠኑ ይችላሉ። ዘርፎቹ የየራሳቸው ባህርያት ያሏቸው በመሆናቸው የትኩረት አቅጣጫቸውም እንዲሁ የተለያየ ነው። ይህ ጥናት በአንድ ገዳም ገዳማዊ ህይወት ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑና ይህም ገዳማዊ ህይወት ከሀይማኖታዊ እንቅስቃሴ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ ጥናቱ በዋናነት ኃይማኖታዊ ፎክሎር/Religious Folklore/ በሚለው ክፍል ላይ ብቻ ትኩረቱን ያደርጋል።

ዶን ዮደር/Don Yoder/ ኃይማኖታዊ ፎክሎርን በሚመለከት የተለያዩ የፎክሎር ባለሙያዎች የተለያዩ ብያኔዎች እንደሚሰጡ ጠቁሞ ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉትን ብያኔዎች ከራሱ ሙያዊ አስተያየት ጋር ያቀርባል። ቻርልስ ጂ. ሌላድ /Charles G. Leland/ ሀገረሰባዊ ሀይማኖት ከክርስትና እምነት መጀመር በፊት የነበረና እስካሁኑ ዘመን ድረስ ያለ የሀይማኖት ቅሪት ነው በሚል የሰጠውን ብያኔ ይህ ንድፈ ሀሳብ የአዝግሞታውያንን ንድፈ ሀሳብ የተከተለ ነው ይላል። እንዲሁም ሀይማኖታዊ ፎክሎርን በብዙ የፎክሎር ባለሙያዎች ዘንድ ከሀይማኖቱ ህግጋት ውጭ ከሚፈጸሙ እምነቶች ወይም ከባእድ አምልኮ ጋር ተያይዞ የሚሰጠውን ብያኔ መሰረት በማድረግ ዮደር/Yder/ ሀይማኖታዊ ፎክሎር በባህላዊ ማህበር ውስጥ በእምነት/Belief/፣ በስርአት/Ritual/፣ በልማድ/Custom/ እና በአፈታሪክ/Mythology/ መካከል ያለ መስተጋብር ማለት እንደሆነ ይጠቁማል። እንግዲህ ከዚህ በመነሳት ሀይማኖታዊ ፎክሎር በሀይማኖታዊ መጻህፍት ውስጥ ካለው አስተምህሮና መደበኛ የአምልኮ ስርአት ጎን ለጎን ወይም በተናጠል የሚታይ በድምሩ ህዝቡ ሀይማኖቱን የሚረዳበትና የሚተገብርበት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል ይላል(Yoder,1974,2-15)።

ላሪ ዳኔልሰን/Larry Danielson/ የዮደርን ሀሳብ በመደገፍ ሀይማኖታዊ ፎክሎር ከኃይማኖት ጋር በአንድነት የሚተገበር ፎክሎር ነው ሲባል ኃይማኖታዊ ፎክሎር በተለያዩ ኃይማኖታዊ ማህበሮች ወይም ቡድኖች ውስጥ የሚገኝ ማለት እንደሆነ ያስረዳል። ይህም ማለት እውቅና ባላቸው ኃይማኖታዊ አምልኮዎች /አገልግሎቶች/ ውስጥና እና ከቤተአምልኮ ውጭ የሚተገበር ነው ማለት ነው። እንዲሁም እውቅና ካለው አስተምህሮ/doctrine/ ጋር በተቃርኖ ወይም በተጣምሮ ሊመጣ ይችላል ይላል። ሀይማኖታዊ ፎክሎር የተለያዩ የፎክሎር ዘውጎችን/genres/ አካቶ የሚመጣ ሲሆን ፎክሎር ያልሆኑ ምንጮችንና ቁሶችን ሊጠቀም እንደሚችልም ጨምሮ ይገልጻል(Danielson,1986, 53/።

ኃይማኖታዊ ፎክሎር የሚባለው ኃይማኖታዊ ልማዶች የሚመረመሩበት መንገድ ነው ማለት ይቻላል። እንደ ሪቻርድ ዶርሰን ገለፃ በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተተው ኃይማኖታዊ ፎክሎር ከቤተአምልኮ ውጭ የሚፈጸምን አምልኮ የሚያካትት ነው(Dorson,1972,4)። ይህ አይነቱ ሀይማኖታዊ ፎክሎር ቀደም ሲል በእነ ሌላንድ /Leland/ እንደተጠቀሱት የክርስትና እምነት ከመምጣቱ በፊት እንደነበሩት አይነት ሀይማኖቶች ያለ መሆኑን ይገልጻል። ነገር ግን ኃይማኖታዊ ፎክሎር ከቤተአምልኮ ውጭ ብቻ ሳይሆን በቤተአምልኮ ውስጥም ከሀይማኖታዊ ስርዓት ጋር ተዋህዶ የሚገኝ ነው። ዳኔልሰን ኃይማኖታዊ ፎክሎሮች በመደበኛው የአምልኮ አገልግሎት ውስጥ ዘወትር የማይፈጸሙ በመሆናቸው በቀላሉ ግልጽ ሆነው የማይታዩ ቢሆንም በቤተአምልኮ ውስጥ የሚተገበሩ ናቸው(Danielson,1986,50/ ይላል። ፈቃደም በበኩሉ የሀይማኖታዊ ፎክሎር ምርምር በቤተሀይማኖት (መስጊድ፣ቤተክርስቲያን፣ ምኩራብ፣ ወዘተ) ክንውኖች ውስጥ በሚከሰቱ መስተጋብሮች ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ(ፈቃደ፣ 1991፣14) ያስቀመጠውን ሃሳብ ስንመለከት ሀይማኖታዊ ፎክሎር በቤተአምልኮ ውስጥ የሚተገበር ለመሆኑ ደጋፊ ማስረጃ ሆኖ እናገኘዋለን። ስለዚህ ሀይማኖታዊ ፎክሎር በቤተአምልኮ ውስጥም ሆነ ከቤተአምልኮ ውጭ የሚገኝ ፎክሎር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ዳኔልሰን ከቤተአምልኮ ውጭ በተለያዩ ቤተሰቦች የሚፈጸሙ የተለያዩ የጸሎት ዓይነቶች ፎክሎራዊ ገጽታ አላቸው ይላል። ይህም ሃይማኖታዊ ፎክሎር ከቤተአምልኮ ውጭ ይፈጸማል ለሚለው ሃሳብ ምሳሌ ሊሆን እንደሚችል ይገልጻል። እንዲሁም በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ የቁርባንን ህብስት ሳያላምጡ መዋጥ እንጂ ማኘክ/ማላመጥ/ በአፍ ደም ይሞላል የሚለው እምነት በቤተ አምልኮ ውስጥ ለሚፈጸሙ ፎክሎራዊ ገጽታዎች ማሳያ ይሆናል (Danielson,1986,50/ ይላል። እንዲሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት

አስተምህሮ ውስጥ ዘፈን የተከለከለ ሆኖ እያለ በታቦት ንግስ ጊዜ ግን የማይከለከል መሆኑ ሀይማኖታዊ ፎክሎር ከሀይማኖቱ አስተምህሮ ጋር ተቃርኖ ሊመጣ ይችላል ለሚለው ማሳያ ይሆናል። ከዚህም ሌላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ኢየሱስ የሐዋርያትን እግር ማጠቡን ምክንያት በማድረግ በፀሎተ ሀሙስ በጳጳሳትና ካህናት የመፈጸሙ የእግር አጠባ ስርአቶችና አይነቶች፣ የሀይማኖት ፎክሎር ከሀይማኖቱ አስተምህሮ ጋር ተጣምሮ ሊመጣ ይችላል ለሚለው ሃሳብ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ፎክሎር ሁልጊዜም የኃይማኖቱን አስተምህሮ ተቃርኖ ብቻ የሚቆም ሳይሆን አስተምህሮውን በሚደግፍ ሁኔታ ሊመጣ ይችላል ማለት ነው።

ኃይማኖታዊ ፎክሎርን በተለያዩ የፎክሎር ዘውጎች/Genres/ ከፋፍሎ ማጥናት ይቻላል። ዳኔልሰን ኃይማኖታዊ ፎክሎር ተለይተው በሚታወቁ ዘውጎች ተወክሎ እንደሚቀርብ ከገለጸ በኋላ በዋናነት የሚከተሉትን ዘውጎች ይዘረዝራል፤ ሀገረሰባዊ ተረክ፣ መዝሙር/ሙዚቃ/፣ እምነት፣ ስርዓት፣ መድኃኒት፣ ጥበብ/አርት/፣ የምግብ ዝግጅት ጥበብ/ስነምግብ/፣ አለባበስ፣ ፎክ ዲሚያኖር/Folk Demeanor/(Danielson,1986,52/። በርግጥ እነዚህ ዘውጎች በኃይማኖታዊ ፎክሎር ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ አንድ ዘውግ ከሌሎች ዘውጎች ጋር ሳይቀላቀል ራሱን ችሎ የአንድን ማህበረሰብ ኃይማኖታዊ ትውፊት ይዞ ሊቀርብ ይችላል ወይ የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ዳኔልሰን የዚህ አከፋፈል መሰረታዊ ክፍተት ነው በሚል ያስቀመጠው አንድ ኃይማኖታዊ ትውፊት በውስጡ ከአንድ በላይ ዘውጎችን አካቶ የሚመጣ መሆኑን ነው። በተለይ ሃይማኖታዊ እምነት /Religious Belief/ በየዘውጎቹ የሚንጸባረቅ በመሆኑ(Danielson,1986,52) ሀይማኖታዊ ፎክሎርን በዘውጎች ከፋፍሎ ለማጥናት እቅፋት እንደሚፈጥር ያስረዳል።

በኃይማኖታዊ ፎክሎር ውስጥ እምነት/Belief/ ማዕከላዊ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። ሪቻርድ ዶርሰን በስነ ማህበረሰብና በስነ መለኮት ተመራማሪዎች እውቅና የተሰጠው ኃይማኖት ሊያሟላቸው የሚገባ ባህርያት እንዳሉ ጠቅሶ የእነዚህ ባህርያት ውህድ ክንውኖች ምክንያታዊነታቸው በእምነት /Belief/ የሚረጋገጥ ስርዓት አምልኮዎች /Rituals/ ተብለው እንደሚጠሩ(Dorson,1972,219) ይገልፃል። በሀይማኖታዊ ፎክሎር ውስጥ የሚንጸባረቁ ስርዓቶችን ሁሉ ምክንያታዊ የሚያደርጋቸው እምነት ነው። ፈቃደ «በሀይማኖት ስርዓቶች ላይ በሚደረገው ጥናት ትኩረቱ በታወቁት የሀይማኖት መጻህፍት ውስጥ ከታዘዘው ውጭ፣ ሰዎች በየራሳቸው በሚከተሏቸው እምነቶችና እምነታዊ ድርጊቶች ላይ ነው» (ፈቃደ፣

1991፣14) በሚል ስለሀገረሰባዊ ሀይማኖት ምርምር የትኩረት አቅጣጫ የገለጸውን ሃሳብ ስንመለከት የምርምሩ ዋና ጉዳይ «እምነትና እምነታዊ ድርጊት» ሆኖ እናገኘዋለን። እንዲሁም የተለያዩ ዘውጎች የሚመሰርቱት ልማድ በጥቅል የሚገለጸው ጥልቀት ባላቸው እምነቶች አማካኝነት(Dorson,1972,3) እንደሆነ ዶርሰን አስፍሮ እናገኘዋለን። እነሲምስ /Sims/ በበኩላቸው ማመን ወይም በአንድ ነገር አማካይነት እምነትን መግለጽ የእምነት መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን ካሉት ብዙ የፎክሎር ዓይነቶች ይህኛው ሀይል ያለው ነው (Sims, 2005,58) በሚል ያሰፈሩትን ጉዳይ ስንመለከት በኃይማኖታዊ ፎክሎር ውስጥ እምነት ዋና ማጠንጠኛ ጉዳይ እንደሆነ መረዳት እንችላለን።

የዚህ ጥናት ማዕከላዊ ነጥብ የሆነው እምነትና እምነታዊ ድርጊት የአንድን ሃይማኖታዊ ማህበር/Group/ ትውፊቶች፣ እሴቶችና አስተሳሰቦች ለይቶ ለመረዳት እምነት/Belief/ መሰረታዊ ጉዳይ ነው የሚል እምነት አለኝ። ከዚህ አኳያ ስለእምነት ምንነት፣ ስለእምነት ዓይነቶችና የፎክሎር ባለሙያው እምነትን ሲያጠና ሊያተኩርበት ስለሚገባው ጉዳይ ለመግለጽ ልሞክር።

### 2.1.2 እምነቶች /Beliefs/

እምነት /Belief/ የሚለው ቃል የምናምነውን ነገርና አምነን የምናደርገውን እንቅስቃሴ /ድርጊት/ የሚያመለክት ሲሆን(Sims,2005,57) ለአንድ ባህላዊ ማህበር/Cultural group/ መንፈሳዊና አለማዊ የሆኑ ጉዳዮችን ወይም መረጃዎችን የመለዋወጫ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል። እነሲምስ/Sims/ እምነት ሲባል ብዙ ጊዜ ከሀይማኖት ቡድኖችና ሃይማኖታዊ ሰነዶች/ጽሁፎች/ ጋር የተያያዘ መሆኑ የተለመደ እንደሆነ ገልጸው ከዚህ ሌላ የእምነት መገለጫ ባዕድ አምልኮ/Superstition/ የሚባለውን እንደሚጨምር በመጠቆም ከዚህ አንጻር እምነት ወይም እምነቶች፦

> ተለምዷዊውን ድርጊትና ባህርይ የሚያቅፉ ሆነው እንዲሆኑልን ወይም እንዲመጡልን የምንፈልጋቸው እንደተጨባጭ ምክር ወይም መፍትሔ ወይም ፈውስ ዓይነት ናቸው። ሃይማኖታዊ ወይም መለኮታዊ የሆኑ ጽንሰሃሳቦች እንደሀተታ ተፈጥሮ ባሉ ቃላዊ ተረኮች አማካይነት ወይም በምልከታና በማህበረሰባችን ውስጥ ባለን ግንኙነት የምንማራቸው ናቸው(Sims,2005,57)

ይላሉ። ሌላው የእምነት ክፍል ደግሞ «ስለዓለም ያለን አተያይና በእኛ ውስጥ ስላሉት ቁስአካላዊ መመሪያዎችና ሃሳቦች የተረዳነውን የምንገልፅበት ሲሆን የእኛን እሴቶች መሰረት

ያደረጉት እምነቶቻችን አመለካከታችንንና ስለሌሎች ሰዎችና ስለአለም ያለንን ግምት የሚመሩና የሚቀርጹ መሰረታዊ መመሪያዎች ናቸው»(Sims,2005,58)። ይህ የእምነት ዓይነት አለማዊ /Secular/ የሚባለው አይነት ሲሆን ለምሳሌ የተቸገረን ስለመርዳት፣ እንግዳ ስለመቀበል፣ ታላቅን ስለማክበር፣ የታመመን ስለመጠየቅ ወዘተ. ባለን አመለካከት ላይ የሚመሰረት እምነት ነው። ይህ ዓይነቱ እምነት ስለአለምና ስለሰው ልጅ ያለንን ግንዛቤ የምንገልጽበት መንገድ ነው ማለት ይቻላል።

ዶን ዮደር/Don Yoder/ እምነትን መንፈሳዊና አለማዊ ብለው በሁለት በመክፈል ብያኔ የሰጡትን የመስኩ ምሁራንን አለማዊም ይሁን መንፈሳዊ እምነት ሁሉም ከአንድ የተወሰነ አውድ ውስጥ ፈልቀው በአንድነት የተዋሃዱ የእምነት ስርዓት/ unified organic system of belief/ አካል ናቸው በማለት እንደሚሞግታቸው እነሲምስ ይገልጻሉ(Sims,2005,60)። በርግጥም መንፈሳዊና አለማዊ እምነቶች/Sacred and Secular Beliefs/ የሚታመኑት /የሚደገፉት/ ልዕለ ተፈጥሮአዊ/Supernatural/ በሆነው አካል ላይ ይመስላል። በመንፈሳዊው እምነት አምላክ ያደርግልኛል/ይከለክለኛል፣ ይሰጠኛል/ይነፍገኛል፣ ይፈውሰኛል/ያሳምመኛል፣ ያጸድቀኛል/ይኮንነኛል፣ ያከብረኛል/ያዋርደኛል ወዘተ. ብሎ ማመን ነው። በአለማዊው እምነትም የታመመን መጠየቅ፣ የተቸገረን መርዳት፣ ታላቅን ማክበር፣ በቅድሚያ መንፈሳዊ/Spiritual/ እረፍት ያስገኛሉ በሚል እምነት የሚፈጸሙ ድርጊቶች ሲሆኑ ቀጥሎ ደግሞ ከአምላክ መልካም ነገር ያስገኛሉ የሚል የእምነት መሰረት ያላቸው ይመስላል።

የጥንቆላ ወይም የአስማት እምነትም የልዕለ ተፈጥሮ መንፈስ ባረፈበት አካል ላይ የመደገፍ እምነት ነው። ለምሳሌ በእኛ ሀገር የውሻ ማላዘን ወይም የጉጉት ጩኸት የልዕለ ተፈጥሮ መንፈስ ያደረባቸው በመሆኑ ልዕለ ተፈጥሮ የሚያመጣውን መዓት/ቅጣት/ ጠቋሚዎች ናቸው ብሎ ማመን ይመስለኛል። ስለዚህ አለማዊውም ይሁን መንፈሳዊው እምነት ዮደር እንደሚለው ከአንድ ልዕለ ተፈጥሮ/አምላክ/ ተቀድተው እንደየአካባቢውና እንደየባህላዊው ማህበር ስርዓትና ልምድ የሚዳብሩና የሚተረጎሙ ሊሆን ይችላል። ይህንን በሚመለከት እነሲምስ የእምነት ጉዳይ ሁልጊዜም በፎክሎር ውስጥ በአብዛኛው የሃይማኖት አካል ሆኖ ይታያል (Sims,2005,60) በሚል አስፍረው እናገኛቸዋለን።

እምነትን የሚያጠና የፎክሎር ባለሙያ ትኩረት ማድረግ ያለበት የእምነቱን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ላይ ሳይሆን በእምነቱና እምነቱ በቀረበበት መንገድ ላይ መሆን አለበት። እነሲምስ የፎክሎር ባለሙያዎች የእምነት ጉዳይ በግልጽ የሚመለከታቸው ቢሆንም የእምነቱን ትክክለኛነትና ተአማኒነት ከመመርመር ይልቅ የእምነቱ ተከታዮች እምነታቸውን በምን መንገድ እንደሚያከናውኑት ትኩረት መስጠት አለባቸው (Sims,2005,103) ይላሉ። ስለዚህ የፎክሎር ባለሙያው እምነትን መሰረት አድርጎ ሲያጠና አማኙ እምነቱን ምን፣ ለምን፣ በምንና መቼ እንደሚከውነው እመመርመር ላይ መመስረት ይኖርበታል።

እምነትና እምነታዊ ድርጊት የሀይማኖታዊ ፎክሎር መሰረታዊ ጉዳዮች መሆናቸውን ተመልክተናል። በሀይማኖታዊ ፎክሎር ውስጥ ትኩረት የሚደረግበት እምነት በተለያዩ የፎክሎር ዘውጎች ሊገለጽ እንደሚችልም ለማየት ሞክረናል። በመሆኑም እምነትና እምነታዊ ድርጊት ለመተንተን በተረክ/Narrative/ እና ስርዓት/Ritual/ ዘውጎች የቀረቡትን እምነቶች መሰረት በማድረግ በቅድሚያ ስለእነዚህ ዘውጎች ምንነትና ከእምነትና እምነታዊ ድርጊቶች ጋር ያላቸውን ተዛምዶ እንመልከት።

### 2.1.3 ስርዓቶች /Rituals/

ቀደም ሲል የተለያዩ ሀይማኖታዊ አመለካከቶች፣ ሃይማኖታዊ መስተጋብሮችና ግለሰባዊ እምነቶች ሁሉ በእምነት ውስጥ እንደሚካተቱ ተገልጿል። በዚህ ደረጃ እምነት ረቂቅና የማይጨበጥ ሆኖ ይታያል። ይህንን ረቂቅ እምነት ተጨባጭ የሚያደረገው ስርዓት /Ritual/ነው። ስርዓት/Ritual/ የአንድን ማህበር ድብቅና ረቂቅ እሴቶችን፣ እምነቶችንና አመለካከቶችን ለፎክሎር ባለሙያውም ሆነ ለማህበሩ አባላት የሚታዩና የሚጨበጡ በማድረግ ረገድ ጠቀሜታው ከፍ ያለ ነው(Sims,2005,97)። ኮታክ/Kottak/ በበኩሉ ሥርዓት ስለተሳታፊዎችና ስለባህላቸው ከፍ ያለ መረጃ ከማስተላለፉም በላይ ከዓመት ዓመት የሚደጋገም፣ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ፣ ዕኑ መልዕክቶችን፣ እሴቶችንና አስተሳሰቦችን ወደድርጊት ለመተርጎም የሚያስችል ነው(Kottak,307,2002,) ይላል። ረቂቅነት ያለውን እምነት ተጨባጭ የማድረግ ባህርይ ያለው ስርዓት ሌላው ጠቀሜታው አካልንና ስሜትን የማሳመን አላማ ያለው መሆኑ ነው(Sims,2005,98)።

የሃይማኖት ፎክሎር ይዘቶች ከሚቀርቡባቸው ዘውጎች/Genres/ አንዱ ስርዓት ነው። እንደሪቻርድ ዶርሰን አከፋፈል ሃይማኖታዊ ፎክሎር የሃገረሰባዊ ልማድ አካል ሲሆን በተዓምራዊነታቸውና በቅድስናቸው ሃይል ያላቸው ልማዶች ደግሞ ስርዓት/ Ritual/ ይባላሉ(Dorson,1972,3) በማለት ይገልፃል። በዚህ አገላለጽ ስርአት መለኮታዊ ሀይል ያለው ልማድ ሆኖ ይታያል። በሌላ ሁኔታም እምነትን ወይም እሴቶችን የያዘ፣ በጥልቀት የሚከወንና ዝግጅት የሚደረግበት፣ ቡድኖች በተከታታይ የሚፈጥሩት ክወና ስርዓት (Sims,2005,95) ይባላል ይላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታም ኮታክ ስርዓቶች የሚዋቀሩበት ቅርጽ ስልታዊ፣ ተደጋጋሚና አጠቃላይ ማህበረሰባዊ ስምምነት ያለው ነው (Kottak,307,2002,) በሚል አስፍሮ እናገኘዋለን። ከእነዚህ ብያኔዎች በመነሳት ስርዓት የሚደጋገም፣ ተለምዷዊ የሆነ፣ አላማ ያለው፣ የተደራጀና ለቡድኑ አባላት ትርጉም የሚሰጥ፣ ክወናና ተጨባጭነት ያለው የልማድ ክፍል ነው በሚል ማጠቃለል ይቻላል።

ስርዓት ክወና አለው ሲባል ስርዓቱንና ከዋኞችን እንዲሁም የስርዓቱን አጀማመርና አጨራረስ የሚጠቁሙ ቅርፆች ይኖሩታል ማለት ነው። እነሲምስ ስርዓት ብዙ የፎክሎር አይነቶችን አንድ ላይ አካቶ እንደሚመጣ በመግለጽ ከነዚህም ውስጥ ቃላዊ፡- ምሳሌ ዜማ፣ መነባነብ፣ ግጥም፣ መዝሙር/ዘፈን/፤ ልማዶች፡- ምሳሌ ምልክቶች፣ ውዝዋዜ/ዳንስ/፣ ወይም ሽብሸባ፤ ቁሶች፡- ምሳሌ ምግብ፣ መፅሃፍ፣ ሽልማት፣ አልባሳት፣ የሚሉት ይገኙበታል(Sims, 2005, 96) ይላሉ። ለምሳሌ የቁርባን ስርዓት ቅዳሴ፣ ዜማ፣ መነባነብ፣ መወድስ፣ ሽብሸባ፣ አልባሳት፣ የህብስቱ መያዣ መሶበ ወርቅ፣ የወይኑ መያዣ ጽዋ እና ሌሎችም ድርጊቶችና ቁሳቁሶች የስርዓቱ አካል ናቸው። እነዚህ ቃላዊ፣ ልማዳዊና ቁሳዊ የፎክሎር ዘሮች አንድ ላይ ተዋህደው ስርዓቱን የተቀደሰ ሆኖ እንዲታይ ያስችሉታል።

ስርዓት ልክ እንደ እምነት ሁሉ መንፈሳዊ /Sacred rituals/ እና አለማዊ /Secular/ ተብለው የሚከፈሉ(Sims,2005,96) ቢሆኑም አልፎ አልፎ ሁለቱም ስርአቶች በአንድነት ሊመጡ ይችላሉ። በስርዓተ አምልኮ/sacred/ ሁልጊዜም ትዕምርቶችና ዘይቤዎች /Symbols and Metaphor/ ጠቃሚ ፅንሰ ሃሳቦችን ወክለው እንዲቀርቡ ይደረጋል። ሬይ ሲ. ቤንጃሚን በበኩሉ ስርዓታዊ ዘይቤዎችና ትዕምርቶች «ምን ተደረገ?» ለሚለው ተፈጥሯዊ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ጠቃሚዎች እንደሆኑ ገልጾ ስርዓቶች በሽታን ለመፈወስ፣ ዘርን ለማብዛት፣ ጠላትን ድል ለማድረግ፣ የሰዎችን ማህበራዊ ደረጃ ለመለወጥ፣ ሀጢአትን ለማንጻት እና መጭውን ጊዜ ለመተንበይ ይከወናሉ(Ray,1976,78) ይላል። ለምሳሌ አንድ

መናኝ በገዳም ውስጥ በአመክሮ ከቆየ በኋላ መንፈሳዊ አገልግሎት ባለው ስርዓት ወደ ምንኩስና ይሸጋገራል። መናኙ እዚህ ደረጃ ላይ የሚደርሰው ብዙ ፈተናዎችን ተቋቁሞ ነውና ይህ ሽግግር የመናኙን መንፈሳዊ ከፍታ ያመላክታል። ይህ መንፈሳዊ ስርዓት ከውጭ ሲያዩት ተለምዷዊ የሆነ ስርዓት ቢመስልም ብዙ ሊተነተኑ የሚችሉ ትዕምርታዊና ዘይቤያዊ የሆኑ ጉዳዮችን የያዘ ነው። ስርዓት ከልማዳዊ ድርጊቶች የሚመነጭ ቢሆንም ከልማድ ከፍ ያለ ይዘትና አላማ አለው።

ስርዓት በመንፈስ ወይም በአለም መለኮታዊ ሃይል ከሚያምን ማንኛውም ወገን /ማህበር/ ጋር የሚዛመድ ሲሆን ይህ አይነቱ ስርዓት በማህበር የሚከወን ነው። ነገር ግን የተወሰኑ ስርዓቶች(ለምሳሌ በቤተሰብ የሚከወን ሊሆን ይችላል)፣ ምናልባትም በግል የሚከወኑና እንዲያውም ምስጢራዊ የሆኑ ስርዓቶች ይኖራሉ(Sims,2005,103)። ነገር ግን በህብረትም ሆነ በግል የሚከወኑ ሁሉም ስርዓቶች እምነትን ተጨባጭ የሚያደርጉ ናቸው። የፎክሎር ባለሙያዎች ስርዓቶችን/Rituals/ የሚያጠኑበት ምክንያት የስርዓቶቹ ውስብስብነትና ድራማዊነት በትርጉም እምቅ/Dense/ መሆን ስለሚያስችላቸው ይህም የማህበሩን ትውፊቶች፣ እምነቶች፣ እሴቶችና ማንነት ለመግለጽ መሰረታዊ ብቃት አላቸው(Sims,2005,96) ብለው ስለሚያምኑ ነው። በመሆኑም የአንድን ማህበር /Group/ እምነት /Belief/ በጥልቀት ለመረዳት ስርዓቶችን መመርመር ትልቅ ዋጋ አለው ማለት ይቻላል። ይህንን በሚመለከት ሬይ/Ray/ ስርዓት «ምን ተባለ?» እና «ምን ተሰራ?» የሚሉ ሁለት ገጽታዎች ሲኖሩት እነዚህን ጥያቄዎች ማሰብም በርካታ ተግባራዊ ጉዳዮችን እንደሚይዝ ይናገራል። ስርዓቶች ማንኛውንም ኃይማኖት ለመረዳትና ለመተንተን በር የሚከፍቱ ቁልፎች መሆናቸውን መረዳት እንደሚገባ ይገልጻል(Ray,1976,78)።

## 2.1.4 ተረኮች/Narratives/

አረፍተ ነገር በቃላት እንደሚዋቀረው ሁሉ ተረክ /narrative/ ደግሞ በሁነትና በድርጊት የሚዋቀር ይሆናል (Oring,1986,122)። ተረክ የሚባለው የታሪክ ሌላው ስያሜ ነው። ተረክ ማለት አንድን ልምድ/ተሞክሮ / በቃል ማስተላለፍ ነው። ተረክ ሙሉ በሙሉ የአንድ ማህበር/ቡድን/ መረጃ /ልምድ/ የመለዋወጫ መሳሪያ ነው (Oring,1986,122) ማለት ይቻላል። በተረክ ውስጥ ድርጊትና ሁነት የግድ የማይቀሩ ናቸው ሲባል የድርጊቱና የሁነቱ ባለቤት ገፀባህርያት፣ ድርጊቱንና ሁነቱ የሚፈጸምበት ስፍራና ጊዜ /መቼት/ አብረው ይመጣሉ ማለት ነው።

አንቶኒ ካምቤል/Anthony Campbell/ ስለሀይማኖታዊ ተረክ ያሰፈረውን ቀጥለን እንመልከት። ካምቤል The Origin of Religion በሚለው መጣጥፉ ምሁራን የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት አድርገው ለሀይማኖት ምንጭ ይሆናሉ ያሉትን ሀሳብ እንደሚገልጹ ጠቁሞ እነዚህ ሀሳቦች ጠቀሜታ ያላቸው ቢሆኑም የሀይማኖት ምንጭ ሊሆን ይችላል የሚሉት እምነትን/Belief/ እንደሆነ ይገልፃል። ነገር ግን የሃይማኖት ምንጩ እምነት ሳይሆን ተረክ/Narrative/ ነው ይላል። ሀይማኖት በአብዛኛው የሚጀመረው በተረክ ይሆንና ቀጥሎ በዚህ ለይ በመመስረት እምነት ይከተላል በማለት አስፍሯል። እምነት የሀይማኖት ምንጭ መስሎ የሚታየው በብዙ ሀይማኖቶች ውስጥ እምነት ማእከላዊ ወይም መሰረታዊ ጽንሰሀሳብ ስለሆነ ነው በማለትም ይገልጻል።

ካምቤል አያይዞም ተረክ የእያንዳንዱ ሀይማኖት ምንጭ እንደሆነና ብሉይ ኪዳን(ሀዲስ ኪዳንን ጨምሮ) የፍልስፍና ድርሰት ሳይሆን የትልልቅ ታሪኮች ስብስብ እንደሆነ አስፍሯል። ክርስትናን ለልጆች ለማስተዋወቅ ሲሞከርም እምነትን ሳይሆን ለማስረጽ ጥረት የሚደረገው የተለያዩ ክንውን ተረኮችን ነው። በመካከለኛው ዘመን በትልልቅ ካቴድራሎች ውስጥ የሚገኙ ሀውልቶችና ስዕሎች የሚገልጹት የክርስቶስንና የቅዱሳኑን ተረኮች ነው። ይህም የሚያሳየው ሰዎች ሀይማኖትን ለመማር የሚሞክሩት በተረክ እንጂ በእምነት ባህርይ አይደለም በማለት ይገልጻል። የክርስትና ሀይማኖት ከሌሎች ሀይማኖቶች በበለጠ በተረክ ላይ ይመስረት እንጂ የሂንዱዝም፣ የቡድሂዝምና የእስልምና ሀይማኖቶችም ምንጫቸው በተረክ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ አስፍሯል።

ካምቤል ሀይማኖት የሚጀመረው/አዲስ ሀይማኖትም ጭምር/ የቅዱሳኑንና የነቢያቱን የህይወት ታሪክ ሰብስቦ በመተረክ እንደሆነ ጠቁሞ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ተራኪ/Story-telling/ በመሆኑ ሁሉም ማህበረሰብ የየራሱ ተራኪዎች አሉት ይላል። የሰው ልጅ ህሊና ተአምራዊና አስደናቂ ሁነት ያለባቸውን ተረኮች በሀይማኖት ውስጥ የመጨመር ስጦታ አለው። እነዚህም እንደእውነት ሆነው በመቆጠር እምነትን የሚያስፋፉ ሲሆን በሀይማኖቱ ውስጥም እንደሀቅና ታሪክ ሆነው ይካተታሉ በማለት አስፍሮ እናገኘዋለን። ከካምቤል ሀሳብ የምንረዳው የሰው ልጅ በሚፈጥራቸው ተረኮች ላይ እምነትን እንደሚመሰርትና እነዚህም ተረኮች የሀይማኖት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው። ዶርሰን ይህንን አስመልክቶ ተረክ የቀደመው ሰው ልማድና እምነት ምንጭ ነው (Dorson,1972,55) ይላል።

ስለዚህ ተረኮች የእምነትም ሆነ የሀይማኖት ምንጭ ናቸው ማለት ይቻላል። እንዲሁም ሀይማኖታዊ ተረኮች በተራኪዎቹ የሚፈጠሩና የሚካተቱ ከሆኑ የአንድን ማህበራዊ ቡድን እምነት፣ እሴትና ማንነት ምን እንደሚመስል ያሳያሉ ማለት ይቻላል።ይህንን አስመልክቶ ዶርሰን/Dorson/ የሰውን ልጅ የአስተሳሰብ ደረጃና እሴቶችን አካቶ የሚገኘው ስርዓተ አምልኮ /Sacred ritual/ በሀተታ ተፈጥሮ/Myth/ እና በአፈ.ታሪክ/Legend/ አማካኝነት ይገለጻል(Dorson,1972,219) በሚል አስፍሮ እናገኛለን። በመሆኑንም የፎክሎር ባለሙያው ተረኮችን በሚያጠናበት ጊዜ ትኩረት ማድረግ ያለበት በተረኮቹ ውስጥ ያሉት ድርጊቶች እውነት ወይም ሐሰት ስለመሆናቸው ማረጋገጫ በመፈለግ ላይ ሳይሆን በድርጊቱ ውስጥ የተራኪውንና የአድማጩን እምነት በመመርመር ላይ መሆን አለበት (Dorson,1972,55፤ Sims,2005,62) የሚለውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ይህ ጥናት በገዳሙ ውስጥ በሚነገሩ ተረኮች አማካይነት የገዳማውያኑን እምነት ለመመርመር ጥረት ያደርጋል።

ገዳማውያን ምን አይነት እምነት እንዳላቸው ለመመርመር ረቂቅ የሆነውን እምነታቸውን በተጨባጭ በሚያንፀባርቁባቸው ስርዓቶች /Rituals/ እና ተረኮች /Narratives/ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ የትኛውን ንድፈ ሃሳብ አስደግፎ መተንተን የተሻለ ነው? ቀጥዬ የምመለከተው የዚህን ጥናት ማጠንጠኛ ንድፈ ሃሳብ ነው።

## 2.1.5 ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ /functional Approach/

በአንድ የገዳም ማህበር እምነት/Belief/ ላይ ትኩረቱን ያደረገው ይህ ጥናት የሚመሰረትበት ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊ /Functional/ ንድፈ ሐሳብ ነው። ገዳማውያን የያዙትን እምነት ለምን ተግባር ይጠብቁታል? እምነታቸውን ከአንዱ ወደሌላው የሚያስተላልፉበት ምክንያት ምንድን ነው? እንዴትስ ያስተላልፉታል? የያዟቸውን እምነቶች ለምን ያምናሉ? በጥብቅ የሚጠብቁት እምነት እና እምነታዊ ድርጊት ለገዳማዊ ህይወታቸው ምን ፋይዳ አለው? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የገዳማውያኑን እምነት ካለው ሙያ(ተግባር)/Function/ አንጻር መመርመሩ የተሻለ ነው የሚል እምነት ስላደረብኝ በተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ/Theory/ ላይ ለመደገፍ ወሰኛለሁ። ከዚህ ሌላም ዶርሰን ፒተር ቦጋተዬሪቭን/Petr Bogatyrev/ ጠቅሶ ተግባራዊ /functional/ ንድፈ ሐሳብ ጥቅም ላይ ከሚውልባቸው መስኮች አንዱ ኃይማኖታዊ ፎክሎር እንደሆነ(Dorson,1972,25) ያሰፈረ በመሆኑ በዚህ ንድፈ ሐሳብ ላይ በመመስረት የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ለመተንተን ወስኛለሁ። በቅድሚያ ተግባራዊ /Functional/

ንድፈ ሐሳብ ቃላዊ፣ ልማዳዊና ቁሳዊ ስብስቦችን የያዙ ፎክሎሮች ለማህበሩ ምን እና እንዴት ይጠቅማሉ የሚለውን የሚያጠና ነው።

> እንደፎክሎር ባለሙያዎች ገለጻ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የአንድን ቡድን ቃላዊ፣ ተለምዶአዊና ጽሑፋዊ ሰነዶች በመመርመር ሰዎች እነዚህን ጉዳዮች ለመጋራት ካላቸው ጥቅም አንጻር ለምንና እንዴት በሚሉ ጥያቄዎች አማካይነት ፈትሾ ተግባራቸውን የሚያሳይ ንድፈ ሐሳብ ነው። ፎክሎርን ስለመተንተን ስንናገር ሰዎች ብዙ ጊዜ «ፎክሎር ለቡድኑ አባላት ምን ያስተላልፋል? ይህንን የሚጋራውስ ማን ነው?» የሚሉ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ። የፎክሎር ባለሙያዎች ፍች /meaning/ ፎክሎር በማህበር ውስጥ ያለውን ተግባር/ሙያ/ መመረመሪያ መንገድ መሆኑን ትኩረት ማድረግ አለባቸው(Sims, 2005, 175)።

ይላሉ። ተግባራዊ /functional/ ንድፈ ሀሳብ የፎክሎሩን ይዘት ከፎክሎሩ ባለቤት ጋር አጣምሮ ፎክሎሩ ባለው ፍች ላይ በመመስረት የፎክሎሩን ተግባር ለመተንተን የሚያስችል ንድፈ ሀሳብ ነው ማለት ይቻላል። ፎክሎር ለቡድኑ አባላት የሚያስተላልፈው ፍች ምንድን ነው? እነማን ናቸው ይህንን ፍች የሚጋሩት? የሚሉትን ጥያቄዎች እያነሳ ፎክሎር ለአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ያለውን ተግባር ያመለክታል። በአጠቃላይ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የአንድ ማህበር እምነት፣ ስርዓትና ትውፊት ባላቸው ፍች መነሻነት ለማህበሩ የሚያበረክቱትን አገልግሎት ተንትኖ የሚያቀርብ ንድፈ ሐሳብ ነው።

ኦሪንግ /Oring/ በተግባረዊ ንድፈ ሐሳብ የሚከተለውን ብያኔ አስፍሮ እናገኘዋለን። ተግባር ስንል አጠቃላይ በሆነ እንቅስቃሴ ወይም ስርአት/system/ ውስጥ የታቀፈ አንድ ወይም ከፊል ሁነት ለአጠቃላዩ እንቅስቃሴ ወይም ሁነት የሚያበረክተው ድርሻ ነው። በዚህ መሰረት አንድ ማህበረሰብ በቋንቋው ወይም በባህሉ አማካይነት የሚገልጸው ነገር ተግባር ሲባል የማህበረሰቡ፣ ማህበራዊ አደረጃጀት ወይም መዋቅር ባለበት ሁኔታ ተጠብቆ እንዲዘልቅ የሚያበረክተው ድርሻ ማለትም የማህበረሰቡን ህልውና በማስጠበቅ ረገድ ያለው ሚና ማለት ነው(Oring,1976,68)። የአንድ ሰው እያንዳንዱ የሰውነት አካል/ብልት/ የየራሱን ድርሻ ወይም ተግባር በተወጣ ቁጥር የሰውየው ሕልውና እንደሚጠበቅ ሁሉ በአንድ ማህበራዊ ቡድን ውስጥ የሚገኙ ፎክሎሮች የየራሳቸውን ተግባር በመወጣት የማህበራዊ ቡድኑ ማህበራዊ አደረጃጀት እንዲቀጠል ማድረግ ይችላሉ ማለት ነው።

ከተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ጋር በተያያዘ በቀዳሚነት ስሙ የሚጠራው ዊሊያም ባስከም /William R. Bascom/ ነው። እንደባስከም አመዳደብ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው የማስተማር ተግባር ነው(Sims,2005,175)። የማህበረሰቡ ሐብት የሆኑት ፎክሎሮች ማህበረሰቡ የሚከተለውን ሰርዓት፣ ህይወቱን

የሚመራበትን መንገድ፣ መልካም የሚባሉና የሚመሰገኑ ምግባራትን ያስተምራሉ፤ ያንጻሉ። ይህንን በሚመለከት ስነቃሎች የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ የአለባበስ፣ የአቀማመጥ፣ የአነጋገር፣ የአካሔድ፣ ስርዓትን ያሳውቃሉ። በህይወት ውስጥ የትጋትን፣ የለጋስነትን፣ የህብረትን፣ ጥቅም አጥብቀው ይሰብካሉ በማለት ፈቃደ (1991፣20) አስፍሯል።

ሁለተኛው የፎክሎር ተግባር እንደሆነ በባስከም የተጠቀሰው የማምለጥ ተግባር ነው። ባህልና ልማድ በሰው ልጅ ላይ ከጫነበት ደንብ፣ እንዲንቀሳቀስ ከወሰነበት ቁሳዊ የባህል አጥር/ድንበር/ በተለያዩ ፎክሎሮች በመዝናናት የሚያመልጥበት ስልት ነው (Sims,2005,176)። የሰው ልጅ ከወትሯዊው የእለት ተእለት የህይወት ውጣ ውረድ ማምለጥ ይፈልጋል። ከአሰልችና ከተደጋጋሚ የህይወት ክስተቶች ሸሽቶ በምናቡ አዲስ አለም ውስጥ መግባት ይሻል(ፈቃደ፣ 1991፣18)። በመሆኑም ሰው በፎክሎር እየተዝናና የሚያስበውን ነገር ሁሉ ከህብረተሰቡ ህግ አፈንግጦ በመግለጽ ያመልጣል። ለምሳሌ ተራቹ የራሱን የፈጠራ ሀሳብ እንዲጨምር እድል የሚፈጥርለት ሲሆን አድማጩም በተራቹ የፈጠራ ችሎታ እየተዝናና ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ከባህላዊው ድንበር አልፎ እንዲሄድ እድል ያገኛል። እነዚህ ፎክሎሮች የሰው ልጅ ለተወሰነ ጊዜ የሆነውና የተደረገው ነገር ሁሉ እንዳልሆነና እንዳልተደረገ፤ ያልሆነውንና ያልተደረገውን ጉዳይ እንደሆነና እንደተደረገ አድርጎ እንዲያስብ ስለሚያችሉት ከመደበኛው ህይወት ወጥቶ አዲስ ህይወት ውስጥ እንዳለ አድርጎ በመቁጠር የተወሰነ እረፍት ያገኝበታል ማለት ይቻላል።

ባስከም በሦስተኛ ደረጃ የገለጸው የፎክሎር ተግባር የመጠበቅ ወይም የመቆጣጠር ተግባር ነው። ፎክሎር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያገኙ ተመሳሳይ ባህርያትን የመጠበቅ ወይም የመቆጣጠር ተግባር አለው። ባህል በፈለገ ጊዜ አንድን ሰው ወደተረጋገጠ የባህርይ መስመር ይመልሳል (Sims,2005,176)። ይህም ማህበሩ ምስጉን እና ድንቅ ከሚላቸው እሴቶች የሚያፈነግጡትን ወይም ለማፈንገጥ ገና ዳር ዳር የሚሉትን በ«አርፈህ-ተቀመጥ» ግሳጼ ወደ ብዙሀኑ አስተሳሰብ መመለስ ነው(ፈቃደ፣ 1991፣20)። ማህበረሰቡ ትክክል አይደሉም የሚላቸውን ስነምግባሮች እንዳይደረጉ፣ እንዳይስፋፉ በመጠበቅ የማህበሩን ደህንነት ለመቆጣጠር ጥረት ያደርጋሉ። እነዚህ ፎክሎሮች ማህበሩ ስህተት የሚላቸው ባህርያት በማረም ትክክለኛ ነው በሚለው መስመር ውስጥ አባላቱ እንዲንቀሳቀሱ የመጠበቅ ተግባር አላቸው።

እንደባስከም አከፋፈል አራተኛው የፎክሎር ተግባር የባህልን ትክክለኛነት /ምክንያታዊነት/ የማረጋገጥ ወይም የማጽደቅ ተግባር የተባለው ነው። ስርዓትን በማክበር፣ እነዚህ ድርጊቶችና ሁነቶች በማህበረሰቡ ህይወት ውስጥ ቦታ እንዲኖራቸው በማድረግ ባህልን የማረጋገጥ ተግባር ይፈጽማሉ(Sims,2005,176)። የአንድ ቡድን ፎክሎር በተለይ በሐተታ ተፈጥሮ አማካይነት እምነቶችን፣ ባህርያትንና ስርዓቶችን የማጽናት ተግባር አለው (Dorson, 1972, 22)። ፈቃደም ይህንን ሃሳብ በመደገፍ የቡድኑን አባላት በስነቃል አማካይነት ከልደት እስከሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ ክንዋኔዎቹ እንዳይከስሙ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ(ፈቃደ፣ 1991፣18) ይላል። ይህ የፎክሎር ተግባር ማህበሩ በሚከተላቸውና በሚያከብራቸው እምነቶች፣ እሴቶችና ትውፊቶች ውስጥ ያሉ ጉዳዮች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ የማሳየት ወይም የማጽደቅ ተግባር አለው። በመሆኑም ፎክሎር እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች ለጊዜው ብቻ ሳይሆን ለወደፊትም እንዲቀጥሉ በተለያዩ ሁኔታዎች አማካይነት የማጠናከር ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

ፎክሎር የነበረውን ባህል ቀጣይነቱ እንዲጠበቅ የሚያደርግ ጠቃሚ መንገድ ነው የሚለው የባስከም ድምዳሜ በእምነትና በአመለካከት ውስጥ ያለውን ለውጥ የማያካትት መሆኑ በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ላይ እንደድክመት የሚጠቀስ መሆኑንም ያስረዳል። ከዚህ ሌላም ይህ ንድፈ ሀሳብ በራሱ ወግ አጥባቂና ለተለያየ አመለካከት እድል የማይሰጥ /ግትር/ ነው የሚል ትችት በብዙ ምሁራን እንደሚቀርብበት እነ ስሚስ ይገልጻሉ(2005,177) ። ሆኖም ንድፈ ሀሳቡ ካሉት አዎንታዊ ገጽታዎች ውስጥ አንዱ ለፎክ ቡድኑ ትኩረት ያደረገ መሆኑና ፎክሎር በቡድኑ አባላት ፍች እንዳለው ተደርጎ እንዲታሰብ ማድረግ መቻሉ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው። እንዲሁም ፎክሎሮች በቡድን አባላት መካከል ዋጋ የሚሰጣቸው እሴቶችና መረጃዎች የመለዋወጫ መንገዶች መሆናቸውን ማሳየቱ (Sims,2005,176) ለፎክሎር ባለሙያዎች ትልቅ አስተዋጽኦ ሳያበረክትላቸው እንዳልቀረ መገመት ይቻላል። በዚህም ምክንያት ይመስላል የፎክሎር ባለሙያዎች በፎክሎር ፍች ላይ ትኩረት እያደረጉ የመጡት። እነሲምስ እንደሚሉት የፎክሎር ቡድኖች ፎክሎርን እንዴት እንደሚጠቀሙበትና ፎክሎር ለቡድኑ አባላት ምን ማለት እንደሆነ ያለውን ስሜት ለማጥናት አስችሏል(Sims, 2005, 176)።

ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ እንደማንኛውም ንድፈ ሀሳብ ድክመትና ጥንካሬ ያለው ቢሆንም የዚህ ጥናት ማጠንጠኛ ንድፈ ሀሳብ እንዲሆን መርጬዋለሁ። ይህንንም ለመወሰን ምክንያት የሆነኝ የገዳማውያኑ እምነትና እምነታዊ ድርጊት ለገዳማዊ ህይወታቸው ያለው ፋይዳ/ጥቅም/

ምንድን ነው የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የተረኮችና የስርዓቶችን ፍች ለማወቅ እንደሚያስችለኝ በመተማመን ነው። በመሆኑም በገዳሙ ውስጥ የሚፈፀሙት ስርዓቶችና የገዳሙን አመሰራረት ምክንያት በማድረግ የሚነገሩ ተረኮች ያላቸውን ፍች በመመርመር ለገዳማውያኑ ገዳማዊ ህይወት ያላቸውን ተግባር/ሙያ/ ለማሳየት ጥረት አደርጋለሁ። ምንም እንኳን ባስከም የገለጻቸውን አራቱንም የፎክሎር ተግባራት የሚመለከቱ ጉዳዮች አልፎ አልፎ መታየታቸው ባይቀርም በዋናነት የምመሰረተው ግን ፎክሎር ባህልን የማጠናከርና የማጽደቅ ተግባር አለው በሚለው ላይ ይሆናል።

## *2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት*

ገዳምና የገዳማትን አመሰራረት ርዕስ ጉዳያቸው በማድረግ በመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ የተሰሩ በርከት ያሉ የመመረቂያ ጽሑፎች አሉ። በተለይም በታሪክና በስነመለኮት ክፍለ ትምህርት ትኩረታቸውን ገዳም ወይም ደብር ያደረጉ በርካታ ጥናቶች ቢኖሩም ለዚህ ጥናት የበለጠ ቅርበት አላቸው ያልኳቸውን ጥናቶች ቃኝቻቸዋለሁ። ከዚህ ውጭ በስነጽሁፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ለማስተርስ ዲግሪ የተሰሩና ከእኔ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የመመረቂያ ጥናቶችም ለመቃኘት ሞክሬአለሁ።

### 2.2.1 በክፍለ ትምህርቱ የተሰሩ ጥናቶች ቅኝት

ታደሰ(1999 ዓ.ም.) በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት «በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ስርዓት እና የገዳማውያን የዕለት ተዕለት ሕይወት ከትዕምርታዊነቱ አንፃር በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳማት» በሚል ርዕስ ጥናቱን አድርጓል።

አጥኚው በአንድነት ገዳማት ውስጥ የሚኖሩ መነኮሳትን የየዕለት ሕይወት መመልከትና የመገልገያ እቃዎችን፣ በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ነገሮች፣ አለባበስ፣ አመጋገብና የፀሎት ስርአታቸውን እንዲሁም የገዳማቱን የአስተዳደርና የሥራ መዋቅር፣ ወዘተ ከትዕምርቱ አንፃር በማገናዘብ መመርመር የጥናቱ ዓላማ መሆኑን ገልጿል። አይይዞም የገዳማውያንን እረፍት፣ ግንዘት እና ፀሎተ ፍትሃት ምሳሌነቱን መሠረት በማድረግ መመርመር ሌላው የዚህ ጥናት ዓላማ እንደሆነ አስፍሯል።

ታደሰ በዚህ ጥናት የገዳማቱን የአስተዳደር ስርአትና የሥራ መዋቅር በተለይም የአበምኔት አመራረጥና የሥራ ኃላፊነት ምን እንደሚመስል ተመልክቷል። አያይዞም የግጭት አፈታት ዘዴና በጥፋተኞች ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች፣ የእንግዶችና አዳዲስ አባላት አቀባበል ምን እንደሚመስ፣ የምንኩስና አቀባበል ስርአት ምን አይነት እንደሆነ ገልጿል።

በዚህ ጥናት ሌላው ትኩረት የተሰጠው ነጥብ የመነኮሳት ገዳማዊ ሕይወት ምን አይነት እንደሆነ መዘርዘር ነው። በመሆኑም የገዳማውያኑን የአመጋገብና የፀሎት ስርአትና ጊዜ፣ የሥራ ክፍፍልና አይነት፣ አለባበስ፣ የመነኮሳት ጡረታና እረፍት ምን እንደሚመስል ዘርዝሮ አቅርቧል። የጥናቱም መተንተኛ ዘዴ ገላጭ (descriptive) የምርምር ዘዴና በትዕምርታዊ መስተጋብራዊነት ቲዎሪ (symbolic interactionism theory) ነው።

ፍሬሕይወት (2000) ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት «በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊ ገጽታ» በሚል ርዕስ ጥናት አድርጋለች። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ንዋየ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየት መሆኑ ተገልጿል።

ፍሬህይወት በጥናቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ከሃይማኖታዊ ገጽታ አንፃር፣ ስለ ንዋየ ቅድሳት ምንነትና የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ከንዋያተ ቅድሳቱ ጋር ስላላቸው ግንኙነት አመልክታለች። አያይዛም የንዋየ ቅድሳት አሠራር ምን እንደሚመስል፣ አገልግሎታቸውና ምሳሌነታቸው ምን እንደሆነ በዝርዝር አቅርባለች።

ሌላው በዚህ ጥናት ትኩረት የተሰጠው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ፎክሎራዊ ገጽታ ምን መልክ እንዳለው ማሳየት ነው። በዚህም ሥር የንዋየ ቅድሳቱን ቁሳዊ የባህል ገጽታ፣ የኅገረሰባዊውን ጥበባት ገጽታና የሀገረሰባዊ ልማድ ገጽታ ትንታኔ የተሰጠበት ሲሆን የንዋየ ቅድሳቱ የተለዋዋጭነት ባህርይ ምን እንደሚመስል በዝርዝር ቀርቧል። ለጥናቱ የተመረጡት ስልቶች አሳሽና ገላጭ ዘዴዎች ሲሆኑ የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት ፎቶግራፍ ከገለፃው ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

ወርቁ (2000) ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት «በሊሙና ቢልቢሎ ወረዳ፣ የጨፌ መድኃኔዓለም፣

ደብረቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም አመሠራረት ፎክሎራዊ ገጽታ» በሚል ርዕስ ጥናቱን አቅርቧል።

የወርቁ ጥናት ዓላማ የገዳሙን አመሠራረት እና በገዳሙ ውስጥ በፈለቀው ፀበል፣ ፀበል የማጥመቅ ሥነ ሥርአትና በገዳሙ የሚኖሩት መነኮሳት የሚፈጽሟቸውን ፎክሎራዊ ገጽታዎች ማሳየት ነው።

የዚህ ጥናት ትኩረት ገዳሙ በአመሰራረት ሂደቱ ምን ምን ድርጊቶች እንደተከናወኑበት፣ ለገዳሙ መመስረት ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምን እንደሆነ፣ ለመመስረቱ ምክንያቱ ማን እንደሆነ፣ ገዳሙ በዚያ አካባቢ በመመስረቱ እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ምን እንደሚመስል አሳይቷል።

አጥኚው በገዳሙ አመሠራረት የሚስተዋሉ ፎክሎራዊ ገጽታዎችን ማለትም ሃገረሰባዊ ትረካዎች፣ አፈ ታሪኮችና ሌሎች በገዳማውያኑ አኗኗር የሚስተዋሉ ፎክሎራዊ ገጽታዎችን ተመልክቷል።

## 2.2.2 ከክፍለ ትምህርቱ ውጭ የተሰሩ ጥናቶች ቅኝት

ጥጋብ (2001) "THE ETHIOPIAN CLAM ON THE MONASTERY DEIR ES-SULTAN IN JERUSALEM, 1850-1994" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ ለታሪክ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት አድርጓል። የጥናቱ ዋና ትኩረት ገዳሙ ከተመሰረተ በኋላ ከ1850ዎቹ እስከ 1994(እ.ኤ.አ) ድረስ ገዳሙ የገጠሙት ተግዳሮቶች ምን እንደሚመስሉ በዝርዝር ማሳየት ነው። አጥኚው በቅድሚያ ስለዴርሱልጣን ገዳም አመሠራረት አስፍሯል። ከዚህም ጋር አያይዞ ስለ ኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ ጉዞና በኢየሩሳሌም ውስጥ ቋሚ ርስት መመስረት ገልጿል።

ጥጋብ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያውያን መንፈሳዊ ቡድኖች አቅም እንዴት እየተዳከመ እንደመጣ ዘርዝሯል። በኢትዮጵያውያን እጅ የነበሩ የቅዱሳን መካናት እንዴት ሊነጠቁ እንደቻሉና በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያውያን የነበራቸውን ቁልፍ ቦታ እንዴት እያጡ እንደመጡም አሳይቷል። ከዚህም ጊዜ ጀምሮ እነዚህ መካናት በኢትዮጵያ እና በግብጽ መካከል የይገባኛል ክርክራቸው ዋና ምክንያት መሆናቸውን ከገለጸ በኋላ አፄ ዮሐንስ 4ኛና ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ስላደረጓቸው የዲፕሎማሲ ጥረቶች ዘርዝሯል።

ጥጋብ በመጨረሻም ዮርዳኖስ እስራኤልን በምትገዛበት ወቅት ኢትዮጵያውያን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ መቆየት የቻለ ስኬት ማግኘት እንደቻሉ፣ በኋላ ግን ጉዳዩ ውስብስብ እየሆነ እንደመጣና የእስራኤልን ፖለቲካ ለማሳካት የተነደፈው ዘዴ በዴርሱልጣን ጉዳይ ላይ ተጽእኖ እንዳሳረፈበት ዘርዝሯል። በመጨረሻም የቅዱሳን መካናት ይገባኛል ጥያቄ አሁንም ድረስ አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ እንደቀጠለ ገልፆ ጥናቱን አጠናቋል።

**ሀይለማርያም** (1991) ˝The Addis Ababa Ganata_ Iyasus Monastery˝ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ ለታሪክ ትምህርት ክፍል ለመጀመርያ ዲግሪ ማሟያነት ጥናቱን አቅርቧል። ጥናቱ በቤተክርስቲያን የስራ ሂደትና በገዳሙ ምስረታ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ ባበረከቱት በራስ ካሳ የስራ ድርሻ ላይ ያነጣጠረ ነው። አጥኚው ከዚህ ጋር አያይዞ ገዳሙ ከመመስረቱ በፊት አሁን በገዳሙ ውስጥ የሚገኘው ፅላት በምን መንገድ እንደተገኘና ከየት እንደተገኘ ገልጿል።

አጥኚው ይህ ፅላት ወደአዲስ አበባ ከመምጣቱ በፊት ራስ ካሳ በሚኖሩበት ፍቼ አካባቢ በሚገኘው በቀራንዮ መድሀኔአለም ቤተክርስቲያን ውስጥ እንደነበርና በኋላም በቆይታ በአዲስ አበባ ቤተክርስቲያን ታንፆለት እንደገባ ዘርዝሯል። ራስ ካሳ ይህንን ቤተክርስቲያን ወደገዳምነት ለመለወጥ በአዲስ አበባ የሚገኙትን ቀሳውስት ሰብስበው ውይይት እንዳደረጉና ሴቶች ወደገዳሙ እንዲገቡ ድርድር እንደተደረገ አስፍሯል። በመጨረሻም በጣሊያን ጦርነት ውቅት ቤተክርስቲያኑ ስለደረሰበት ችግር በመዘርዘር ጥናቱን አጠናቋል።

**መዝገቡ** (2001) ˝The Mystical Experience of the Monastic Life in the Traditional context of the Ethiopian Orthodox Tewahido church˝ በሚል ርዕስ ለስነመለኮት ትምህርት ክፍል ጥናቱን አቅርቧል። የአጥኚው የጥናት ትኩረት እንዲጠብቋቸው በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አባቶች የጻፏቸውን ህጎችና መተዳደሪያ ደንቦች መመርመር እንደሆነ ገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ ገዳማውያን የእግዚአብሔርን መንገድ ተከትለው የሚሄዱበትን አቅጣጫ ካለው ልማድ ጋር እያገናዘበ ማቅረብ ሌላው የዚህ ጥናት ትኩረት መሆኑን አስቀድሞ አስፍሯል።

አጥኚው የጥናቱን ክልል በዚህ መልክ ካስተዋወቀ በኋላ የምንኩስና ስርዓትን፣ የምንኩስና አመሰራረት እና በምንኩስና ህይወት ውስጥ የመንፈሳዊ አኗኗር ልምምድን ሁኔታ ዘርዝሯል።

ከዚህም ጋር አያይዞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እና ገዳማት እድገትና መስፋፋት ምን እንደሚመስል ተመልክቷል። ለዚህም ከታሪካዊ ዳራው አንጻር እያነጻጸረ ለማሳየት ሞክሯል። አጥኝው መረጃዎችን የሰበሰበው ከአምስት የአንድነትና የህግ ገዳማት ነው።

መረጃ የተሰበሰበባቸው ደብረሊባኖስ አቡነ ተክለሀይማኖት፣ ማህበረ ስላሴ፣ ሀይቅ እስጢፋኖስ፣ ሰበታ ቤተደናግልና አዲስ አበባ ምስካየ ህዙናን መድህኔአለም ገዳማት ናቸው። አጥኝው ገዳማዊ ህይወት ምን እንደሚመስል አስፍሯል። ከዚህም ጋር በተያያዘ በተለያዩ አባቶች ተጽፈዋል የሚባሉት የምንኩስና ስርዓትና ደንቦች በገዳማውያኑ ዘንድ በምን ያህል መጠን ተግባራዊ እየሆኑ እንዳለ አሳይቷል።

ሚካኤል (2002) ″Monastic Life and Related Problems in the 20th Century in the Ethiopian Orthodox Church″ በሚል ርዕስ ለስነመለኮት ትምህርት ክፍል ያቀረበው ጥናት ለዚህ የተዛማጅ ጥናት ቅኝት ሌላው ተጠቃሽ ጥናት ነው። አጥኚው ለጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የመነኮሳትን የእለት ከእለት የገዳም ህይወት መመርመርን ነው። ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎች ከአምስት ገዳማት ተሰብስበዋል። በዚህ ጥናት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የመነኮሳቱ ማህበራዊ ገጽታ፣ መነኮሳቱ ከገዳሙ ውጭ ካለው ማህበረሰብ ጋር የላቸው ቁርኝትና በዘመን ሂደት በገዳማቱ ስርዓትና በገዳማውያኑ አኗኗር ላይ የታየው ለውጥ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው።

አጥኝው የዘመኑ ወጣቶች ገዳማዊ ህይወትን የሚመርጡበት ምክንያት ምን እንደሆነ እና የመነኮሳቱ ገዳማዊ ህይወት የሚመዘንባቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምንኩስናን በማስመልከት የወጡት ህጎችና መመሪያዎች ምን መልክ እንዳላቸው ዘርዝሮ አቅርቧል። አያይዞም የዘመኑ ስልጣኔ በዚህ የገዳማዊ ህይወት ላይ ያለው አወንታዊና አሉታዊ ተጽእኖ ምን እንደሚመስልና በ1967 ዓ.ም በመሬት ላራሹ አዋጅ ምክንያት ገዳማት መሬቶቻቸውን ሲወረሱ በገዳማውያኑ ላይ የደረሱባቸው ችግሮች ምን መልክ እንዳላቸው አሳይቷል።

ከላይ ለመቃኘት የተሞከሩት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር አንድነት ባይኖራቸውም በተወሰነ መልኩ ዝምድና አላቸው ማለት ይቻላል። የጥናቶቹ ክልል በገዳማትና ደብሮች ላይ መሆኑ አንዱ የሚያመሳስላቸው ጉዳይ ሲሆን የተወሰኑት ጥናቶች በገዳማትና ደብሮች አመሰራረትና

በገዳማውያኑ ህይወት ላይ ትኩረት ማድረጋቸው ሌላው ተመሳስሏቸው ነው ማለት ይቻላል። ይህ ጥናት በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ ከአመሰራረቱ ጋር ተያይዘው በሚተረኩ ተረኮችና አምልኳዊ ስርዓቶች ውስጥ የሚታየው የገዳማውያኑ እምነትና እምነታዊ ድርጊት ለገዳማዊ ህይወታቸው ያለውን ፋይዳ መመርመር በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር መጠነኛ የሆና ዝምድና አላቸው። ነገር ግን ከዚህ ጥናት ጋር የበለጠ ቅርበት ያለው የታደሰ አይችሉህም ጥናት ነው። ይህ ጥናት ከታደሰ ጥናት የሚለየው በተረኮችና አምልኳዊ ስርዓቶች በሚገለጸው እምነትና እምነታዊ ድርጊት የሚመሰረት መሆኑ ነው። የታደሰ ጥናት ትኩረት በሁለት ገዳማት በሚገኙ በገዳማውያን የእለት ከእለት ህይወት የሚንጸባረቁ ስርዓቶች ከትዕምርታዊነታቸው አንጻር መመርመር በመሆኑ ሁለቱ ጥናቶች ስርዓት በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ይመሳሰላሉ።

በመሆኑም ታደሰ የመነኮሳት ገዳማዊ ህይወት በሚለው ምዕራፉ ስለጸሎትና አመጋገብ ስርዓት፣ ስለስራ ክፍፍልና አይነት፣ ስለገዳማውያን አለባበስና ስለመነኮሳት ጡረታና እረፍት፣ ስለምንኩስና አቀባበል ስርዓት የተመለከታቸው ስርዓቶች ምንም እንኳን በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚፈጸሙ ቢሆንም ድግግሞሽ እንዳይፈጠር በሚል ይህ ጥናት አላካተታቸውም። ይሁን እንጂ ታደሰ ስለተግባር ቤት፣ ስለግጭት አፈታትና ስለአበምኔት ምርጫ ያሰፈረው ሃሳብ ይህ ጥናት ትኩረት ባደረገበት ገዳም ስርዓቱ የተለየ ሆኖ ስላገኘሁት በድጋሚ በዚህ ጥናት እንዲካተቱ አድርጌአቸዋለሁ።

# 3. የገዳም ህይወት አጀማመር እና በጣና ሐይቅ ደሴቶች ውስጥ የሚገኙ ገዳማት

## *3.1 በኢትዮጵያ የገዳም ህይወት አጀማመር እና የገዳም ኑሮ አይነቶች*

በኢትዮጵያ የገዳም ህይወት አጀማመር ምን እንደሚመስል ከማየታችን በፊት ለመንደርደሪያ ያህል ዓለም አቀፍ ጅማሮው ምን እንደሚመስል በጥቂቱ እንመልከት። የምንኩስና /የብህትውና/ ሕይወት የክርስትና ሃይማኖት ከመጀመሩ በፊት በምስራቅና በሩቅ ምስራቅ አገሮች ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች ዘንድ ተግባራዊ የሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ነው (ምክረሥላሴ፣ 2000፣356)። ለምሳሌ ከቅድመ ልደተ ክርስቶስ/ቅ.ል.ክ./ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት የነበሩት <ኤሴኔስ>[1] የተባሉት የአይሁድ ማህበረሰብ አባላት ከጨው /ሙት/ ባሕር በስተሰሜን ምዕራብ ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ በኩል ኩምራን (Kumran) በሚባል ሥፍራ በገዳም ውስጥ ማህበር መስርተው ይኖሩ ነበር(ምክረ ሥላሴ፣2000፣ 358፤ ገሰሰ፣ 1998፣ 15)። እነዚህ መናንያን ናዝራዊ[2] በመባል ይጠራሉ። መቅደሳቸው ጋዲ በሚባል በረሃ ውስጥ ይገኝ ስለነበር ለፀሀዩ ዋዕይ ሲሉ እንደቆብ ያለ ነገር በራሳቸው ላይ ያደርጉ ነበር(ልዑለ ቃል፣ 2002፣83)።

ከክርስቶስ ልደት በኋላ ደግሞ ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው የኤሴኖች ማህበር በነበረበት ሁኔታ ቀጥሎ ዮሐንስ መጥምቁን የመሰለ ተጠቃሽ ባህታዊ አፍርቷል። ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ/ቆሮንቶስ በረሃ/ ገብቶ በብህትውና ቆይቷል (ምክረሥላሴ፣ 2000፣357፤ ሰሎሞን፣ 2001፣87፤ ተከስተ ብርሃን፣1995፣7)። ከክርስትና መጀመርም በኋላ ይህ የምንኩስና /የብህትውና/ ኑሮ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በነበሩ ክርስቲያኖች ዘንድ የተለመደ እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ዕብራውያን ሰዎች ላይ «ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ ዓለም

---

[1] ኤሴኔስ፣ መሲህ መጥቶ የጦር ኃይልን አቋቁሞ ፍልስጤምን ነፃ ያወጣል የሚለውን የፈሪሳውያን እምነትና ተስፋ ተቃውመው ሌላ ንዑስ ቡድን በመፍጠር ከፈሪሳውያን ተከፍለው በምዕራባውያን ሰሜን ሙት ባህር /ዮርዳኖስ አካባቢ/ ገዳም መስርተው ይኖሩ ነበር። ልዩ ስሙ ኩምራን በተባለው ቦታ የሚኖሩት እነዚህ ወገኖች መጻህፍትን በመጻፍ ልዩ ልዩ የእጅ ስራዎችንና የግብርና ስራን መተዳደሪያቸው በማድረግ፣ ጸሎትን በማድረስ፣ ሰንበትን በማክበር፣ኃጢአትን ለማስወገድ የንፅህና፣ የጥምቀት፣ የንስሃና የኑዛዜ ስርዓትን በመፈጸም ይኖሩ ነበር። ኤሴኖች/ኤሴኔስ/ በዚህ ስርዓተ ብህትውና ተጠምደው ሲኖሩ በ 68 ዓ.ም በአይሁዳውያን ነፃ አውጭ ኃይሎች ጦርነት ምክንያት ይህ ገዳም የነፃ አውጪ ግንባሮች ደጋፊ እንደሆኑ ተቆጥሮ ሮማውያን ፈፅመው ደመሰሱት(ገሰሰ፣1998፣15)።

[2] ናዝራዊ፣ ማለት ከክፉ ነገር ሁሉ የተከለከለ፣ ስዕለት፣ ብጽአት ያለበት፣ መላ ህይወቱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ፣ በሰውነቱም ሁሉ የተቀደሰና የተለየ ማለት ነው(ልዑለ ቃል፣2002፣84)።

አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፣ በዋሻና በምድረ ጉድጓድ ተቅበዘበዙ» /ዕብ.11፣37/ በሚል የሰፈረውን ሀሳብ በመጥቀስ ይገልጻሉ (ማህበረ ቅዱሳን፣1987፣9፤ ያረጋል፣ 1985፣ 186)። የመጀመሪያው የምንኩስና ደረጃ በግል የሚደረግ የብህትውና ወይም የምነና ኑሮ ሲሆን ምንም እንኳን በተባሕትዎ መኖር ከጥንት ዘመን የመጣ ይሁን እንጂ በግብጽ ሀገር የብሕትውናን ኑሮ የጀመረው በ250 ዓ.ም አባ ጳውሊ ዘዱብ የተባለው ባህታዊ ነው(ምክረሥላሴ፣ 2000፣ 359፤ ማህበረ ቅዱሳን፣1987፣9፤ ያረጋል፣ 1995፣ 188፤. Tsirpanlis,1991,152)። ቀጥሎ የመጣው ባህታዊ አባ እንጦንስ ሲሆን በእሱ ሕይወት የተማረኩ ባህታውያን በእሱ በአት/መኖሪያ/ ዙሪያ ባሉ ዋሻዎች መኖር ጀመሩ(ምክረ ሥላሴ፣2000፣316፤Tsirpanlis,1991,152፤ያረጋል፣1995፣188፤ሰሎሞን፣2001፣88፤ ተከስተ ብርሃን፣ 1995፣ 5)።

በኋላም ብቻቸውን በብህትውና ከሚኖሩት ሌላ ብዙ መነኮሳት በአንድነት በመኖር እያንዳንዳቸው በአንድ አበምኔት ስር የሚተዳደሩ ብዙ አንድነት ገዳማት በየቦታው መመስረት ጀመሩ። የገዳምን ህይወት በ325 ዓ.ም ታቤኔ በሚባል ስፍራ የጀመሩት ግብፃዊው አባ ጳኩሚስ ሲሆኑ ከመሞታቸው አስቀድሞ መልአክ ተገልጦ መነኮሳቱ የሚተዳደሩበትን ደንብ እንደ ገለፀላቸው ይነገራል(ምክረ ሥላሴ፣2000፣370፤ ማህበረ ቅዱሳን፣1987፣9፤ ሰሎሞን፣ 2001፣93)።

በግብጽ የተጀመረው የምንኩስና ስርዓት በመላው የመካከለኛው ምስራቅ ተስፋፍቶ እጅግ ብዙ ገዳማት ተመስርተዋል። ቅዱስ ኤዎስጣቴዎስ የተባለው ጳጳስ ምንኩስናን በአርመን ያስፋፋ ሲሆን የቂሳሪያ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ባስልዮስ (330-379) በታናሿ እስያ (ዛሬ ቱርክ በሚባለው አካባቢ) የምናኔን ኑሮ በመመስረት ዛሬ በግሪክና ሩሲያ አብያተ ክርስቲያናት የሚገለገሉበትን የመነኮሳት ሕግ አውጥቷል። ሶሪያዊው ቅዱስ ኤፍሬም በበኩሉ በሶሪያና በመሶጴጦምያ አያሌ ገዳማት እንዲመሰረቱ አድርጓል። ቅዱስ ሂላሪየን (st Hilarion) ደግሞ በፍልስጤም ጋዛ ውስጥ ገዳማዊ ሕይወት በመጀመር አስፋፍቷል(ምክረ ሥላሴ፣2000፣371፤ Tsirpanlis, 1991,153፤ ያረጋል፣1995፣193፤ ማህበረ ቅዱሳን፣1988፣10)

በምዕራባውያን የምንኩስናን ህይወት ከግብፅ በመማርና በመለማመድ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ገዳማትን በመመስረትና በማስፋፋት የእስክንድርያው ፓትሪያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ፣ የሚላኖው ጳጳስ ቅዱስ አምብሮስ (Ambrose)፣ ማርቲን ኦቭ ቱርስ /Martin of

Tours/ የተባለው የፈረንሳይ ጳጳስ እና ቤኔዲክት (Benedict of Nursia)፣ ተጠቃሾች ናቸው (ምክረ ሥላሴ፣2000፣372፤ማህበረ ቅዱሳን፣1988፣11፤ Tsirpanlis,1991,156)።

በመካከለኛው ምሥራቅም ሆነ በምዕራብ አገሮች አንድነት ገዳም ከመመስረቱ በፊት በቅድሚያ የብህትውና ኑሮ እንደነበር ይነገራል። የምንኩስና ሕይወት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በአምስተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ በአባ ጳኩሚስ ዘመን ቢሆንም የብህትውና ኑሮ በሀገሪቱ ከተጠቀሰው ጊዜ ቀደም ብሎ እንደተለመደ የሚጠቁሙ አንዳንድ መረጃዎች አሉ። ከእነዚህም መረጃዎች ውስጥ ስርዓተ ምንኩስና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት አባ አሞንዮስ የተባለ ባህታዊ በተንቤን ቆላ ደብረ አንሳ በተባለው በረሃ በፆምና በፀሎት ተወስኖ ይኖር ነበር። እንዲሁም አባ ዮሐኒ የተባለ ባህታዊ በብህትውና ሲጋደል ከቆየ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ብሔረ ሕያዋን በመላዕክት እጅ እንደወሰደው ይነገራል(ማህበረ ቅዱሳን፣1988፣11)።

ገዳማዊ ሕይወት በኢትዮጵያ ውስጥ ከመጀመሩ በፊት ጥቂት ኢትጵያውያን መናንያን በተለያዩ የግብጽ ገዳማት ይኖሩ ነበር። ከእነዚህም ውስጥ በተለይ በግብፅ ቤተክርስቲያን ዘንድ በተጋድሎው የሚታወቀውና በቅድስናው የሚከበረው ሙሴ ጸሊም አስቄጥስ ገዳም ውስጥ እንደነበረ ይገለፃል(ያረጋል፣ 1995፣ 195)።

ገዳማዊ ሕይወት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ስማቸው ጎልቶ በሚታወቀው ቀድሞ ዘሚካኤል በኋላ አባ አረጋዊ  በተሰኙት መናኝ አማካይነት ነው። አባ አረጋዊ ተሰዐቱ/ዘጠኙ/ ቅዱሳን ከሚባሉት አንዱ ናቸው። እኒህ መነኩሴ ቅዱስ ጳውሎስ ካረፈ በኋላ በእርሱ እግር በተተካው ደቀ መዝሙሩ በቅዱስ ቴዎድሮስ አማካይነት ምንኩስናን ተቀብለውና ስርዓተ ገዳምን አጥንተው ከሌሎች ስምንት መነኮሳት ጋር በመሆን ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ ይነገራል። ዘጠኙ ቅዱሳን የሚባሉት ሮማውያን በኬልቄዶን ጉባኤ ያልተስማሙትን አባቶች በሚያሳድዱበት ዘመን ከሮም፣ ከትንሹ እስያና ከመካከለኛው ምስራቅ የተሰደዱ ሲሆን ምንኩስናን ከግብፅ ተምረው በ480 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል (ያረጋል፣1995፣195፤ ማህበረ ቅዱሳን፣1988፣11 ፤ተከስተ ብርሃን፣1995፣5)።

ዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ ጀምሮ ሁሉም የየራሳቸውን ገዳም መስርተዋል። በተለይ አባ አረጋዊ የመሠረቱት ደብረ ዳሞ ገዳም ለምንኩስና መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ኢትዮጵያውን አባቶችን ያፈራ ገዳም ነው። ሰሎሞን የዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ለክርስትና እምነት መስፋፋትና አሁን ላለበት እድገት ካለው አስተዋጽኦ በተጨማሪ

ለቅዱሳት መጻሕፍት መጻፍና መተርጎም አይነተኛ ሚና ነበረው ይላል። ከዚህ በተጨማሪም ለትምህርት፣ ለማህበራዊ ኑሮ፣ ለኪነ ጥበብ መዳበር፣ ለስነ ጽሑፍ እድገትና መስፋፋት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክቷል። እንዲሁም የጣኦት አምልኮን ለማስወገድ እንዳስቻለ ጨምሮ ገልጿል (2001፣ 116)።

የገዳም ሕይወት በኢትዮጵያ ለመስፋፋት የበቃው በኢትዮጵያውያን እና ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ በገቡ ቅዱሳን አማካይነት ነው። ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ዘጠኙ ቅዱሳን በተጨማሪ ሌሎች ቅዱሳን አባቶች ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ይነገራል። ከእነዚህ ቅዱሳን መካከል የሚጠቀሰው አባ ሊባኖስ ስርዓተ ምንኩስናን በአባ ጳኩሚስ ተቀብሎ በ486ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት 80 ዋሻዎችን አንጾ ስርዓተ ምንኩስናን አስፋፍቷል። በተጨማሪም ጉንድ ገዳምን የመሰረተው ፍልስጤማዊው አባ ዮሐንስ፣ በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ከግብፅ መጥቶ መንዝ ውስጥ ዋሻ በመፈልፈል ማህበረ መነኮሳትን ያቋቋመው አርባ ሐራ (አቡነ ሐራ)፣ በትግራይ ተንቤን ፀፀራ ወረዳ በሚገኘው ዋሻ ገዳም የመሠረተው ሶሪያዊው አባ ኖብ፣ የዝቋላን ገዳም የመሠረተው ግብፃዊ አባ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተጠቃሾች ናቸው(ማህበረ ቅዱሳን፣፣ 1988፣11)።

በደብረ ዳሞ ገዳም በአባ ዮሐኒ እጅ የመነኮሰው ኢትዮጵያዊው አባ ኢየሱስ ሞአ ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ በመሄድ የአንድነት ገዳም መስርቷል። ከደብረ ዳሞ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ውስጥ ለገዳማዊ ህይወት መስፋፋት ዋና ማዕከል ሆኖ ያገለገለው በአባ ኢየሱስ ሞአ የተመሰረተው የሐይቅ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ነው። ይህ ገዳም በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ያሉትን ታላላቅ ገዳማት የመሰረቱ ቅዱሳን አባቶች የተገኙበት ገዳም እንደሆነ ይነገራል። ከእነዚህም ውስጥ አባ ተክለሃይማኖት፣ አባ በፀሎተ ሚካኤል፣ አባ ሂሩተ አምላክ እና ሌሎች ተጠቃሾች ናቸው(ያረጋል፣ 1995፣ 195)። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም የተመሰረተውም በአባ ሂሩተ አምላክ እንደሆነ ይነገራል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የምንኩስና እና የገዳማት ታሪክ ውስጥ ከሦስተኛው እስከ አስራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለው ጊዜ በአብዛኛው ከውጭ በመጡ ቅዱሳን አባቶች ሥርዓተ ምንኩስና የተስፋፋበት ሲሆን ከአሥራ ሁለተኛው እስከ አስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ ደግሞ ከመላ ኢትዮጵያ በተነሱ ቅዱሳን አባቶች ስርአተ ምንኩስና እና የገዳማት ትክል /ምስረታ/ ከሰሜን ወደ ምዕራብ፣ ምሥራቅና ደቡብ የተስፋፋበት ወቅት ነበር ማለት

ይቻላል። ከአስራ ሁለተኛው እስከ አሥራ አምስተኛው መቶ ዓመት የነበረው ዘመን በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ለገዳማዊ ህይወት ወርቃማ ዘመን ነበር (ማህበረ ቅዱሳን፣ 1988፣12፤ ያረጋል፣ 1995፣ 196)።

የገዳም ሕይወት በብህትውና እና በማህበር ሊመራ ይችላል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የተለያዩ ዓይነት ገዳማዊ የአኗኗር ስርአቶች አሉ። እነዚህ ገዳማዊ የአኗኗር ስርዓቶች በተለያዩ ምሁራን የተለያየ አከፋፈልና ስያሜ ተሰጥቷቸው እናገኛለን።

አባ ጎርጎርዮስ የገዳም አይነቶችን በሁለት ከፍለዋቸው እናገኛል። አንደኛው የንፍሮ ገዳም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የህግ ገዳም ይባላል። የንፍሮ ገዳም የሚባለው በመነኮሳቱ አንድነት /Cenobitic/ የሚተዳደር ነው። በእንዲህ አይነቱ የገዳም አኗኗር ውስጥ መነኮሳቱ ገለልተኛ በሆነ ቦታ ቤተክርስቲያን ሰርተው በአንድነት እየሰሩና በአንድነት እየተመገቡ ይተዳደራሉ። የመነኮሳቱ አኗኗር በአንድነት የሚመገቡበትን ንፍሮ ቀቅለው ወይም ዳቤ/ከስንዴ ወይም ከዳጉሳ እህል የሚዘጋጅ ወፍራም እንጀራ ነው/ ጋግረው ስለሆነ የንፍሮ ገዳም ተብሏል። የህግ ገዳም የሚባሉት ደግሞ የርስት ስሪታቸውና አስተዳደራቸው እንደ አድባራት ነው። ከአድባራት የሚለዩት ቆሞሳት ብቻ ስለሚያስተዳድሯቸው ነው። የገዳሙ አገልጋዮችም መነኮሳት ወይም ደናግል መሆን አለባቸው። የህግ ገዳም የተባሉት ገዳማት ተብለው እንዲጠሩ ከባለስልጣን ከመታዘዙ በቀር በገዳማት ስርዓት ስለማይመሩ ነው(1991፣179)።

ሌሎች ምሁራን ደግሞ ገዳማዊ የአኗኗር ስርዓትን የቁሪትና የአንድነት ገዳማት በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል። የቁሪት ገዳም የሚባለው የአኗኗር ስርዓት ለየግል የተገኘውን ሰርቶ በመመገብ በጸሎትና በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ግን በአንድነት የሚካፈሉበት ስርዓት ነው (ዳኛቸው፣ 1999፣ 175)። ይህ የአኗኗር ስርአት በማህበር መኖር ከመጀመሩ በፊት የነበረውን የምነና(የብህትውና) ኑሮ የሚከተል ወይም የሚመሳሰል ነው (ምክረሥላሴ፣ 2000፣ 369)። የቁሪት ገዳም እንደ ሌሎቹ ገዳማት ተመሳሳይ የሆነ የምናኔ ጠባያት አሉት። ከዚህ በተለየ ሁኔታ የቁሪት ገዳም ከአንድነት ገዳም የሚለየው በዚህ ገዳም የተወሰነ የግል ንብረት ይዞታ የሚፈቀድ በመሆኑ ብቻ ነው(ብርሃኑና ሌሎች፣ 1990፣24)።

የአንድነት ገዳም ብዙ መነኮሳት በማህበር የሚኖሩበት ገዳም ነው። በዚህ ገዳማዊ ሕይወት እያንዳንዱ እንደ ችሎታውና ዝንባሌው በተለያየ ተግባርና አገልግሎት ላይ በመሰማራትና የተገኘውን ውጤት በጋራ በመጠቀም የሚኖርበት ሕይወት ነው። በዚህ ዓይነቱ ገዳም ምንም

ዓይነት የግል ንብረት ይዞታ አይፈቀድም (ምክረ ሥላሴ፣ 2000፣ 369፤ ዳኛቸው፣ 1999፣ 175፤ ብርሃኑና ሌሎች፣ 1990፣ 23)።

ከእነዚህ ምሁራን ሀሳብ በመነሳት የገዳም ዓይነቶች በሦስት ይከፈላሉ ማለት ይቻላል። አንደኛው የህግ ገዳም ነው። ይህ የገዳም ዓይነት ብዙ ጊዜ ከፍ ያለ ደረጃ ላላቸው ደብሮች የሚሰጥ ስያሜ ሆኖ ገዳማዊ ስርዓቱ በምልዐት/በተሟላ ሁኔታ/ የማይፈጸምበት ነው። ሁለተኛው የቁሪት ገዳም ሲሆን ገዳማውያን ከመንፈሳዊው ህይወታቸው በቀር ቀሪ ገዳማዊ ህይወታቸውን በተናጠል የሚመሩበት የገዳም አይነት ነው። ሦስተኛው ደግሞ የአንድነት(የንፍሮ) ገዳም የሚባል ሲሆን ይህ ገዳማዊ ህይወት ሙሉ በሙሉ በማህበሩ ህግ የሚመራና ኑሮው በማህበር/በአንድነት/ ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ ጥናት ከሦስቱ የገዳም አይነቶች ትኩረት የሚያደርገው በአንድነት ገዳም ላይ ነው።

በአንድነት ገዳም ያለበቂ ምክንያትና ያለገዳሙ ማህበር ፈቃድ ከገዳሙ ወጥቶ መዘዋወር አይፈቀድም። በአመጋገብ ደረጃ የገዳሙ ቀኖና የሚፈቅደውን የምግብ አይነትና መጠን ተላልፎ መመገብ የተከለከለ ሲሆን ሌሎችን ለማገልገል መትጋት የዚህ ገዳማዊ ኑሮ ግዴታ ነው። በእርጅና ወይም በህመም ምክንያት ለመሥራት የማይችል አቅመ ደካማ ካልሆነ በቀር በተረጂነት እንዲኖር የሚፈቅድም ሆነ የሚፈቀድለት ገዳማዊ የለም። በአጠቃላይ አንድነት ገዳም መነኮሳት በማህበር የሚኖሩበት እንደመሆኑ መጠን በአበላል፣ በአለባበስ፣ በሥራ፣ እና በሌሎች ጉዳዮች ማህበሩ ያስቀመጠውን ደንብ በማክበር የሚኖርበት ገዳማዊ ሕይወት ነው። በዚህ ገዳም በማህበር ሰርቶ በማህበር የሚኖርበት ሕይወት ቢሆንም አንዳንዶቹ መናንያን ከመንፈሳዊ ምልአት/ምሉእ/ ደረጃ ላይ ሲደርሱና በብህትውና መኖር ፈልገው ሲጠይቁ ማህበሩ ከፈቀደላቸው ከገዳሙ አንድነት ሳይለዩ በብህትውና ሊኖሩ ይችላሉ(ብርሃኑና ሌሎች፣ 1990፣ 24)።

## *3.2 ጥናቱ በተካሄደበት በጣና ሐይቅ ደሴቶች ውስጥ የሚገኙ ገዳማት*

ጣና የሚለው ስያሜ ማርያም፣ ልጇና ዮሴፍ በስደት በዚህ ሀይቅ አካባቢ በነበሩበት ጊዜ መልአክ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ሲነግራቸው ዮሴፍ ህጻኑን «ጸአና በደመና»/በደመና ጫናት/ በሚል ከተናገረው ሐረግ «ጸአና» ከሚለው ቃል እንደተገኘ ይነገራል። ጣና ሐይቅ በኢትዮጵያ ውስጥ በትልቅነቱ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ሐይቅ ሲሆን 3600 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት አለው። ከባህር ወለል በላይ በ1630 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል። በሐይቁ ከሚገኙት

37 ደሴቶች ውስጥ በ20ዎቹ ደሴቶች ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትን የሚከተሉ ገዳማትና አድባራት ይገኙባቸዋል። ከ700 ዓመት በላይ እድሜ ያላቸው እነዚህ ገዳማትና አድባራት በተለያየ ደረጃ ታሪካዊ የሆኑ ቅርሶችን አካተዋል(የክልል 3 ቱሪዝም ቢሮ፣ 1986፣5፤ ዘመድኩን፣ 1992፣ 183)። በእነዚህ ደሴቶች ውስጥ ከሃያ በላይ ገዳማትና አድባራት ቢኖሩም የዚህ ጥናት ትኩረት በገዳም ላይ በመሆኑ በገዳምነት የሚታወቁትን ሰባት ገዳማት አጠር ባለ መንገድ ለመቃኘት እሞክራለሁ። ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርግበትን የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም በተመለከተ የተጠቃለለ ዳራ በቀጣዩ ክፍል የሚቀርብ በመሆኑ በዚህ ክፍል በድጋሚ አይቀርብም።

በደቡብ ጎንደር ዞን ሀገረ ስብከት በደራ ወረዳ በጣና ሐይቅ ምስራቃዊ ጫፍ ውስጥ የሚገኘው የጣና ቂርቆስ ገዳም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ982 ዓመተ ዓለም ተመስርቷል (ዘመድኩን፣ 1992፣223) ይባላል። ጣና ቂረቆስ የአባቶችና የእናቶች አንድነት ገዳም ሲሆን የአባቶች ገዳም ጣና ቂርቆስ በመባል ሲጠራ የእናቶች ገዳም ደግሞ ደምበዛ ቁስቋም ይባላል። ይሁን እንጂ የእናቶች ገዳም በአባቶች ገዳም ስም ተጠቃሎ ስለሚጠራ ራሱን የቻለ ገዳም ስለመሆኑ አይታወቅም። የጣና ቂርቆስ ገዳም ቤተክርስቲያን አሰራር የአራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ሲሆን በውስጡም በርካታ ቅርሶችን አካቶ ይገኛል። ከእነዚህም ውስጥ የኦሪት መሰዊያ እቃዎች፣ ቅዱስ ያሬድ የመጀመሪያውን የዜማ መጽሐፍ ሲፅፍ ለቀለም መበጥበጫነት የተጠቀመባቸው ድንጋዮች፣ የኦሪታውያን የብረት መንበር፣ የአቡነ ሰላማ/ፍሬምናጦስ/ መቋሚያና የብረት መስቀል፣ ከብርጭቆ የተሰራ የብርሌ ቅርጽ ያለው ከኢየሩሳሌም እንደመጣ የሚነገርለት የንጉስ ሰሎሞን የእጅ መታጠቢያ፣ ከአንድ ሜትር በላይ ቁመት ያላቸው ሁለት የእንጨት መቅረዞች፣ ቁመቱ 75 ሰንቲ ሜትር፣ ርዝመቱ ደግሞ 5 ሜትር የሆነ በሐዋርያትና በነብያት ስዕል ያሸበረቀ ከብራና የተሰራ ልፋፈ ጽድቅ/ተጣጣፊ ብራና/(ቀዳማዊ ምኒልክ የሙሴን ፅላት ከኢየሩሳሌም ማስመጣቱን የሚገልጽ ነው)፣ ስዕልና ሌሎች ተጠቃሾች ናቸው(የአማራ ብሔራዊ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣1991፣77፤ ዘመድኩን፣1992፣ 225)።

ለሴቶች መግባት በማይፈቀድበት በዚህ ገዳም ውስጥ ማርያም ከልጇ ከኢየሱስና ከዮሴፍ ጋር ሦስት ወር ከአስር ቀን እንደቆየች(ዘመድኩን፣1992፣224፤ተስፋ፣1988፣171) የሚነገር ሲሆን ጥላው የሂደችው የአንገት ጌጧም በዚህ ገዳም ይገኛል (የክልል 3 ቱሪዝም ቢሮ፣ 1986፣9)። የዚህ ገዳም የቀድሞ መስራች ናቸው የሚባሉት አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን (ፍሬምናጦስ) ናቸው( ዘመድኩን፣1992፣226)።

ሌላው በዚህ ሀይቅ የሚገኘው ገዳም መንዳባ/ማንዳባ/ መድኃኔዓለም ገዳም ይባላል። ይህ ገዳም በሐይቁ ሰሜናዊ ዳርቻ ጎርጎራ ወደብ አካባቢ የሚገኝ ገዳም ነው። ከፊል የገዳሙ ክፍል ከየብስ ጋር የሚያያዘው ይህ ገዳም በ13ኛው ክፍለ ዘመን አባ አሳይ በተባሉ መንፈሳዊ አባት ተመስርቷል(ዘመድኩን፣ 1992፣ 218፤ የክልል 3 ቱሪዝም ቢሮ፣ 1986፣ 14)። ምንም እንኳ የገዳሙ የመጀመሪያው የቤተክርስቲን አሰራር ምን ዓይነት ቅርጽ እንደ ነበረው ባይታወቅም በአሁኑ ሰዓት በክብ ቅርፅ በድንጋይ የታነፀ ቤተክርስቲያን አለው። የገዳሙ መስራች አባ አሳይ ድንጋይን እንደጀልባ ተጠቅመው ሐይቁን የተሻገሩ ሲሆን ይህን ድንጋይም እስከዛሬ ድረስ ገዳሙ በቅርስነት እየጠበቀው ይገኛል። አባ አሳይ በዚህ ተዓምራዊ ድርጊታቸውና ከሌሎች ልቀው በመገኘታቸው «ማን እንደአባ» እንደተባሉና በጊዜ ብዛት ማን እንደ አባ ከሚለው ሐረግ መንዳባ/ማንዳባ/ የሚል የገዳሙ መጠሪያ እንደተፈጠረ ይነገራል(የክልል 3 ቱሪዝም ቢሮ፣ 1986፣14፤ ዘመድኩን፣1992፣218)። በዚህ ገዳም ሴት እንዲገባ የማይፈቀድ ሲሆን የመስራቹ አጽም በተጠረበ እንጨት ውስጥ ተቀምጦ ይታያል። የቀድሞ ስዕሎች ተቀዳድደው ያለቁ ቢሆንም አዳዲስ ስዕሎች ተስለው እንደሚታዩ ይነገራል።

በጣና ሐይቅ ደቡባዊ ምስራቅ የሚገኘው ሪማ(ሬማ) መድኃኔዓለም ገዳም ሌላው ተጠቃሽ ገዳም ሲሆን የተመሰረተው በአፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግስት አባ ኖብ በተባሉ መንፈሳዊ አባት ነው። እኒህ አባት ከደብረ ሊባኖስ የመጡ መነኩሴ ሲሆኑ ንጉሱን «ሪም (በግዕዝ ትንሽ ማለት ነው) የምንሰግድበት መሬት ስጠን» ብለው ጠይቀው በተሰጣቸው መሰረት ገዳሙን መስርተዋል። ሪም የሚለው የግዕዝ ቃል በጊዜ ብዛት ሪማ(ሬማ) ተብሎ ገዳሙም ሪማ(ሬማ) መድኃኔዓለም ተብሎ ሊጠራ ችሏል። የገዳሙ መስራች የአባ ኖብና የሌሎች ሰዎች አፅም ሳይፈርስ በቤተ መቅደሱ የሚገኝ ሲሆን አባ በርቶሎሜዎስና አፄ ሰርፀ ድንግል በዚህ ገዳም ውስጥ ተቀብረዋል (ዘመድኩን፣1992፣236) ይባላል።

ሌላው ገዳም ክብራን ገብርኤል ሲሆን በጣና ሐይቅ ደቡባዊ ዳርቻ ላይ ይገኛል። ከዚህ ገዳም ጎን እንጦንስ የሚባል የሴቶች ገዳም የነበረ ቢሆንም ሴት መናንያን ወደ ሌሎች ገዳማት በመሰደዳቸው ምክንያት ገዳሙ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ምንም አልነበረበትም(የክልል 3 ቱሪዝም ቢሮ፣ 1986፣ 10)። አሁን ግን ቤተክርስቲያን ተሰርቶለትና የኢየሱስ ታቦት ገብቶበት ገዳሙ ወደ ወንዶች ገዳምነት ተለውጧል(የአማራ ብሔራዊ ክልል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ 1991፣ 63)። ክብራን ገብርኤል በአምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት ከደብረ

ሊባኖስ ገዳም በመጡት አባ ዘዮሐንስ በተባሉ አባት የተገደመ ገዳም ነው (ዘመድኩን፣ 1992፣ 190)። ቤተክርስቲያኑ ክብ ቅርፅ ያለው ሲሆን በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ ያሉት አምዶች ከድንጋይ የተጠረቡ ናቸው።

ከመቅደሱ ግድግዳ ጋር ተያይዞ በተሰራ ክፍል ውስጥ የገዳሙ መስራች የአባ ዘዮሐንስ መቃብር ይገኛል። በዚህ ገዳም ውስጥ ሉቃስ እንደሳላት የሚነገርላት ስዕለ ማርያም፣ ከብረት የተሰራው የአባ ዘዮሐንስ የፀሎት ልብስ፣ የአፄ ኢያሱ አልጋና ሰይፍ፣ የንጉስ ተክለ ሐይማኖት ተደራራቢ አልጋ፣ ከእንጨት የተሰራ መቅረዝና አገልግል፣ መስቀሎች፣ የገበታ ላይ ስዕሎችና የብራና መጻሕፍት ይገኙበታል(የአማራ ብሔራዊ ክልል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣1991፣ 64፤ ዘመድኩን፣ 1992፣190)። በዚህ ገዳም እንዳለች የተገለጸችው ሉቃስ ሳላት የምትባለው የማርያም ምስል በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳምም እንዳለች መረጃ አቀባዮቹ ነግረውኛል። እዚህ ላይ አንድ ስዕል በሁለት ገዳማት ውስጥ ሊኖር ስለማይችል የቀረበው መረጃ ክፍተት እንዳለበት የሚያሳይ ነው።

ሌላዋ ተጠቃሽ ገዳም ከባህር ዳር ከተማ ሰሜናዊ ምዕራብ አቅጣጫ የምትገኘው የዑራ (ውራ?) ኪዳነ ምህረት ገዳም ስትሆን በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት በአባ ዘዮሐንስ እንደተመሰረተች ይነገራል(የአማራ ብሔራዊ ክልል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ 1991፣ 64፤ ዘመድኩን፣ 1992፣ 66)። ዘመድኩን በበኩሉ ቤተክርስቲያኗ የተመሰረተችው በ14ኛው ክፍለ ዘመን ቢሆንም በገዳምነት የፀናችው ግን በአፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግስት(1632-1706) በአባ ዮሐንስና በአባ ፋሲል(ዘመድኩን፣1992፣192) እንደሆነ አስፍሯል። በአንድ ጎኑ ከየብስ ጋር የሚገናኘው ይህ ገዳም የሐይማኖት ስዕሎች፣ ጥንታዊ የብራና መጻህፍትን፣ የነገስታት ዘውዶችን፣ ካባዎችንና መስቀሎችን በቅርስነት ይዞ ይገኛል። ቤተክርስቲያኗ በክብ ቅርፅ የተሰራች ናት። ታቦቷም መስራቹ አባ ዘዮሐንስ ከግብፅ ካመጧቸው አራት ታቦታት ውስጥ አንዷ ናት። በዑራ ኪዳነ ምህረት ገዳም ሴቶች እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል (ዘመድኩን፣1992፣193፤ የክልል 3 ተቱሪዝም ቢሮ፣1986፣ 7)።

ሌላው በጣና ሐይቅ ደሴት ከሚገኙት ገዳማት መካከል አንዱ ናርጋ ስላሴ ገዳም ነው። በክረምት ወራት በሀይቁ ሙላት ሳቢያ ወደ ደሴትነት የሚለወጠውና በበጋ ወራት ደግሞ ውሃው ሲጎድል የደቅ ደሴት ምዕራባዊ አካል የሚሆነው የናርጋ ስላሴ ገዳም የወንዶችና የሴቶች የቁሪት ገዳም በመባል ይጠራል። ቤተክርስቲያኑን ያሳነፁት አፄ ኢያሱ ብርሀን ሰገድ

(1722-1747) እና እናታቸው የአፄ በካፋ ባለቤት እቴጌ ምንትዋብ ናቸው (ዘመድኩን፣ 1992፣ 213፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ 1991፣ 67)። የናርጋ ስላሴ ገዳም ቤተክርስቲያን በክብ ቅርፅ ከድንጋይ፣ ከኖራና ከእንጨት የተሰራ ሲሆን መቅደሱ በጥንታዊ ስዕሎች ያጌጠ ነው። የጎንደር ዘመን የኪነ ህንፃ ፍርስራሾች በግቢው ውስጥ ይገኛሉ። በቅርስነት የሚጠቀሱት የእቴጌ ምንትዋብና የልጃቸው የአፄ ኢያሱ አልጋና ካባ፣ ልዩ ልዩ የብራና መፃሕፍትና የእጅ መስቀሎች ይገኙበታል። ሌሎችን ቅርሶች የኢጣሊያ ጦር እንደዘረፋቸው ይነገራል(የአማራ ብሔራዊ ክልል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ 1991፣ 69፤ ዘመድኩን፣ 1992፣213)።

ሌላው ተጠቃሽ ገዳም ደብረ ገሊላ ገዳም ነው። በንጉስ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት ማብቂያ ላይ የፊሊጶስ ደቀመዝሙር የሆኑትና ምንኩስና ከአባ ፊሊጶስ የተቀበሉት(ተክለ ጻድቅ፣ 1951፣ 46) አባ ዘካርያስ ገሊላ በተሰኘው ደሴት የራሳቸውን ማህበር አቋቁመዋል። የዚህም ማህበር መመስረት በክርስቲያኑ ወገን አዲስ መነቃቃት የፈጠረ ሲሆን አማኝ ባልሆነው የሐይቁ ደቡባዊ ክፍልም ጠንካራ ሆነው እንዲወጡ አስችሏቸዋል(ታደሰ፣1972፣194)። በርግጥ ይህ ገዳም አሁን ምን ሁኔታ ላይ እንዳለ መረጃ ማግኘት አልቻልኩም።

በጣና ሐይቅ ውስጥ የሚገኙ ገዳማት ቤተክርስቲያናት አብዛኛዎቹ በክብ ቅርጽ የተሰሩ ሲሆኑ ዘመናቸውም በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት ነው። ከእነዚህ ገዳማት ውስጥ የጣና ቂርቆስና የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ቤተክርስቲያን ብቻ በአራት ማዕዘን ቅርጽ የተሰሩ ናቸው። መረጃ አቀባዮቹ የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የቤተክርስቲያን አሰራር የኖህ መርከብ ቅርጽ ያለው መሆኑ ከአለም ሀጢአት የመዳኛ መንገድ መሆኑን የሚያሳይ ተምሳሌታዊ ፍች እንዳለው አመላካች ነው ይላሉ። ምንም እንኳን ቤተክርስቲያናቱ ፈርሰው እንደገና ሲሰሩ መጀመሪያ ከነበራቸው ቅርጽ በተለየ ቅርፅ ሊሰሩ ስለሚችሉ የመጀመሪያውን ቅርጽ ለማወቅ የተሟላ መረጃ ማግኘት ባይቻልም አሁን ባለው ሁኔታ በአስራ አራተኛው ክፍለ ዘመን የተገደሙ ገዳማት ቤተክርስቲያናት ቅርጻቸው ክብ ነበር ማለት ይቻላል። በጣና ሐይቅ ያሉት ብዙዎች ገዳማትና አድባራት(ከጣና ቂርቆስና ከዳጋ እስጢፋኖስ ገዳማት በቀር) በአፄ አምደ ጽዮን የተመሰረቱ መሆናቸው፣ ንጉሱ በዚህ ዘመንና በዚህ አካባቢ ሀይማኖት የማስፋፋት ትልቅ ፍላጎት እንደነበረው መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ ሌላም በአካባቢው ትልቅ የአገዛዝ ተጽዕኖ የመፍጠር ፍላጎት ሳይኖራቸው አይቀርም የሚል ግምትም ያሳድራል።

እነዚህን ገዳማት የሚያመሳስላቸው ሌላው ጉዳይ ሰባቱ ቅዱሳን ከዋክብት በሚባሉት መነኮሳት መመስረት መቻላቸው ነው። አባ ታዲዎስ ደብረ ማርያምን፣ አባ ዘዮሐንስ ክብራን ገብርኤልን፣ አባ በትረማርያም ዘጌን፣ አባ ሂሩተ አምላክ ዳጋ እስጢፋኖስን፣ አባ አሳይ መንዳባን፣ አባ ዘካሪያስ ደብረ ገሊላን፣ አባ ፍቅረ እግዚእ ዮሐንስ ደግሞ ጣና ቂርቆስን መስርተዋል (የአማራ ብሔራዊ ክልል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣1991፣ 65)። ታደሰ ታምራት Church and State in Ethiopia በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ የጣና ቂርቆስ መስራች እንደሆኑ ስማቸው የተጠቀሰው መናኝ የጣና ቂርቆስን ማህበር ከተቀላቀሉ በኋላ ማህበሩ በጥሩ ሁኔታ እየተጠናከረ እንደሄደ እንጂ(1972፣191) ገዳሙን እንደመሰረቱ ተጠቅሶ አይገኝም። እነዚህ መስራች መነኮሳት አብዛኛዎቹ ከሸዋ የመጡ ሲሆን በወቅቱ በነበሩት በአፄ አምደ ጽዮን ጥበቃና ድጋፍ ይደረግላቸው ነበር። እነዚህ መናኞች ገዳማትን መስርተውና አደራጅተው በመሰረቱት ገዳም የተቀበሩ ናቸው። የመሀል ዘጌን የመሰረቱት አባ በትረ ማርያምና የዳጋ እስጢፋኖስን ገዳም የመሰረቱት አባ ሂሩተ አምላክ በመሰረቷቸው ገዳማት ውስጥ ታቦት ተቀርፆላቸው በስማቸው ቤተክርስቲያን ታንፆላቸዋል።

በተመለከትናቸው ገዳማት ውስጥ የሚጠቀሱ የተለያዩ ተአምራት ያሉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ከሐይቁ ጋር ተያይዘው የሚተረኩ ናቸው። የመንዳባ መድኃኔዓለምና የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መስራቾች ድንጋይን እንደጀልባ ተጠቅመው ሐይቁን እንደተሻገሩ ይነገርላቸዋል። የደብረ ማርያም ደብር መስራች አባ ታዲዎስ ሐይቁን እንደ ባህረ ኤርትራ ከሁለት በመክፈል የተሻገሩ ሲሆን አባ በትረ ማርያም በሐይቁ ላይ አጽፋቸውን/ልብሳቸውን/ አንጥፈው በመቋሚያቸው እየቀዘፉ መሻገረ መቻላቸው ይነገራል(ዘመድኩን፣1992፣198)። በጊዜው የአካባቢው ማህበረሰብ ክርስትናን ያልተቀበለ በመሆኑና በክርስትናውም መስፋፋት ተቃውሞ ስለነበረው እነዚህ ተአምራት የገዳሙን መስራቾች የበለጠ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ሳያደርጉ እንዳልቀሩ መገመት ይቻላል።

በጣና ሐይቅ የሚገኙት ገዳማት ብዙዎቹ ታሪካዊ የሚባሉ ቅርሶች ያሏቸው ሲሆን ሁሉም ማለት ይቻላል ሐይማኖታዊ በሆኑ ስዕሎች ያጌጡ ናቸው። ከቅርሶቹ መካከል የብራና መጻሕፍት፣ የነገስታት የወግ እቃዎች፣ መስቀሎች፣ አፅሞች፣ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። አንድ ንጉስ የተቀበረበት ቤተክርስቲያን ከፍተኛ ክብርና ደረጃ ያለው በመሆኑና በየጊዜውም የገንዘብና ሌሎች ድጋፎች ስለሚያገኝ(ተክለ ጻድቅ፣1951፣181) የነገስታት አጽሞች በተለያዩ አድባራት በክብር ሲጠበቁ ይታያሉ። በጣና ቂርቆስ ገዳም ውስጥ የኦሪት መሰዊያ

እቃዎች መገኘቱ የተለየ ያደርገዋል። አንዱ ገዳም ከሌላው ገዳም የቆየና የተለየ ታሪክ መኖሩን ለማጠየቅ/ለማስመስከር/ እነዚህን ቅርሶች እንደማስረጃነት ይጠቀሙባቸው ይሆናል። በተለይም ለነገስታቱ የወግ እቃዎች የተለየ ትኩረት እንደሚሰጡ መረዳት ችያለሁ። በአብዛኛዎቹ ገዳማት(ከዑራ ኪዳነ ምህረትና ከናርጋ ስላሴ ገዳም ውጭ) ሴቶች እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም።

በጣና ሐይቅ ዙሪያ ያሉትን ታሪካዊ ሁኔታዎች በምንመለከትበት ጊዜ በጎጃምና በጣና ሐይቅ አካባቢ ለነበረው ሐይማኖት መስፋፋት የአምደ ጽዮን ጠንካራ የመንግስት ስልጣን ከፍተኛ የሆነ ሚና ነበረው። በዚህ አካባቢ ባለው የቤተክርስቲያን መስፋፋት ላይ በተከዜና በጣና ሐይቅ መካከል የነበሩት ፈላሻዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ነበራቸው(ታደሰ፣1972፣192)። በጣና ሐይቅ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ፈላሻዎች ናቸው። እነዚህም ህዝቦች በወቅቱ የኦሪት እምነት ተከታዮች ነበሩ። ሌሎች የአካባቢው ህዝቦችም ክርስትናን ያልተቀበሉ ስለነበሩ በቤተክርሰቲያን የመስፋፋት እንቅስቃሴ ላይ ደስተኛ አለመሆናቸው ይነገራል። ከዚህ ጊዜ በኋላም በጣና ቂርቆስ ደሴት ያለው የገዳም ህይወት በተለይም አፄ አምደ ጽዮን ሙስሊሞችንና ፈላሻዎችን ድል ካደረጉ(ተክለጻድቅ፣ 1951፣62) በኋላ የጣና ሐይቅ ዙሪያ የክርስቲያኖች እንቅስቃሴ ዋና ማዕከል ለመሆን በቅቷል(ታደሰ፣1972፣193)።

አፄ አምደ ጽዮን በተለይ ዋና ተቀናቃኛቸው በሆኑት ፈላሻዎች አካባቢ መንግስታቸውን ለማጠናከር በጣና ሐይቅ አካባቢ ገዳማትን ማስፋፋትን እንደስትራቴጂ የተጠቀሙበት ይመስላል። ታደሰ ታምራት አፄ አምደ ጽዮን ከጣና ቂርቆስ በተጨማሪ በጣና ሐይቅ ባሉ ቦታዎች ሁሉ የገዳም ህይወት ማዕከላት እንዲስፋፉ ያደርጉ እንደነበር አስፍረዋል። የዚህም ምክንያት የጎጃምንና የፈላሻን ከተሞች የክርስትና እምነት ተከታይ ለማድረግ ነው። ለዚህም እንቅስቃሴ የአባ አሮን ተከታዮችና የደብረ አሰቦው(አሁን ስሙ ደብረ ሊባኖስ ገዳም የተባለው ነው (ተክለጻድቅ፣ 1951፣ 105) ፊሊጶስና እንዲሁም አባ ዘዮሐንስ ከደሴቱ ውጭ ክርስትናን ለማጥመቅ ሙከራ በማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው አስፍረዋል(1972፣193)።

በጣና ሀይቅ ዙሪያ ስላሉት ገዳማትና አድባራት የተገኙት መረጃዎች እንደመነሻ መልካም ቢሆኑም ስለገዳማቱና አድባራቱ የተሟላ መረጃ የያዙ ሆነው አላገኘኋቸውም። በተለይም ገዳማቱንና አድባራቱን ለይተው ከማመልከት ይልቅ አንድ ጊዜ ደብር አንድ ጊዜ ደግሞ ገዳም በማለት እያቀላቀሉ ሲጠቀሙባቸው ይታያሉ። በርግጥ አንድ ገዳም በመጀመሪያ ሲመሰረት

በገዳምነት ሊመሰረት ይችላል። ቆይቶ ደግሞ ገዳምነቱ ቀርቶ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ሊሰጥ ይችላል። እንደገና ደግሞ ተመልሶ ወደ ገዳምነት ሊሸጋገር ይችላል። ለምሳሌ አሁን ደብረ ማርያም የተሰኘው ደብር በአጼ ዘርአ ያዕቆብ እና በአጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ/1674-1698/ ዘመነ መንግስት ጊዜ ገዳም እንደነበርና በዚህም ጊዜ የገዳሙ መነኮሳት በነገስታቱ ከፍ ያለ ክብር የነበራቸው መሆኑን (ስርግው፣1981፣160) ሰፍሮ እናገኛለን። የዳጋ እስጢፋኖስም ገዳም መጀመሪያ ቤተክርስቲያን፣ ቀጥሎ ገዳም፣ እንደገና ቤተክርስቲያን፣ አሁን ደግሞ ገዳም ሆኖ ይገኛል። ስለዚህ ይህ ጉዳይ እንደችግር የሚጠቀስ ቢሆንም በየጊዜው ሊከሰት የሚችለውን መለዋወጥ ግምት ውስጥ በማስገባት ገዳማቱን ወይም አድባራቱን በሚገባ በማጥናትና ለይቶ በማመልከት ተገቢ የሆነ መረጃ ማስፈር ያስፈልጋል።

በተለይም አሁንም ሆነ ቀደም ሲል በገዳምነት የማይታወቁትን አድባራት ገዳም እያሉ ማስፈር ተገቢ መስሎ አልታየኝም። ሌላው በተመለከትኳቸው መረጃዎች እንደክፍተት የማነሳው ለሴቶች ገዳም ትኩረት መስጠት አለመቻላቸውን ነው። በተለይም በጣና ቂርቆስ የሚገኘው የሴቶች ገዳም ስለመኖሩ እንኳን በስም የገለጹበት አጋጣሚ አለመኖሩ እንደችግር የሚጠቀስ ነው። ከዚህ ሌላ ገዳማቱና አድባራቱ የተመሰረቱበትን ጊዜ በዘመን ጠቅልለው በማስቀመጣቸውና የተመሰረቱበት ትክክለኛ ጊዜ በግልጽ ባለመስፈራቸው ከወቅቱ የሃገሪቱ ታሪክ ጋር እያነጻጸሩ ለማጥናት አስቸጋሪ ይሆናል።

## 3.3 የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት

የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም በምዕራብ ጎጃም ሃገረ ስብከት በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ጣና ሐይቅ ደሴት ላይ የሚገኝ ገዳም ነው። የዚህ ገዳም መስራች እንደሆኑ የሚጠቀሱት አባ ሂሩተ አምላክ ናቸው። ዘመኑም በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት በ1268 ዓ.ም ነው። አባ ሂሩተ አምላክ የአፄ ይኩኖ አምላክ የወንድም ልጅ እንደሆኑ ይነገርላቸዋል(ዘመድኩን፣1992፣205፤ ዳንኤል፣1999፣ 559፣ ሰሎሞን፣ 2001፣ 168)።

በመጀመሪያ የገዳሙ መሥራች አባ ሂሩተ አምላክ ወደ ዳጋ ደሴት ታቦተ እስጢፋኖስን ይዘው መጥተዋል። በደሴቷ ቀደም ብላ ታቦተ ማርያም የነበረች በመሆኗ በአንድነት ሲያገለግሉ ቆይተው ታቦተ ማርያም ወደ ደቅ ደሴት እንድትሄድ ሲደረግ ገዳሙ በእስጢፋኖስ ስም ዳጋ እስጢፋኖስ ተብሎ ተሰይሟል (ዘመድኩን፣1992፣ 206፤ ዳንኤል፣ 1999፣ 650 ሰሎሞን፣ 2001፣168)። በሌላ በኩል ግን ይሄ ገዳም በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት(1298/9?-

1328(9?) እንደተመሠረተ በግልጽ የተቆረቆረበትን ጊዜ የሚያፋልስ/የሚለውጥ/ የታሪክ መረጃም አለ። ሥርግው ሃብለሥላሴ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም በ14ኛው ምዕት እንደተመሰረተ ጠቅሰው በቃል የቆየው ትውፊት ግን አፄ ይኩኖ አምላክ እንደመሰረተው አድርጎ እንደሚያስረዳ(1981፣196) አስፍረው እናገኛለን።

አባ ሂሩተ አምላክ ወደ ደሴቱ የገቡበትና በዚህ ደሴት የምንኩስና ሕይወት የጀመሩበት ጊዜ ምናልባት በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት በ1268 ዓ.ም ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። ዳጋ እስጢፋኖስ እንደ አዲስ ቤተክርስቲያን ታንፆለትና የገዳሙ ስም ዳጋ እስጢፋኖስ ተብሎ የተሰየመበት ዘመን ግን በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት (በ14ኛው ክፍለ ዘመን ) ሊሆን ይችላል። በርግጥ አባ ሂሩተ አምላክ የአጼ ይኩኖ አምላክ የወንድም ልጅ ከነበሩና በሀይቅ እስጢፋኖስ ገዳም አብረው ከነበሩ በንጉሱ እየተደገፉ ዳጋ እስጢፋኖስን መመስረት ችለው ይሆናል። ከዚህ ውጭ በጣና ሀይቅ አካባቢ ያሉ ገዳማት አብዛኞዎቹ በንጉስ አምደጽዮን ዘመነ መንግስት የተመሰረቱ በመሆናቸው ምናልባትም ስርግው እንደሚሉት ይህ ገዳም ከነህንፃ ቤተክርስቲያኑ የተመሰረተው በ14ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ የሚገለጸውን መረጃ መቀበል አያስቸግርም።

በዚህ ደሴት ላይ በአብርሃ ወአጽበሃ ዘመነ መንግሥት በ347 ዓ.ም በማርያም ስም ቤተክርስቲያን ታንፆ ነበር። የዳጋ እስጢፋኖስ መሥራች ገዳሙን በእስጢፋኖስ ስም ሲያቀኑ በ13ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ወይም በ14ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የማርያም ቤተክርስቲያንን በደቅ ደሴት ላይ ለሕዝባውያኑ በቅርበት እንድትሠራ አድርገዋል። ከዚህም ጊዜ ጀምሮ አባ ሂሩተ አምላክ ለአካባቢው ማሕበረሰብ መንፈሳዊ አባት በመሆን ክርስትናን ማስፋፋት እንደቻሉ ይነገርላቸዋል። ይህች ቤተክርስቲያን ዛሬ ኮታ ማርያም በሚል መጠርያ ትታወቃለች።

አባ ሂሩተ አምላክ ስርዓተ ምንኩስናን የተማሩት በሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ነው። በወቅቱም የሐይቅ እስጢፋኖስ መምህር የሆኑት የአባ ኢየሱስ ሞአ ረድ ነበሩ። በዚህ ገዳም ውስጥ እያሉ አባ ሂሩተ አምላክ የአቃቤ ሰዓትነት ስልጣን አግኝተዋል። አባ ሂሩተ አምላክ በተሰጣቸው ማዕረግ ጥቂት ጊዜ ካገለገሉ በኋላ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቀው ከሰው ተለይተው እግዚአብሔርን በገዳም ለማገልገል ይወስናሉ። በመሆኑም አምላካቸውን በፀሎት በለመኑት መሠረት ሕቡአን/ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የሚታዩ ስውራን ማለት ነው/ የሆኑ መነኮሳት

ከኢየሩሳሌም ቀራ በምትባል እንደ አጋዘን ባለች እንስሳ ታቦተ እስጢፋኖስንና ታቦተ ጊዮርጊስን ጭነው ይዘውላቸው እንደመጡ ይነገራል። በኋላም አባ ሂሩተ አምላክ ታቦተ ጊዮርጊስ በዚያው በሐይቅ እስጢፋኖስ ፊት ለፊት በሚገኝ ቦታ ላይ እንዲተከል ካደረጉ በኋላ ታቦተ እስጢፋኖስን ይዘው ወደ ዳጋ ደሴት መምጣታቸውን የገዳሙ መነኮሳት ይገልጻሉ።

አባ ሂሩተ አምላክ ከወሎ ሐይቅ እስጢፋኖስ ተነስተው መልአክ እየመራቸው ጣና ሐይቅ መድረሳቸው ይነገራል። ጣና ሐይቅ እንደደረሱ በሐይቁ ላይ የሚጓዙበት ምንም ዓይነት መጓጓዣ ስላልነበራቸው አምላካቸውን በጸሎት ጠየቁት። በዚህ ጊዜ አምላካቸው ሁለት ድንጋዮች አቀረበላቸው (አንዱ ትልቅና አንዱ ትንሽ ድንጋይ ነው)። ከዚያም አንዱን ጅፍጅፍ[3] አንዱን ታንኳ[4] አድርገው በመቋሚያቸው እየቀዘፉ ዳጋ ደሴት ሊደርሱ ችለዋል(አባ ወልደ ሃና፣ 2002 ካ.ቁ.1A)። «የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ቢኖራችሁ የምትፈልጉትን ማድረግ ትችላላችሁ» ባለው መሠረት አባ ሂሩተ አምላክ የሚጠልቀውን ድንጋይ እንደ ታንኳ ተጠቅመው እዚህ ገዳም ደርሰዋል(አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002 ካ.ቁ.1 B) በማለት ይገልጻሉ። አባ ሂሩተ አምላክ የተጓዙባቸው እነዚህ ድንጋዮች ዛሬ ከሲሚንቶ በተሰራ መሰረት የፃድቃን ማረፊያ ተብሎ በተሰየመው ቦታ ላይ በክብር ተቀምጠዋል። የቀዘፉበትን መቋሚያቸውን ግን በቅርስ መጠበቂያ እቃ ቤትም ሆነ በንዋየ ቅድሳት ማስቀመጫ ቤት እንደሌለ አረጋግጫለሁ።

መስራቹ ከጣና ሐይቅ እንደወጡ ያረፉበት እና ለመጀመሪያ ጊዜ ፀሎት ያደረሱበት ቦታ ዛሬም ድረስ አቃቤ ሰዓት በሚል ሥያሜ ይጠራል። አቃቤ ሰዓት የመስራቹ የአባ ሂሩተ አምላክ የስልጣን ስም ነው። ይህም ቦታ ዛሬም ድረስ በመነኮሳቱና ገዳሙን ለመጎብኘት በሚመጡ ሰዎች ይጎበኛል። ገዳሙ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በነገስታቱ ድጋፍ ሲደረግለት እንደነበር መረጃ አቀባዮቹ ነግረውኛል። በመሆኑም ቤተክርስቲያኑ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ፣ አፄ ፋሲልና አፄ ሱስንዮስ እድሳት ተደርጎለታል(ሰሎሞን፣ 2001፣ 168)። የገዳሙን የእቃ ቤት አፄ ፋሲል ያሰሩት ሲሆን ከሳር ወደ ቆርቆሮ የቀየሩት ደግሞ አፄ ኃይለሥላሴ ናቸው። እንዲሁም ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ገዳሙን ከጎበኙ በኋላ ለገዳሙ ስምንት ሺህ ብር ሰጥተው ተመልሰዋል ይባላል(አባ ወልደ ሃና፣2002፣ ካ.ቁ.1A)።

[3] ጅፍጅፍ፦ ታንኳውን የሚቀዝፈው ሰው የሚቀመጥበት ማንኛውም አይነት መቀመጫ ነው።

[4] ታንኳ፦ከቀርቀሀና ከሸንበቆ ከደንገል የተበጀ የባህር መንገደኛ በላዩ ተቀምጦ የሚሻገርበት(ደስታ፣1962፣1264) ማለት ነው።

እንግዲህ ይሄ ገዳም ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በንባስታትና ምእመናን ትልቅ ትኩረት ሲሰጠው የነበረ መሆኑን መገመት ይቻላል።

በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ውስጥ የተለያዩ ቅርሶች ተመዝግበው ይገኛሉ። እነዚህ ቅርሶች በተለያየ መንገድ የተሰበሰቡ ናቸው። ብዙዎቹ ቅርሶች ግን ነገሥታት በረከት እናገኝበታለን በሚል እምነት ወይም ረጅም ጊዜ ተጠብቆ ይቆይልናል ከሚል ግምት ሊሆን ይችላል በስጦታ የተበረከቱ ቅርሶች ናቸው። ከዚህ ሌላ በተለይ በቅርስነት የተመዘገቡት መጻሕፍት ከሌሎች አድባራት በተሻለ ሁኔታ ጥበቃ ይደረግላቸዋል በሚል አምጥተዋቸው በዚሁ የቀሩ መጻሕፍት አሉ። ሌሎች ደግሞ የነገሥታቱ አስከሬን ወደዚህ ገዳም ለቀብር ሲመጣ አብረው መጥተው ሳይመለሱ የቀሩ ይገኙበታል። በአጠቃላይ እነዚህ ቅርሶች በተለያዩ ዘመናት ከተለያዩ ሰዎችና ቦታዎች ተሰብስበው የመጡ ሲሆን ገዳሙ እነዚህን ቅርሶች ለብዙ ዓመታት ሲንከባከባቸውና ሲጠብቃቸው ኖሮ እስከዚህ ዘመን ደርሰዋል።

በዚህ ገዳም ከሚገኙት መጻሕፍት ውስጥ ገድለ ሰማዕታት (የዓመት)፣ ግብረ ሕማም ባለሃረግ፣ ወንጌል ዘወርቅ፣ ርቱዐ ሃይማኖት፣ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ፣ ቀሌምንጦስ፣ ተአምረ ማርያም፣ የአምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ (ኦሪት) ባለሃረግ፣ የተሰኙት መጻሕፍት ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት ከተወሰኑ ገዳማትና ደብሮች ውጭ በብዙዎች የማይገኙ መሆናቸውን በገዳሙ መረጃ የሰጡኝ አባቶች ነግረውኛል። እነዚህ መጻሕፍት በቅርስ ጥበቃ የተመዘገቡ ቢሆንም አንዳንዶቹ በተለይም የአምስቱ መጻሕፍተ ሙሴ (ኦሪት) የተወሰኑ ገጾች የተቆራረጡ መሆኑን ተመልክቻለሁ። ከእነዚህ መጻሕፍት ውጭ በገዳሙ ውስጥ በድምሩ 84 መጻሕፍት መኖራቸውን ቆጥሬ አረጋግጫለሁ። ሁሉም መጻሕፍት በብራና የተፃፉ ናቸው።

በዚህ ቤተመዘክር ውስጥ ከተመለከትኳቸው ቅርሶች መካከል ለዚህ ገዳም በአፄ ዳዊት የተበረከቱ ስጦታዎች የነሐስ መስቀል (መሰቀሉ የሚከፈትና የሚዘጋ)፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰቀለበት ግማደ መስቀል ላይ ተፈልፍሎ በሌላ መስቀል ላይ የተለበጠ እና በዝሆን ጥርስ ያጌጠ የእጅ መስቀል፣ የወርቅ ዘውዳቸውና የነሐስ ነጋሪታቸው ይገኙበታል።

ከግማደ መስቀሉ/ኢየሱስ የተሰቀለበት ቁራጭ መስቀል ነው/ ላይ ተፈልፍሎ የተሰራ እንደሆነ የተገለፀው መስቀል በርግጥም በአፄ ዳዊት መሰራቱ ያጠራጥራል። ምክንያቱም ወደፊት እንደምናየው የኢየሱስን ግማደ መስቀል ወደ ኢየሩሳሌም ተላልከው ያስመጡት አፄ ዳዊት እንደሆኑ የተለያዩ መጻሕፍት ይገልፃሉ። እነዚህ መጻሕፍት ንጉሱ ግማደ መስቀሉን ለመቀበል

ወደ ስናር (ይሄ ግዛት አሁን በሱዳን ክልል ውስጥ የሚገኝ ነው) ሂደው መልእክተኞችን እንደተቀበሉና በዚህም ደስታ ሆኖ እየተከበረ እያለ በመካከሉ የተቀመጡባት በቅሎ ረግጣቸው እንደሞቱ አስፍረዋል። ይህ ከሆነ ታዲያ ንጉሱ መቼ አስፈልፍለው አሰሩት የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ምናልባት ንጉሱ ከሞቱ በኋላ ልጃቸው አፄ ዘርዐ ያዕቆብ በማስፈልፈል አሰርተው በአባታቸው ስም ለገዳሙ ሰጥተው ከሆነ ጉዳዩ አሳማኝነት ይኖረዋል።

የሆነ ሆኖ እንደተባለው ይሄ መስቀል ከግማደ መስቀሉ ላይ ተፈልፍሎ የተሰራ ከሆነ በቅርስ ሐብቱ የበለፀገ በማድረግ የገዳሙን ታሪካዊነት አጉልቶ ያሳያል። ምናልባት ከግማደ መስቀሉ ጋር በተያያዘ ለግሸን ማርያም የሚሰጠውን ታሪካዊነት የሚጋራ ነው። በተለይም ተቀብሮ ይገኛል በሚል ከሚጠቀሰው ግማደ መስቀል በአይን የሚታየው ይሄ መስቀል ትልቅ ዋጋ አለው ማለት ይቻላል። ገዳማውያን ስለገዳሙ ታሪካዊነት ሲናገሩ እንደማስረጃ ከሚጠቅሷቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የዚህች መስቀል በዚህ ገዳም ውስጥ መገኘት ነው። በርግጥም ይህ መስቀል የግማደ መስቀሉ አካል መሆኑ ከተረጋገጠ የግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ መቀመጥ ትልቅ ማስረጃ ሊሆን ይችላል። ገዳማውያን ግን በዚህ ላይ ፍጹም ጥርጣሬ ስለሌላቸው ስለዚህች መስቀል የግማደ መስቀሉ አካል መሆንና ታሪካዊነት በሙሉ ልብ ሲናገሩ ይደመጣሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ለዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ከአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ተሰጡ ከሚባሉ ስጦታዎች ውስጥ ከኢየሩሳሌም ያስመጡት የወርቅ መስቀል፣ የማርያም ሥዕል፣ የእጅ መስቀል፣ በግሪክና በግዕዝ ቋንቋ የተፃፈበትና የአልማዝ ፈርጥ ያለበት ባለ ሰገባ ሰይፍ፣ የንግሥናቸው የወርቅ ዘውድና የነሐስ ነጋሪታቸው ይገኙበታል። እነዚህን ስጦታዎች ንጉሱ ከመሞታቸው በፊት በስጦታ ያበረከቷቸው ወይም አፅማቸው ወደዚህ ቦታ ሲመጣ በዚሁ ቀርተው በንጉሱ ስም የተመዘገቡ ይሆኑ በግልጽ እንደማይታወቅ ያነጋገርኳቸው የእቃ ቤቱ ጠባቂዎች ነግረውኛል።

በተጨማሪም በአፄ ፋሲል ተበርክተዋል በሚል ከተመዘገቡት ቅርሶች መካከል የወርቅ ቅብ ያለው ተገጣጣሚ አልጋ፣ ባለሦስት እግር ዙፋን /ወንበር/፣ የወርቅ ዘውድ፣ ካባ፣ ቀንደ መለከት (የጎሽ ቀንድ እንደሆነ ነግረውኛል)፣ የነሃስ ነጋሪት ይገኙባቸዋል። ከዚህ ሌላ እቴጌ ጣይቱ የኢሳይያስና ኤርሚያስ ትንቢት መጽሐፍና አንድ ቀሚሳቸውን(ቀሚሱ "እቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ" የሚል ጽሁፍ የተጠለፈበትና በርካታ የመስቀል ጥልፍ ያለው የሐር

ቀሚስ ነው) ለገዳሙ ሰጥተዋል። በዚህ ቤተመዘክር የገዳሙ አበምኔቶች /መምህራን/ ይለብሷቸው የነበሩና አሁን በቅርስነት የተቀመጡ አራት ካባዎች ይገኛሉ።

ከዚህ ሌላ ዳጋ እስጢፋኖስን ከሌሎቹ ገዳማት የተለየ የሚያደርጉትና ብዙዎች እንዲጎበኙት ምክንያት የሚሆኗቸው በቅርስነት የተቀመጡት አፅሞች ናቸው። ከእነዚህ አፅሞች መካከል የአፄ ዳዊት፣ የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ፣ የአፄ ሱስንዮስና የአፄ ፋሲል ይገኙበታል። እነዚህ አጽሞች ከአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የኢየሩሳሌም አስጎብኝ ድርጅት ባሰራላቸው የመስታወት ሳጥን ውስጥ ይገኛሉ። ከእነዚህ አጽሞች በተጨማሪ ሌሎች 10 ነገስታትና 9 ጳጳሳት በዚህ ገዳም ውስጥ እንደተቀበሩ ይነገራል።

የእቃ ቤቱ ኃላፊ አባ ወልደ ሀና እና የእቃ ቤቱ ጠባቂና አስጎብኝ አባ ገብረ ሕይወት እንደነገሩኝ በዚህ ገዳም የሚገኙት አፅሞች አብዛኛዎቹ የተቀበሩ በመሆናቸው፣ ያልተቀበሩትም በመፈራረሳቸው፣ ከዚህ ሌላም የትኛው አፅም የማን እንደሆነ መለየት ባለመቻሉ ከአራቱ ነገሥታት ውጭ ሌሎች አፅሞች በመስታወት ሊቀመጡ አልቻሉም። በዚህ ገዳም ስለተቀበሩት 10 ነገሥታትና 9 ጳጳሳት ዝርዝር መረጃ ስለመኖሩ በጠየቅኋቸው መሰረት የጳጳሳቱ ዝርዝር የሌለ ቢሆንም የነገሥታቱን ስም ዝርዝር በገዳሙ ከሚገኘው ስንክሳር ላይ እያነበቡ ነግረውኛል። በዚህም መሠረት በዚህ ገዳም ከተቀበሩት ነገሥታት መካከል አፄ ካሌብ፣ አፄ አይዙር፣ አፄ ይኩኖ አምላክ፣ አፄ ይስሐቅ፣ አፄ ልብነ ድንግል፣ አፄ ገላውዲዎስ፣ አፄ በእደ ማርያም፣ አፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ፣ አፄ ዳዊት(የአዲያም ሰገድ ኢያሱ ልጅ) እና አፄ ተክለሃይማኖት (አንድ እጁ) ይገኙበታል።

የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም መነኮሳት የአፄ ሱስንዮስን አስከሬን በገዳሙ ውስጥ አናስቀብርም በማለታቸው ምክንያት በተቀሰቀሰ አለመግባባት መነኮሳቱ ሁሉ እንደተሰደዱና የገዳሙም ገዳማዊ ህይወት እንደተቋረጠ(አባ ተክለ ዮሐንስ፣2002፣ካ.ቁ.2A) የሚናገሩ አባቶች ቢኖሩም በአንጻሩ ሌሎች አባቶች ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመነ መሳፍንት ድረስ በተጠናከረ ሁኔታ እንደቀጠለና የመቋረጥ አጋጣሚ እንዳልተከሰተበት ይነገራል። ለዚህም እንደ ማስረጃ የሚጠቀሰው በእነዚህ ዘመናት በነበሩት በገድለ አፍቅረነ እግዚእ፣ በአፄ ዳዊት፣ በአፄ ሱስንዮስ፣ በአፄ ፋሲለደስ፣ በቋራው ኢያሱ አዲያም ሰገድ ብርሃን ዜና መዋዕሎች ለዳጋ እስጢፋኖስ የተለያዩ ስጦታዎች የሰጡ መሆናቸው መገለፁ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ የገዳሙ መነኮሳት በፀሎቶቻቸው እንዲያስቧቸው መማፀናቸውን እና ስለ

አበምኔቶች በእነዚህ ዜና መዋዕሎች የተገለፁ ጉዳዮች ያሉ በመሆናቸው ገዳሙ የተቋረጠበት ዘመን ላለመኖሩ እንደማስረጃ ይጠቀሳል (አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.6A) ።

ገዳሙ እስከ ዘመነ መሳፍንት ድረስ የመቋረጥ ሁኔታ ባይገጥመውም በዘመነ መሳፍንት የመዳከም አደጋ ገጥሞት ነበር። ይህ ዘመን አገሪቱ በተለያዩ ደጃዝማቾች ባልተማከለ ሁኔታ የምትገዛበት ወቅት ስለነበርና በእነዚህ የተለያዩ ገዥዎች መካከል በየጊዜው የሚከሰት ጦርነት ስለነበር ይሄ ሁኔታ ለገዳሙ ምቹ አልነበረም። ከዚህ በተጨማሪም ገዳሙ የሚተዳደረው በሚሰጠው ርስትና ጉልት ነው። በዘመነ መሳፍንት ጊዜ በየጊዜው የሚለዋወጡት ገዥዎች /ራስ፣ ደጃዝማች/ ለገዳሙ የሚሆነውን ርስትና ጉልት የሚሰጡበትና የሚከለክሉበት ሁኔታ ያጋጥም ስለነበር ይሄ ጉዳይ ለመነኮሳቱ የተረጋጋ ሕይወት እንቅፋት ሆኖ ነበር። ስለዚህ በዘመነ መሳፍንት ጊዜ በሰላም መጥፋትና በቀለብ እጥረት ምክንያት ገዳሙ ተዳክሞ ነበር ማለት ይቻላል (አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.6A፤ አባ ወልደ ሃና፣2002፣ካ.ቁ.1A) ።

ነገር ግን ከዳግማዊ ቴዎድሮስ መነሳት ጋር ተያይዞ ገዳሙ እንደገና ተጠናክሮ ሊቀጥል ችሏል። ንጉሱም በየጊዜው ገዳሙን እንደነበኙና ሥጋ ወደሙ እንደ ተቀበሉበት ይነገራል። ከዚህ ቆየት ብሎ ግን በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን በኋላ ጊዜው በውል ባይታወቅም የገዳሙ ሕግጋት ሁሉ ተጥሶ ሴቶች ገብተው ክርስትና እንዳስነሱበትና ቦታውም በደብርነት እንዳገለገለ ይነገራል። የአካበቢው ማሕበረሰብም ወደ ደሴቱ በመግባት ሁሉም የየራሱን ቡና በመትከል መጠቀም ጀምሮ ነበር። በዚህም ምክንያት ቀደም ሲል የነበረው የገዳም ሕይወት ሊቋረጥ ችሏል (አባ ወልደ ሃና፣2002፣ካ.ቁ.1A ፤አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.6A) ።

የተቋረጠውን የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ሕይወት እንደገና ሙሉ በሙሉ አስተካክሎ ለማስቀጠል መምህር ወልደትንሳኤና ሌሎች አባቶች እንቅስቃሴ ማድረግ ይጀምራሉ። ጊዜውም በአፄ ኃይል ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ1944 ዓ.ም አካባቢ ነበር። አባ ወልደ ትንሳኤ አቤቱታቸውን በፓትርያርኩ በአባ ቴዎፍሎስ አማካይነት ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ያስረዳሉ(ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም፣ የታተመበት ዓ.ም አልተገለጸም፣22) በመጨረሻም ንጉሱ የገዳሙ ስርዓት እንዲመለስ ባስተላለፉት ትእዛዝ መሰረት ገዳሙ እንደገና ሊቋቋም ችሏል።

የአካባቢው ሰዎች ገዳሙ በሚገኝበት ደሴት ላይ ቡናና ሌሎች አትክት እያመረቱ መጠቀም ስለጀመሩ ሳይሆን አይቀርም በገዳሙ መቋቋም ላይ የተወሰነ ተቃውሞ ነበራቸው። አባ ወልደ ሰንበት ይህን አስመልክተው ሲናገሩ የመነኮሳት የአንድነት ሕይወት የአካባቢውን ማሕበረሰብ

ሊጎዳ አይችልም። ነገር ግን አንዳንድ ጽንፈኛ አመለካከትና የግል ተጠቃሚነታቸውን የማሳደግ ፍላጎት ያላቸው የአካባቢው መኳንንት ገዳሙ እንዳይጠናከር እንቅፋት ሆነው ነበር። በአንጻሩ የአካባቢው ሕዝብ ከመነኮሳቱ ሕብረትና ፀሎት እጠቀማለሁ ብሎ ስለሚያምን በገዳሙ እንደገና መጠናከር ላይ ተቃውሞ የለውም። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች በዚህ ገዳም ውስጥ የተለያዩ የግብርና ውጤቶችን እያመረቱ ቤተሰባቸውን ያስተዳድሩ ስለነበር ምትክ ቦታ ሳይሰጣቸው አካባቢው በገዳምነት ሲከለል ቅሬታ ሊፈጥርባቸው ችሏል(አባ ተክለ ዮሐንስ፣ 2002፣ካ.ቁ.1A፤አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.6A)።

የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም እንደገና በገዳምነት እንዲከለል ከፍተኛ ተጋድሎ ያደርጉ ከነበሩ ብዙ አባቶች መካከል አባ ተክለሃይማኖት የሚባሉ መነኩሴ ይጠቀሳሉ። እኚህ አባት መንፈሰ ጠንካራ ስለነበሩ ችግር የሚፈጥሩ አንዳንድ የአካባቢው ነዋሪዎች በእርሳቸው ላይ የተለያዩ ችግሮች ቢፈጥሩባቸውም ችግሩን ሁሉ በዘዴና በጥበብ አልፈው የገዳሙ አንድነት እንዲጠበቅ አድርገዋል(ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም፣ የታተመበት ዓ.ም አልተገለፀም፣ 23)። መምህር ወልደ ትንሳኤም ብዙ ፈተናዎችን ተጋፍጠው እንዳለፉ ይነገራል።

በመጨረሻ ከብዙ ትግል በኋላ ገዳሙ በአፄ ኃይለሥላሴ ትዕዛዝ እንደገና ሲቋቋም አባ ወልደ ትንሳኤ ገዳሙ ታሪካዊነቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ብዙ ደክመዋል። በቅርቡ በሞት የተለዩት አቡነ በርናባስን (የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ናቸው) ያን ጊዜ መነኮሳትን እንዲያስተምሩላቸው ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ተነጋግረው ደመወዝ በማስፈቀድ ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አምጥተዋቸው በዚህ ገዳም ለአራት ዓመት እንዲያስተምሩ አድርገዋል(አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.4.A)።

ገዳማት ከደርግ ዘመነ መንግሥት በፊት ባሉት ዘመናት በርስትና ጉልት ይተዳደሩ ነበር። ነገስታትና አንዳንድ ባለርስቶች ገዳማውያን አባቶች በጸሎታቸው እንዲያስቧቸውና በረከት ለማግኘት ሲሉ መሬት፣ የተለያየ ሀብትና ንብረት፣ ለሃይማኖት መገልገያ የሚሆኑ ንዋያተ ቅድሳትን ይለግሱ ነበር(ዳኛቸው፣1999፣175)። የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳምም ይተዳደርበት የነበረውን ርስትና ጉልት ደርግ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ በመሬት ላራሹ አዋጅ ምክንያት ተነጥቋል። በአሁኑ ሰዓት ገዳማውያን በራሳቸው ጥረት ለመተዳደር ሙከራ እያደረጉ ይገኛሉ(አባ ወልደ ሚካኤል፤አባ ወልደሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.6B) ።

ገዳሙ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ሴት ልጅና የሴት ፆታ ያላቸው እንስሳትም ጭምር ወደ ገዳሙ እንዳይገቡ ይከለከላል። ይህም የሆነው ገዳማውያን በገፀ ሴት እንዳይፈተኑ በመታሰቡ ነው። ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ከወንዶች ጋር ለጉብኝት ወደ ገዳሙ የሚመጡ ሴቶች ገዳሙ ውስጥ መግባት ባይፈቀድላቸውም ከሃይቁ ድንጋግ/ዳርቻ/ ላይ በተሰራች ማስተናገጃ ቤት ውስጥ ተስተናግደው ይመለሳሉ። ገዳሙ ከመንፈሳዊና ከተለያዩ ስርአቶች አንፃር የአባቶችን ትውፊት ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ምንም እንኳ በዚህ ገዳም ውስጥ እነ አባ የዱሩ (የቀድሞ ስማቸው አባ ሞገስ ነው) ቀደም ሲል እንደሚያደርጉት የሰሌን ቆብና የቆዳ ልብስ፣ የማይለበስ ቢሆንም በመመገቢያ ቁሳቁሶች የጥንቱን ትውፊት ለመጠበቅ ይሞከራል (አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.2B፤ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም፣/የታተመበት ዓ.ም አልተገለጸም/፣23)።

በዚህ ገዳም ውስጥ ተምረው ምንኩስናን ከተቀበሉ በኋላ ተዘዋውረው ያስተማሩና በተጋድሎ ያለፉ ቅዱሳን አባቶች እጅግ ብዙ ናቸው። ገዳሙ ለአካባቢው ማህበረሰብ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን ከማስተማሩ ባሻገር ገዳሙ ውስጥ በሚገኘው ቅርስ ሳቢያ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችና የውጭ አገር ቱሪስቶች መስህብ በመሆኑ ሰፊ ማህበራዊ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል። ገዳሙ በዘላቂነት ከተረጅነት ወጥቶ ራሱ የሚተዳደርበትን መንገድ ለማመቻቸት ጥረት እያደረገ የሚገኝ ሲሆን ወደፊት ከዚህ የተሻለ ሥራ ለመሥራት እቅድ እንዳለው ይናገራሉ (አባ ሀይለማርያም፣ 2002፤ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም፣8)።

በዳጋ ጢፋኖስ የሚገኙ ገዳማውያን በአሁኑ ወቅት በደሴቱ ውስጥ ቡናና ሌሎች ተክሎችን እያመረቱ ይተዳደራሉ። ገዳሙ የእርሻ መሬት ያለው ሲሆን የከብት እርባታም እያከናወነ ይገኛል። ሦስት ያህል በነዳጅ የሚሰሩ ወፍጮዎች አሉት። እነዚህ ወፍጮዎች ሁለቱ በደቅ ደሴት ለአካባቢው ህብረተሰብ አገልግሎት ሲሰጡ ተመልክቻለሁ። ስራውን የሚያከናውኑት ገዳማውያን ናቸው። ከዚህ ሌላ ገዳሙ በደቅ ደሴት አንድ የአትክልት መሸጫ ሱቅ አለው። ገዳማውያን ከደቅ ደሴት ወደገዳሙ የሚመላለሱባቸው ሁለት ጀልባዎች ያሏቸው ሲሆን ከእነዚህ ውጭ ሌሎች ሁለት ለአሳ ማጥመጃ የሚሆኑ ጀልባዎችን ለጣና ቂርቆስ ገዳም በውሰት እንደሰጡም ነግረውኛል።

ገዳሙ ራሱን ችሎ እንዲንቀሳቀስ ለማስቻል በሚደረገው ጥረት የዳጋ እስጢፋኖስ የልማትና የእድሳት ኮሚቴ ተቋቁሞ በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 13 ውስጥ 500 ካ.ሜ. ቦታ በሊዝ

በመግዛት ባለ አራት ፎቅ ህንፃ እያስገነባ ይገኛል። በተጨማሪም ገዳሙ በዚሁ ቀበሌ ከአንድ አባት በስጦታ ባገኘው 250 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ለሁለት ቤተሰብ የሚሆን መኖሪያ ቤት ማሰራት ችሏል። በዚህ ገዳም ውስጥ በአሁኑ ሰዓት ከ100-150 የሚደርሱ መናንያን ይገኙበታል ተብሎ ይገመታል።

## 4. ከዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች ትንተና

በዚህ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ተረኮች ትንታኔ ይሰጥባቸዋል። እነዚህ ተረኮች ከገዳሙ አመሰራረትና ገዳሙ አሁን ካለበት ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። ትንተናው ትኩረት የሚያደርገው በተረኮቹ ውስጥ የገዳማውያኑ እምነት ምን እንደሚመስል በመመርመር ላይ ይሆናል። በዚህም መሰረት በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የሰበሰብኳቸውን ተረኮች ቅድመ ገዳም ታሪክ፣ ለገዳሙ መመስረት እንደምክንያት የሚጠቀሱ ጉዳዮች፣ የገዳሙ ቅድስና እና ገዳሙን እንደገና መልሶ የማጠናከር እንቅስቃሴ በሚሉ ክፍሎች መድቤአቸዋለሁ። እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች መሰረት ያደረጉትን የገዳማውያኑን ተረኮች በተለያዩ ማንጸሪያዎች አማካይነት ተንትኜ አቀርቤአለሁ።

### *4.1 ቅድመ ገዳም ተረክ*

ዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም በአባ ሂሩተ አምላክ አማካይነት በ1268ዓ.ም እንደተመሰረተ ቀደም ሲል በጥናቱ ዳራ ላይ ተገልጿል። ይህም ገዳሙ የሚገኝበት የዳጋ ደሴት ከ1268ዓ.ም በፊት ምን ነበረበት የሚል ጥያቄ ያስነሳል። የገዳሙ መነኩሴ አባ ወልደ ሰንበት በገዳሙ የሚገኘውን ስንክሳር /የገድል መጽሐፍ/ ምንጭ በማድረግ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል።

«የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ከመመስረቱ በፊት ደሴቱ በማርያም ስም የታነጸ ቤተክርስቲያን ነበረበት። ይህች ቤተክርስቲያን በአካባቢው የሚገኘው ሕዝበ ክርስቲያን ስርአተ አምልኮ የሚፈጽምባት ናት። በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኘው ስንክሳር/የገድል መጽሐፍ/ ቤተክርስቲያኗ በአብርሃ ወአጽብሃ ዘመነ መንግሥት በ347ዓ.ም እንደተመሰረተች ይናገራል። አብርሃ ወአጽብሃ በዘመኑ ከነበሩት ጳጳስ ከአባ ሰላማ(ከሳቴ ብርሃን) ጋር ይህችን ቤተክርስቲያን ከመሠረቱ በኋላ በአካባቢው የነበረውን ማህበረሰብ ክርስትና እያስተማሩና እያጠመቁ ለሦስት ዓመታት ያህል በዚህች ደሴት መቀመጣቸው ይነገራል» ይላሉ።

ስለ ቅድመ ገዳሙ ታሪክ ተጨማሪ ማብራሪያ የጠየቅኋቸው አባ ወልደ ሰንበትም በትውፊት እንደተላለፈው ገዳሙ ከመመስረቱ በፊት ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ከአክሱም እስከ ምድረ

አምሐራ ድረስ በኦሪት ሕግ ይተዳደር የነበረ ሲሆን በወቅቱም ታላላቅ ምኩራባት ተሰርተው ነበር ይላሉ። እነዚህ ምኩራባት በጣና ሐይቅ ዙሪያ ባሉ ታላላቅ ደሴቶች፣ በርኤሳን፣ በመርጡለ ማርያም፣ በተድባበ ማርያም፣ በአክሱም ጽዮንና በብርብር ይገኙ ነበር። ስለዚህ ከአብርሃ ወአጽብሃ ዘመነ መንግሥት በፊት በጣና ሐይቅ ዙሪያ የሚኖሩ ሕዝቦች የኦሪት እምነት ተከታዮች ነበሩ ማለት ይቻላል ይላሉ። በኋላም ክርስትና መሰበክ እንደጀመረ አብርሃ ወአጽብሃ የተባሉት ነገሥታት አባ ሰላማን በመያዝ ወደ ምድረ አምሐራ አንድም ክርስትናን ለማስፋፋትና ለማጥመቅ በሌላም መንገድ መንግሥታቸውን ለማጠናከር መጥተዋል። ሕገ ክርስትናን ሲያስፋፉም ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፀዋል። ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት መካከል በዚህ ደሴት የነበረችው ታቦተ ማርያም አንዷ ናት። ይህችም ደሴት የአባ ሰላማ የማጥመቂያ ቦታ ሆና አገልግላለች። ለዚህም "ወመጽኡ አቡነ ሰላማ ወክሌቱ ነገሥት ክቡረ ከመይስበኩ ሕገ ክርስትና ለምድረ አምሐራ" የሚል አብነት ይገኛል (አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002፣ካ.ቁ1B፤አባ ተክለ ዮሐንስ፣2003፣ ካ.ቁ.1A)።

የአካባቢው ማህበረሰብ ኦሪትን ይከተል እንደነበር ማስረጃ ሆነው የሚቀርቡት በአካባቢው አንዳንድ አድባራት(ለምሳሌ በጣና ቂርቆስ) ተቀምጠው የሚገኙ የኦሪት መሰዊያ እቃዎች ናቸው። በርግጥ ታደሰ ታምራት እንደሚገልጸው ፈላሻዎች ከተከዜ ጀምሮ እስከጣና ሀይቅ ድረስ ይኖሩ ነበሩ(1972፣192)። እነዚህን የመሰዊያ እቃዎች ይጠቀሙባቸው የነበሩት የአካባቢው ማህበረሰብ ወይስ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ቤተ እስራኤላውያን/ፈላሻዎች/ የሚለው ጥያቄ እስካሁንም ድረስ በቂ መልስ ያላገኘ ጉዳይ ነው። ነገር ግን የአካባቢው ማህበረሰብ ኦሪትን ይከተል ወይም ፓጋን ይሁን እነአባ ሰላማ ዳጋ በተባለው ደሴት ላይ ቤተክርስቲያን ማቋቋማቸው ግን ጥያቄ ሊያስነሳ አይችልም። ሆኖም የአሁኑ የክርስትና ህይወት መነሻው ኦሪት እንደሆነ በመጠቆም እጅግ ወደ ኋላ ተስቦ መተረኩ አማኙ የእምነቱን ምንጭ/የት መጣነት/ አውቆ በእምነቱ እንዲጸና ትልቅ ዋጋ ሊኖረው ይችላል። እንዲሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች«ቀድመን ኦሪትን ስለተቀበልን አህዛብ አንባልም» የሚል የመከራከርያ ሀሳብ ያላቸው ወገኖች አሉ። ስለዚህ ገዳማውያን እነዚህን የኦሪት ቁሶች እንደማስረጃ በመጥቀስ የእምነታቸውን ቀደምትነት በምክንያት ለማስረጽ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።

ታቦተ ማርያም ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ 13ኛ/14ኛ?/ ክፍለ ዘመን ድረስ በዳጋ ደሴት ነበረች። ታቦቷ በአምደ ጽዮን የመንግስት ስልጣንና በአባ ሂሩተ አምላክ የክህነት

ስልጣን አማካይነት ወደ ደቅ ደሴት እንድትሄድ ከመወሰኑ ውጭ የሄደችበት ሌላ ምክንያት አልተጠቀሰም። ነገር ግን በደቅ ደሴት የሚገኘው ሕዝበ ክርስቲያን በየጊዜው ሐይቁን እያቋረጠ ለአምልኮ ቤተክርስቲያን ፍለጋ ለመምጣት በሚፈጠርበት ችግር ምክንያት በክርስትና ሕይወቱ ላይ መዳከም ይከሰታል በሚል ሥጋት ቤተክርስቲያኗን ወደ ሕዝቡ ለማቅረብ ስለታሰበ ሳይሆን አይቀርም ብሎ መገመት ይቻላል። ወይም ደግሞ ገዳሙን የመሰረቱት አባ ሂሩተ አምላክ ገና ከመነሻው ታቦተ እስጢፋኖስን ከሐይቅ እስጢፋኖስ ይዘው መጥተው ስለነበር ገዳሙን በዚህ ሰማዕት ስም ለመሰየም ካላቸው ጽኑ ፍላጎት የመነጨ ሊሆን ይችላል። ከዚህም ሌላ የደቅ ደሴት ወደፊት እንደምናየው የተለያዩ ነገሥታት ከባእድ አምልኮ ጋር በተያያዘ ጥፋተኛ ናቸው ያሏቸውን ሰዎች የሚያስሩባት ደሴት እንደመሆኗ መጠን ይህንን ባዕድ አምልኮ ለመከላከልና ክርስትናን ለማጽናት ስለታሰበ ሊሆን ይችላል። ያለዚያ ደግሞ ብዙ ጊዜ ህይወቱን በተጋድሎ ባሳለፈ ጻድቅ ስም ቤተክርስቲያን አንጾ ገዳም የመመስረቱን ልማድ(አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣159) ተግባራዊ ለማድረግ ሊሆን ይችላል። በእነዚህ ወይም ከእነዚህ ውጭ በሆነ በሌላ ምክንያት ታቦተ ማርያም በደቅ ደሴት "ኮታ"[5] በተሰኘች ቦታ ላይ ተሰርታለች።

ኮታ ማርያም በደቅ ደሴት ላይ የዳጋ እስጢፋኖስ መሥራች አባ ሂሩተ አምላክ እንዳሰሯት ይነገራል። ቤተክርስቲያኗ በምትሰራበት ጊዜ ማን እንዳመጣቸው ሳይታወቅ በኃይቁ ድንጋግ[6] ላይ ረጃጅምና ወፋፍራም ግንዶች ተጥለው ይገኛሉ። እነዚህ ግንዶች በአካባቢው ካሉ ዛፎች ጋር የማይመሳሰሉ በመሆናቸው በእግዚአብሔር ተዓምር ጎርጎራ ማዕበል (ከጎርጎራ አቅጣጫ የሚመጣ ማዕበል ነው) እንዳመጣቸው ይታመናል። በእነዚህም ግንዶች አማካይነት ቤተክርስቲያኗ በአማረ ሁኔታ ልትሰራ ችላለች። ከዚህም ጊዜ ጀምሮ አባ ሂሩተ አምላክ ለአካባቢው ማሕበረሰብ የሃይማኖት አባት ሆነው ክርስትናን ለማስፋፋት ችለዋል (አባ ተክለዮሐንስ፣2003፣ካ.ቁ.1B፤አባ ወልደ ሰንበት፣2002፣ ካ.ቁ 2A) ።

[5]አባ ወልደሰንበት ሲናገሩ አፄ ፋሲል ለአንዳንድ ሥራ ወደ ደሴቷ ሲመጡ የማረፊያ ድንኳን የሚተክሉበትን ቦታ "ፋሲል ከኛ" በሚል ሲጠራ ስለነበርና ቤተክርስቲያኗም በዚያ ቦታ ላይ ስለታነፀች "ፋሲል ከኛ" ከሚለው ሐረግ ውስጥ "ከኛ" የሚለውን ቃል በመውሰድ "ኮታ" ተብሏል የሚሉ የአካባቢውሽማግሌዎች አሉ። ከዚህ በተለየም ቤተክርስቲያኗ ቀደም ሲል ተሰርታበት የነበረውን ቦታ ቀይረው ሲሰሩ ትንሽ "ኮተት" አድርገን እንስራት ሲሉ "ኮተት" ከሚለው ቃል "ኮታ" የሚል ስያሜ እንደተሰጣት ይናገራሉ (አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ካ.ቁ1B)። ከዚህ ሌላ ደግሞ በዚህ አካባቢ የኦሮምኛ ተናጋሪ ህዝቦች ሊኖሩ ስለሚችሉ "ኮታ" የሚለው ቃል "ወደዚህ ኑ" የሚል የአማርኛ ፍች ስላለው ቃሉ ከኦሮምኛ ቋንቋ የተወሰደ ሊሆን ይችላል። በርግጥ ኮታ ማርያም ስያሜውን "ከፋሲል ከኛ"ወይም "ኮተት" ከሚለው ቃል ወይም ደግሞ "ኮታ» ከሚለው የኦሮምኛ ቃል ስለመገኘቱ ተጨማሪ ማስረጃ ማግኘት ባይቻልም እስከ አፄ ኢያሱ /አድያም ሰገድ/ ዘመነ መንግሥት ድረስ ደቅ ማርያም እየተባለች ትጠራ ነበር (ተክለፃድቅ፣1961፣205)።

[6] ድንጋግ፣ዳርቻ፣ ዳር፣ ወሰን፣ ድንበር፣ ወደብ፣ ገደብ፣ አፋፍ፣ ጠረፍ ማለት ነው( ኪዳነ ወልድ፣1948፣354)።

በሐይቁ ድንጋግ ላይ ስለተገኙት ግንዶች የሚተርከው ተረክ አስፈላጊነቱ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል። በርግጥ ትክክለኛ መልስ ማግኘት ባይቻልም የተለያዩ መላምቶች ማስቀመጥ ይቻላል። የመጀመሪያው መላምት ቤተክርስቲያኗ ወደአንድ ሺህ አመት አካባቢ ከቆየችበት ቦታ (ደሴት) እንድትነቀል መደረጉን የሚቃወሙ ወገኖች ስለነበሩ የታቦተ ማርያም ወደ ደቅ ደሴት መሄድ የእግዚአብሔር ፈቃድ /እግዚአብሕር የወደደው ጉዳይ/ እንደሆነ ለማሳየት ሊሆን ይችላል። ከዚህ ሌላም ገዳሙ በገዳምነት እንዲከለል ያልፈለጉ ወገኖች (እነዚህ ሰዎች ደሴቱን በርስትነት የያዙ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ) በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ጣልቃ እንደመግባት ተሰምቷቸው እንዲፈሩና እንዲሸማቀቁ ሊሆንም ይችላል። ወይም ደግሞ ታቦተ ማርያም ወደ ደቅ ደሴት መሄድና ገዳሙ በእስጢፋኖስ ስም መሰየሙ የእግዚአብሔር ሃሳብ እንጂ የሰው ሃሳብ እንዳልሆነ ለማስረፅ ይሆናል። በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ይሄ ተረክ የገዳሙን መስራች ቅዱስነት ሁሉም ወገን የተቀበለው ይመስላል። ይሄ ተረክ እስከዚህኛው ትውልድ ድረስ መተረኩ ዋናው ምክንያት የመስራቹን ቅዱስነት ለማፅናትና ይሄ ቅዱስ አባት በመሰረተው ገዳም ውስጥ መገኘትም ለቅድስና ዋና መሰረት እንደሆነ ለማሳየት ይመስላል።

አሁን ዳጋ እስጢፋኖስ እየተባለ የሚጠራው ገዳም ቀድሞ ደቅ እስጢፋኖስ እየተባለ ይጠራ ነበር። እስጢፋኖስ በዘመነ ሐዋርያት በድንጋይ ተወግሮ በመገደሉ ምክንያት ቀዳሚ ሰማዕት የሚል ስያሜ የተሰጠው ሐዋርያ ነው(ሐዋ.፣7፣54)። ገዳሙ በዚህ ሰማዕት ስም መሰየሙ የገዳሙ ማህበራዊ አንድነት ልክ እንደ እስጢፋኖስ ማህበራዊ አንድነት ያለው ነው ከሚል እምነት እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ ነግረውኛል። ደቅ ማለት ምን ማለት ነው? ደቅ የሚለውን ስያሜ እንዴት ሊያገኝ ቻለ? ይህንን ስያሜ ማን ነው የሰጠው? ለሚሉት ጥያቄዎች መረጃ አቀባዩ አባ ወልደ ሰንበት በሚከተለው ተረክ አማካይነት ምላሽ ሰጥተውኛል።

አባ ወልደ ሰንበት ስለደቅ ደሴት ስያሜ አመጣጥ ገድለ አባ አፍቅረነ እግዚእን በምንጭነት ጠቅሰው ይናገራሉ። አባ ገብርኤል የሚባሉ ግብፃዊ ጳጳስ ነበሩ። በዚህም ጊዜ አንድ ንጉሥ ነበር።(ግዕዙ «ወአሀዱ ንጉስ» ይለዋል እንጂ ስሙን አይጠቅስም ብለውኛል) በዚህ ዘመን "ከናዚራን" የሚባሉ መናፍስትን የሚከተሉ ሰዎች ነበሩ (ባዕድ አምልኮ ተከታዮች ማለት ነው)። እነዚህ ሰዎች በጳጳሱ በአባ ገብርኤል ላይ በቅናትና በምቀኝነት ይነሱባቸዋል። በዘመኑም ከነበረው ንጉሥ ጋር ለማጣላት ብዙ ጥረት ያደርጋሉ። በተለይም በጳጳሱ ቤት

ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩት አገልጋዮች ከሕገ ሰብ ውጭ ለሰው ተፈጥሮ የማይመች ሥራ እንደሚሠሩና ሰብአዊ ባህርይ ያለውን የሰው ልጅ እንደሚመገቡ በመግለጽ ይከሷቸው ነበር። ንጉሱ ግን የጳጳሱን ደግነትና፣ የሃይማኖታቸውን ጽናት ስለሚያውቅ ክሳቸውን አይቀበለውም።

አንድ ቀን ንጉሱ ጳጳሱን ለመጠየቅ ወደ ቤታቸው ይሄዳል። በዚህም ጊዜ ጳጳሱ ለንጉሱ ግብር ለማብላት ይዘጋጃሉ። የጳጳሱ አገልጋዮችም ግብር አዘጋጁን በሚል ለንጉሱ አንድ ሕፃን አርደው በድስት በማብሰል በጨርቅ ሸፍነው ያቀርቡለታል። የተሸፈነው ሲከፈት ምግቡ ከህፃን ገላ የተዘጋጀ ምግብ መሆኑን ንጉሱ ሲመለከት ይደነግጣል። በኋላም ንጉሱ "የሰው ሥጋ መብላት የእንስሳ ሥጋ ከመብላት ይሻላልን?" በማለት ጳጳሱን በቁጣ ጠየቃቸው። በዚህ ጊዜ ጳጳሱ በጣም ደነገጡ። ነገር ግን ወዲያው እግዚአብሔር ለጳጳሱ የሰው ተንኮል መሆኑን ገለፀላቸው። ተነስተውም "አንተኑ ሕፃን መኑ ቀተለከ ተናገር ለጽድቅከ" /"አንተ ህፃን ሆይ ለጽድቅህ/ለእውነትህ/ ስትል ማን እንደገደለህ ተናገር"/ አሉ። ይህን ጊዜ የተሰራው ወጥ በሰብአዊ አንደበት "ክህነትከሰ ቅድስት ይእቲ" /ክህነትህ የተቀደሰች ናት/ በማለት ዘመዶቹ አርደውና አብስለው በድስት እንዳቀረቡት ይመሰክራል።

በዚህን ጊዜ ንጉሱ መኳንንቱን ሁሉ ሰብስቦ ይህን ሥራ የሰሩትን ሁሉ ለፍርድ አቀረባቸው። መኳንንቱም ከባድ ጥፋት ስላጠፉ ዘራቸው ይመተር[7]/ይጥፉ/ ብለው ይፈርዳሉ። ንጉሱም አበይቱን /ትልልቆችን/ ሁሉ በሰይፍ ያስገድላቸዋል። በኋላም በጳጳሱ ምልጃ ህፃናቱና ሴቶች ከሞት ይተርፋሉ ። ሆኖም ንጉሱ እነዚህን ህፃናትና ሴቶች ማየት አልፈልግም በማለቱ ጣና ሐይቅ ውስጥ ወደሚገኝ ትልቅ ደሴት እንዲጋዙ ይደረጋል። ይህችም ደሴት የህፃናትና የግዞት ደሴት ስለሆነች ደቅ ተባለች። "ደቅ" ማለት በግዕዝ "ሕፃን" ማለት ነው (አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002፣ .ቁ1B)።

ከዚህ ተረክ መረዳት የሚቻለው ደቅ በተባለው ደሴት ላይ በግዞት የሰፈሩት የባዕድ አምልኮ ተከታዮች መሆናቸውን ነው። በዘመኑ በጣና ሀይቅ አካባቢ የነበሩ ሕዝቦች ክርስትናን ያልተቀበሉ በመሆናቸው በተለይ ፈላሻዎችና እምነት አልባ የሆኑት የአካባቢው ሰዎች የክርስትናን መስፋፋት ይቃወሙ ነበር (ታደሰ፣1972፣192)። በዚህም ምክንያት በክርስትና እምነት ተከታዮችና በአካባቢው ማህበረሰብ መካከል አንዳንድ አለመግባባቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል። ስለዚህ ይህ ተረክ ይህንን ሃሳብ መነሻ አድርጎ አንዱ ስለሌላው

[7] ይመተር፣ይቆረጥ፣ ይቀራረጥ፣ ይበጠስ፣ ይለይ፣ ይሻር፣ጨርሶ ይጥፋ (ኪዳነ ወልድ፣1948፣828) ማለት ነው።

ያለውን ግምት የሚገልጽበት ነው ማለት ይቻላል። ነገር ግን ይህ ተረክ አሁን ድረስ መተረኩ ለአሁኑ ገዳማዊ ሕይወት ምን ፋይዳ አለው የሚለው ጥያቄ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። የመጀመሪያው ሀሳብ በአሁኑ ጊዜ የሚገኘው የክርስትና ሕይወት ብዙ ፈተናዎችን ተቋቋሞ እዚህ ላይ እንደደረሰ ለገዳማውያን ለማሳየትና የክርስትና ሕይወት እና ተግዳሮት የማይላቀቁ በመሆናቸው ገዳማውያን የሚመጣባቸውን ፈተና በጽናት እንዲቋቋሙ ለማስተማር ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የአካባቢውን ስያሜ የት መጣነት በራሳቸው አተያይ ከገለጹ በኋላ እነሱ ስለሌላው ማህበረሰብ ያላቸውን እምነት በማስረጽ ገዳማውያን ለዚህ ማህበረሰብ ከክርስትና ሕይወቱ አንጻር ሀላፊነት እንዳለባቸው ለማስተማር ይሆናል። አባ ሂሩተ አምላክ 60 ዓመት እንቅልፍ ሳይተኙ የድንጋይ ቆብ በማድረግ ለአካባቢው ማህበረሰብ እንደ ጸለዩና ክርስትናን እንዳስፋፉ ይነገርላቸዋል። በመሆኑም የአሁኑ ገዳማዊ የአካባቢው ማህበረሰብ ያለውን ሀይማኖታዊ መሰረት በመረዳት ሃላፊነቱን እንዲወጣ ለማስገንዘብ ይሆናል። ወይም «እነሱ እንዲህ ናቸው እኔ ግን እንዲህ ነኝ» በማለት የራስን ማንነት ለመገንባት ሊሆን ይችላል።

በርግጥ በደቅ ደሴት የነበሩ ሕዝቦች ሁሉ ወደዚህ ደሴት የመጡት ከላይ በቀረበው ተረክ መሰረት ነው ወደሚል ድምዳሜ መድረስ ባይቻልም ደሴቷ የተለያየ የኃይማኖትም ሆነ የፖለቲካ ወንጀል ፈፅመዋል የተባሉ ሰዎች የግዞት ቦታ እንደነበረች ግን ቀዋየ የምጠቅሳቸው የታሪክ መጻሕፍት ይገልጻሉ። በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት "ቤተ ደስክ" የምትባል የዛር አይነት የነበረች ሲሆን እንደወርቅ የምታበራና በአማኞቿ ላይ የሞት ሽረት ስልጣን የነበራት ናት (ስርግው፣1981፣135)። ንጉሱ ለዚህች የዛር መቅደስ የሰገዱ ሰዎችን ከራሱ ዘመዶች ጀምሮ በባርነትና በሞት እንደቀጣና በክፉ ሥራው "ዘርዐ ሰይጣን" የተባለውን ዘርዐ ጽዮን በግዞት ወደ ሐይቅ እንዲጋዝ(ተክለፃድቅ፣1951፣158) እንዳደረገው ሰፍሮ እናገኛለን። በርግጥ በዚህ ገለፃ ላይ ሃይቁ የትኛው እንደሆነ አልተገለጸም።ይሁን እንጂ ከሌሎች ሀይቆች ይልቅ ጣና ሀይቅ ለግዞት ካለው ምቹነት አንጻር የግዞት ቦታው ደቅ ደሴት ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። በተጨማሪም አፄ በእደ ማርያምን "ፈረስ ይጋልባል እንጂ የመንግሥትን ሥርአት ለመፈፀም ፍርድ አይሰማም፤ ልጅ ነው" ብለው ያሟቸውን ሰዎችና ሌሎቹን ሰዎች ጭምር የእግራቸውን ሥር /ቋንጃቸውን/ እየቆረጡ ወደ ደቅና ሌሎች ቦታዎች አግዘዋቸዋል (ተክለፃድቅ፣ 1951፣236)።

ከዚህ ሌላም አፄ ፋሲል በሚቱ በአባ ስምኦን እግር ጳጳስ እንዲላክላቸው ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ከአባ ማቴዎስ ጋር ሲላላኩ እንደነበር አንድ ሐሰተኛ ግብፃዊ ተልኬአለሁ ብሎ

በመምጣት ሥራ የጀመረ ቢሆንም በኋላ ግን ጓደኛው የሆነ ሰው ሐሰተኛ መሆኑን እንደተናገረበት ወዲያው ተይዞ በደቅ ሊታሰር ችሏል(ተክለፃድቅ፣ 1961፣157)። በአፄ ሀዝብ ናኝ ዘመን የደብረ ጽሞና ገዳም መስራች በነበሩት በአባ ሲኖዳ ላይ ንጉሱን የሚቃወም ንግርት ተናግረሃል በሚል ክስ ቀርቦባቸው በአፄው ትዕዛዝ ወደደቅ ደሴት እንደተጋዙና ህይወታቸው እዚያው እንዳለፈ ገድላቸው ይናገራል(የአማራ ብሔራዊ ክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣1991፣67)።

እንግዲህ በተለያዩ ዘመናትና ንጉሶች የተለያየ ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች/ቡድኖች ሊሆን ይችላሉ/ ለጥፋታቸው እንደ መቀጫ ከሚወሰንባቸው ቅጣት መካከል ግዞት ይገኝበታል። ለግዞት ከሚመረጡት ቦታዎች መካከል ከማህበረሰብ የተነጠሉ፣ እንደልብ መንቀሳቀስ የማይቻልባቸው፣ ለቁጥጥርና ለክትትል አመቺ የሆኑ ቦታዎች ናቸው። ደቅ ደሴት ከሌላው ማህበረሰብ ለመገናኘት የግድ ብዙ ሰዓት በዋና የጣና ሐይቅን ማቋረጥ ይጠይቃል። ይሄ ደሴት በተለይ ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ ሰዎች ጥፋት መፈጸማቸው በባለሥልጣናት ከታመነ ያለ ርህራሄ ይጋዙበት የነበረ ቦታ እንደሆነ መገመት ይቻላል።

አባ እስጢፋኖስ በሚከተለው ሃይማኖት(ለስዕል፣ ለመስቀልና ለንጉስ አንሰግድም የሚሉ ናቸው) በእሱና በሌሎች ወገኖች በተፈጠሩ አንዳንድ ልዩነቶች ምክንያት በርካታ መከራዎችን የተቀበለ ሲሆን ከነተከታዮቹ ብዙ የግዞት/የስደት/ አጋጣሚዎችን አስተናግዷል። ከእነዚህም የግዞት ቦታዎች መካከልም እስከ ባህረ ሰፍ እንደተሰደደና "ባሕረ ሰፍ" ጣና ሃይቅ ሊሆን እንደሚችል ግምት ያላቸው መሆኑን ሰፍሮ እናገኛለን። እንዲያውም ደቀ እስጢፋኖስ በሃይቁ ላይ ባለ ደሴት "ደቀ እስጢፋ" የሚባል ገዳም መስርተው እንደነበር ይታመናል (ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማርያም ገዳም፣ 1996፣ 14)። እንዲሁም ጌታቸው በበኩላቸው ደቂቀ እስጢፋኖስ በመጀመሪያ እስከ ጣና ባህር እንደተሰደዱና (2002፣73) በኋላም ወደጎጃም እንዲጋዙ ተደርገው አፍንጫቸውን፣ ምላሳቸውንና ቋንጃቸውን በመቁረጥ ጎን በተሰኘችው ደሴት ላይ በግዞት እንዳስቀመጧቸው (2002፣160) አስፍረው እናገኛለን። በመጀመሪያው ስደት እስጢፋኖስ ከሌሎች መነኮሳት ጋር አብረው የተሰደዱ ሲሆን በሁለተኛው ስደት ጊዜ ግን ስለመኖራቸው ተገልጾ አላገኘሁም።

ምናልባት ጻጋ እስጢፋኖስ የነበረችው ታቦተ ማርያም ወደደቅ ደሴት ሄዳ የተተከለችው ደቂቀ እስጢፋ በዚህ ደሴት ለግዞት መጥተው ኖረው የእነሱን እርምጃ ለመቃወምና የአካባቢውን ሕዝብ ከእነሱ አስተምህሮ ለመከላከል ይሆን የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ሆኖም አባ ወልደ ሰንበት

ደቂቀ እስጢፋ የሚባሉት ወደ ደቅ ደሴት ተሰደው ነበር የሚለው ግምት ፍፁም ስህተት ነው ይላሉ። ለምሳሌ በአገው ምድር ዳንጉር በሚባል አካባቢ "ደቀ እስጢፋ" የሚባል ገዳም አለ። ይህም እንዲሁ የስም መመሳሰል እንጂ ከአባ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉዶ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም(አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.2.A) በማለት በአፅንኦት ይገልጻሉ።

በርግጥ ደቂቀ እስጢፋ (የእስጢፋኖስ ተከታዮች) የተነሱበትንና የተስፋፉበትን ዘመን በሚገባ ማጥናት ከደቅ ደሴት ወይም በጣና ሃይቅ ውስጥ ከሚገኙት ሌሎች ደሴቶች ጋር ያላቸውን ተያያዥነት ለመገንዘብ ያስችላል። ደቂቀ እስጢፋኖስ የተነሱት በአጼ ይሥሐቅ(1406-1426) ዘመነ መንግስት(ጌታቸው፣2002፣24) እንደሆነ ሰፍሮ እንገኛለን። «ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ» በሚለው መጽሐፍ ውስጥ የእስጢፋኖስ ተከታዮች አብዛኛው እንቅስቃሴ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን እንደሆነ ይገልፃል። ይህ ሀሳብ ታቦተ ማርያም ወደደቅ ደሴት ሄደች ከሚባለው ጊዜ ጋር የማይቀራረብ በመሆኑ የታቦቷ ወደደሴቷ መሄድ ከደቂቀ እስጢፋኖስ ጋር የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ መረዳት ይቻላል።

ይሁን እንጂ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል ደቂቀ እስጢፋ በሚል የሚጠራቸው በጣና ደሴት በቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም የሚያገለግሉትን መነኮሳት ወይም ይህንን አዲስ ሀሳብ ያመነጨውን የእስጢፋኖስን ተከታይ መነኮሳት ይሁን (1951፣191) ማረጋገጫ እንዳልሰጠ አስፍረዋል። በመሆኑም የአሁኑ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ከደቂቀ እስጢፋኖስ ጋር ግንኙነት የለውም ወይም አለው ብሎ በእርግጠኛነት መናገር አይቻልም። ከዚህ በተለየ ሁኔታም በ15ኛው ምዕት ደቀ እስጢፋ የሚባል ኢትዮጵያዊ የቅኔ ሊቅ ለአጼ እስክንድር(1470-1480) ቅኔ እንዳስተማረና የመጨረሻ የህይወት ዘመኑን ያሳለፈው ከጣና ደሴቶች በአንዲቱ ስለነበር ያቺ ደሴት እስካሁን በስሙ እንደምትጠራ(ስርግው፣1981፣136) ሰፍሮ የሚገኝ በመሆኑ ይህ ጉዳይ ወደፊት ሰፋ ያለ ጥናት የሚጠይቅ መስሎ ይታየኛል።

እንግዲህ በዳጋ ደሴት የነበረችው ታቦተ ማርያም ወደ ደቅ ደሴት የሄደችው በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት (በ14ኛው ክፍለ ዘመን) በመሆኑና ደቂቀ እስጢፋኖስ የሚባሉት የስደት ዘመን ከ1426-1460 (በ15ኛው ክፍለ ዘመን) በመሆኑ የታቦቷ ወደ ደቅ ደሴት እንድትሄድ መደረጉ ከደቂቀ እስጢፋ ጋር የሚያያይዘው ነገር አይኖርም ማለት ይቻላል። ይህም ሲባል ግን እነዚህ ቤተሰቦች (የእስጢፋኖስ ተከታዮች) ወደደሴቷ አልተጋዙም ወይም ገዳም መስርተው አልነበረም ለማለት አይደለም። ስለዚህ እስካሁን በተመለከትናቸው የታሪክ ሆነ

የቃል ማስረጃዎች ደቅ ደሴት ነገስታት የተለያየ ወንጀል ፈፅመዋል ያሏቸውን ግለሰቦች (ወይም ቡድኖች) የሚያግዙበት ደሴት መሆኑን ነው።

በጠቃላይ የገዳሙን ቅድመ ታሪክ በተመለከተ ገዳማውያን የሚያቀርቡት ተረክ ከታሪክ ድርሳናት ጋር በተወሰነ ደረጃ የሚቀራረብበት ሁኔታ ያለ መሆኑን መገመት ይቻላል። የገዳማውያን ተረክ ተዓምራዊነት ያላቸውን ጉዳዮች የሚያካትት ሲሆን በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ቅዱሳን ተብለው የሚጠሩት ምን ያህል በልዕለ ተፈጥሮ እንደሚደገፉ የሚያመላክቱ ናቸው። እነዚህ ተረኮች አሁን ላለው ገዳማዊ የአካባቢውን ሁኔታ ካለው ቅድስና አንጻር መሰረቱን አደላድሎ የሚያሳውቅ ነው ማለት ይቻላል።

## *4.2 ለዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መመሥረት እንደምክንያት የሚጠቀሱ ጉዳዮች*

### 4.2.1 ለመስራቹ ከኢየሩሳሌም ታቦት መምጣት

አባ ሂሩተ አምላክ ስርዓተ ምንኩስናን የተማሩት በሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በ13ኛው ክፍለ ዘመን ነው። በወቅቱም የሐይቅ እስጢፋኖስ መምህር የሆኑት የአባ ኢየሱስ ሞአ ረድ ነበሩ። በዚህም ጊዜ በዚህ ገዳም ውስጥ በክርስትና አማኞች ዘንድ በተለይም ከገዳማትና ከክርስትና መስፋፋት ጋር በተያያዘ ከፍ ባለ ስም የሚጠሩት መነኮሳት (አባ ተክለሃይማኖት፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና ሌሎች) ከአባ ሂሩተ አምላክ ጋር ስርአተ ምንኩስናን ተምረዋል። ከዚህም ሌላ የነጋሲ ዘር የሆነው የይኩኖ አምላክ አባት/አድያም ሰገድ?/ ልጁ ይኩኖ አምላክ በዛጉዬ ነገሥታት እንዳይገደልበት ፈርቶ ለገዳሙ መምህር ለአባ ኢየሱስ ሞአ በአደራ ሰጥቶት ስለነበር እርሱም በዚህ ገዳም ውስጥ ይገኝ ነበር(ተክለፃድቅ፣ 1951፣10፤ ዘመድኩን፣ 1992፣205፤ አባወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ. 2.A)።

በዚህ ጊዜ በአባ ተክለሃይማኖትና በይኩኖ አምላክ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት አባ ተክለሃይማኖት መንግሥትን ከዛጉዬ ወደ ሰሎሞናዊው ስርዎ መንግሥት ለመመለስ ሊረዱቸውና በዚሁ ምክንያት ይኩኖ አምላክ ከነገሱ ሲሶ/አንድ ሦስተኛ/ መንግሥት ሊሰጧቸው ተስማምተዋል። በዚህም መሰረት ይኩኖ አምላክ እንደነገሱ ለተክለሃይማኖት ሲሶ መንግሥትንና የእጨጌነት ማዕረግ፣ በፀሎት ለረዷቸው ለአባ ኢየሱስ ሞአ እና በሐይቅ ገዳም በእርሳቸው እግር ስር ለሚተካው መምህር የአቃቤ ሰዓትነት ማዕረግ ተሰጣቸው። በዚህም መሠረት በዚህ ገዳም ውስጥ የነበሩ የወንድማቸው ልጅ የሆኑት አባ ሂሩተ አምላክ አቃቤ

ሰዓትነትን[8] ማዕረግ ማግኘት ችለዋል። አባ ሂሩተ አምላክም ሆኑ አባ ተክለሃይማኖት ማዕረጋቸውን የተቀበሉት በአባ ኢየሱስ ሞአ አማካኝነት ነው(ዘመድኩን፣1992፣205፤ ተክለፃድቅ፣1951፣21 እና 23፤ አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.2A)።

ስምምነቱ የአቃቤ ሰዓትነት ማዕረግ ለአባ ኢየሱስ ሞአና በእሳቸው እግር ለሚተካው አበምኔት እንደሚሰጥ የሚገልጽ ቢሆንም አባ ኢየሱስ ሞአ በህይውት እያሉ ለምን ለአባ ሂሩተ አምላክ እንደተሰጣቸው ግልፅ አይደለም። አባ ሂሩተ አምላክ የአቃቤ ሰዓትነትን ሹመት የወሰዱት አባ ኢየሱስ ሞአ ሹመቱን ለመውሰድ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ይሆን ወይም አባ ሂሩተ አምላክ አፄ ይኩኖ አምላክ የወንድም ልጅ ስለሆኑ ይሆን በቂ መረጃ ማግኘት አልቻልሁም። አፄ ይኩኖ አምላክ ለሁለቱ መነኮሳት የሰጧቸውን የመንግሥትና የቤተክህነት ስልጣን አባ ተክለሃይማኖት ሲቀጥሉ አባ ሂሩተ አምላክ ግን በተሰጣቸው ማዕረግ ጥቂት ጊዜ ካገለገሉ በኋላ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቀው ከሰው ተለይተው እግዚአብሔርን በገዳም ለማገልገል ይወስናሉ። ለዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መመሥረት እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች አንዱ መሥራቹ አምላካቸውን በፀሎት በለመኑት መሠረት ሕቡእን የሆኑ መነኮሳት ከኢየሩሳሌም ቶራ በምትባል እንደ አጋዘን ባለች እንስሳ ታቦተ እስጢፋኖስንና ታቦተ ጊዮርጊስን ጭነው ይዘውላቸው መምጣታቸው ነው። በኋላም እነዚህ ሁለቱ ታቦታት በሐይቅ ገዳም ለተወሰነ ጊዜ ይቆያሉ። አባ ሂሩተ አምላክም በሐይቅ እስጢፋኖስ የሚገባቸውን ያህል ካገለገሉ በኋላ ታቦተ ጊዮርጊስ በዚያው በሐይቅ እስጢፋኖስ ፊት ለፊት በሚገኝ ቦታ ላይ እንዲተከል ካደረጉ በኋላ ታቦተ እስጢፋኖስን ይዘው ወደ ዳጋ ደሴት ይሄዳሉ(አባ ወ/ሰንበት፣2002፣ካ.ቁ B፤አባ ሀይለማርያም፣2002)።

ከኢየሩሳሌም ስለመጡት ስለእነዚህ ሁለት ታቦታት አመጣጥ በአባ ሂሩተ አምላክ ቅድስናና በእግዚአብሔር ፈቃድ የተፈፀመ ተዓምር እንደሆነ አባ ወልደ ሰንበት ነግረውኛል። ይሁን እንጂ በዚህ ወቅት በሃይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ላይ ጥናቱን እያደረገ የሚገኘው ጓደኛዬ ተስፋዬ ተገኝ እንደነገረኝ ለሃይቅ እስጢፋኖስ ገዳም መመሥረት ምክንያት ነው ተብሎ ቃለመጠይቅ ካደረገላቸው ሰዎች ሲገለጽ የሰማው ሁለቱ ታቦታት ለአባ ኢየሱስ ሞአ ከኢየሩሳሌም በዚችው ቶራ በተባለችው እንስሳ ሕቡአን እንዳመጡላቸው ነው። በመሆኑም እነዚህ የተባሉት ሁለት ታቦታት የመጡት ለአባ ኢየሱስ ሞአ ወይስ ለአባ ሂሩተ አምላክ የሚል ጥያቄ ያስነሳል።

[8] አቃቤ ሰዓት ማለት፣ ንጉሱ በግብር ወይም በጉባኤ በተቀመጠ ጊዜ ዓቃቤ ሰዓቱ በትረ ወርቅ ይዞ ቆሞ የህግንና የወግን፣ የሥርአትን ነገር እያስተናበረ ያከናውናል። ዓቃቤ ሰዓት ታላቅ የተከበረ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክህነት ባለስልጣን ነው (ተክለፃድቅ፣ 1951፣23)።

ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም በ13ኛው ምዕተ ዓመት የተመሠረተ ገዳም ነው። ገዳሙ ከዚሁ ምዕተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ እስከ 16ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ የገነነ ስም ነበረው(ዳኛቸው፣ 1999፣ 188)። ይሂ ገዳም በገዳምነት በ13ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ይጀመር እንጂ በቅዱስ እስጢፋኖስ ስም ቤተክርስቲያኑ የተሰራው በንጉስ ድልነዓድ ዘመነ መንግሥት (902-912) ነው። ይህንንም አስመልክቶ ሉሌ መላኩ አባ ኢየሱስ ሞአ ተሠርቶ ወደነበረው ወደ ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ሄደው መንፈሳዊ ትምህርት ቤትና የአንድነት ገዳም መሠረቱ(ሉሌ፣ 1997፣ 66) ይላል።

እዚህ ላይ መረዳት የሚቻለው የእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን በገዳም ስም ከመመሥረቱ ከ400 ዓመት በፊት የተሰራ ቤተክርስቲያን መሆኑን ነው። ስለዚህ አባ ኢየሱስ ሞአ ታቦተ እስጢፋኖስ ከኢየሩሳሌም በሕቡእን አማካይነት መጥቶላቸው ገዳሙን ሊመሰርቱ እንደቻሉ የሚነገረው ተረክ እውነተኛነት ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል ማለት ነው። ይሂ ማለት ግን ለአባ ሂሩተ አምላክ እንደመጣላቸው ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም። ምናልባት ግን አባ ሂሩተ አምላክ በሐይቅ እስጢፋኖስ ስርአተ ምንኩስናን የተማሩና ብዙ የአገልግሎት ዘመን የነበራቸው በመሆኑ ከዚህም ጊዜ በኋላ ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ ሲሄዱ ታቦተ እስጢፋኖስን ይዘው እንደነበር ስለሚታመን ከኢየሩሳሌም የመጣው ታቦተ እስጢፋኖስ ምናልባት ለእሳቸው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ሊያሳድር ይችላል።

ከዚህ በተለየ ሁኔታ ቶራ በሚል ስም የምትጠራ እንስሳ ነበረች ወይ? ወይስ ደግሞ በ13ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ የነበረች ሆና አሁን የጠፋች እንስሳ ናት? ወይስ ይህች እንስሳ በመንፈሳዊው ዓለም ህቡእን ተብለው እንደሚታወቁት ሁሉ እነዚህም እንስሳት ለእነዚህ ህቡእን ሰዎች የሚያገለግሉ ልዩ የእንስሳ ዘሮች ይሆኑ ይሆን የሚልም ጥያቄ ያስነሳል።

ቶራ[9] የሚለው የእብራይስጥ ቃል እንደሆነና ሁለት ፍችዎች እንዳሉት በኪዳነ ወልድ መዝገበ ቃላት ላይ ሰፍሮ እናገኛለን። አንደኛው የዚህ ቃል ፍች ህግ፣ ስርዓት፣ ኦሪት፣ ዐስርቱ ቃላት የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእንስሳ መጠሪያ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን ነው(1948፣ 894)። የዚህ ቃል ፍች በእብራይስጥ ኦሪት የሚል ፍች እንዳለው ያመለክታል። ይሁን እንጂ ቶራ የተሰኘው የእብራይስጥ ቃል ከተሰጠው ፍች በተጨማሪ በእብራይስጥ ቋንቋ የእንስሳ መጠርያ ሆኖ ስለማገልገሉ መዝገበ ቃላቱ አያመለክትም። ነገር ግን ይህንኑ ቃል የአማርኛው

[9] ቶራ፣ ቦኽር፣ የበረሀ እንስሳ፣ የፌቆና የዋልያ ወገን፣ ቀንዱ ረዥም፣ ዐጽቃም፣ ባለብዙ ቅጥያ፣ ዥራቱ አጭር፣ የሰሳ አይነት፣ ወተታም(ዘዳ፣14፣5)(ኪዳነ ወልድ፣1948፣894)

ቋንቋ የእንስሳ መጠርያ በማድረግ ይጠቀምበታል። እንዲሁም የዚችን እንስሳ ስዕል የኢትዮጵያ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ በአረቄ ጠርሙስ ላይ ቀንዶ በሚል ስያሜ እንደ ንግድ ምልክት ይጠቀምባታል።

እንደእኔ ሀሳብ በዚህ ተረክ ውስጥ ህቡአን ቶራ በተሰኘው እንስሳ ታቦት/ጽላት ማለታቸው ነው/ ከእስራኤል ጭነው እንዲያመጡ ሲደረግ ዓላማው ይህንን ታቦት ከተለመደው ታቦት የላቀ ክብር ያለው አድርጎ ለማሳየት ይመስለኛል። ታቦተ ጽዮንን ሊነኩ የሚፈቀድላቸው ከእስራኤላውያን ከ12ቱ ወገን አንዱ የሆነው የሌዊ ዘሮች ብቻ ናቸው። ብዙ ጊዜም ታቦቱን የሚያጓጉዙት በሰረገላ ወይም በ4 መሎጊያ ተሸክመው ነው (2ኛሳሙ.6፣3፤ዘፀ.10፣8፤ ኢሳ.3፣4፤1ኛ ዜና.15፣14-15)። በዚህ ተረክ ውስጥ እነዚህን ታቦታት ከእስራኤል ይዘው የመጡት ህቡአን ናቸው። እነዚህ ለማንኛውም ሰው የማይታዩ የሚባሉት ቅዱሳን ልክ እንደሌዋውያን ዘሮች ታቦታትን ለመንካት ፈቃድ ያላቸው እንደሆኑ ለማሳየት የፈለጉ ይመስላል። ታቦተ ጽዮን ብዙ ጊዜ በሰረገላ እንደሚጓጓዝ ሁሉ እነዚህ ታቦታትም ቶራ በሚል ስም በምትጠራው እንስሳ ተጭነው እንዲመጡ ሲደረግ አሁንም የታቦታቱን ቅድስና ለማመልከት የታሰበ ይመስላል። ጭነቱም አስርቱ ቃላት በላዩ ላይ የተጻፈበት መሆኑና ጭነቱ የተጫነበት እንስሳ ስም ፍች አስርቱ ቃላት ማለት በመሆኑ የጭነቱንና የተጫኙን ቅድስና አጣምሮ የሚጠቁም ይመስላል።

የሆነ ሆኖ ለዚህ ተረክ ይህች እንስሳ መመረጧ ፋይዳው ምንድን ነው የሚል ሀሳብ ማንሳት ይቻላል። ምናልባት ከተለመዱት የእንስሳት ዝርያዎች ይልቅ ይህች ቶራ በሚል ስም የተጠራችው እንስሳ የተመረጠችበት ምክንያት ጭነቱን፣ አምጭዎችን፣ አስመጭውንና ክንውኑን ፍጹም ቅድስና ለማላበስ ይመስለኛል። ይህም ከሆነ ታዲያ በተለይ ለአስመጪው ፍጹም መታዘዝን የሚያስርፅ፣ ለገዳሙም ትልቅ ከበሬታ የሚፈጥርና አሁን በገዳሙ ለሚገኙት ገዳማውያንም መንፈሳዊ ጉልበትን የሚያላብስ ይሆናል።

ይሁን እንጂ የታቦታቱ ከኢየሩሳሌም መምጣት አሁንም ሌላ ጥርጣሬ የሚፈጥር ሁኔታ አለው። በኢየሩሳሌም በተለይ በህገ ኦሪት ጊዜ ከሙሴ ውጭ (ይህም ለአንድ ጊዜ ብቻ የተደረገ ነው) (ዘፀ:25:10) ታቦት የቀረፀም ሆነ ያስቀረፀ ሰው መኖሩን አላውቅም። በአዲስ ኪዳንም ቢሆን በኢየሩሳሌም ታቦት አገልግሎት እየሰጠ አይገኝም። ታዲያ በተረኩ የታቦታቱን ምንጭ ኢየሩሳሌም ማድረግ ለምን አስፈለገ ሊባል ይችላል። ምናልባት ተረኩን ለታቦተ ጽዮን ምንጭ

ከሆነችው ከኢየሩሳሌም ጋር ማዛመዱ የታቦቱን ኃያልነት ይበልጥ አጉልቶ ለማሳየት ወይም የእስጢፋኖስን ታቦት ከታቦተ ጽዮን ጋር በአቻነት እንዲታይ ለማድረግ ይሆናል። ወይም ደግሞ በጣና ሐይቅ አካባቢ የሚኖሩትን ፈላሻዎች ከታቦተ ጽዮን ጋር የተለየ ትስስር አላቸው ተብሎ ስለሚታሰብና በጊዜው የክርስትናን መስፋፋት ይቃወሙ ስለነበር እነዚህን ፈላሻዎች ወደክርስትና እምነት እንዲሳቡ ለማድረግ ሊሆንም ይችላል።

ይህም ከሆነ ደግሞ ከታቦታት ሁሉ በተለይም በሀገር ውስጥ ከሚቀረፁት ታቦታት ይበልጥ ቅድስናና ክብር እንዳለው አድርጎ ያሳያል ማለት ነው። ይህም እውነት ከሆነ ገዳሙን በገዳምነቱ እንዲሁም ገዳማውያንን በገዳሙ ውስጥ ያላቸውን ህይወት ያፀናላቸዋል ማለት ይቻላል። በአጠቃላይ የታቦተ እስጢፋኖስ በህቡአን አማካይነት ከኢየሩሳሌም መምጣት የታቦቱን ፍጹም ቅድስና ሁሉም ወገን የተቀበለው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህም በመሆኑ ገዳሙ በዚህ ታቦት ስም መሰየሙ የሚያግባባና ተቀባይነት ያለው ይመስላል። የዚህም ጥቅል ውጤት የገዳሙን ቅድስና፣ ታላቅነትና ታሪካዊነት የሚያፀና ሲሆን ለገዳማዊው ህይወትም ፅኑ መሠረት ሆኖ ያገለግላል ማለት ይቻላል።

### 4.2.2 ለመስራቹ ገዳሙን በርስትነት መቀበል

ሌላው ለዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም መመሥረት እንደምክንያት የሚጠቀሰው ሕቡአን/ለማንኛውም ሰው የማይታዩ ቅዱሳን ሰዎች/ የተባሉት መነኮሳት (የቀደሙት ይሁኑ ሌሎች አይታወቅም) አባ ሂሩተ አምላክን አግኝተው ካነጋገሯቸው በኋላ እግዚአብሔር ዳጋ የተሰኘውን ደሴት የዘላለም ርስት አድርጎ የሰጣቸው መሆኑን ስለነገሯቸውና ገዳሙን እንዲመሰርቱም መመሪያ ስለሰጧቸው ነው ይባላል(አባ ወልደ ሃና፣ 2002፣ ካ.ቁ. 1. A)።

አባ ሂሩተ አምላክ ገና ወደዚህ ደሴት ከመምጣታቸው በፊት በሕቡአኑ ሰዎች አማካይነት ገዳሙ የሁልጊዜም ርስታቸው እንደሆነ ተነገሯቸዋል ተብሏል። በተጨማሪም ገዳሙን እንዲመሰርቱም መመሪያ እንደተሰጣቸው ተገልጿል። ከዚህ ሌላም መስራቹ በዳጋ ደሴት የእስጢፋኖስን ገዳም ሊመሰርቱ የቻሉት ለመነኮሳቱ የአባትነት ፀጋ የተሰጣቸው መሆኑ ቃል ስለተገባላቸው እንደሆነም ነው የሚታመነው። ህቡአን የሚባሉት ለተቀደሱ ሰዎች ካልሆነ በቀር ለሌሎች የማይታዩ ቢሆንም አባ ሂሩተ አምላክ የበቁ መነኩሴ በመሆናቸው ይመስላል ተገልፀው ያነጋገሯቸው ነበር። እንዲያውም አባ ሂሩተ አምላክ ወደዚህ ደሴት ሲመጡ በገዳሙ አካባቢ ሦስት ህቡአን አግኝተው ወደዚህ ገዳም ይዘዋቸው እንደመጡና እነዚህም ህቡአን ከአባ

ሂሩተ አምላክ በኋላ ገዳሙን በአበምኔትነት አገልግለው እንዳለፉ ይነገራል በማለት አባ ተክለ ዮሐንስ ነግረውኛል። ይህ ጉዳይ በምንናው ህይወት ትልቅ ሊባል የሚችል የቅድስና ደረጃ ነው። የተሰጣቸው የአባትነት ፀጋም ከእሳቸው አልፎ የገዳሙን የመንፈስ አባትነት በአካባቢው የክርስቲያን ወገን ሁሉ የሚያጸና ይመስላል። በህቡእን የተነገራቸው የገዳሙ ርስትነትና የአባትነት ፀጋ አሁን ላለውም ሆነ ወደፊት ለሚመጣው ገዳም የገዳማዊ ህይወቱን የሚያፀና ይሆናል ማለት ይቻላል። በርግጥ እዚህ ላይ ገዳሙ የዘላለም ርስታቸው ስለመሆኑና ለመነኮሳቱም የሁልጊዜ አባት ስለመሆናቸው እንዴት ባለ መለኪያ መረጋገጥ ይችላል የሚል ጥያቄ ማንሳት ይቻላል?

ምንም እንኳን የተለያየ ቡድን የተለያየ ማገናዘቢያ ሊኖረው ቢችልም መሥራቹ የመሰረቱት ገዳም ከሰባት መቶ ዓመታት በላይ በገዳምነት ፀንቶ መቆየቱ ትልቅ መለኪያ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ሌላም ይሄ ገዳም እስከ አሁንም ድረስ ብዙ መናንያን የሚገኙበትና ምናልባትም ተፈላጊ ገዳም መሆኑ፣ እንዲሁም በመሥራቹ የተቀመጡት ስርዓቶች አሁንም ድረስ የተከበሩ መሆናቸው ሌላው መለኪያ አይሆንም ማለት አይቻልም። መሥራቹ ባቋቋሙት ገዳም ውስጥ አገልግሎታቸውን ፈጽመው ከአረፉ ከብዙ ዘመን በኋላ በስማቸው ቤተክርስቲያን ታንፆላቸውና ታቦት ተቀርፆላቸው ሲታይ በርግጥም በሕቡእን ቀደም ሲል የዘላለም ርስታቸው ተደርጎ እንደተሰጣቸው የተነገራቸው ቃል ኪዳን አልተፈፀመም ለማለትም ይከብዳል። ከዚህ አኳያ ገዳማውያን ለአባ ሂሩተ አምላክ የተገባላቸው ቃል ኪዳን መፈጸሙን ማመናቸው የእሳቸውን መንገድ በመከተል ነገ ሊደርሱበት የሚችሉትን መንፈሳዊ ደረጃ/ብጽእት/ የሚያመላክታቸው በመሆኑ በገዳማዊ ህይወታቸው ላይ ጽኑ መሰረት ይተክልላቸዋል ብሎ መገመት ይቻላል።

## 4.3 የዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም ቅድስና

የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም በገዳሙ በሚኖሩ መናንያን ዘንድ ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ ይታመናል። ይህም ቅድስና ፈጣሪ በቅዱሳኑ ላይ አድሮ በሚገልጸው ሀይልና በአካባቢው ላይ በሚፈጥረው አንዳንድ ተዓምራት አማካይነት እንደሚገለጽ ያምናሉ። እስቲ ደግሞ ገዳማውያኑ የገዳሙን ቅድስና አስመልክተው የሚተርኳቸውን ተረኮች፣ በእነዚህ ተረኮች ላይ ያላቸውን እምነትና ተረኮቹ ለገዳማውያኑ ያላቸው ፋይዳ ምን እንደሚመስል እንመልከት።

### 4.3.1 የገነት ነፋስ የሚነፍስበት ገዳም መሆኑ

የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በርካታ መናንያንን አስተናግዷል። ይህ ገዳም በብዙ መነኮሳትና ምእመናን ዘንድ ቅዱስ ቦታ ተደርጎ ስለሚቆጠር እንደ ማስረጃ የሚጠቀሱ በርካታ ተረኮች አሉ። ከእነዚህ ተረኮች ውስጥ አንዱ በገዳሙ ውስጥ ያነጋገርኳቸው አባ ወልደ ገብርኤል የገለጹልኝ ነው። አባ ወልደ ገብርኤል ስለዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አሰያየም ሲናገሩ ዳጋ ማለት ገበያ፣ ደጋ፣ ገነት ማለት እንደሆነ የቀደሙት አባቶች ሲናገሩ ሰምቻለሁ ይላሉ። ገበያ ሲባልም መንፈሳዊም ሆነ ስጋዊ ግብይት (ለስጋ የሚሆን ምግብና ለመንፈስ የሚተርፍ በረከት) እንደልብ ይገኝበታል ለማለት መሆኑን፤ ደጋ ናት ሲባልም ደሴቷ በትልልቅ ዛፎች የተከበበች በመሆኗ ቀዝቃዛ ናት ለማለት መሆኑን፤ እንዲሁም ገነት ናት ሲሉ ሰላማዊና ቅዱስ ቦታ ናት ለማለት መሆኑን ጨምረው ገልጸውልኛል። እንዲሁም ዳጋ እስጢፋኖስ በተሰኘው መጽሔት ውስጥ የአንድነት ገዳሙ በተፈጥሮና በፀጋ እግዚአብሔር የከበረ፣ በመዓዛ ገነት የተዋበ፣ ውስጣዊ ሕይወትን የሚያድስ፣ እንደ ደብረሲና እንደ ደብረታቦር የተመረጠ በየሳምንቱ እሁድ ከሰዓት በኋላ የገነት ነፋስ የሚነስፍበት ቦታ ነው (ዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም፣ /የታተመበት ዓ.ም አልተገለፀም/፣8) የሚል ሀሳብ ሰፍሮ እናገኛለን።

አባ ወልደሰንበት እሁድ ከሰዓት በኋላ ይነፍሳል ስለሚባለው የገነት ነፋስ ጉዳይ ለጠየቅኳቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥተውኛል። የገነት ነፋስ ይነፍስበታል ሲባል መዓዛ ገነት፣ መዓዛ ቅዱሳን ይነፍስበታል ማለት ነው። "ገነት" ቤተክርስቲያን ናት። በቤተክርስቲያን የገነት ነፋስ የሚነፍስ ከሆነ ወይም መዓዛ ገነት ካለ ደግሞ በዳጋ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ቤተክርስቲያን የገነት ነፋስ ይነፍሳል ለማለት ነው። በርግጥ ገነትን ውሃ ከሚያጠጡ አራት ወንዞች መካከል አንዱ ግዮን ነው። ግዮን/አባይ/ ደግሞ በዚህ ገዳም አካባቢ ስለሚገኝ ወይም ደግሞ ግዮን ጣናን አቋርጦ ስለሚያልፍና ይህም ደሴት በዚህ ሃይቅ ተከቦ የሚገኝ በመሆኑ በተዘዋዋሪ ደሴቱ ከግዮን ወንዝ ስለሚጠጣ ይህን አመሳጥረው ደሴቱ የገነት ነፋስ ይነፍስበታል በማለት እየተናገሩ ይሆናል። በዚህ ደረጃ ደሴቱን ከእውነተኛዋ ገነት ጋር እያመሳሰሉ ከሆነ ግን ስህተት ነው። ምክንያቱም ገነት በምድር አይደለችም (አባ ወልደ ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.6) ይላሉ።

ይሁን እንጂ ዕለት መርጦና ሰዓት ቆርጦ እሁድ ከሰዓት በኋላ የገነት ንፋስ ይነፍሳል የሚለው አገላለጽ በማንኛውም አብያተ ክርስቲያን ሥርክ ከሚነፍስ ነፋስ የተለየ ስለሚመስልና ዘወትራዊ ከሆነው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ልዩ እንደሆነ የሚገልጽ በመሆኑ እንደተባለው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ የሚያካትት አይመስልም። ስለዚህም በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት የሚነፍሰው ነፋስ አንድም በቀጥታ ከገነት የሚነፍስ ነፋስ ነው ወይም ደግሞ ገነት ውስጥ የሚነፍሰው ነፋስ አምሳያ ነው ለማለት መሆን አለበት። ከዚህም በተለየ ሁኔታ አባ ወልደ ገብርኤል ዳጋ እስጢፋኖስ ሰላማዊና ቅዱስ የአትክልት ቦታ በመሆኗ አባቶች ገነት ብለው እንደሚጠሯት የነገሩኝ በመሆኑ ዳጋ እስጢፋኖስን እንደገነት፣ ነፋሷን ደግሞ እንደገነት ነፋስ የመቁጠር አዝማሚያ እንዳለ መረዳት ይቻላል። ምንም እንኳን በቦታው በተገኘሁበት የሰንበት ዕለት ገዳማውያኑ ቀኑን ምክንያት በማድረግ ከሌሎች ቀናት የተለየ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ባልመለከትም ለገዳሙ ንጽህና ያላቸው ጥንቃቄና እንክብካቤ ገዳሙን እንደገነት ከማሰብ የመነጨ ሊሆን ይችላል። ምንም እንኳን የገነት መአዛን አሽትቶ ለመለየት መንፈሳዊ ብቃት ያስፈልግ እንደሆነ ባላውቅም በቆይታየ እሁድ ከሰዓት ልዩ የገነት ነፋስ መንፈሱን ማረጋገጥ አልቻልኩም። ነገር ግን ይኸው እሁድ ከሰዓት በኋላ የገነት ነፋስ ይነፍሳል የሚለው ልማድ አሁንም ድረስ መነገሩ ግን ገዳሙ እጅግ የከበረና መንፈሳዊ ጸጋ ያለው ነው የሚለውን እምነት የሚያሰርፅ ነው። ይህም ለገዳሙ ማህበረሰብ አባላት ትልቅ የመንፈስ እረፍት እንደሚሰጣቸውና ለገዳማዊ ህይወታቸውም ትልቅ ፅናት እንደሚፈጥርላቸው መገመት ይቻላል።

ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም እንደ ደብረ ሲና ነው ሲባል የሲና ተራራ ሙሴና እግዚአብሔር የተገናኙበት ተራራ እንደሆነ (ዘፀ.19-24) ስለሚታመን ይህም ገዳም ገዳማውያኑና እግዚአብሔር የሚገናኙበት፣ የሚነጋገሩበት፣ ቃል ኪዳን የሚገባቡበት፣ የተቀደሰ ተራራ ነው ለማለት ይመስላል። በዳጋ ተራራ ላይ እግዚአብሔር መንፈሳዊ መመሪያውን ሲገልጽ ገዳማውያን እንደሙሴ ሆነው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝና መመሪያ የሚቀበሉበት ነው ማለት ነው። ይህም የዳጋ እስጢፋኖስን ገዳም እንደ ደብረ ሲና የተቀደሰ አድርጎ የማሰብና ገዳማውያኑም እንደሙሴ በእግዚአብሔር የተመረጡ እንደሆኑ አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያ ያለው ይመስለኛል። ደብረታቦር የተሰኘውም ተራራ የእግዚአብሔር መለኮት የተገለጸበት እንደሆነ ይታመናል። የዳጋ እስጢፋኖስን ገዳም ከዚህ ተራራ ጋር ማመሳሰል ገዳሙ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይል የሚገለጽበት ስፍራ ነው የሚል እምነት ያለ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ይህ እምነት ገዳሙን ከሌሎች ገዳማት ወይም ስፍራዎች የተለየና

የተቀደሰ መሆኑን የሚያሰርጽ በመሆኑ ገዳማውያን እናገኛለን ብለው ተስፋ የሚያደርጉት የቅድስና ደረጃ በዚህ ገዳም እንደሚሳካላቸው የሚያሳምን ይመስለኛል።

## 4.3.2 ተፈጥሯዊ አቀማመጡ ትዕምርታዊነት ያለው መሆኑ

የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ደሴት አቀማመጥ ሦስት የተለያዩ ትእምርቶችን እንደሚያመለክት ገልፀውልኛል። የደሴቱን ከፍተኛውን ቦታ ብቻ ሲመለከቱት የመሶበ ወርቅ ቅርፅ ይኖረዋል። እንዲሁም ይሄ ደሴት የትምእርተ መስቀል ቅርጽ ያለው ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ ከኖህ መርከብ ጋር የተመሳሰለ ቅርጽ እንዳለው ይናገራሉ። እንዲሁም ገዳሙ በተደጋጋሚ ጊዜ በመብረቅ በመቃጠሉ ይህ ቃጠሎ እንዲቆም ገዳማዊያን ሰባኤ ይዘው ፈጣሪያቸውን በጠየቁት መሰረት ቤተክርስቲያኑ በኖህ ቅርጽ እንዲሰራ አምላክ ባዘዘው መሰረት ይህ ቤተክርስቲያን የኖህ መርከብ ቅርጽ ያለው ሆኖ እንዲሰራ ተደርጓል ይላሉ። እነዚህ ትዕምርቶች ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ጎላ ጎላ ብለው የሚጠቀሱ ጉዳዮችን የሚወክሉ ናቸው። ለመሆኑ መስቀል፣ መሶበ ወርቅ፣ የኖህ መርከብ የተሰኙት ትዕምርቶች ተምሳሌታዊ ፍቻቸው ከገዳማዊ ህይወት ጋር ሲዛመድ ምን መልክ ይኖረዋል?

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትምህርት መሠረት የኖህ መርከብ የቅድስት ማርያም ምሳሌ ነው፤ ወይም ማርያም በኖህ መርከብ ትመስላለች በሚል ይነገራል። የኖህ መርከብ በውስጧ ያሉትን ሕዝብና የአራዊት ዝርያዎችን ከጥፋት ውሃ እንደአዳነች ሁሉ ማርያምም በውስጧ ባደረው ጌታ አማካይነት የሰው ዘርን ከሲኦል ፍዳ የማዳኗ ምሳሌ ነው። ይህም የማደሪያውን ቅድስና እና የአዳሪውን የልዕለ ተፈጥሮ ሐይል ባለቤት መሆንን ያሳያል። በመርከቧ ኖህና ፍጥረቱ እንደዳኑ ሁሉ በማርያምም ምክንያት የአዳም ዘሮች ሁሉ ከሲኦል መከራ የመዳናቸው ምሳሌ ነው። ይህም ደሴት /ገዳም/ ከኖህ መርከብ ጋር ሲመሳሰል ተምሳሌታዊ ፍቺው የኖህ መርከብ በውስጧ ያሉትን ከጥፋት ውሃ እንደአዳነች ሁሉ ይህም ገዳም ከዓለማዊ ግብር እና ከሥጋዊ ፈተና ጠብቆ ወደዘላለማዊ ሕይወት የሚያስገባ መንፈሳዊ መርከብ ነው ማለት ነው።

ሌላው ተምሳሌት ደግሞ መስቀል ነው። መስቀል የኢየሱስ ክቡር ደምና ቅዱስ ሥጋ ያረፈበት በመሆኑ ለሰው ልጆች ድኅነት መሠረት ነው። ከዚህ ሌላም ኢየሱስ በመስቀል ብዙ መከራ ስለተቀበለበት መስቀል የመከራ ተምሳሌት ሆኖ ይታያል። ይህም ገዳም የመስቀል ቅርጽ

አለው ሲባል አንድም መልክዐ ምድራዊ አቀማመጡ የክርስትና ተምሳሌትን የያዘ ነው ማለት ሲሆን አንድም ደግሞ መስቀል መከራ በመሆኑ ብዙ መከራ ተቀብለው ፀጋ የሚያገኙበት ቦታ ነው ማለት ነው። ስለዚህ መስቀል የሥጋ ፈተና፣ የመከራና የመታመቅ ምሳሌ ሆኖ ፍጻሜው ግን የመንፈስ ድኅነት እንደሆነ ሁሉ ይህም ገዳም መስቀል ነው ሲባል በሥጋ የመከራ ደሴት ሆኖ በመንፈስ ግን የዘላለማዊ ሕይወት ማግኛ መንገድ ነው ማለት ነው። ከዚህ አንፃር ይህ ገዳም በኖህ ኦሪትን፣ በመስቀል ደግሞ ክርስትናን በመቀበል ኦሪትንና ሐዲስ ኪዳንን አስተባብሮ ለአምልኮታዊ ስርዓቱ እንደሚጠቀምበት ያሳያል።

መሶበ ወርቅ የተባለው ደግሞ ቅዱስ ኤፍሬም "ሕቡዕ የሆነ መና ያለብሽ መሶበ ወርቅ አንቺ ነሽ" /አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንፁህ እንተ ውስቴታ መና ሕቡዕ/ ያላት በመሆኑ መሶበ ወርቅ የማርያም ምሳሌ ነው። ብዙ ጊዜ በመሶበ ወርቅ የሚቀመጠው ሕብስት ነው። ሕብስት ደግሞ ለማንኛውም የሰው ልጅ ሁሉ የሚሆን ምግብ ነው። ህብስት የክርስቶስ ሥጋ ምሳሌ ሆኖም የቁርባር ስርዓት ይፈጸምበታል። በመሆኑም ይሄ ገዳም ሥጋና ደም ዘወትር የሚፈተትበት /ቁርባን የሚፈጸምበት/፣ ቃለ እግዚአብሔር ዘወትር የሚሰማበት፣ ጌታ የሚመሰገንበትና ቅዱሳን የሚከብሩበት ቦታ በመሆኑ ከመሶበ ወርቅ ጋር እንደተነፃፀረ ነግረውኛል።

መሶበ ወርቅ በማርያም የሚመሰል ከሆነ መሶበ ወርቁ /በማርያም/ ያደረው የሰው ልጅ ሁሉ ቢመገበው ሊድን የሚችልበት ሕብስት ኢየሱስ ነው ማለት ነው። መሶበ ወርቅና ማርያም የሕብስቱና የኢየሱስ ማደሪያ በመሆናቸው ተመሳሳይ ሆኑ ማለት ነው። ይህም ገዳም መሶበ ወርቅ ነው ሲባል ማደሪያ ነው ማለት ነው። በመሶበ ወርቁና በማርያም አዳሪው ሕብስቱና ሕቡዕ መና የተባለው ኢየሱስ ነው ብለናል። ታዲያ በመሶበ ወርቅ የተመሰለው ይሄ ገዳም ማደሪያ ከሆነ አዳሪው ማን ነው የሚል ጥያቄ ሲነሳ ከሕብስቱ ጋር መነፃፀር የሚችለው መናኙ ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህም ይመስላል መነኮሳት ምድራውያን መላዕክት ሰማያውያን ሰዎች ናቸው(ፍትሐ ነገስት፣1990፣103) የሚባሉት። ይህ ገለፃ ገዳማውያንን ፍጹም ንፁህና ፃድቅ አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያ አለው። ኢየሱስ በመስቀል መከራን ሲቀበል የሰው ልጆችን ለማዳን ነው። አንድ መናኝ በሥጋ መከራን ሲቀበል ግን የራሱን ነብስ የዘላለም ሕይወት እንድትወርስ ለማድረግ ነው። ገዳማውያን በገዳም ውስጥ ሕይወታቸውን በማሳላፋቸው ብቻ የሰውን ልጅ ማዳን ይችላሉ ማለት ባይቻልም ስለዓለም መዳን የሚያምሩና የሚጸልዩ በመሆናቸው፣ እንዲሁም ከገዳሙ እየወጡ የሰውን ልጅ በማስተማር ጌታ ይወደዋል ወደሚባል ሕይወት መመለስ ከቻሉ በርግጥም የሕብስቱን /የኢየሱስን/ ሚና መተካት ባይችሉም

አስተዋጽኦቸው ሚዛን የሚደፋ ነው። ስለዚህ ይህ ገዳም የመሶበ ወርቅ ቅርጽ አለው ማለት የተመረጡና የተቀደሱ ገዳማውያን የሚኖሩበት ቅዱስ ገዳም እንደሆነ ይታመናል ማለት ነው።

ከዚህ በተለየ ሁኔታም በመሶበ ወርቁ ውስጥ እንዳለው ሕቡዕ ሕብስት ሁሉ መሶበ ወርቅ በተባለው በዚህ ገዳም ውስጥ ሕቡዕ የሆኑ ቅዱሳን ይኖሩበታል ተብሎ ይታመናል ማለት ይቻላል። አባ ተክልዮሐንስ በዚህ ገዳም ውስጥ ያሉ ህቡአን ወደፊት ምን እንደሚገጥማቸው የነገሯቸው ገዳማውያን እንደነበሩ ከገለጹልኝ በኋላ በእሳቸውም ዘመን አባ በኩረ የሚባሉ አባት በ1986 ዓ.ም በፋሲካ ፆም ውስጥ እንደተሰወሩ/ህቡዕ እንደሆኑ/ አውቃለሁ ብለውኛል። በርግጥ ብዙ ገዳማውያን እኚህን አባት እብድ ናቸው ሲሉ የነበሩ ቢሆንም እንደኔ እምነት ግን የበቁ አባት መሆናቸውን አምናለሁ ይላሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ አባ ገብረሕይወት በበኩላቸው የሚከተለውን ተረክ አጫውተውኛል።

አንድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በክረምት ቤተሰቦቹ ወደሚኖሩበት ወደዚህ ገዳም አካባቢ መጥቶ የእረፍት ጊዜውን ሲያሳልፍ አሳ በማጥመድ ቤተሰቦቹን ይረዳ ነበር። አንድ ቀን ይሄ ገዳም በሚገኝበት አካባቢ አሳ እያጠመደ ሳለ አንድ ረጅምና ነጭ ፅሂም ያላቸው መነኩሴ በቅል ውኃ ሲቀዱ በድንገት ይመለከታቸውና ይደነግጣል። ወዲያው ደግሞ ይሰወሩበታል። በኋላ ሲረጋጋ ውኃ የሚቀዱበትን ቅል ትተዋት እንደተሰወሩ ይመለከትና ቅሏን ወደቤቱ ይዟት ይሄዳል። ከዚህ ቀን ጀምሮ እኚህ ሰው ሌሊት በሕልሙ ቅሌን አምጣ እያሉ ይጨቀጭቁት ጀመር። የልጁ ቤተሰቦችም ልጃቸው በየቀኑ እየቃዠ ማደሩን ተመልክተው ምክንያቱን ሲጠይቁት አሳ ሲያጠምድ አንድ መነኩሴ አይቶ ዘወር ሲል ቅላቸውን ትተው እንደተሰወሩ እሱም ትተውት የሄዱትን ቅል ይዞ መምጣቱንና አሁን ግን በየሌሊቱ እየመጡ ቅሌን አምጣ እያሉ እንደሚያስፈራሩት ይነግራቸዋል። በኋላም ቤተሰቦቹ ቅሏን ካገኘበት ቦታ እንዲመልስ ይነግሩታል። እሱም ቅሏን እንደተባለው ባገኘው ቦታ ላይ ከመለሰ በኋላ በሰላም ማደር ጀመረ።

በዚህ ገዳም ውስጥ ሕቡአን የሚባሉ ቅዱሳን ይኖሩበታል ተብሎ እንደሚታመን ይህ ተረክ በግልጽ ያሳያል። እነዚህ ሕቡአን አንዳንድ ጊዜ ብቻ ለሰው የሚገለፁ ቢሆንም በአብዛኛው ግን ከሰው እይታ የተሰወሩ ወይም መሰወር የሚችሉ ናቸው። በተረኩ ላይ እንደምንረዳው እነዚህ ሕቡአን ከሥጋ ለባሽነት አልፈው ረቂቅነት ባሕርይ ይዘው በሕልም መገለጽ የሚችሉ ናቸው። በሌላ ሁኔታ ደግሞ ለሥጋ የሚያስፈልገውን ውኃ ያውም የሰው ልጅ በሚጠቀምበት ቁሳቁስ

የሚጠቀሙ ሥጋውያን ይሆናሉ። እነዚህ ሕቡአን ብዙ ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጠንካራ ለሆኑና መንፈሳዊ ፀጋ ተላብሰዋል ለሚባሉ ገዳማውያን እንደሚገለፁላቸው አባ ኃይለ ራጉኤል ነግረውኛል። ያም ቢሆን ገዳሙ መሶበ ወርቅ ነው ሲባል እንደመሶበ ወርቅ ማደሪያ በሆነው በዚህ ገዳም ውስጥ ሕቡአን እንደ ሕቡዕ ሕብስት አዳሪ ሆነው እንደሚኖሩ የሚያሳይ ይመስላል። የህቡአን በዚህ ገዳም መገኘትም ገዳሙ ቅድስና አለው የሚል እምነትን ያሰርጻል። ገዳሙ ቅድስና አለው የሚለው እምነት ደግሞ ገዳሙ በገዳምነት፣ ገዳማውያኑም በገዳማዊ ህይወታቸው ጸንተው እንዲኖሩ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ለማለት ያስችላል።

#### 4.3.3 የተሰወረ የመድኃኔዓለም ኃይል ስለመኖሩ

በዚህ ገዳም ውስጥ "ስውሩ መድኃኔዓለም" በሚል ስም የሚጠራ ቦታ አለ። ቦታው ይህንን ስያሜ ያገኘው ያስቀመጠው /ያመጣው/ ሰው ሳይታወቅ አንድ የኢየሱስን ስቅለት የሚያሳይ ስዕል በመገኘቱ ነው። የተገኘበት ጊዜ በውል ባይታወቅም በኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ይታመናል። ይህም ምስል ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ተዓምራት እንደፈፀመ ይነገራል። በተለይም በአካባቢው በክረምት ወቅት ዝናብ ሲጠፋ/ሲቋረጥ/ ከገዳሙ ውጭ ያለው ማህበረሰብ ይህንን ስዕል በመውሰድ ምህላ/ጸሎት/ ይይዝበታል። ብዙ ጊዜም ዝናብ እንዲዘንብ አድርጓል የሚል አስተያየት ይሰነዘራል። በዚህም ምክንያት ስዕሉ «አፍሮ አይገባ» ይባላል። ይህ ስዕል ከገዳሙ ውጭ አድሮ አያውቅም(አባ ተክለዮሐንስ፣2003፣ካ.ቁ.2A)።

በርግጥ በገዳማት እና መናንያን ይኖሩበታል ተብሎ በሚገመት በረሐ ውስጥ የሰው አፅም ሲገኝ በአውሬ የተበላ ወይም በእግዚአብሔር ሞት ያለፈ መናኝ እንደሆነና ከአፅሙ አካባቢ ጭራ፣ መቋሚያና የተለያዩ ሐይማኖታዊ ስዕሎች ወድቀው ሲገኙ የዚህ መናኝ ንብረቶች እንደሆኑ ይገመታል። በዚህም ጊዜ እነዚህ የመማጸኛ ስዕሎችና መቋሚያዎች /የመናኙ ንብረቶች/ ለበረከት እየተባለ ለአካባቢው ቤተክርስቲያን እንደሚሰጡ አንዳንድ መነኮሳት ነግረውኛል። ከዚህ አንፃር በዚህ ገዳም የተገኘው ስዕል በምንና ህይወቱ ካለፈ አንድ አባት የቀረ ንብረት ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል። ምክንያቱም ስዕሉ ከተለመዱት ስዕሎች የተለየ ሁኔታ የማይታይበት በመሆኑ ነው።

ይሁን እንጂ የዚህ ስዕል መገኘት በገዳማውያኑም ሆነ በአካባቢው ምዕመናን ዘንድ ትልቅ መንፈሳዊ ዋጋ እንዳለው ተደርጎ ይታመናል። ስዕሉ የተገኘበት ቦታም ስውሩ መድኃኔዓለም በሚል ሲሰየም የተሰወረና አንድ ቀን ግን ሊታይ (ሊገለፅ) የሚችል ታቦተ መድኃኔዓለም

ወይም የመድኃኔዓለም ቤተመቅደስ አለ ብሎ የማመን አዝማሚያ አለው ማለት ነው። ያለዚያ ደግሞ በዚህ ቦታ የተሰወረው የመድኃኔዓለም ሃይል አንድ ቀን ይገለጻል የሚል እምነት ያለ መሆኑን ነው። ዞሮ ዞሮ ገዳማውያን በዚህ ቦታ(በስውሩ መድኃኔዓለም) ብዙ መንፈሳዊ በረከት ይገኝበታል የሚል እምነት ያላቸው በመሆኑ ለገዳማዊ ህይወታቸው ትልቅ ዋጋ አለው ማለት ይቻላል።

### 4.3.4 ጠላትን የመደምሰሻ ሀይል የሚገለጽበት መሆኑ

በአንድ ወቅት የገዳሙን ንብረት ለመዝረፍ እና መነኮሳቱን ለመጨፍጨፍ አንድ መቶ ሃያ አምስት ታንኳዎችን በማሰባሰብ በእያንዳንዱ ታንኳ ላይ ከአስር ሰው በላይ በመሆን ተጭነው የመጡትን ወንበዴዎችና ነፍሰ ገዳዮች ፈርኦንና ሠራዊቱ በባህረ ኤርትራ እንደሰጠሙ ወደገዳሙ ለመድረስ አንድ ኪሎ ሜትር ሲቀራቸው ሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ኃይል ግርማውን በገለፀ ጊዜ ታላቅ የባህር ሞገድ ተነስቶ ሁሉንም እንዳሰጠማቸው በገዳሙ የሚገኘው ገድለ ቅዱስ እስጢፋኖስ ይናገራል(ዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም፣/የታተመበት ዓ.ም አልተገለጸም/7)።

ይህ ተረክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኖህ ዘመን አመጸኞች በጥፋት ውሃ እንዳለቁ (ዘፍ.7፣1-24)፣ እንዲሁም የፈርኦን ሰራዊት በኤርትራ ባህር እንደሰጠሙ (ዘፀ.14፣26-31) ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይነት አለው። ይህ በቅድስና የሚገለጸው ገዳም ጠላቶች ከተነሱበት እንደማይሸነፍና እስከመጨረሻው እንደሚቀጣቸው የሚያመላክት ነው። ይህም ቅድስናው በኃይሉ ብርታት ይገለጻል ማለት ነው። በተለይ በሐይቅ በተከበበች ትንሽ ደሴት ውስጥ ለሚኖር መናኝ፣ ራሱን የሚከላከልበት ምንም መሳሪያ ለሌለው ባህታዊ፣ ሸሽቶ የማምለጫ አማራጭ ቀዳዳ ለሌለው መነኩሴ እንዲህ አይነቱ ተረክ ትልቅ ጉልበት እንደሚሆነው መገመት ይቻላል። ገዳማውያን የሚመጣባቸውን ችግር ሁሉ ሊቋቋምላቸው የሚችል አንዳች ኃይል እንዳለ ማሰብ ትልቅ መረጋጋትን ይፈጥርላቸዋል። ይህ ተረክ በገዳሙ ላይ ያለው መንፈሳዊ ኃይል በገዳማውያኑ ላይ የሚነሳውን ጠላት ማጥፋት የሚችል ጉልበት ያለው መሆኑን የሚያመላክት ስለሆነ ገዳማውያን በገዳሙ መንፈሳዊ ኃይል ላይ እንዲመኩ ያስችላቸዋል ማለት ይቻላል። ይህም ለገዳማዊ ማህበራዊ ህይወታቸው ትልቅ መረጋጋትን ሳይፈጥርላቸው አይቀርም የሚል ግምት አለኝ።

ከገዳሙ ጋር የተያያዙ ገድሎች በአመዛኙ ሐይቁን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው ምናልባትም ጥናት የሚያስፈልገው ቢሆንም የተለያዩ ገድሎች እንደየአካባቢያቸው ሁኔታ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት አሳድሮብኛል። በግብፅና በኢትዮጵያ በረሀማ ቦታዎች የሚገኙ መነኮሳት የሚፈፀምላቸው ተዓምራት ከአናብስትና አስፈሪ ከሆኑ እንስሳት ጋር የተያያዘ ነው። አባ ጳውሊ በሞቱ ጊዜ አንበሳ የቀብራቸውን ጉድጓድ ቆፍሯል(ምክረ ሰላሴ፣200፣360)። አባ አረጋዊ እና አባ ሳሙኤል በአንበሳና በዘንዶ ተጓጉዘዋል። እንዲሁም ማርያም በግብፅና በኢትዮጵያ በርሀ በስደት ላይ እያለች ስድስት የሚሆኑ አናብስት አገልግለዋታል፤ ሰግደውላታልም(ተስፋ፣1988፣154)። የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳምም በሐይቅ የተከበበ ደሴት እንደመሆኑ መጠን የገዳሙ ብዙው ተዓምር ከሐይቁ ጋር የተያያዘ ነው። መስራቹ በድንጋይ ታንኳ ሲጓዙ፣ የገዳሙ ጠላቶች በሐይቁ ሲሰጥሙ፣ ሐይቁ ለቤተክርስቲያን መስሪያ ግንድ ይዞ ሲመጣ እንመለከታለን። ስለዚህ በገዳሙ ደሴት ዙሪያ ያለው ሐይቅ ለገዳማውያኑ ጠላቶቻቸውን የሚያጠፋላቸው ሐይላቸው፤ ሲያሻቸው ደግሞ ትሩፋት የሚያመጣላቸው በረከታቸው በመሆኑ ልዩ ትርጉም አለው።

በመምህር ወልደ ሥላሴ ላይ ጥቃት ለመሰንዘር በታንኳ ሲመጣ የነበረ አንድ የአካባቢው ሰው ሐይቁ ላይ እንዳለ ማዕበል ተነስቶ ታንኳውን ይገለብጥበታል። በኋላም ጠብመንጃው ኃይቁ ውስጥ ገብቶ ይጠፋበታል። በመጨረሻ ሕይወቱን በመከራ አትርፎ ተዓምሩን ሊመሰክር ችሏል። በቅርብ ጊዜ ደግሞ አንድ ሰው የገዳሙን እንጨት ሰርቆ በታንኳ በመጫን ወደ ቤቱ ያስገባል። ወዲያው እስጢፋኖስ በገሀድ በሰው ተመስሎ «ንብረቴን አትመልስም ወይ?» እያለ ቢጠይቀውም እሱ ግን ዝምታን ይመርጣል። በኋላ በዚያው ሌሊት የእሱ፣ የወንድሙና የልጁ ቤት ከነንብረታቸው ይቃጠላል። የሰረቀውም እንጨት አብሮ የተቃጠለ ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰውየው አይን ሊጠፋ ችሏል(አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.3B. እና ካ.ቁ.4A፤ አባ ተክለዮሐንስ፣ካ.ቁ.1B)። እነዚህ ተረኮች ከደሴቱ ስፋት አንፃር ገዳማውያን ንብረቶቻቸውን ለመጠብቅ ስለሚቸገሩ የአካባቢው ህብረተሰብ እጁን በገዳሙ ንብረት ላይ እንዳያነሳ የማስጠንቀቂያ ደወል ሳይሆኑ አይቀርም የሚል ግምት አለኝ። ከዚህም ባለፈ ግን ታቦተ እስጢፋኖስ ንብረቱን ለመጠበቅ ሲል ሃይል እንደሚጠቀም የሚታመን መሆኑን ያመለክታል። ይህም በስጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ አቅጣጫ ገዳማውያኑ በራስ የመተማመን አቅማቸው እንዲጎለብት ትልቅ ዋጋ ያበረክታል ማለት ይቻላል።

በሌላ ሁኔታም በ1987 ዓ.ም በዚህ ገዳም የሚገኙ ሁለት መነኮሳት ወደአራት ኲንታል የሚሆን የገዳሙን ቡና ለቅመውና አድርቀው ይደብቃሉ። በአጋጣሚ አንድ አባት በጫካ ሲዘዋወሩ የተደበቀውን ቡና ያገኙታል። ይህንንም ለማህበሩ ያሳውቃሉ። በኋላም ማህበረ መነኮሳቱ በተሰበሰቡበት ይህንን ስራ ማን እንደሰራ ቢጠየቅ እኔ ነኝ የሚል ጠፋ። የጉዳዩን ባለቤት በአውጫጭኝ መልክ ለማጣራት ቢሞከርም መፍትሔ ሊገኝ አልቻለም። በኋላ ማህበረ መነኮሳቱ ለሰባት ቀን ቡናው በተገኘበት ቦታ ላይ ጸሎት አደረጉ። በሰባተኛው ቀን ይህንን ስራ የሰሩት መነኮሳት ይታመማሉ። በኋላ እነዚህ መነኮሳት ራሳቸው አምነው ለማህበረ መነኮሳቱ ይናዘዛሉ። ማህበሩም ለሰባት ቀን እንዲታሰሩና ለአንድ ዓመት ደግሞ ከገዳሙ ሳይወጡ ቀኖና እንዲይዙ ይፈረድባቸዋል። በኋላ መነኮሳቱ ዓመት ሳይቆዩ ሁለቱም እንደሞቱ ይነገራል። ይህ ተረክ ገዳሙ ባለው ቅድስና ኃይሉን ሲገልጽ በገዳማውያኑም ሆነ ገዳማዊ ባልሆነው አካል ላይ ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነው። ይህ ተረክ ገዳማውያን ከገዳሙ ስርዓት እንዳያፈነግጡ በአርፈህ ተቀመጥ ማስጠንቀቂያ የመቆጣጠር ተግባሩን ይወጣል የሚል እምነት አለኝ።

### 4.3.5 አጽሞች ለማረፊያነት የሚመርጡት ቦታ መሆን

በአጠቃላይ የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ለሕሙማን ፈውስ፣ አዕምሮአቸው ለተጨነቀ የስነ ልቡና መረጋጋትን የሚፈጥርና መንፈሳዊ እርካታን የሚያላብስ ገዳም እንደሆነ ይነገርለታል። ገዳሙ ለጠላቶቹ ሳይደፈር፣ ወዳጆቹን ደግሞ ሳያሳፍር የኖረ መንፈሳዊ ቦታ ነው። በዚህም ምክንያት ገዳሙ ከአብርሃ ወአጽብሃ ዘመነ መንግስት ጀምሮ በርካታ ነገሥታትና ጳጳሳት ጎብኝተውታል። እነዚህም ነገሥታትና ጳጳሳት ቦታውን ጎብኝተው ሦስት እና አራት ሱባኤ ይይዙበት እንደነበር ይነገራል። በተለይም አፄ ቴዎድሮስ ብዙ ጊዜ ሥጋ ወደሙ ይቀበሉበት እንደነበር የቤተክርስቲያኗ መጻሕፍት እንደሚመሰክሩ ተጠቅሶ እናገኛለን (ዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም፣/የታተመበት ዓ.ም አልተገለጸም/ 8)።

እዚህ ላይ መረዳት የሚቻለው ነገሥታትና ጳጳሳት ከገዳሙ ቅድስና እንዲሁም ለገዳሙ ካላቸው ክብር አንፃር በአጸደ ስጋ እያሉ በቦታው ተገኝተው ከበረከቱ ለመካፈል የሚፈልጉ መሆኑን ነው። ሲሞቱም ለገዳሙ ካላቸው አክብሮት አጽያ በዚህ ገዳም እንዲቀበሩ የሚናዘዙ መነኮሳቱ ይናገራሉ። ። አንዳንዶች ደግሞ በሌላ ቦታ ቢቀበሩም አፍልሰው ወደዚህ ገዳም እንዲያመጧቸው በራዕይ የሚገልጹ አሉ ይላሉ። ዳጋ እስጢፋኖስን ከሌሎቹ ገዳማት የተለየ የሚያደርጉትና ብዙዎች እንዲጎበኙት ምክንያት የሚሆኗቸው በቅርስነት የተቀመጡት አፅሞች ናቸው። ከእነዚህ አፅሞች መካከል የአፄ ዳዊት፣ የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ፣ የአፄ ሱስንዮስና

የአፄ ፋሲል እንደሆኑ የሚነገርላቸው ይገኙበታል። እነዚህ አጽሞች ከአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የኢየሩሳሌም አስጎብኝ ድርጅት ባሰራላቸው የመስታወት ሳጥን ውስጥ ይገኛሉ። ከእነዚህ አጽሞች በተጨማሪ ሌሎች 10 ነገስታትና 9 ጳጳሳት በዚህ ገዳም ውስጥ እንደተቀበሩ ይነገራል።

የገዳሙ እቃ ቤት ኃላፊ አባ ወልደሀና እና የእቃ ቤቱ ጠባቂ እና አስጎብኝ አባ ገብረ ሕይወት እንደነገሩኝ በስም ከሚታወቁት ነገስታት አፅሞች ውጭ ያሉት አብዛኛዎቹ የተቀበሩ በመሆናቸው፣ ያልተቀበሩትም በመፈራረሳቸው፣ ከዚህ ሌላም የትኛው አፅም የማን እንደሆነ መለየት ባለመቻሉ የሌሎች ነገሥታት አፅሞች በመስታወት ሊቀመጡ እንዳልቻሉ ነግረውኛል። በዚህ ገዳም ስለተቀበሩት 10 ነገሥታትና 9 ጳጳሳት ዝርዝር መረጃ ያለ ስለመሆኑ በጠየቅኋቸው መሰረት የጳጳሳቱ ዝርዝር የሌለ ቢሆንም የነገሥታቱን ስም ዝርዝር ከስንክሳሩ ላይ እያነበቡ ነግረውኛል። በዚህም መሠረት በዚህ ገዳም ከተቀበሩት ነገሥታት መካከል አፄ ካሌብ፣ አፄ አይዙር፣ አፄ ይኩኖ አምላክ፣ አፄ ይስሐቅ፣ አፄ ልብነ ድንግል፣ አፄ ገላውዴዎስ፣ አፄ በእደ ማርያም፣ አፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ፣ አፄ ዳዊት(የአዲያም ሰገድ ኢያሱ ልጅ) እና አፄ ተክለሃይማኖት (አንድ እጁ) ይገኙበታል።

በተጨማሪም ተክለፃድቅ መኩሪያ አፄ ዘድንግል የተባሉት ንጉስ ካቶሊክ ሆነዋል በሚል ጦርነት ተከፍቶባቸው ሲሞቱ እንደሌሎች ነገሥታት በክበሬታ ሳይቀበሩ እንደቀረና በኋላም ከእርሳቸውና ከአፄ ያዕቆብ ቀጥለው የተነሱት ጓደኛቸው አፄ ሱስንዮስ ሲነግሱ ሬሳቸውን ከተቀበሩበት ዛፍ ስር አስወጥተው ጣና በዳጋ ደሴት በክበሬታ እንዳስቀበሯቸው(1961፣ 121) ተፅፎ የሚገኝ ቢሆንም የአፄ ዘድንግል ስም ከላይ ከተጠቀሱት 10 ነገሥታት ዝርዝር ውስጥ አይገኝም። ስንክሳሩ የእኚህን ንጉስ ስም ያላካተተው ምናልባት ንጉሱ ካቶሊክ ሆነዋል ተብለው ስለታመነባቸውና በወቅቱ የነበሩት ጳጳስ ለእኚህ ንጉስ እንዳይታዘዙ ስላወገዙ ይሆን የሚል ጥያቄ ያስነሳል። በመሆኑም በተክለፃድቅ መጽሐፍ ወይም ገዳሙ ውስጥ በሚገኘው ስንክሳር የመረጃ ክፍተት እንዳለ ያመለክታል። ሆኖም እስካሁን የተዘረዘሩት ነገሥታትና በቁጥር የተጠቀሱት ጳጳሳት በሙሉ ወይም በከፊል በዚህ ገዳም ውስጥ ተቀብረው ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪም ስማቸው ያልተጠቀሱ ነገስታት (የተሟላ መረጃ ማግኘት ባይቻልም) በዚህ ገዳም ተቀብረው ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ያሳድራል። ያም ሆነ ይህ ግን የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ከጥንት ጀምሮ የነገሥታት አጽም ማረፊያ ሆኖ እንዳገለገለ መረዳት ይቻላል።

አፅሞቹ ወደዚህ ገዳም እንዴት ሊመጡ ቻሉ ለሚለው ጥያቄ ገዳማውያኑ ገዳሙ የተቀደሰ በመሆኑ አንድም ነገስታቱ ከተቀበሩ በኋላ በራዕይ እንዲያፈልሷቸው በመግለጻቸው፤ አንድም ደግሞ ከመሞታቸው በፊት እዚህ ቦታ ለመቀበር በመናዘዛቸው ምክንያት ነው የሚል መልስ ይሰጣሉ። ነገር ግን ለዚህ ጥያቄ ታሪካዊና ሀይማኖታዊ ሰነዶች ምን መልስ አላቸው?

አፄ ዳዊትን ለሞት ያበቃቸው የተቀመጡባት በቅሎ ግንባራቸው ላይ ክፉኛ ስለረገጠቻቸው ነው። አፄ ዳዊት በኢትዮጵያና በግብፅ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት የመጡት የኢየሩሳሌሙ ፓትርያርክ ወደሀገራቸው ሲመለሱ ኢየሱስ የተሰቀለበትን እውነተኛ የመስቀል እንጨት አንድ ቁራጭ እንዲላክለት ለኢየሩሳሌም ገዳም ባለስልጣናት ብዙ የወርቅ ስጦታ አስይዞ ሰዎች እንደላከና መልእክቱ የደረሳቸው የገዳሙ ባለስልጣናትም ንጉሱ ከላከው ብር ግማሹን የኢየሱስ መቃብር በሚገኝበት በጎልጎታ አስቀምጠው በግማሹ ሉቃስ እንደሳላት የሚገለጸውን ምስለ ፍቁር ወልዳ፣ የጌታችን ስዕል አክሊለ ሦክ እንዳደረገ ያለበት (ኵርዓተ ርእሱ የሚባለውን) ገዝተው ከግማደ መስቀሉ ጋር ላኩለት (ተክለፃድቅ፣ 1951፣117)።

እዚህ ላይ መስቀሉ የመጣበት ቦታና የአመጣጥ ምክንያት ሁለት የተለያየ አተራረክ አለው። አንደኛው ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አፄ ዳዊት ራሳቸው ግብጽ ድረስ ዘምተው ይዘውት መጡ (አባ ጎርጎሪዮስ፣ 1991፣ 43) የሚልም ተረክ አለው። ከግማደ መስቀሉ ጋር የመጡት ሁለት ስዕሎች እንደሆኑ ተክለፃድቅ መኩሪያና አባ ጎርጎሪዮስ ይስማማሉ። ሰሎሞን <u>የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት</u> በሚለው መጽሐፉ በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ውስጥ አገኘሁት ያለውን "መስቀል ዘዮም" የተባለውን መጽሐፍ ጠቅሶ ከግማደ መስቀሉ ጋር 27 የሚሆኑ ተጨማሪ ንዋየ ቅድሳት አብረው እንደመጡ አስፍሯል (2001፣ 191)። በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ያነጋገርኳቸው የእቃ ቤቱ ኃላፊ አባ ወ/ሃና ቀድም ሲል ከተጠቀሱት ሁለት ስዕሎችና ከግማደ መስቀሉ በተጨማሪ የሚካኤል ታቦት አብሮ እንደመጣ ገልፀው ይሄ ታቦት የት እንዳለ ባይታወቅም ሉቃስ የሳላት "ምስለ ፍቁር ወልዳ" ግን በዚህ ገዳም ትገኛለች ብለውኛል። በአጠቃላይ እነዚህ መረጃዎች ግማደ መስቀሉ ስለመጣበት ቦታና አብረው ስለመጡት ንዋየ ቅድሳት ተመሳሳይ የሆነ መረጃ እንደሌላቸው መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ የሚጠይቅ ቢሆንም ጉዳዩን ያነሳሁት የንጉሱን ሞት ም ክንያትና ወደዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የመጡበትን ምክንያት ለመፈተሽ በመሆኑ አሁን ወደዚያው እንለፍ።

አፄ ዳዊት በዘመነ መንግሥታቸው ግማደ መስቀሉን ያመጡላቸው መልዕክተኞች በስናር በኩል አልፈው ሲመጡ ሄደው እንደተቀበሏቸውና በዚህም ክብረ በዓል ላይ የተቀመጡባት ባዝራ /ፈረስ/ ረግጣቸው እንደሞቱ ተገልጿል። «በግንባሩ ላይ የስብራቱ ምልክት እስከዚህ ጊዜ ድረስ በዳጋ ደሴት ይኖራል። ግዕዙ ("ወሃሎ ትዕምርተ ስብራት ውስተ ግንባሩ እስከ ይእዜ በደሴተ ዳጋ") ይላል»(ተክለፃድቅ፣ 1951፣ 111፤ ጎርጎሪዮስ፣ 1991፣ 44)። ተክለፃድቅ ይህን የግዕዙን አገላለጽ ባሴት ረኒ የተባለው ወደ ፈረንሳይኛ ሲተረጉመው ለስብራቱ ምልክት በደጋ ደሴት ግንባሩ በሚባለው (ሥፍራ) መታሰቢያ እንዲሆንለት የቆመለት ሃውልት እስከ ዛሬ ይታያል በሚል ያስቀመጠው ትርጉም አሻሚነት እንዳለው አስፍረዋል። እኔም ለጥናት ወደ ገዳሙ በሄድኩበት ጊዜ የመታሰቢያ ሃውልት መኖሩን አልተመለከትኩም። በገዳሙ ያነጋገርኳቸው አባቶችም እንዲህ አይነት ሀውልት ስለመኖሩ አልነገሩኝም።

በመጨረሻም አፄ ዳዊት ሃያ ዘጠኝ ዓመት ኢትዮጵያን ከገዙ በኋላ በ1404 ዓ.ም ጥቅምት 9 ቀን ሞተው በዳጋ ደሴት/ደቂቀ እስጢፋኖስ/ ተቀበሩ(ተክለፃድቅ፣ 1951፣ 120)። ይሁን እንጂ ይህ ቀንና ዓመተ ምህረት ንጉሱ በባዝራ ተረግጠው የሞቱበት ቀን ስለመሆኑ አያረጋግጥም። ምክንያቱም በተረገጡበት እለት እንዳልሞቱ ግማደ መስቀሉን ተጉለት ቤተ መንግሥቱ አጠገብ ቤተክርስቲያን አሳንጸው እዚያ እንዳሳረፉት (ተክለፃድቅ፣ 1951፣ 118) የሚገልጽ መረጃ ያለ በመሆኑ ነው።

አፄ ዘርአ ያዕቆብ የአባታቸውን አጽም ከሙዋል ሰዎች አስመጥተው ባሰሩት በደብረ ነጎድጓድ ቤተክርስቲያን እንዳስቀመጡት(ተክለፃድቅ፣ 1951፣ 181) የተገለጸ መረጃ ቢኖርም አፅሙ በዚህ ቦታ /የሙዋል ሰዎች በተባለው ቦታ/ ምን ያህል ጊዜ እንደተቀመጠ፣ ለምን ወደ ደብረ ነጎድጓድ ማምጣት እንዳስፈለገ፣ እዚህ ቤተክርስቲያን ምን ያህል ጊዜ እንደቆየና መቼ ወደ ዳጋ ደሴት እንደሄደ መረጃ አላገኘሁም። ይሁን እንጂ ንጉሥ እንደሞቱ በቀጥታ ዳጋ እስጢፋኖስ እንዳልመጡ መረዳት ይቻላል። ይህም የሚቹ ንጉሱ ፍላጎት ወይም ኑዛዜ ሳይሆን በሕይወት ያሉት ወራሾቹ ወይም የተተኪው ንጉሥ ፍላጎት እየተፈጸመ እንደነበር ያሳያል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ጐላ ብለው ከሚጠቀሱ ክንውኖች ውስጥ አንዱ ኢየሱስ የተሰቀለበት መስቀል ቁራጭ/ግማደ መስቀል/ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ መቀመጥ ነው። የግማደ መስቀሉ በዚህች ሀገር መገኘት በኦርቶዶክስ ክርስቲያኑ ወገን ለታቦተ ጽዮን ከሚሰጠው ዋጋ የሚተናነስ አይመስልም። በርግጥ የእነዚህ ክንውኖች እውነተኛነት

በብዙ ሐይማኖታዊ መጻህፍት፣ የታሪክ ድርሳናትና የምርምር ሰነዶች ዘንድ አነጋጋሪ ጉዳዮች ሆነው እስከዚህኛው ትውልድ ድረስ የቀጠሉ ቢሆንም ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሐይማኖት መጻህፍት ስለግማደ መስቀሉ መምጣት ሳይጠራጠሩ ያሰፍራሉ። ታዲያ ይህንን ኢየሱስ የተሰቀለበትን ግማደ መስቀል ያስመጡት አፄ ዳዊት ለቤተክርስቲያኗ ትልቅ ስራ ሰርተው አልፈዋል ማለት ይቻላል። ይህንን ትልቅ ውለታ ያደረገ ንጉስ አጽም በዚህ ገዳም በክብር እንዲጠበቅ መደረጉ ከታሪካዊነቱ ይልቅ ሃይማኖታዊ ዋጋው ከፍ ያለ ነው። ይህም የገዳሙን ቅድስና አጉልቶ ከማሳየቱም በላይ ለገዳማዊው ህይወት የተለየ ትርጉም ይኖረዋል ማለት ይቻላል።

ሌላው በዚህ ገዳም ውስጥ ትልቅ ግምት የሚሰጠው የአፄ ዳዊት ልጅ የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ አጽም ነው። የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ አጽም ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ የመጣበት ሁኔታ በሁለት መልክ የማቀርበው ሲሆን አንደኛው በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ መረጃ አቀባዮቹ የገለፁልኝንና ሁለተኛው በመጽሐፍ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ ነው። ተክለፃድቅ መኩሪያ ስለአፄ ዘርዐ ያዕቆብ የቀብር ቦታ በፓሪስ ቤተመጻሕፍት የሚገኘውን የነሙሴ ረኔ ባሴትና ሌሎች ያሳተሟቸውን ታሪከ ነገሥት ጠቅሰው "እረፍቱኒ ለሐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ኮነ አመ 3 በጳጉሜ ወመቃብሪሁ በደሴተ ዳጋ"(1951፣209) እንደሚል አስፍረዋል። በርግጥ ይሄ መረጃ በዳጋ እስጢፋኖስ እንደተቀበሩ እንጂ የሞቱበትንና ወደ ደሴቱ ተወስደው የተቀበሩበትን ጊዜ አያመላክትም። ለዚህ ጥያቄ ግን ሌላ ቦታ ላይ በቂ መልስ ይሰጣል።

ተክለጻድቅ በታሪከ ነገሥቱ ላይ የሰፈረውን የአፄ ናዖድን ዜና መዋዕል መሰረት አድርገው "ከሞቱ 30 ዓመት የሞላቸው የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዐጽም ከነበረበት ቦታ ወጥቶ ዳጋ ደሴት ሄዶ መቀመጡን፤ አጽሙ ከተቀበረበት ምዕራፈ ጻድቃን (የጻድቃን ማረፊያ) ከሚባለው ዛፍ ሥር ከዐጽሙ ውስጥ ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ነች (ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም) የሚል ድምጽ ስለተሰማ የጽድቃቸው ታላቅነትና ከፍታቸው መታወቁን፤ እስከዚህ ጊዜ ድረስም በአፅማቸው ላይ ለጸለየና ለተማጸነ ሰው ተዓምራት መደረጉን(1951፣283) ይገልፃሉ።

ይህ ገለጻ የዘርዐ ያዕቆብ አፅም የት ቦታ እንደነበር አያመለክትም። ይሁን እንጂ ለ30 ዓመት ያህል ዐፅሙ በሌላ ቤተክርስቲያን ውስጥ አርፎ እንደነበር ይጠቁማል። "ምዕራፈ ጻድቃን" እሚባለው ዛፍ ሥር የሚለው ቀጥሎ በሚቀርበው ተረክ ውስጥ ቦታው አጽሙ ከመጣ በኋላ የተሰጠው ስያሜ ይሁን ቀድሞም የነበረ በግልጽ አያመለክትም። እንዲሁም እዚህ እተባለው

ቦታ ላይ አጽሙን እንዳሳረፉት እንጂ እንደቀበሩትም አያሳይም። ለሁሉም ለንጽጽር እንዲያመች በቃል ከመነኮሳት የተገነረኝ ተረክ ምን እንደሚመስል እንመልከት።

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ እንደሞቱ ሌላ ቦታ ተቀብረው ነበር። ነገር ግን ንጉሱ ያረፉበት ቦታ የጌታ ፈቃድ ስላልሆነ ለመኳንንቱና ለአባቶች በሕልምና በራዕይ ተገልፆ አፍልሱኝ ይላል። በኋላም ከተቀበሩበት ቦታ አፅማቸው ሲወጣ ዳ…ዳ…ዳ…. የሚል ድምጽ ይናገራል። አባቶችና መኳንንቱ በዚህ "ዳ" ፊደል የሚጀምር በጣም ብዙ ቦታ መፈለግ ይጀምራሉ። ነገር ግን ተስማሚ ቦታ ማግኘት አልቻሉም። በመጨረሻም ምናልባት "ዳ" ያለው "ዳጋ" ለማለት ይሆናል ብለው አፅሙን ወደዚህ ገዳም ይዘውት መጡ። አፅሙን እዚህ ቦታ አምጥተው እንዳሳረፉት ወዲያው "ይህች የዘለዓለም ማረፊያዬ ናት" /ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም/ በሚል ተናገረ። ከዚህች ቀን ጀምሮ ይህች ቦታ /አጽሙ ለመጀመሪያ ጊዜ ያረፈባት ቦታ/ የጻድቃን ማረፊያ እየተባለች ትጠራለች(አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.4A፤ አባ ወልደሃና፣ 2002፣ ካ.ቁ.1A)።

አፄ ዘርዐ ያዕቆብ አባታቸው እንዳስመጡት የሚነገርለትን ግማደ መስቀል ለማሳረፍ "መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ አስቀምጥ" የሚል ራዕይ ስለተነገራቸው(አንዳንዶቹ በሰማይ ላይ ይህንኑ ዐረፍተ ነገር ጽፎ አሳያቸው የሚሉ አሉ) መስቀለኛ ቦታ ያለው ቤተክርስቲያን ለማግኘት ብዙ እንደተንከራተቱ ሁሉ ከሞቱም በኋላ እርሳቸው ሊያርፉበት የፈቀዱትን ቦታ ለማግኘት ከ30 ዓመት በላይ ደክመዋል። በመጨረሻ መስቀሉ በመስቀለኛ ቦታ ላይ ሲያርፍ የእሳቸውም ዐጽም የመስቀል ቅርጽ ባለው ገዳም ሊያርፍ ችሏል። መስቀሉ ከፊል/ቁራጭ/ ሲሆን ንጉሱም ከፊል/አፅም ብቻ/ አካል ነበሩ። ሁለቱም ከነከፊልነታቸው መንፈሳዊ ኀይል ያላቸው ተደርጎ ይታመናል። አጽሙ የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የሁል ጊዜ ማረፊያው መሆኑን ራሱ በቃሉ አጽንቷል። እንደኔ እምነት ግን ይሄ አጽም ብዙ የተንከራተተ በመሆኑና መሄድ የለመደ ስለሆነ ገዳማውያን እንደገና ከገዳማቸው ፈልሶ እንዳይሄድ በመስጋት ተዓምራዊ የሆነ ክስተት መስጠትን እንደመፍትሄ የተጠቀሙበት ይመስለኛል። እንደገዳማውያኑ እምነት ግን ይህ ሁኔታ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የአፄ ዘርዐ ያዕቆብን ፃድቅነት ወይም የቦታውን ቅዱስነት አመላካች ነው የሚል እምነት አላቸው ማለት ይቻላል። ወይም ደግሞ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ፃድቅ በመሆናቸው ለፃድቅ ሰው የሚገባውን የተቀደሰ ቦታ ማግኘታቸውን ለማሳየት ይሆናል የሚል ግምት ይፈጥራል።

የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ አጽም ከ30 ዓመት በኋላ ቃል አውጥቶ መናገሩ በሥጋዊ አመለካከት አንፃር ሲታይ የሚያሳምን ባይሆንም መንፈሳውያኑ መነኮሳት ግን ትንሽ እንኳን ጥርጣሬ የሚያጭርባቸው አይመስልም። በርግጥም በአንዳንድ መንፈሳዊ ተረኮች አጽሞች ቃል አውጥተው ሲናገሩ ማዳመጥ የተለመደ ነው። ለምሳሌ ቀደም ሲል በቀረበው ተረክ ውስጥ ወጥ ሆኖ የተሰራው ሕፃን በተዓምር አንደበት አውጥቶ ሲናገር እንሰማለን። ስለዚህ የአጽሞች ንግግር አንድም ከአጽሙ ጻድቅነት በሌላም ሁኔታ ቅዱስና ፃድቅነቱን ከሚመሰክርለት አካል ጋር የሚያያዝ ተዓምራዊ ክንውን ነው። ስለዚህ የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ አፅም ቃል አውጥቶ የመናገሩ ተዓምር ከንጉሱ ፃድቅነትና ከቦታው ቅዱስነት አንጻር ሊያያዝ የሚችል ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል።

ወደኋላ መለስ ብለን የአፄ ዘርዐ ያዕቆብን ታሪክ በምናይበት ጊዜ ከአስተዳደራዊ ስራቸው በተጨማሪ የቤተክርስቲያን የበላይ መሪ ሆነው ማገልገላቸውን እናገኛለን። በዘመናቸውም ለቤተክርስቲያኗ ሰባት የሚሆኑ መጻሕፍት የፃፉ ሲሆን ተጨማሪ መጻሕፍት ከአረብኛ ወደግዕዝ አስተርጉመዋል። ከአዳሎችና ከፈላሾች ጋር ብዙ ጊዜ ተዋግተዋል። የጣዖት አምልኮንና የእስጢፋኖስ ተከታዮችን አስተሳሰብ ለመስበር የመረረ እርምጃ ወስደዋል። በተጨማሪም በእሳቸው አዋጅ ቅዳሜን እንደሰንበት እንድትከበር ማድረግ ችለዋል (ተክለፃድቅ፣1951፣194-196)። እነዚህን ዋና ዋና ክንውኖች ስንመለከት አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ውስጥ ደምቆ የሚታይ ታሪክ ያላቸው ንጉስ ነበሩ ማለት ይቻላል።

በርግጥ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ በተቃራኒ በኩል የሚቆሙ ወገኖች ንጉሱን እንደጨካኝ፣ አረመኔ፣ ጭፍንና ማመዛዘን የማይችሉ አድርገው ይፈርጇቸዋል። ይህንን አስተያየት በደምሳሳው ስህተት ነው ማለት ባይቻልም ንጉሱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካላቸው አስተዋጽኦ አንፃር ሲገመገሙ ግን ከፍ ያለ ስፍራ የሚሰጣቸው ናቸው ማለት ይቻላል። በዚህም ምክንያት የእኒህ ንጉስ አፅም ለቤተክርስቲያኗ ልዩ ትርጉም አይኖረውም ማለት አይቻልም። ይህም ልዩ ትርጉም ለምዕመናን፣ ለገዳሙና ለገዳማውያን ከንጉሱ ንግስና ይልቅ መንፈሳዊነታቸው(ቅድስናቸው) ደምቆ ሊታያቸው ይችላል። ስለዚህ የንጉሱን አፅም በክብር መጠበቅ በጥቅል ለገዳሙ ቤተክርስቲያኗ የጣለችበትን ትልቅ አደራ መሸከም ሲሆን ለገዳማውያኑ ደግሞ ንጉሱ የተገባለትን ቃል ኪዳን መውረስ መቻል እንደሆነ መገመት

ይቻላል። የንጉሱ አጽም በአፍልሱኝ ጥያቄ ስለመምጣቱ ግን ደጋፊ ማስረጃ ማግኘት አልቻልኩም።

ሌላው የዳጋ እስጢፋኖስን ገዳም ታሪካዊነት ከሚያፀኑት ጉዳዮች መካከል የሚጠቀሰው የአፄ ሱስንዮስና የአፄ ፋሲል አጽሞች በዚህ ገዳም መገኘት ነው። የሁለቱን አባትና ልጅ አጽሞች መቼና ማን ወደዚህ ገዳም እንዳመጣቸው የሚገልጽ መረጃ አላገኘሁም። ይሁን እንጂ የገዳሙ መነኮሳት አፄ ሱስንዮስ የኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸውን ክደው ስለነበር ኃጢአታቸው እንዲሰረይላቸው ልጃቸው ለተማጽኖ ወደዚህ ገዳም እንዳስመጧቸው ይናገራሉ። የአፄ ፋሲል አፅም ግን ቀደም ሲል ንጉሱ በዚህ ገዳም እየተገኙ ሱባኤ ይይዙ ስለነበር ሲሞቱ አፅማቸው በእዚህ ቦታ እንዲያርፍ ስለተናዘዙ(አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.4A) እንደሆነ ገልጸውልኛል።

ይሁን እንጂ የታሪክ ድርሳናት ሁለቱ ነገሥታት እንደሞቱ በአባቶቻቸው መቃብር አጠገብ እንደተቀበሩ እንጂ በቀጥታ ወደዚህ ገዳም እንደመጡ አይገልጹም። የአፄ ፋሲል ሬሳ አዘዞ(ደብረሊባኖስ) አቡነ ተክለሃማኖት ቤተክርስቲያን በአባቶቻቸው መቃብር አጠገብ የተቀበረ(ተክለፃድቅ 1961፣ 157) በመሆኑ ቅድሚያ ወደዚህ ገዳም እንዳልመጣ ያመላክታል። ይሄ መረጃ የሚያሳየው የአፄ ፋሲልም ሆነ የአፄ ሱስንዮስ አጽም ያረፈው አዘዞ (ጎንደር ከተማ አካባቢ ያለ ቦታ ነው) ከአባቶቻቸው መቃብር ጎን ነው። የሁለቱም ነገሥታት አፅሞች ከዚህ በፊት እንዳየናቸው ሁለት አፅሞች ሁሉ ከተቀበሩ በኋላ ፈልሰው የመጡ ናቸው ማለት ይቻላል። ታዲያ መነኮሳቱ እንደሚሉት ሁለቱ አፅሞች አንዱ ለተማጽኖ ሌላው በኑዛዜ ምክንያት የመጡ ከሆኑ እንደሞቱ ወደዚህ ገዳም ለምን እንዳልመጡ ምላሽ ማግኘት አይቻልም።

አፄ ሱስንዮስ በንጉስነት ዘመናቸው የኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸውን በመተው የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ሆነው ነበር። ከእሳቸው አልፎ ህዝቡ ሁሉ የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆን በማወጃቸው ምክንያት በተቀሰቀሰ የርስ በርስ ጦርነት መጠኑ እጅግ ብዙ ህዝብ አልቋል። በመጨረሻ ንጉሱ ምላሳቸው ተጐልጉሎ ሲሞቱ ልጃቸው አፄ ፋሲል ነግሰው የታወጀው አዋጅ ተሽሮ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተመልሷል። ታዲያ ገዳሙ የአፄ ሱስንዮስን አፅም እንደቅርስነት የሚጠብቀው ለምንድን ነው ሲባል አንድም ቤተክርስቲያኗ የከፈለችውን ዋጋ እለት እለት ለመዘከር ሊሆን ይችላል። አንድም ደግሞ የአሸናፊነቷን ግርማ አድምቃ ለማሳየት ይሆናል። ወይም ደግሞ አፅሙ በነገስታት ትዕዛዝ የመጣ ከሆነ ይህንን ትዕዛዝ

አለመቀበል ስለማይችሉ ይሆናል። ከሁሉም በላይ ግን ወደዚህ ገዳም የመጡት ሀጢአታቸው እንዲሰረይላቸው ነው የሚለው ተረክ አጽማቸው በዚህ ቅዱስ ገዳም በማረፉ ምክንያት በህይወት እያሉ የሰሩት ሀጢአት ይሰረዝላቸዋል የሚል እምነትን የሚያሰርጽ በመሆኑ ለገዳማውያኑ ገዳማዊ ህይወት ትልቅ ጥንካሬን ይፈጥራል ማለት ይቻላል።

አፄ ፋሲል ከንግስና ዘመናቸው በፊት ምንም እንኳ በአባታቸው ወገን ሆነው ለሀይማኖታቸው ሲሉ የሸፈቱትን የተዋጉ ቢሆንም አባታቸው ትክክል አለመሆናቸውን እየነገሩ ለማሳመን ይጥሩ ነበር (ተክለፃድቅ፣ 1961፣138)። በኋላም እሳቸው ሲነግሱ የቀደመውን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እንዲመለስ አድርገዋል። እኚህ ንጉስ የሃገሪቱን የሃይማኖት አቅጣጫ መሪ የለወጡ ናቸው ማለት ይቻላል። ምናልባት እሳቸውም የአባታቸውን መንገድ ተከትለው ቢሆን ኖሮ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት ውስጥ  የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት የሚኖረው ሚዛን አሁን ካለው የተለየ ሊሆን ይችል ይሆናል። ስለዚህ የእሳቸው አፅም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ገጥሟት የነበረውን ፈተና እና ይህንንም ፈተና የተወጡላትን ጀግና የሚያስታውስ ይሆናል። ገዳሙ የእኚህን ንጉስ አፅም በክብር ሲጠብቅ ከአባት፣ ከወገን፣ ከዘመድ ትስስርና ፍላጎት ይልቅ ለእምነት መጋደል ያለውን ታላቅ ዋጋ እያስታወሰ ይሆናል።

በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኙት የነገሥታትና የጳጳሳት አጽሞች ወደገዳሙ የመጡበት ምክንያት በውል ባይታወቅም ምናልባት በፍትሐ ነገስቱ ላይ እንደሰፈረው በማዕረግ ከእርሱ ጋር የሚተካከል የቅዱስ ሰው ሬሳ በተቀበረበት በተከበረ ቦታ ስጋውን ይቅበሩት(ፍትሐ ነገስት፣1990፣195) የሚል ህግ ያለ በመሆኑ እነዚህ ሁሉ አፅሞች በዚህ መነሻነት መጥተው ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል። ወይም ደግሞ የነገሥታቱ ልጆች ባላቸው የግል ፍላጎት ሊሆን ይችላል። ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም እነዚህ አፅሞች በገዳሙ እንዲያርፉ የቀደመ ፍላጎት ባይኖረውም አሁን በሚያደርገው ጥብቅ ጥበቃ ግን ለመጭው ትውልድ በሰላም እንዲተላለፉ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው መረዳት ይቻላል። በተለይም የቀደሙ አባቶችን አፅም መጠበቅ ሃይማኖታዊ መነሻ እንዳለው የሚያምነው ይሄ ገዳም በተለያየ ምክንያት መነሻነት አፅሞችን በክብር ይጠብቃል።

ይህም ሆኖ ግን ይህ ገዳም አጽመ ነገሥታትን እንደ አጽመ ቅዱሳን በጥንቃቄ የሚጠብቅበት ምክንያት ምንድን ነው? ገዳማት አጽምን እንደ ቅርስነት ለመጠበቅ ሃይማኖታዊ መነሻ አላቸው ወይ? እነዚህ አጽሞች በቅርስነት እንዲያርፉ /እንዲጠበቁ/ የገዳሙ ፍላጎት ነው ወይ?

አጽሞች ለገዳማውያንም ሆነ ለምእመናን ጎብኝዎች ምን ጥቅም ይሰጣሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል።

### 4.3.6 ከአጽሞች ትሩፋት የሚያገኝ ገዳም መሆኑ

ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም አጽመ ነገሥታትን በክብር እንደ ቅርስ የሚጠብቀው በተለያዩ ምክንያቶች እንደሆነ መነኮሳት ገልጸውልኛል። አንደኛው የቅዱሳን አባቶች አጽም ቅዱስና የተከበረ ስለሆነ ለአለውም ሆነ ለሚመጣው ትውልድ በረከት ይኖረዋል በሚል ስለሚታመንበት ነው። ይህንንም ሲያስረዱ አጽመ ነገስታት የተቀቡ ነገሥታት ናቸው። ቅባቱም ቅዱስ ነው። ሌላው ደግሞ እነዚህ ነገሥታት ከዳዊት ዘር የተወለዱ ነገሥታት በመሆናቸው ቅድስና አላቸው። "እነሆ ዳዊትን ቀባሁት፤ እንዳልዋሸውም ማልሁለት። እስከ ትውልደ ትውልድ ድረስ ዘሩ ይነግሳል" (መዝ፡ 88፣20)(ወቀባይክዎ ለዳዊት ገብርዩ ወኢየሱስ ወጽአ እመአፉዬ ምዕረ መአርኩ ለዳዊት ገብርዬ) የሚል ቃል ኪዳን የተገባላቸው ናቸው። ስለዚህ እንኳን የእነሱ አጽም ቀርቶ ሥጋ ወደሙ የተቀበለ (በቅዱስ ሥጋውና በቅዱስ ደሙ የከበረ) የማንም ክርስቲያን አጽም ቢሆን እንኳን የተከበረ ነው ተብሎ ይታመናል። በዚህ ምክንያት ገዳሙ የእነዚህን ነገሥታት አጽም በክብር ይጠብቃል ብለውኛል። ሌላኛው የእነዚህ ነገሥታት አፅም ለሀገሪቱ ታሪክ ማስረጃ ነው በሚልና ይህም ለትውልዱም ሆነ ለሃይማኖቱ ትልቅ ሃብት ነው በሚል እምነት ገዳሙ በክብር ይጠብቃቸዋል። ሌላው ጉዳይ ግን ልክ እንደ ኤልሳዕ ከአፅመ ቅዱሳን ኃይል ይደረጋል ተብሎ ሰለሚታመን ገዳሙ የነገስታቱን አፅም በክብር ይጠብቃል (አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.4A) በማለት ነግረውኛል።

እንግዲህ በዚህ ገለፃ ነገሥታት በአፀደ ሥጋ እያሉ በቅዱስ ቅባት የተቀደሱ በመሆናቸውና ይሄ ቅድስናም ከሞቱ በኋላም ስለማይጠፋ ሊከበሩ እንደሚገባ ይታመናል። ከዚህ ሌላ አንድ ሰው የአምላክን ሥጋና ደም ወስዶ ከተቀደሰ በኋላ ቢሞት እንኳን በድኑ ወይም አጽሙ ቅድስናው እንደማይለየው (እንደማይሻር) ያሳያል። በእርግጥ ይህንን ምክንያት ብንቀበል እንኳ ከነገሥታቱ አጽም መካከል የሚገኘውን የአፄ ሱስንዮስ አጽም ስናስብ ጥያቄ ይፈጥርብናል። ንጉሱ በዘመነ መንግሥታቸው ካቶሊክ ሆነው በዚህም ምክንያት በተቀሰቀሰ የርስ በርስ ጦርነት ብዙ ሰው እንዳለቀ ታሪክ ያስረዳል። ይህ ከሆነ ታድያ የንጉሱን አፅም ቅድስና እንዴት መቀበል ይቻላል? ወይስ ደግሞ የንግስና ቅባት በክህደትም እንኳ አይረክስም ለማለት ነው? በርግጥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ዘንድ ስለንጉሱ ጉዳይ ሲነሳ በወቅቱ ክህደት

በመፈፀማቸው ምላሳቸው እንደተጎለጎለና በኋላ ግን ንስሃ ገብተው እንደሞቱ ይተርካሉ። ይሄን ጉዳይ ግን የካቶሊክ አማኞች አይቀበሉትም።

ምክንቱም አፄ ሱስንዮስ ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተመልሰው ወይም በካቶሊክነታቸው ጸንተው ስለመሞታቸው የሚታወቅ ነገር የለም። ይህንን በሚመለከት ተክለጻድቅ ከታሪክ ፀሐፊዎች ውስጥ ካቶሊክ የሆኑት ንጉሱ በዚያው በካቶሊክነታቸው ፀንተው ሞቱ በሚል ሲጽፉ፤ ኦርቶዶክስ የሆነው ታሪክ ፀሐፊ ደግሞ ንስሃ ገብተውና ወደ ኦርቶዶክስነት ተቀይረው ሞቱ(1961፣ 139) በሚል እንደሚጽፉ አስፍረው እናገኛለን። ስለዚህ ይሄ አፅም በገዳሙ ውስጥ ለታሪክ መዘክርነት በሚል እንደተቀመጠ የሚነገረው ሃሳብ ተገቢ ሊሆን ይችላል። ንጉሱ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት ላይ ፈጽመዋል ከሚባሉት ተግባር አንጻር በተለይ በራሱ በኦርቶዶክስ አማኙ ዘንድ አጽሙን ቅዱስ አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያ አለ የሚለው ጉዳይ ግን አጠያያቂ ይመስለኛል። ይህ ሲባል ግን የካቶሊክ አማኝ ከሆኑ ቅዱስ መሆን አይችሉም ለማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባል።

ገዳሙ የነገስታቱን አጽም በክብር የሚጠብቅበትን ምክንያት ከዚህ በተለየ መንገድ ማየት ይቻላል። ይህም በአንድ ዘመን ገናና የነበረ ንጉስ የሚቀበርበት /የሚያርፍበት/ ቤተክርስቲያን ወይም ገዳም ከሚያገኘው መንፈሳዊና ማህበራዊ ክብር እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር የሚያያዝ መስሎ ይታየኛል። ይህንን በሚመለከት ተክለጻድቅ አንድ ንጉስ የነገሰበት ደብር፣ የተቀበረበት ቤተክርስቲያን ክብርና ደረጃ እንዳለውና ገንዘብና ልብስ በየጊዜው ከወራሹ ንጉስ እንደሚሰጠው (1951፣ 182) አስፍረው እናገኛለን። ስለዚህ ገዳማት ሊያገኙት ከሚችሉት ጥቅም አኳያ የነገስታትን አፅም በክብር የሚጠብቁበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል መገመት ይቻላል።

አባ ወልደ ሰንበት አፅምን በቅርስነት መጠበቅ ሀይማኖታዊ መነሻ ያለው ስለመሆኑ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ እንደሚከተለው መልሰውልኛል። አጽም እንደ ቅርስ የሚጠበቀው ሃይማኖታዊ መነሻ ስላለው ነው። አዳም ሲሞት የአዳምን አፅም ልጁ ሴት ሲጠብቅ ነበር። የሴትን አፅም ደግሞ ተከታዩ ትውልድ ሲጠብቀው ነበር። እነ ሄኖክ፣ መላልኤም እና ያሬድ አፅመ አበውን ሲጠብቁ ነበር። ኖህ በበኩሉ አጽመ አበውን እንደ ታቦት አድርጎ ወደ መርከቡ ይዞ ገብቶ ነበር። መልከ ጼዴቅም እንዲሁ አፅመ ቅዱሳንን ይጠብቅ እንደነበር በመጽሐፍ ላይ ሰፍሮ ይገኛል። ዮሴፍ አባቱ ያዕቆብ ከሞተ በኋላ ስጋውን በአልጋው ላይ ያቅፈው ነበር(ዘፍ፡50፣1)። እስራኤላውያንም ከግብጽ ባርነት ሲወጡ ሙሴና ኢያሱ የዮሴፍን አጽም

ይዘው ወጥተዋል(ዘፀ፡13፣19)። ይህም ሲደረግ የኖረው የአበው አጽም ቅዱስና ክቡር ስለሆነ ነው። በእነሱ አፅም ተማጽኖም ረድኤትና በረከት ሲያገኙ ኖረዋል(ትንሳኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣ 1990፣ 194፤ አባ ወ/ሰንበት፣2002፣ካ.ቁ. 4A) ።

ከዚህ ገለጻ አንፃር እስራኤላውያን የአባቶቻቸውን አፅም የመጠበቅ ልማድ ነበራቸው ማለት ይቻላል። በተለይ ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች ብዙዎቹ በኦሪት (በብሉይ ኪዳን) ስማቸው ጎላ ብሎ የሚነሳ ነው። ነገር ግን በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የሚጠበቁት የነገስታት አጽሞች ናቸው። የነገሥታት አጽም እንደተባለው በእግዚአብሔር የተቀቡ ናቸው ብሎ በማመን እንደ አፅመ ቅዱሳን እየተቆጠሩ ካልሆነ በቀር ከላይ እንደማስረጃ ከተዘረዘሩት ሰዎች ጋር የሚጣጣም ሆኖ አላገኘሁትም። ምክንያቱም ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦች (ከዮሴፍ በቀር) የሚታወቁት በንጉስነታቸው ሳይሆን በሃይማኖት መሪነታቸው ነው። በርግጥ በወቅቱ ነገስታት የሀይማኖቱንና የመንግስቱን ስልጣን ሁሉ ደርበው የሚይዙበት ሁኔታ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል። ነገር ግን 9 ያህል ጳጳሳት እንደተቀበሩበት በሚነገርበት በዚህ ገዳም ውስጥ የአንድም ቅዱስ ጳጳስ አፅም በክብር እየተጠበቀ አለመገኘቱ እንደተባለው ቅዱሳን ያበረክቱታል ከሚባለው ጥቅም ይልቅ ነገሥታት ከሚሰጡት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር የተያያዘ ይመስላል።

በፍትሐ ነገስቱ ላይ የሞቱ ሰዎች አጥንት በእግዚአብሔር ዘንድ የተናቀና የረከሰ ባለመሆኑ የሞቱትን ሰዎች በድን አትናቁ(ፍትሐነገስት፣1990፣194) በሚል የሰፈረውን ሀሳብ ስንመለከት አፅሞች አንዳች ጥቅም ሊኖራቸው እንደሚችል አመላካች ነው። ስለአፅሞች ጥቅም መነኮሳት የሚከተለውን ገልጸውልኛል። አፅመ ነገሥታት ቅዱሳን በመሆናቸው ከእነሱ ረድኤትና በረከት ይገኛል። አጽማቸው መማፀኛ ይሆናል። ለቤተክርስቲያኗም ሃብቷና ግርማዋ ናቸው። በርግጥ አንዳንዶቹ ከነገሥታት አጽም ቆርጠው በመውሰድ መናፍስትን ለመሳብ የሚጠቀሙ ቢኖሩም ገዳሙ ግን የነገስታቱን አጽም የሚጠብቀው ለዚህ አላማ አይደለም። ይሁን እንጂ ከነገስታቱ አፅም አንዳች ኃይል ይገኛል ተብሎ ይታመናል። ለምሳሌ የነቢዩ ኤልሳዕ አጽም ሙት አስነስቷል(2ኛነገስት፡13፣20)። በአጽመ ቅዱሳን ላይ ኃይል ያለ ስለሆነ ተዓምር ይደረጋል። ፃድቃን ሰማዕታት በተቀበሉት መከራ ቃል ኪዳን እንደሚሰጣቸው ሁሉ እነዚህ ነገሥታት በተሰጣቸው ቃል ኪዳን መሰረት አጽማቸው ለገዳሙም ሆነ ለሃገር ረድኤትና በረከት ይሰጣሉ ተብሎ ይታመናል(አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.4.A፤ አባ ወ/ሃና፣ 2002፣ ካ.ቁ.1A) ይላሉ።

በዳጋ እስጢፋኖስ የተቀበሩትና ያልተቀበሩት አጽመ ነገሥታት እንዲሁም ሌሎች ጳጳሳት ካላቸው ቅድስና አንፃር ለገዳማውያንም ሆነ ለሀገር በእጅጉ በረከት እየሰጡ እንደሆነ ይታመናል። የኤልሳዕ ሙት አጽም ከሞት እንዳስነሳ ሁሉ (2ኛ ነገስት 13፣20) እነዚህም አጽሞች ተዓምር ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይታመናል። ቀደ ም ሲል በተክለፃድቅ መኩሪያ የታሪክ መጽሐፍ ላይ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ አጽም አጠገብ አምኖ ለተማፀነ ተዓምር ሊደረግለት ይችላል ተብሎ እንደሚታመን መስፈሩን ተመልክተናል። ከዚህ ጋር በተያያዘም ከእነዚህ ነገሥታት አጽም አካል ላይ ትንሽ ቁራጭ ከተገኘ ለብዙ ነገር ሊውል እንደሚችል (መናፍስትን ከመሳብ ጋር በተያያዘ ነው) ይታመናል።ለምሳሌ የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ አፅም ጥይት አያስመታም ተብሎ ይታሰባል(ይስማዕከ፣2001፣177)።

እዚህ ላይ መረዳት የሚቻለው አፅሞች ብዙ ተዓምር ሊያደርጉ ይችላሉ ብሎ ማመን ጥንትም ሆነ አሁን ያለ ልማድ መሆኑን ነው። በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳምም በክብር የተቀመጡት እነዚህ አፅሞች እንዲህ አይነት ተዓምር አደረጉ የሚባል መረጃ ባላገኝም ተዓምር ሊያደርጉ ይችላሉ ተብሎ እንደሚታመን ግን ማረጋገጥ ችያለሁ። ከነገስታት አፅም እንደተባለው በተገባላቸው ቃል መሰረት በረከት የሚገኝ ከሆነ ረቂቅና የማይጨበጥ የሆነውን መንፈሳዊ እርዳታ (ትሩፋት) ተጨባጭና ቅርብ ያደርገዋል። ይህም መንፈሳዊነትን አርቅቆና አርቆ ከመመልከት ይልቅ አግዝፎና አቅርቦ እንዲታይ የሚያደርግ በመሆኑ ለመንፈሳዊው ተጋድሎ ትልቅ መሳሪያ ሆኖ ሳያገለግል እንዳልቀረ መገመት ይቻላል።

## *4.4 ገዳሙን መልሶ ከማጠናከር እንቅስቃሴ ጋር የሚነገሩ ተረኮች*

የዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም መነኮሳት የአፄ ሱስንዮስን አስከሬን በገዳሙ ውስጥ አናስቀብርም በማለታቸው ምክንያት በተቀሰቀሰ አለመግባባት መነኮሳቱ ሁሉ እንደተሰደዱና የገዳሙም ገዳማዊ ህይወት እንደተቋረጠ(አባ ተክለ ዮሐንስ፣2002፣ካ.ቁ.2A) የሚናገሩ አባቶች ቢኖሩም በአንጻሩ ሌሎች አባቶች ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመነ መሳፍንት ድረስ በተጠናከረ ሁኔታ እንደቀጠለና የመቋረጥ አጋጣሚ እንዳልገጠመው ይነገራሉ። በኋላ ግን በዘመነ መሳፍንት የተዳከመው የገዳም ህይወት በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት እንደገና ተጠናክሮ የቀጠለ ቢሆንም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ገዳማዊ ህይወቱ ሊቋረጥ ችሏል። የተቋረጠውን የገዳም ሕይወት እንደገና ለማስቀጠል መምህር ወልደ ትንሳኤና ሌሎች አባቶች እንቅስቃሴ ማድረግ ይጀምራሉ። አባ ወልደ ትንሳኤ ገዳሙን ለማቋቋም በሚወጡ በሚወርዱበት ጊዜ ከአካባቢው መኳንንት ጋር ከፍተኛ ግጭት ውስጥ ይገባሉ። ይሄ ገዳም እንደገና እንዳይደራጅ

የሚፈልጉት እነዚህ ሰዎች በጠላትነት ይነሱባቸውና አባ ወልደ ትንሳኤን ለመግደል ያቅዳሉ። በዚህም መሠረት የአባ ወልደ ትንሳኤ ጠላቶች አንድ ቀን በዚሁ በገዳሙ ጉዳይ ላይ በዳኛ ፊት ለመነጋገር ቀጠሮ ይዘው ይጠሯቸዋል። የተገናኙትም ዘጌ ከሚባል ቦታ ከአንዲት ሴት ቤት ነው። እነዚያ የአባ ወልደ ትንሳኤ ጠላቶች ይህችን ሴት በገንዘብ ደልለው ለአባ ወልደ ትንሳኤ በምትሰጣቸው ጠላ ውስጥ መርዝ እንድትጨምርበት ይሰጧታል።

ከዚያም በስምምነታቸው መሠረት ሴትዮዋ ለሁሉም ጠላ ሰጥታቸው ወደ ጓዳ ትገባለች። በኋላም ስለገዳሙ ጉዳይ እየተነጋገሩ እያሉ የሴትዮዋ ሕፃን ልጅ ከውጭ እየሮጠ ይገባል። ሕፃኑ እንደገባም አባ ወልደ ትንሳኤ የተቀረበላቸውን ጠላ እንዲሰጡት ይጠይቃቸዋል። እሳቸውም አንስተው ይሰጡታል። ልጁ የተሰጠውን ጠላ ይጠጣል። ወዲያው ልጁ በሰው ፊት ይወድቅና ይሞታል። እናቱ ይህን ስታይ «እኔ ነኝ ልጄን የገደልኩት» እያለች መጮህ ትጀምራለች። በኋላ «ምንድን ነው?» ተብላ ስትጠየቅ «እነ እገሌ» በሚል ስማቸውን ጠርታ «በአባ ወልደ ትንሳኤ መጠጥ ውስጥ መርዝ ጨምሬ እንድሰጣቸው አታለውኝ ነው ልጄን ለሞት ያበቃሁት» አለቻቸው (አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቁ.3B)።

አባ ወልደ ትንሳኤ በቅዱሳኑ ተራዳኢነት ይመስላል ሕይወታቸው ሲተርፍ እሳቸውን ለመግደል የተባበሩት ደግሞ ሲቀጡ እንመለከታለን። ይህም ገዳሙ እንደገና ተጠናክሮ እንዲቀጥል የአምላክ ፍላጎትና ፈቃድ ስለሆነ ይህንን ለማደናቀፍ እጁን የሚያነሳ ቢኖር አይቀጡ ቅጣት ይቀጣል የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ይመስላል። ገዳማውያን ይህንን ተረክ ሲተርኩ ሁልጊዜም በአምላካቸው ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ለመጠቆምና ጠላቶቻቸውም እንዲሸማቀቁ ለማድረግ ይመስላል። ጠላቶቻቸው ግን በተደረገው ተዓምር ሳይደናገጡ ወይም የተፈጠረውን ድርጊት እንደ ተራ አጋጣሚ ቆጥረውት ሊሆን ይችላል ሌሎች የጥፋት መንገዶች እንዳቀዱባቸው አባ ወልደሰንበት ነግረውኛል።

ቀደም ሲል የታቀደው እቅድ እንደከሸፈ ሲመለከቱ ሌላ እቅድ ያዘጋጃሉ። በዚህም መሠረት ከጠላቶቻቸው መካከል አንዱ በቀጥታ በበዓታቸው/በቤታቸው/ ውስጥ እንዳሉ በጥይት እንዲገድላቸው ይታቀዳል። ግድያውን ለመፈጸም የታዘዘው እቅዱን ለማሳካት መሳሪያ ታጥቆ ሃይቁን በታንኳ ለመሻገር ጉዞ ይጀምራል። በኋላም ግማሽ ርቀት ያህል እንደተጓዘ የተሳፈረበት ታንኳ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሳይታወቅ ይገለበጣል። በዚህም ጊዜ የያዘው መሳሪያ ሃይቁ ውስጥ ይገባል። እሱም በብዙ ትግልና መከራ ሕይወቱን አትርፎ ወደ መጣበት

ይመለሳል። በማግስቱ ይህ ሰው ወደ ገዳሙ ድረስ በመሄድ አባ ወልደ ትንሳኤን አግኝቶ ነገሩን ሁሉ በዝርዝር ከተናዘዘላቸው በኋላ ይቅር እንዲሉት እግራቸው ሥር ይወድቃል። በመጨረሻም ከዚህ ሁሉ ትግል በኋላ ገዳሙ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ትዕዛዝ እንደገና ይቋቋማል። አባ ወልደ ትንሳኤም ገዳሙ ታሪካዊነቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ብዙ ደክመዋል። በአጠቃላይ አባ ወልደ ትንሳኤ የዚህ ገዳም አበምኔት ሆነው ባደረጉት በጎ ሥራ ገዳሙ እንደ ቅርስ ይቆጥራቸዋል። ለዚህም ባረፉበት ጥቅምት 14 ቀን ቅዳሴ ይቀደስላቸዋል። በየዓመቱ በስማቸው (ስማቸው እየተጠራ) ዳዊት ይደገምላቸዋል። ያረፉት ጎርጎራ መንዳባ መድኃኔዓለም በሚባል ገዳም ውስጥ ቢሆንም ይኖሩበት የነበረው በአታቸው (ቤታቸው) ተዘግቶ በክብር የሚጠበቅ ሲሆን የእሳቸውን በዓት ገዳሙ እንደቅርስ ይቆጥረዋል (አበ ወልደ ሚካኤል፣2003፤አባ ወ/ሰንበት፣ 2002፣ ካ.ቂ.4.A) በማለት ይገልጻሉ።

ገነትን ውሃ ከሚያጠጧት ወንዞች መካከል አንዱ እንደሆነ የሚታመነው የግዮን ወንዝ የጣና ሀይቅን ተቀላቅሎ ስለሚያልፍ ይህ ሀይቅ የተለየ ቅድስና እንዳለው ቀደም ሲል ለመግለጽ ሞክሬአለሁ። ሐይቁ ለገዳማውያኑ የአትክልት ማጠጫና የጽዳት አገልግሎት የውሃ ምንጭ በመሆን ገዳሙ የገነት መዓዛ እንዲኖረው ከማስቻሉም ባሻገር ገዳማውያን ከጠላቶቻቸው የሚጠበቁበት አጥር ሆኖ ያገለግላል ማለት ይቻላል። ስለዚህ በዚህ ገዳም ያሉ ነገሮች ሁሉ ቅዱስ መሆናቸው ስለሚታመን ሲያስፈልግ የቅድስና በረከት የሚሰጡ፣ ሲያስፈልግ ደግሞ ጠላትን የሚከላከሉ አጥሮች ይሆናሉ ተብሎ ይታሰባል። ይህም ገዳሙም ሆነ ገዳማውያኑ በአምላክ የተቀደሱና የተመረጡ መሆናቸውን እንደሚቀበሉ የሚያመላክት ይመስለኛል።

በአጠቃላይ በእነዚህ ተረኮች ገዳማውያን ገዳማዊ ህይወታቸው የት እና እንዴት እንደተጀመረ፣ ምን ዓይነት ሂደቶችን እንዳለፈ፣ እነማን ምን እንደሰሩ፣ አሁን ምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አደላድለው የሚገልጹባቸው ናቸው። ገዳማውያን አሁን እየተከተሉት ያለው ገዳማዊ ህይወት ምንጩ የት እንደሆነ አስረግጠው ለማለፍ ጥረት ያደርጋሉ። የገዳማዊ ህይወታቸው መነሻ ከቅዱሳኑ ተግባር የሚጀምር በመሆኑ እነዚህን ቅዱሳን መሰረት በማድረግ ይተርካሉ። ገና ከመነሻው የእነሱ ቅዱሳን እነማን እንደሆኑ፣ ምን አይነት መንፈሳዊ ኃይል እንዳላቸው፣ ምን ምን የተቀደሱ ተግባራትን እንዳከናወኑና በልዕለ ተፈጥሮ እንዴት እንደተመረጡና እንደሚደገፉ ይተርካሉ። ከእነዚህ ቅዱሳን ውጭ የሆኑት እነማን እንደሆኑ፣ ምን እንደሚሰሩና ምን እንደሚያምኑ፣ ምን ዓይነት ድክመት እንዳለባቸውና በተረኮቻቸው እያጥላሉ የራሳቸውን ማህበራዊ ህይወት ያደላድሉባቸዋል። እነዚህ ተረኮች ገዳማውያን ከስር

የተመሰረቱበትን መንፈሳዊ መዋቅር አደላድሎ በመግለጽ አሁን ላለው ማህበራዊ ስርአት/System/ የት መጣነት የማስረጽ ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

ሌላው እነዚህ ተረኮች የቅዱሳኑን ሰብዕናና አስደናቂ ተግባራትን አጉልተው ከማሳየት በተጨማሪ ድርጊቶቹ የሚከናወኑባቸውን ሥፍራዎች ቅዱስ አድርጎ የማሳየት ባህርያት ይታይባቸዋል። እነዚህ ተረኮች ገና ከመነሻው ገዳሙ በልዕለ ተፈጥሮ የተቀደሰና ለቅድስና የተመረጠ ሥፍራ እንደሆነ ለማመልከት ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ። በተለይም ገዳሙ በተፈጥሮ አቀማመጡ እጅግ ምስጢራዊነት የተላበሰ፣ ሰማያዊ ከሚባለው ህይወት ጋር የተወሰነ ጉዳይ የሚጋራ፣ እንዲሁም የልዕለ ተፈጥሮ/አምላክ/ መለኮት የሚገለጽበት፣ የህቡአን መኖሪያ፣ እንዲሁም በቅድስና ውስጥ የሚገኝ ሌላ ቅድስና ያለው መሆኑን የሚገልጹ ተረኮች ናቸው። ተረኮቹ ቦታው ረቂቅ የሆነው የልዕለ ተፈጥሮ መንፈስና ኃይል የተመሰረተበት እንደሆነ የማሳየት አቅም አላቸው ማለት ይቻላል። እነዚህ አይነቶቹ ተረኮች ለገዳማዊ ስርዓት/System/ በልዕለ ተፈጥሮ ኃይል መመካት የማስቻል ተግባርን እየተወጡ ይገኛሉ የሚል እምነት አለኝ።

## 5. የገዳሙ አምልኳዊ ስርአቶች/Sacred Rituals/

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለዳጋ እስጢፋኖስ አምልኳዊ ስርዓት ትንተና ለመስጠት እሞክራለሁ። ቀደም ሲል ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቴን ባቀረብኩበት ክፍል ውስጥ እነስሚስ(2005,103) አምልኳዊ ስርዓትን በማህበርና በግል የሚከወኑ በማለት በሁለት እንደሚከፍሏቸው አመልክቻለሁ። በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ትንተና የምሰጥባቸውን አምልኳዊ ስርዓቶች በማህበር የሚከወኑና በግል የሚከወኑ በማለት በሁለት ከፍዬ ለማሳየት ጥረት አደርጋለሁ። በቅድሚያ የምመለከተው በማህበር የሚከወኑትን ሲሆን በግል የሚከወኑትን አምልኳዊ ስርዓቶች አስከትዬ አቀርባለሁ። የትንተናው አካሄድ በቅድሚያ አምልኳዊ ስርዓቶችን በሚመለከት ከመረጃ አቀባዮቼ የሰበሰብኳቸውንና እኔም በአካል ተገኝቼ የተመለከትኳቸውን መረጃዎች በማጠናቀር ከገለጽኩ በኋላ ትንተናዬን አስከትላለሁ።

### *5.1 በማህበር የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች*

#### 5.1.1 በጸሎተ ማዕድ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች

ጸሎተ ማዕድ የሚባለው በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ መናንያን በአንድነት የሚሳተፉበት የማዕድ ፀሎት ፕሮግራም ነው። በቅድሚያ ፀሎተ ማዕድ የሚለው ፀሎት ተደርጎበት ማዕዱ የሚበላበትን ቤትና የፀሎት መርሐ ግብሩን የሚወክል ጥምር ቃል ነው።

ለፀሎተ ማዕድ የሚሆነው ሕብስት የሚዘጋጀው በተግባር ቤት ውስጥ ነው። ይህ ሕብስት ትኩስ እንደሆነ ወደ ፀሎተ ማዕድ መድረስ ይኖርበታል። በመጀመሪያ ሕብስቱ ተጋግሮ እንደወጣ ከጓያ የተሰራ ሽሮ ወጥ ይቀባና በተቀባበት በኩል ተጋጥሞ እንደ አነባበሮ ይዘጋጃል። የተነባበረው ሕብስት ግምጃ በለበሰ መሶበ ወርቅ ውስጥ ይቀመጣል። በመቀጠልም በማንቀረቀሪያ ውሃ ይቀዳል። ዝግጅቱ እንዳለቀ መጋቢው ከተግባር ቤቱ ወጥቶ ለፀሎተ ማዕድ ብቻ ተለይቶ የሚታወቀውን የደወል ዓይነት ደውሎ ይመለሳል። በኋላም መጋቢው ነጠላውን አደግድጎ በተግባር ቤቱ እንደቆመ ቀጥሎ እጓል መጋቢው /ረዳት መጋቢው/ ለመጋቢው መሶበ ወርቁን ያሸክመዋል፤ ዕዋው ያለበትን ማንቆርቆሪያም ይጠሰዋል። መጋቢው ሕብስቱንና ፅዋውን ተሸክሞ በፀሎተ ማዕዱ እንደደረሰ ሕብስቱን ከመሶበ ወርቁ አውጥቶ በአውዱ ላይ ያስቀምጠውና አውዱ ለብሶት የነበረውን ግምጃ ያለብሰዋል። መሶበ ወርቁ ግን ግምጃውን እንደለበሰ ይቀመጣል።

በመቀጠል ማህበረ መነኮሳቱ ወደ ፀሎተ ማዕዱ እንደገቡ አበምኔቱ ካሉ አበምኔቱ፣ አበምኔቱ ከሌሉ ደግሞ ካህኑ የፀሎቱን ሥነሥርዓት በፀሎት ይከፍታሉ። በመቀጠል ዳዊት አስደጋሚው ለእያንዳንዱ የፀሎተ ማዕዱ ታዳሚ ዳዊት[10] ያድላል። ቀጥሎም ፀሎተ ነቢያትና ማህልይ ዘሰሎሞን ይደገማል። ጊዜ ካለና የሰው ቁጥር ብዙ ከሆነ እንደገና ከዳዊት ጀምሮ ሁሉም በድጋሚ ይታደላል። በኋላም ካህኑ በአቡነ ዘበሰማያት የዳዊትን ፀሎት ያሳርጉና ቀጥለው ፀሎተ ማርያም እንዲደገም መመሪያ ይሰጣሉ። ፀሎተ ማርያም እንዳለቀ ውዳሴ ማርያም ይታደላል። ይሄም እስከ ይዌድስዋ መላዕክት ከተደገመ በኋላ አሁንም ካህኑ በፀሎት ያሳርጋሉ። ቀጥሎ መልክአ ማርያም ተደግሞ ካህኑ ያሳርጋሉ። ከዚያም መልክአ ኢየሱስ ተደግሞ ካህኑ ካሳረጉ በኋላ ብቻቸውን ሳህልለከን ይደግማሉ። ሲጨርሱም በፀሎት ያሳርጉና ፀሎተ ሃይማኖት፣ ፀሎተ እግዝእትነ ማርያምና አቡነ ዘበሰማያት ብለው ያሳርጋሉ።

በመጨረሻም ሕብስቱን እንዲፈትት/እንዲቆርስ/ የተመረጠው መነኩሴ የገቡትን ፋጋዎች/የቅል መመገቢያዎች/ ይቆጥራል። በእነዚህም ፋጋዎች ልክ ህብስቱን ይፈትታል። ተፈትቶ ሲያልቅ ረዳቱ የተፈተተውን ሕብስት በየፋጋዎቹ ላይ ይቆንናል/እየመጠነ ያስቀምጣል/። ከዚያም እያንዳንዱ መነኩሴ የየራሳቸውን ፋጋ አንስተው በመውሰድ ዳዊት በደገሙባቸው ቦታዎች ላይ ሆነው ልብሳቸውን በመሸፋፈን ይመገባሉ። ዲያቆኑ ለእያንዳንዱ መነኩሴ ጽዋውን እየቀዳ ይሰጣቸዋል። ሁሉም ተመግበው ሲጨርሱ ዲያቆኑ ተነስቶ ስብሃት ይልና ካህኑ በአቡነ ዘበሰማያት ያሳርጋሉ። በመቀጠልም ዲያቆኑ ፀሎተ እግዝእትነ ማርያም፣ የጊዮርጊስ ፍጡነ ረድኤት አርኬ መርገፍ ያስደግምና መሬት ላይ ወድቆ ለሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ፀሎተ ማርያምን ይደግማል። በፀሎት አስቡኝ ያሉ አባቶች ካሉ መጋቢው ለማህበሩ ያቀርብና ስለእነርሱ ወድቆ ፀሎተ ማርያም ይቀበላል። በመጨረሻም ምናልባት ማህበሩ ሊወያይበት የሚገባ ጉዳይ ካለ መጋቢው ያቀርብና ማህበሩ መክሮ ይወስናል። ከዚያም ዲያቆኑ መሶበ ወርቁን ተሸክሞ ወደ ተግባር ቤት ይዞ ሲሄድ መነኮሳቱም እሱን ተከትለው ከፀሎተ ማዕዱ ይወጣሉ። መሶበ ወርቁ ሳይመለስ ማንም መውጣት አይፈቀድለትም።

---

[10] ዳዊት ያድላል ሲባል 150 የሚሆነው መዝሙረ ዳዊት አስር አስር ክፍል ባለው በ15 ቦታ ላይ ተከፍሏል። የመጀመሪያው አስር ፍካሬ ሲባል ሁለተኛው አስር ደግሞ አድህነኒ ይባላል። ሦስተኛው አስር አምላኪዬ የሚል መጠሪያ አለው።ሁሉም የዚህ አይነት ስያሜ አላቸው። ስለዚህ መጀመሪያ "ፍካሬ" በሚል የታደለው ሰው ከ1-10 የሚደርሱ መዝሙሮችን ይደግማል ማለት ነው። ዳዊት አስደጋሚውም እነዚህን ስያሜዎች ለዳዊት ደጋሚዎች እያደለ 150 የሚሆኑ መዝሙሮች ይደገማሉ ማለት ነው።

ሕብስቱ እሁድና ቅዳሜ ከስንዴ ከመዘጋጀቱ ውጭ ከሌላው ሕብስት የተለየ አይደለም። የሚዘጋጅበት ቦታም ሆነ አዘጋጅዎቹ የገዳሙ እኅል መጋቢዎች ናቸው። የአቆራረሱ መጠን በፀሎተ ማዕዱ በተገኙት መነኮሳት ቁጥር የሚወሰን ይሆናል። ስለዚህ በዚህ ቅርጽ ወይም በዚህ መጠን ዓይነት ቁረስ ተብሎ አይወሰንም ማለት ነው።

የፀሎተ ማዕድ ሃይማኖታዊ መሠረቱ ወንድሞች በህብረት ቢሆኑ መልካም ነው (መዝ./133/፣1-2) የሚለውና እነሆ በእሁድ ሰንበትም በማዕድ ተቀምጠን ነበር፤ ጳውሎስም ማዕዱን አንስቶ ባረከ በሚል የሰፈረው ሃሳብ ነው። ከሁሉም በላይ ግን ዋናው መሠረቱ ኢየሱስ ነው። ይሄውም ኢየሱስ በፀሎተ ማዕድ ሕብስቱንና ፅዋውን አንስቶ ከባረከ በኋላ ለሐዋርያት ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ እንደሆነ በመግለጽ (ማቴ. 26፥26፤ 1ኛ.ቆሮ. 11፥20-22) ለሐዋርያት አከፋፍሏቸዋል። ይህንን መነሻ በማድረግ የፀሎተ ማዕድ ሥነሥርአት ይከናወናል። ፀሎተ ማዕድ በዚህ ሃይማኖታዊ መነሻ ተመስርቶ በገዳሙ ውስጥ ዋና የአንድነታችን መሠረት ሆኖ እያገለገለ ይገኛል በማለት ይገልጻሉ።

ከዚህ ሌላ ለፀሎተ ማዕዱ ከሚሰጠው ክብር አኳያ ሃይማኖታዊ መነሻው ብሉይ ኪዳን እንደሆነ ይነገራል። በብሉይ ኪዳን ለፈጣሪ የሚቀርብ መስዋዕት፣ እንደዚሁም ካህኑና ቤተሰቡ የሚመገቡት የመስዋዕት ምግብና ተረፈ መስዋዕት የሚባለው ሕዝቡ መስዋዕት ካቀረቡ በኋላ የሚመገቡት ምግብ ነው። ይህም የተለያየ የመስዋዕት ደረጃ እንዳለ ያሳያል። ሁሉም የተከበረ መስዋዕት እንደሆነ የሚታወቅ ቢሆንም የአክብሮት ደረጃው አንጻራዊ ክብደት የሚሰጠው/ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ አክብሮት የሚደረግለት/ መስዋዕት አለ ማለት ነው። ፀሎተ ማዕድ በተለያዩ አድባራት ምዕመናን በእለተ ሰንበት እንደሚመገቡት አይነት የሰንበት ቂጣ ወይም መክፈልት አይደለም። ከዚህም ሌላ ፀሎተ ማዕድ ከተራው ሕብስት የተለየ በመሆኑ ክብር ያለው ቢሆንም እንደ ሥጋ ወደሙ/ቁርባን/ የሚቆጠር አይደለም። ሥጋ ወደሙ የሚከብረው በቅዳሴ እንደሆነ ገልፀውልኛል።

ፀሎተ ማዕድ ፀሎት የተደረሰበት ስለሆነ መነኮሳት ማንኛውንም ዓይነት እድፍና ጉድፍ /ኃጢአት/ ተናዝዘው የሚቀበሉት እንደሆነ ነገረውኛል። በፀሎተ ማዕዱ ከመነኮሳት በተጨማሪ ጥቁር ራስ[11] የሚባሉትም ይሳተፋሉ። ነገር ግን እነዚህ ጥቁር ራስ የተባሉት የገዳሙ ማህበር

[11] ጥቁር ራስ የሚባለው በአመክሮ ላይ የሚገኝና ያልመነኮሰ መናኝ ነው። ገዳሙ የማህበሩ አባል አድርጎ የተቀበለው በመሆኑ በማህበሩ ህግ የመተዳደር ግዴታ አለበት።

የአንድነቱ አባል ሆነው እንዲኖሩ የፈቀደላቸው ናቸው። ወደ ፀሎተ ማዕድ ሲገባ ሁሉም ልብሱን አደግድጎና ጫማውን አውልቆ መሆን እንዳለበት ይነገራል። ታጥቆና እጅ ነስቶ መቆም ከጥንት ስርአተ ቤተክርስቲያን የመጣ ነው። ቅዱስ ኤፍሬም የማርያምን ምስጋና ሲያቀርብ እጅ ነስቶና ታጥቆ ነው። ከዚህም ሌላ ኢየሱስ ወገቡን ታጥቆ የሐዋርያትን እግር እንዳጠበ እንረዳለን። ስለዚህ ወደ ፀሎተ ማዕድ አደግድጎ የሚገባው ለክብርና ለምስጋና የሚገባ በመሆኑ ነው ይላሉ።

ወደፀሎተ ማዕድ ሲገባ ጫማ የሚወለቀውም ክብር ለሚገባው ሁሉ ክብር ለመስጠት ነው። ጌታ በደብረሲና ለሙሴ ሲገለጥለት "ይህች የምትረግጣት ምድር የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ" (ዘፀ.3፣5) ባለው መሠረት ፀሎተ ማዕድ ቃለ እግዚአብሔር የሚነገርበትና ቅዱስ ማዕድ ያለበት ቦታ በመሆኑ ጫማ ይወለቃል። በሥርአተ ቤተክርስቲያን ወደ አብያተ ክርስቲያን ሲገባ ጫማ እንደሚወለቅ ሁሉ ይህም ፀሎተ ማዕድ እንደቤተክርስቲያን አይነት ክብር የሚሰጠው በመሆኑ ጫማ ይወለቃል።

ቤተክርስቲያን ለፀሎት አገልግሎት ብቻ እንደሚገባበት ሁሉ ፀሎተ ማዕድም ከፀሎት ውጭ ለሌላ አገልግሎት ወይም ለሌላ ልዩ ተልዕኮ አይውልም። ስለዚህ ፀሎተ ማዕድ ለፀሎት ካልሆነ በቀር ለማረፍ ወይም ለመቀመጥ አይገባበትም። ፀሎተ ማዕድ የተለየ ክብር ስለአለው በሰንበትና በአበይት በዓላት ቀን ቦታውን ለመባረክና ለመቀደስ ሲባል በገዳሙ ካህናት አማካይነት ይታጠናል። ካህናቱ ሲያጥኑ የሚፀልዩትም የቡራኬ ፀሎት ነው።

በሰንበት፣ በበዓላትና አርድዕት/አገልጋዮች/ ከሥራ ውጭ በሚሆኑባቸው እለት ሁሉ ማንኛውም የማህበሩ አባል በፀሎተ ማዕድ መርሐግብር የመሳተፍ ግዴታ አለበት። ይህንንም መጋቢው በየጊዜው ይቆጣጠራል። በአንድነት መፀለይ የታዘዘ በመሆኑ የማዕዱን ፀሎት ማስታጎል አይፈቀድም። ፀሎተ ማዕዱን ማንኛውም ሰው ሊመገበው አይችልም። ሳህልለክ የተደገመበትን ሕብስት እንዲመገቡ የሚፈቀድላቸው ገዳሙ በአባልነት የተቀበላቸው ወይም አንድነቱን የተቀበሉ ብቻ ናቸው። ነገር ግን «በደዌ ዳኛ፣ በአልጋ ቁራኛ» ለተያዘና ሕመም ለፀናበት ሰው ከህመሙ እንዲድን በመጋቢው ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል። ከዚህ ውጭ ግን ማንም ሰው መመገብ አይችልም። ሕብስቱን እንዲመገቡ ከሚፈቀድላቸው መነኮሳት መካከል በሕመም፣ በአቅም ማነስና በተለያዩ ምክንያቶች ህብስቱን መጨረስ ያቃተው መናኝ ቢኖር የተረፈውን ህብስት ይዞ ሊሄድ ይችላል። ነገር ግን ሌላ ህብስት ሳይመገብ አቆይቶ መብላት

ይኖርበታል። ከዚህ ውጭ ግን በብህትውና፣ «በደዌ ዳኛ፣ በአልጋ ቁራኛ» የተያዙ አባቶች ካሉ በያሉበት በሊቀ አበው አማካኝነት ይወሰድላቸዋል።

መነኮሳት በፀሎተ ማዕድ የሚሰጣቸውን ህብስት ሲመገቡ ልብሳቸውን ተሸፋፍነው መሆን አለበት። ልብሳቸውን ተሸፋፍነው ስለሚመገቡበት ምክንያት በስርዓተ ጳኩሚስ የተደነገገ ስለሆነ ነው። በስርዓተ ጳኩሚስ ላይ እያንዳንዱ መነኩሴ የተሰጠውን ድርጎ/ድረሽ/ ሲመገብ ተሸፋፍኖ መሆን አለበት። እርሱንም የሚያዩት እጁና ፋጋው ብቻ ይሁኑ ስለሚል ነው ይላሉ። የመሸፋፈናቸውም ምክንያት ነቀፋን ለማራቅ ነው። ይህም አንድ ሰው ሲመገብ «ልቅ ልቅ ይጎርሳል» ወይም «ብጥስ ጣል ያደርጋል» በሚል አንዱ ሌላውን እንዳይነቅፍ ወይም ሳይመገብ የሚሄድ ቢኖር ለትሩፋት ነው በሚል ከንቱ ወዳሴ ውስጥ እንዳይገባ ነው።

ፀሎተ ማዕድ የሚባለው ክፍል እንደቤተክርስቲያን ቅድስትና መቅደስ የሚባል ክፍል አለው። ቅድስት በሚባለው ክፍል ጥቁር ራስና በአመክሮ ላይ ያሉት የሚፀልዩበት ሲሆን መቅደስ በሚባለው ደግሞ መነኮሳትና ካህናት የሚፀልዩበት ክፍል ነው። በመቅደሱ ማዕከል ወለል ላይ ፀሎተ ማዕዱ የሚፈተትበትና የሚቀመጥበት ግምጃ የለበሰ ጠረጴዛ ይገኛል። ከዚህ ጠረጴዛ ጀርባ የአባምኔቱ መቀመጫ ይገኛል። ይሄ ወንበር አበምኔቱ ዘወትር በፀሎተ ማዕድ ሲሳተፉ የሚቀመጡበትና ዳዊት የሚደግሙበት ነው። በእሳቸው ወንበር ላይ ሊቀመጥ ስልጣን ያለው ሰው የለም። ምናልባት ከእሳቸው በፊት የነበሩ አበምኔት ካልተቀመጡበት በቀር አበምኔቱ ባይኖሩ እንኳ ሌላ ሰው አይቀመጥበትም። በየጊዜው ስማቸው እየተጠራ የሚፀለይላቸው የማህበረ እስጢፋኖስ በርካታ አባላት ስም ዝርዝር በታሸገ /ላምኔት በተደረገ/ ወረቀት ተሰቅሎ ይታያል። ለአምልኮታዊ ስርዓት መፈፀሚያ የሚሆኑ የቅዱሳን ስዕሎችም ተሰቅለው ይገኛሉ።

በዚህ በፀሎተ ማዕድ ውስጥ የተለያዩ ጥቅሶች ይታያሉ። ከእነዚህም ውስጥ "በተሰበረ ልብ፣ በፈሪሃ እግዚአብሔር ወደ ፀሎተ ማዕድ እንምጣ" ፣ "ደወል ሲደወል ቀደም ብሎ መምጣት ትህትናና ታዛዥነት ነው" ፣ "ኑሮዬ የመነኮሳት ነውን ወይስ ገና በሽፍትነቴ ነው ያለሁት?" የሚሉት ይገኙበታል።

በፀሎተ ማዕዱ የተፀለየበት ህብስትና ፅዋ በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙ ሰዎችን ይፈውሳል ተብሎ ይታመናል። ለዚህም የሆድ ህመም የነበረባቸው ብዙ መነኮሳት መፈወሳቸውን ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ። ፀሎተ ማዕድ ከአጋንንት ፈተና የሚራቅበት፣ ከስጋና ከደም ጋር

ሲዋሃድ ጤና የሚገኝበት፣ ከመንፈስና ከስጋ ደዌ የሚፈወስበት እንደሆነ ይናገራሉ። በአጠቃላይ ፀሎተ ማዕድ መድሃኒት ነው ማለት ይቻላል ይላሉ።

እንግዲህ ከቀረበው ገለጻ በመነሳት ይህንን አምልኳዊ ስርዓት እንደሚከተለው ለመመርመር እሞክራለሁ። ፀሎተ ማዕድ የአንድነት ምሳሌ ነው። በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ትልቅ ክብር የሚሰጠው የፀሎተ ማዕድ ስርዓት ሃይማኖታዊ መነሻው የሐዋርያት ሕብረት /አንድነት/ ነው። በክርስቶስ ያመኑ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ከሐዋርያት ጋር በነበሩበት ጊዜ ጥሪት ቅሪታቸውን ሸጠው ለሐዋርያት በማስረከብ በአንድነት የሚመገቡ ሲሆን ምግባቸውም የፍቅር ግብዣ እየተባለ ይጠራ ነበር(አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣ 142፣ የሐዋ.ሥራ 2፥42፣ ቀዳ.ቆሮ.11፥20-22)። በዚህ ገዳም ውስጥ የሚኖሩ ገዳማውያን ይህንን መነሻ በማድረግ በአንድነት ፀልየው በአንድነት ይመገባሉ።

ሆኖም ሐዋርያት ሲከተሉት ከነበረው ክርስቲያናዊ ሕይወት ፀሎተ ማዕድ ብቻ የተቀዳ አይመስልም። የተወሰኑ ነገሮች እየተጨመሩበት ቅርፁን የለወጠ ቢሆንም በየሳምንቱ እሁድ በቤተክርስቲያን አውደ ምህረት የሚፈተተው ፀሪቀ መበለት፣ ተዝካረ ሰንበት፣ ዝክር፣ ተዝካርና ማህበር ከሐዋርያት ማህበር የተወሰደ(አባ ጎርጎርዮስ፣1991፣143) እንደሆነ መገመት ይቻላል። ያም ሆነ ይህ ሐዋርያት ሲከተሉት የነበረው የጋራ ኑሮ ሲቀየር ወይም ሲቀር ክርስቲያናዊው ህይወት የተቋረጠ ባይሆንም በዚህ ገዳም ግን ፀሎተ ማዕድ ከሌለ አንድነት እንደሌለ ይታመናል። አንድነታቸው እንዲጠበቅም የጸሎተ ማዕድ ስርአት ተጠብቆ እንዲዘልቅ በጥንቃቄ ይጠብቁታል።

የፀሎተ ማዕድ መርሐ ግብር የሚከናወንበት ቤት የአምልኮ ሥርዓት ከሚፈፀምበት ቤተክርስቲያን ጋር የሚቀራረብ ክብር ተሰጥቶት እናያለን። ቤቱ ቅድስትና መቅደስ የሚባሉ ክፍሎች ያሉት መሆኑና በየጊዜው በካህናት የሚባረክና የሚታጠን መሆኑ፤ ጫማ ተወልቆ የሚገባበትና ከፀሎት ውጭ ለማረፊያነት ክልክል መሆኑ፤ ወደዚህ ቤት ለመግባት ኃጢአትን ተናዞና በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ መሆኑ ቤቱ የተቀደሰ ሆኖ እንደሚታመንበት የሚያስገነዝብ ነው። በእርጅና ወይም በህመም ምክንያት ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ያልቻሉ አባቶች ጸሎተ ማዕድ ከተሳተፉ ቤተክርስቲያን እንደሄዱ ይቆጠርላቸዋል። የጸሎተ ማዕድ ማዕከላዊ ጉዳይ ቅድስና ነው ማለት ይቻላል። ወደዚህ የተቀደሰ ቤት ለመሄድ ሲታሰብ ዘወትራዊ የሆነውን

ፀሎት ከማድረግ ባለፈ ራስን ለመቀደስና ለመባረክ እንደሆነ ይታመናል። ለዚህም ይመስላል ገዳማውያን ለፀሎተ ማዕዱ ጥብቅ ስርዓት ተገዥ የሚሆኑት።

ለፀሎተ ማዕዱ ስርዓት ማሳረጊያ የሚሆነው በዚህ ቤት ተፈትቶ/ተቁርሶ/ የሚበላው ሕብስት ነው። ይህ ሕብስት በዝግጅቱ ከተራው ሕብስት የተለየ ባይሆንም በዚህ ቤት ከተፀለየበት በኋላ ግን ተራነቱ ይቀርና የተቀደሰ ሕብስት እንደሚሆን የሚታመንበት ይመስላል። በዚህም ምክንያት ከማህበረ መነኮሳቱ ውጭ የሆነ ወይም ገዳሙ በአባልነት ያልተቀበለው ሰው ሊመገበው አይፈቀድለትም። ይህም የሆነው ሕዝባውያን አብረው አይብሉ (ትንግኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣1990፣113) የሚለውን ድንጋጌ መነሻ በመያዝ ይመስላል። ሕብስቱን ቅዱስና ክብር የሚገባው እንደሆነ በማሰብ ሲመገቡ እንደ ፀሪቀ መበለትና ቁርባን ተሸፍነው ነው።

ይህ ሕብስት በሽተኞችን ይፈውሳል፣ ከአጋንንት ፈተና ያርቃል፣ የተጨነቁትን ያረጋጋል፣ መንፈሳዊ ሀይልን ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመንበት ሕብስቱ ባለው ቅድስና ምክንያት የገዳሙ መድኃኒት ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ገዳማውያን ለሥጋቸው ማቆያ የሚከፋፈሉት መቁኑን/የእለት ምግብ/ ከፀሎተ ማዕዱ ሕብስት ውጭ የሚሰጣቸው በመሆኑ የፀሎተ ማዕዱ ሕብስት አንድም ከሕመማቸው ለመዳን፣ ወይም የሥነ ልቡና መረጋጋት ለማግኘት አንድም ደግሞ የሥጋ ምግብ ተመግበው በመንፈስ ለማደግ ወይም ቅድስናን ለማግኘት የሚመገቡት ሕብስት ነው ማለት ይቻላል።

ፀሎተ ማዕድ ቀደም ሲል መነሻው የሐዋርያት ክርስቲያናዊ ሕይወት እንደሆነ ተገልጿል። ከሐዋርያት ክርስቲያናዊ ሕይወት በተቀዳው የጽዋ ማህበር (አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣ 143) ስርዓት ውስጥ ሁሉም ሰው ከሚበላው ሕብስት በተለየ ሁኔታ በምትጋገር ሕብስት ላይ ተፀልዮ ማህበርተኛው ብቻ ይመገቧታል። ይህም የአንድነታቸው መግለጫ እንደ ሆነች ስለ ሚታመንበት ነው። ጽዋውም ተፀልዮበት ሁሉም በአንድነት ይቃመሱታል። በዚህም ምክንያት ይመስላል ሕብስቱም ጽዋውም በሽተኛ ይፈውሳል ተብሎ የሚታመነው(አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣ 144)። ይህ የጽዋ ማህበር ስርአትና እምነት ከፀሎተ ማዕድ ስርአትና እምነት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ይታያል። ከዚህ ሌላ ፀሎተ ማዕድ የጌታን የመጨረሻው ራት(ማቴ.26፣26፤ ማር.14፣22፤ ሉቃ. 22፣17፤ 1ኛ ቆሮ.11፣17) መነሻ በማድረግ እንደተጀመረ ይታመናል። የገዳሙ አባቶች ፀሎተ ማዕድ የጌታን ራት መነሻ አድርጎ እንደተጀመረ ገልጸው ነገር ግን ቁርባን የሚከብረው በቅዳሴ በመሆኑ የቤተክርስቲያን አይነት ቁርባን ነው ማለት እንዳልሆነ

ያስገነዝባሉ። ይሁን እንጂ እንደእኔ እምነት ፀሎተ ማዕድ ከቁርባን ጋር ተቀራራቢነት ያለው ይመስለኛል።

ለቁርባን የሚሆነው ሕብስት የማያድር፣ የማይተርፍ (ትንሣኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣1990፣139) ሲሆን የፀሎተ ማዕድ ሕብስትም ትኩስና የማይተርፍ መሆኑ ያመሳስለዋል። ማንም ሳይፆም ቁርባን መቀበል (ዝኒ ከማሁ፣ 140) እንደማይፈቀድለት ሁሉ የፀሎተ ማዕዱን ሕብስትም ከምግብ በኋላ መብላት አይፈቀድም። ከቁርባን በፊት ሰው ሰውነቱን መርምሮ ንፁህ ያድርግ (ዝኒ ከማሁ፣140) እንደሚል ሁሉ የፀሎተ ማዕድን ሕብስት ለመመገብም የግድ ተናዝዞና ራሱን ከኃጢአት አንጽቶ መሆን እንዳለበት ተቀምጧል። ከዚህ ሌላ በሁለቱም ስርዓቶች ለህብስቱና ለፅዋው ከሚሰጡት ትልቅ ክብር የሚመነጭ ይመስላል ሲመገቡ ተሸፋፍነው መሆኑ ያመሳስላቸዋል። ስለዚህ ፀሎተ ማዕድ፣ ቁርባን፣ በጽዋ ማህበር መጀመሪያ ለበረከት በሚል የሚከፋፈሉት ህብስትና ፅዋ፣ ፀሪቀ መበለትና ዝክር ምንጫቸው የጌታ ራት ሲሆን የተወሰነ መመሳሰልም ይታይባቸዋል ማለት ይቻላል።

ቀደም ሲል የጸሎተ ማዕድ ማዕካላዊ ጉዳይ ቅድስና ነው ብያለሁ። ስለዚህ ጸሎተ ማዕድ በገዳሙ የሚከወኑትን አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ሁሉ መንፈሳዊነትን በማላበስ ትክክለኛነታቸውን የማጽናት ተግባር አለው ማለት ይቻላል። ቀደም ሲል እደተገለጸው በቤቱና በቤቱ ዙሪያ መንፈሳዊ ድባብ ለመፍጠር ጥረት ይደረጋል፤ በዚህ መንፈሳዊ መነሳሳት ውስጥ የተለያየ የጸሎት ስነስርዓት ይካሄዳል፤ በመጨረሻም የተቀደሰው ህብስትና ጽዋ ይቀርባል። በዚህ ጥልቅ በሆነ መንፈሳዊ ሁኔታ ውስጥ የተለያዩ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን የሚሹ ጉዳዮች ለውይይት ይቀርባሉ፤ ትዕዛዛት ይተላለፋሉ። ገዳሙን የሚመለከቱ እቅዶች ይታቀዳሉ፤ ሹመት ይሰጣል፤ ይሻራልም። ጥፋተኛ ይቀጣል፤ ምህረት ይደረግለታል። ፀሎተ ማዕድና(ቤቱንም፣ስርዓቱንም ለማለት ነው) በዚህ ቤት የሚፈተተው/የሚቆረሰው/ ሕብስት የተቀደሰ ነው ተብሎ እንደሚታመን ተጠቅሷል። በተቀደሰ ቤት የሚፈተተውን የተቀደሰ ሕብስት የሚመገብ ማህበርም የተቀደሰ ማህበር ነው የሚል አንድምታ አለው። በተቀደሰ ቤትና በቀደሰ ማህበር የሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችም ሁሉ የተስተካከሉና ፍትሃዊነት ያላቸው ናቸው ተብሎ እንዲታመን ያደርጋል ማለት ይቻላል።

በዚህ ጸሎተ ማዕድ ውስጥ የሚደረጉ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በሰው እንደበት የሚገለፁ ቢሆንም የእግዚአብሔር ሃሳብና ውሳኔዎች እንደሆኑ ይታመናል። ገዳማውያንን በዚህ ቤት ውስጥ ሹመት ሲሰጣቸው እግዚአብሔር እንደሾማቸው፣ ሲሻሩም እግዚአብሔር እንደሻራቸው፣

በጥፋታቸው የእስራት ፍርድ ሲፈረድባቸውም እግዚአብሔር እንደፈረደባቸው ያምናሉ። ገዳማውያን በነፍሳቸው፣ በምክራቸው፣ በሥጋቸው ጭምር አንድ ሊሆኑ እንደሚገባ(ትንሣኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣1990፣ 107፤ አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣ 142) የተደነገገ በመሆኑ በዚህ የተቀደሰ ቤት ውስጥ የሚወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ሁሉ የእግዚአብሔር ውሳኔ እንደሆነ ስለሚታመን ማንም ገዳማዊ በውሳኔው ሊያጉረመርም አይችልም። በዚህ ምክንያት የፀሎተ ማዕድ ሥርአት የገዳሙ አንድነት እንዳይፋለስ ዋልታ ሆኖ የሚጠብቅ በመሆኑ ገዳማውያን ለአንድነታቸው ሲሉ የፀሎተ ማዕድ ሥርዓትን ያከብሩታል፤ ይጠብቁታል።

### 5.1.2 በተግባር ቤት የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች

ተግባር ቤት ማለት የሥራ ቤት ማለት ነው። ቤተ እግዚአብሔርም /የእግዚአብሔር ቤት/ ይባላል። ቤተ እግዚአብሔር ደሀ፣ ባለፀጋ፣ ብርቱ፣ ደካማ፣ ሳይባል ሁሉም የገዳሙ ማህበር የሚተዳደርበት ቤት ነው። አድልዎ የሌለበት ቤት ነው። ተግባር ቤት እንግዳ ቢመጣ የሚስተናገድበት፣ ማህበረ መነኮሳቱ የእለት ጉርሳቸውን የዓመት ልብሳቸውን የሚቆነኑበት/የሚታደሉበት/ ቤት ነው። ቤተ እግዚአብሔር የገዳሙ ስጋዊም ሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል በመሆኑ ከቤተክርስቲያን ቀጥሎ ልክ እንደ ፀሎተ ማዕድ ትልቅ ክብር የሚሰጠው ቤት ነው።

በቅድሚያ በተግባር ቤት ውስጥ እኅል መጋቢው / የመጋቢው ልጅ ወይም የመጋቢው ረዳት ማለት ነው/ እንጀራውን ለመጋገር ሊጡን ሲያቀጥን አቡነ ዘበሰማያት ይደግማል። እንጀራውን የመጋገሪያ ሰዓት ሲደርስ ምጣዱን ከማስማቱ በፊት ፀሎተ ወንጌል ይደግማል። ይህንንም እየደገመ ምጣዱን ያሰማል፤ ጋግሮ ሲያበቃ እሳቱን አጥፍቶ መከሬታውን /እንጀራውን/ በተገቢው ቦታ ላይ አስቀምጦ ሲጨርስ እንጀራውን በጋገረበት ቦታ ላይ ወድቆ ፀሎተ እግዝእትነ ማርያምና አቡነ ዘበሰማያት ይደግምና የእለቱን ስራ ያጠናቅቃል።

መቁነን ወይም ድርጎው ለየመነኮሳቱ ከመሰጠቱ በፊት በተግባር ቤቱ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት አሉ። በመጀመሪያ እኅል መጋቢዎች የመነኮሳቱን የመቁነን ማከፋፈያ ፋጋዎች እንደተቀመጡበት የመቁነን አይነትና መጠን መግለጫ በመሰብሰብ በአይነት በአይነታቸው ወደተግባር ቤት በማስገባት ይደረድሯቸዋል። የመቁነን መጠንና ዓይነት ሲባልም ገዳማዊው በእለቱ ሊመገበው የሚፈልገው የመቁነን መጠንና አይነት ማለት ነው። እነዚህም ኩርማን፣

ምላጭ፣ ንፍሮ፣ ኩርማን ከንፍሮ፣ ምላጭ ከንፍሮ የሚባሉ ዝርዝሮች ናቸው። እነዚህ የምግብ ዝርዝሮች በካርቶን ተፅፈው ግድግዳ ላይ ተሰቅለዋል። መነኩሴው /መናኙ/ በእለቱ ኩርማን መመገብ የሚፈልግ ከሆነ ፋጋውን ኩርማን በሚለው ዝርዝር ላይ ተከልሎ በተቀመጠ ቦታ ያስቀምጣል። ምላጭ የሚፈልግም እንዲሁ ምላጭ በሚለው ቦታ ላይ፣ ኩርማን ከንፍሮ የሚፈልግም እንዲሁ ኩርማን ከንፍሮ በሚለው ዝርዝር ላይ ፋጋውን ያስቀምጣል ማለት ነው። በመሆኑም እጓል መጋቢዎች እነዚህ በአይነት በአይነታቸው የተቀመጡትን ፋጋዎች ወደተግባር ቤት እንደየአይነታቸው ያስገቧቸዋል።

በመቀጠልም የተግባር ቤቱ ይዘጋል። ይህም የሚሆነው በውጭ ያለ ሰው እንዳይመለከት ነው። ከዚያም መጋቢው ህብስቱን በተዘጋጀው የእንጨት አውድ ላይ / አውድ የሚባለው በክብ ቅርፅ የተዘጋጀ ጣውላ ነው/ በማስቀመጥ ይፈትተዋል። አንዱን ሙሉ እንጀራ / መኮሬታ/ ከስምንት ይፈትተዋል። ከስምንት ሲፈትተው አንድ መኮሬታ ስምንት ምላጭ ይወጣዋል ማለት ነው። በኩርማን ሲታሰብ ደግሞ አንዱ መኮሬታ አራት ኩርማን ይሆናል። የምላጭ ግማሽ ደግሞ ሰንጢ ይባላል። ስለዚህ አንድ ሙሉ እንጀራ አራት ኩርማን፣ ስምንት ምላጭ፣ አስራ ስድስት ሰንጢ ይሆናል ማለት ነው። ሰንጢ የሚባለው በዘወትሩ መቁኑን ውስጥ የሚካተት ሳይሆን መናኙ በህመም ወይም በሌላ ችግር ምክንያት መመገብ ባይችል ሊሰጠው የሚችል የመቁኑን ዓይነት ነው።

የአቆራረሱ አይነት ከሀይማኖቱ ስርዓት ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ነግረውኛል። በቤተክርስቲያን ስርዓት አንድ ካህን በቅዳሴ ወቅት ባርክ ምስራቀ፣ ወምዕራበ፣ ሰሜነ፣ ወደቡበ፣ ነስአ፣ ወአዜበ፣ ባህረ፣ ወሊበ ብሎ ይባርካል። በዚህ አገላለፅ በአራቱ ማዕዘን አራት ንዑስ ማዕዘናት አሉ ማለት ነው። የእንጀራውም አፈታተት የዚህ ምሳሌ ነው። ከዚህ ሌላም ቤተክርስቲያን ስምንት ማዕዘን ያላት በመሆኑ መኮሬታው የስምንቱ የቤተክርስቲያን ማዕዘናት ምሳሌ ነው ማለት ነው። በርግጥ እንጀራውን በተፈለገው መንገድ ቆርሶ ማቅረብ ቢቻልም የቤተክርስቲያኗ አባቶች ከምስጢራት ጋር አዛምደው የጀመሩት በመሆኑ ገዳማውያን ይህንን ጠብቀው እየሰሩ እንደሚገኙ ገልፀውልኛል። ከዚህ ሌላም በሀገሪቱ ባህል ክብ ምጣድ እንጂ አራት ወይም ሦስት ማዕዘን ምጣድ ባለመኖሩ ለዚህ የአቆራረስ አይነት ሌላው አስገዳጅ ምክንያት ሆኗል። ይህም ቢሆን የአንድ ምጣድና የሦስት ጉልቻ ባህል የስላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚያሳይ በመሆኑ የሀገሪቱ ባህል ከሃይማኖቱ ያልራቀ መሆኑን ያመለክታል ይላሉ።

መጋቢው ህብስቱን ፈትቶ ከጨረሰ በኋላ ከእጓል መጋቢዎች ጋር በመሆን አቡነ ዘበሰማያትና ፀሎተ እግዝእተነ ማርያም ደግመው እንደመነኮሳቱ ፍላጎት እየተረዳዱ ይቆንናሉ። ከዚህ በኋላ መጋቢው ህብስቱ እንደተቆነነ አረጋግጦ ሲጨርስ እና ሰዓቱ ሲደርስ ከተግባር ቤቱ ወጥቶ የመቁኑን ደወል ይደውላል። ደወሉ እንደተደወለም ማህበረ መነኮሳቱ ወደ ተግባር ቤቱ በር ይሰበሰባሉ። ሁሉም እንደተሰበሰቡ መጋቢውና እጓል መጋቢው ተጎንብሰው ካህኑ አቡነ ዘበሰማያትና ፀሎተ እግዝዕትነ ማርያም ይደግምላቸዋል። በመጨረሻም ቤተ እግዚአብሔር ያስፋ፣ ክንዳችሁን ከቁርጥማት፣ ደረታችሁን ከውጋት ይሰውራችሁ፤ ማህበሩን ሰላም ያድርግልን፤ አገራችንን ይጠብቅልን ብለው ከጨረሱ በኋላ መቁነኑ እንዲወጣ ትዕዛዝ ይሰጣሉ። በኋላም መጋቢው ከእጓል መጋቢዎች ጋር ሆኖ መቁነኑን ወደውጭ ያወጣላቸዋል። ከዚያም እያንዳንዱ መናኝ የየራሱን ፋጋ እያነሳ ይዞት በመጣው አኮፋዳ/ኮረጆ/ ከገለበጠ በኋላ ፋጋውን ነገ ሊመገበው በሚፈልገው የመቁኑን ዝርዝር ውስጥ አስቀምጦ ይሔዳል።

የአንድ መነኩሴ ከፍተኛው የድርጎ መጠን ኩርማን ነው። ንፍሮ በሚኖር ቀን ደግሞ ከፍተኛው የድርጎ መጠን ኩርማን ከንፍሮ ይሆናል ማለት ነው። ምንም እንኳ በገዳሙ የሚመረቱ አትክልቶች ብዙ ጊዜ/እንዲህ ስለሚታመን/ ለገበያ የሚቀርቡ ቢሆንም አልፎ አልፎ ከምግቡ ጋር ይቆነንላቸዋል። አንድ መነኩሴ የሰይጣን ፈተና ባደረበት ጊዜ ማለትም ሰይጣን ምግቡን ከሰውነቱ በሚወስድበት ጊዜ ኩርማን ከንፍሮ በላይ ሊሰጠው ይችላል። ይህም የሚሆነው በመነኩሴው የአንሶኛል ጥያቄ መሠረት ነው። መጋቢውም አንድ ጊዜ፣ ሁለት ጊዜ፣ ሦስት ጊዜ ይሰጠውና ወደ ቀድሞው ሁኔታ ካልተመለሰ ፀሎተ እግዝእትነ ማርያም ይደገምለት በማለት አዝዞ ያሰናብተዋል።

የተግባር ቤቱን መኮሬታ /እንጀራ/ የሚቀርሰው በመጋቢነት የተሾመው መናኝ ብቻ ነው። ይህም የሆነው ቁርሶ እንዲመገብ ፤ ቀዶ እንዲያለብስ ማህበሩና ፍትሐ ነገስቱ ያዘዘው በመሆኑ ነው። የአቀራረሱም ቅርፅ ቀደም ብሎ ከተገለፀው ውጭ መቁረስ የተከለከለ ነው። ይህንን መኮሬታ ለሱባኤም ሆነ ለጉብኝት የሚመጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ሊመገቡ ቢፈልጉ ይፈቀድላቸዋል። በተግባር ቤት ብዙ ጸሎት ስለሚደረግበት ሰዎች በዚህ ገዳም የሚዘጋጀውን መኮሬታ ሲመገቡ የታመሙት ተሽሏቸው፣ የተጨነቁት ተረጋግተው፣ ያዘኑት ተፅናንተው እንደሚመለሱ መረጃ ሰጪዎቹ ይመሰክራሉ። በዚህ ቤት የሚገኘው አመድም እምነት ይሆናል። አንዲት ሴት ይህንን ዳቤ በልታ ወንድ ልጅ እንደወለደችና ስሙንም እስጢፋኖስ ብላ እንደ አወጣችለት እዚህ ድረስ በመምጣት መስክራለች። እንዲሁም ባህር ዳር ሆስፒታል

የምትሰራ ነርስ ይህንን ዳቤ በልታ ከኩላሊት በሽታ እንደተፈወሰች ከዚህ ገዳም የኩላሊት በሽታ ታመው ወደ ባህር ዳር ሆስፒታሉ ለሄዱት አባ ካሳ ለተባሉ አባት ተናግራለች። እሷም እነሀን አባት ካከመቻቸው በኋላ መድሀኒቱንና የተረፋትን የገዳሙን ድርቆሽ ጭምር እንደሰጠቻቸው ይወራል። ይሁን እንጂ የገዳሙ ምግብ ከዳጉሳ የሚዘጋጅ በመሆኑና ወጡም የጓያ በመሆኑ በዚህ ገዳም ብዙ መነኮሳት የሚሞቱት በኩላሊት በሽታ እንደሆነ ነግረውኛል።

ተግባር ቤት /ቤተእግዚአብሔር/ መንፈሳዊ ተግባራት የሚከናወንበት ቤት ነው። ጌታ የሐዋርያትን እግር አጥቦ እናንተም ለታናናሾቻችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው(ዮሐ፡13፣14-20) ባለው መሠረት እንግዳ ሲመጣ በዚህ ተግባር ቤት የሚያገለግሉ እኳል መጋቢዎች እግሩን ያጥቡታል። ለልዩ ልዩ ተልዕኮ ወደ ውጭ ሂደው የነበሩ መነኮሳት ሲመለሱም በዚሁ ክፍል እግራቸውን ይታጠባሉ። ከዚህ አኳያ ተግባር ቤት የወንጌል ቃል ወደተግባር የሚለወጥበት ክፍል ነው ማለት ይቻላል። በዚህ ክፍል መጋቢውና እኳል መጋቢዎች አቡነ ዘበሰማያትና ፀሎተ እግዝእትነ ማርያም ይደግሙበታል። በሰንበት ቀንና በሌሎች አበይት በዓላት ካህናት ያጥኑታል። ክብር ለሚገባው ክብር ስጡት በሚለው ቃል መሠረት ለዚህ ተግባር ቤት ትልቅ ክብር እንደሚሰጠው ግልፀውልኛል።

በዚህም ምክንያት "ይህች ቦታ የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ"(ዘፀ፡3፣5) የሚለውን የኦሪት ቃል መሠረት በማድረግ ወደተግባር ቤት ሲገባ ጫማ አውልቆ ክንብንብ አውርዶ ነው። በማንኛውም የገዳሙ ክፍል እንደማይደረግ ሁሉ ይህ ክፍልም ይበጥ ጨዋታና ፌዝ የሚነገርበት ቤት እንዳልሆነ አጥብቀው ይናገራሉ። ወደዚህ ቤት የሚገቡት መጋቢውና እኳል መጋቢዎች ብቻ ናቸው። ማህበረ መነኮሳቱ ለስራ ወይም ለሌላ ተግባር እንዲሁም እንግዶች መጐብኘት ቢፈልጉ የሚገቡት መጋቢው ሲፈቅድላቸው ብቻ ይሆናል። ተግባር ቤቱን ለመጠበቅ ተቆልፎ አያውቅም፤ ነገር ግን ማንም አይገባም። በተግባር ቤት በር ላይ ያለመጋቢው ፈቃድ መግባት ክልክል ነው የሚል ማስጠንቀቂያ ተጽፎ ይታያል።

በተግባር ቤት አበምኔቱ ለተለያዩ ተግባራት ሲመጡ የሚያርፉበት ወንበር አለ። ነገር ግን መጋቢውም አልፎ አልፎ ይቀመጥበታል። ቤተክርስቲያንና ፀሎተ ማዕድ ውስጥ እንደሚገኙት ወንበሮች ማንም እንዳይቀመጥበት የተከለከለ አይደለም ማለት ነው። በዚህ ቤት ውስጥ ከሸክላ የተሰሩና በቆዳ የተለበጡ የቅባት ማስቀመጫ ማሰሮዎች አሉ። ከትልልቅ የዛፍ ግንድ ተጠርበው የተዘጋጁ ለሊጥ ማቡኪያነት የሚያገለግሉ ገንዳዎችም ተቀምጠዋል። እነዚህ ትልልቅ ገንዳዎች በበዓላት ጊዜ እንግዳ ሲበዛ ብቻ አገልግሎት ላይ ይውላሉ። ወደፀሎት

ማዕድ የሚሄደው መሶበ ወርቅና ማንቆርቆሪያ ዘወትር በዚህ ቤት ውስጥ ነው የሚቀመጠው። በአጠቃላይ ለገዳሙ የሚያስፈልጉ ቁሳዊ ነገሮች ሁሉ በዚህ ተግባር ቤት ውስጥ ይገኛሉ። የሚበስሉት እህሎች፣ ሊጥ፣ መኮሬታ፣ ምጣዶች፣ ወጥ የሚሰራባቸው ብረት ድስቶች፣ ንፍሮ የሚቀቀልባቸው ጋኖች፣ ሊጥ የሚቦካባቸው ገንዳዎች፣ ገዳሙ ለዓመት ቀለብ የያዛቸው እህሎች፣ ልብሶች/ አቡጀዴዎች/ ምዕመናን ከውጭ ያበረከቷቸው ስጦታዎችና ማንኛውም ዓይነት አላቂ ንብረቶች በዚህ ተግባር ቤት ውስጥ ይገኛሉ።

ተግባር ቤት እውነተኛ የእግዚአብሔር ቤት ሆኖ እንዲታይ የተለያዩ መንፈሳዊ ተግባራት ሲፈፀሙበት ይታያል። ይህ ቤት ከቤተክርስቲያን ቀጥሎ ክብር ከሚሰጠው ከፀሎተ ማዕድ የማያንስ ክብር አለው። እንጓል መጋቢዎች እንደ ጸሪቀ መበለት ጋጋሪዎች መኮሬታውን ሲጋግሩ በፀሎትና በምህላ (አባ ጎርጎርዮስ፣ 1991፣ 143) ነው። ይሄ ፀሎትና ምህላ መኮሬታው ረድኤት በረከት እንዲኖረው ያስችላል ተብሎ ይታመናል። መኮሬታው ሲቆረስም፣ ሲቆነንም ሆነ ተቆንኖ ሲወጣ ይፀለያል። የመኮሬታው አቆራረስ የኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካህናት በቅዳሴ ወቅት ሲባርኩ የሚጠቀሙበትን አራት ማዕዘንንና ስምንት ንዑስ ማዕዘናትን የተከተለ መሆኑ በዚህ ቤት ያለውን መንፈሳዊ ተግባር ያጎላዋል። ይህም መሆኑ ይህ ተግባር ቤት እንደማንኛውም የማብሰያ ቤት ሳይሆን እግዚአብሔር ያለበት ቅዱስ ቤት አድርጎ የመቁጠር አዝማሚያ እንዳለ ያሳያል።

ይህንንም የበለጠ ለማስረጽ ለአምልኮ መፈፀሚያ በሚውሉ ቤቶች የሚፈፀሙ አንዳንድ መንፈሳዊ ተግባራት ይከወኑበታል። ከእነዚህም ውስጥ በገዳሙ የሚገኙ ካህናት በዕለተ ሰንበትና በበዓላት ቀናት ይህንን ተግባር ቤት ያጥኑታል። እንዲሁም እግዚአብሔር ለሙሴ ይሀች ቦታ የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ (ዘፀ 3÷5) ያለውን ትዕዛዝ መሠረት በማድረግ ወደዚህ ቤት የሚገባን ማንኛውም ሰው ጫማውን አውልቆ እንዲሆን ደንግገዋል። እንዲሁም ተግባር ቤት ጨዋታ ፌዝ የማይነገርበት ቤት መሆኑ ለገዳማውያኑ ቤቱ መንፈሳዊ ድባብ ያለው ሆኖ እንዲታያቸው ያደርጋል። ከዚህ ሌላም በቤተክርስቲያን ለቁርባን የሚሆነው ሕብስት ሲፈተት ቅድስቱ እንደሚዘጋው ሁሉ የገዳሙ መቁኑን ሲፈተትና ሲቆነን ተግባር ቤቱ ይዘጋል። ወደ ተግባር ቤቱ ከመጋቢውና ከእጓል መጋቢዎች ውጭ ያለ መጋቢው ፈቃድ ማንም ገዳማዊ እንዲገባ አይፈቀድለትም። ተግባር ቤቱ አይቆለፍም፤ ማንም ገዳማዊ ግን ለመግባት ድፍረት የለውም።

ቤተ እግዚአብሔር በሚል የሚጠራው ተግባር ቤት እንደስሙ የእግዚአብሔር ቤት ነው በሚል ስለሚታመንበት በውስጡ የሚከወነው ሥራ ሁሉ አድልዎ የሌለበት ነው የሚል እምነት ያሳድራል። መነኮሳት ሊመገቡት የሚፈልጉትን መጠን ያህል (የፍላጎት መጠኑ ገደብ ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) ማግኘት ስለሚችሉ፤ ድርጎው የሚሰፈርበት እቃና ሰፋሪው መናኝ አንድ መሆኑ፣ የመነኮሳት መቁኑን ማውጫ ፋጋዎች ተመሳሳይ በመሆናቸው ሰፋሪው የአንዱን ከሌላው ለመለየት አይችልም ተብሎ ስለሚታመን፣ የሚዘጋጀው መቁኑን አንድ አይነት በመሆኑና ሹም በመሆኑ ተለይቶ የጣፈጠ ምግብ ይዘጋጅለት ስለማይባል ተግባር ቤት አንዱን መናኝ ከሌላው የማይለይ ተደርጎ ይቆጠራል። በአልባሳትም በኩል እንዲሁ አንድ አይነት ልብስ፣ በቂ በሆነ ልክ፣ ያለ አድልዎ፣ ይከፋፈላል ተብሎ ይታመናል። አድሏዊነት አለመኖሩም ግጭት እንዳይፈጠር፣ የገዳሙ አንድነት እንዳይናጋ፣ የእኔ እበልጥ ስሜት እንዳይጎለብት፣ የግል ሀብት የማፍራት ፍላጎት እንዳይኖር፣ በአጠቃላይ ሰላም እንዳይደፈርስ ያግዛል ማለት ይቻላል።

ስለዚህ በተግባር ቤት ውስጥ የሚደረገው አምልኳዊ ስርዓት በገዳሙ ውስጥ ፍትሀዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል አለ የሚለውን እምነት የማጠናከር ተግባር አለው የሚል እምነት አለኝ። በተግባር ቤት ውስጥ የሚፈጸመው አምልኳዊ ስርዓት ተግባር ቤቱ የተቀደሰና እግዚአብሔር ያለበት ቤት እንደሆነ እንዲታመን አስችሏል። እግዚአብሔር ባለበትና በተቀደሰ ቤት የሚዘጋጅ ማንኛውም ምግብ ደግሞ እንዲሁ የተቀደሰና የተባረከ እንደሚሆን እንዲታመን ያደርጋል። በተቀደሰ ቤት የተቀደሰውን ስራ የሚያከናውኑት ገዳማውያንም የተቀደሱ በመሆናቸው እነሱ የሚያከናውኑት የሀብት ክፍፍል ፍጹም ፍትሐዊና የእግዚአብሔር እጅ ያለበት እንደሆነ እንዲታመን ያደርጋል። ይህ እምነት ከማህበረ መነኮሳቱ አዕምሮ ፀንቶ እንዲኖር ስለሚፈለግ ይመስላል ገዳማውያኑ በተግባር ቤት ዙሪያ ላለው ስርዓተ አምልኮ ተገዥ ናቸው። ማህበረ መነኮሳቱ በጋራ ሰርተው በጋራ የሚኖሩበት በመሆኑ ገዳሙ የአንድነት ገዳም ነው።ተግባር ቤት ገዳማውያን ለሥጋቸው ወጥተው ወርደው የሰሩት የሥራ ውጤት የሚቀመጥበትና የሚከፋፈልበት ቤት በመሆኑ በዚህ ቤት ዙሪያ የብክነት ወይም የፍትሐዊነት ሥጋት ቢፈጠር ማህበሩ ሰላማዊ የአንድነት ኑሮን ለመቀጠል ከማይችልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል። ስለዚህ በተግባር ቤቱ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳለበትና በዚህ ቤት የሚያገለግሉ ገዳማውያንም ቅዱሳን እንደሆኑ አድርጎ ማመን መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን ይህም በሀብታቸው ደህንነት ላይ ሥጋት እንዳይፈጠር የማድረግ ሙያ አለው ማለት ይቻላል።

### 5.1.3 በምርጫ ስዩማን የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች

ሰባቱ ስዩማን የሚባሉት የገዳሙ መንፈሳዊና ስጋዊ አስተዳዳሪዎች ናቸው። እነዚህ የገዳሙ አስተዳዳሪዎች / ወይም የገዳሙ የቦርድ አባላት ማለት ይቻላል/ በገዳሙ ማህበር ነፃ ፈቃድ የሚመረጡ አካላት ናቸው። ሰባት ስዩማን መሰየማቸው በእብራውያን ሰባት ቁጥር ፍጽምት የሆነች ቁጥር በመሆኗ የገዳሙ ስርዓትም ፍጹም የሆነ ህግን የተላበሰ መሆኑን ለማመልከት እንደሆነ ይናገራሉ። የሰባቱ ስዩማን የምርጫ ሂደት ምን እንደሚመስል ከማየታችን በፊት በቅድሚያ ሰባቱ ስዩማን የሚባሉት ማን ማን እንደሆኑ እንመለከት።

አንደኛው አበምኔት ወይም መምህር ይባላል። አበምኔት የገዳሙ የበላይ ኃላፊ ነው። "አብ" ማለት አባት ማለት ሲሆን "ምኔት" ማለት ደግሞ ገዳም ማለት ነው። ስለዚህ አበምኔት ማለት የገዳም አባት ማለት ነው። አበምኔት የገዳም የነብስና የስጋ አባት ሆኖ ገዳሙን በበላይነት የሚያስተዳድር ነው። ሁለተኛው መጋቢ ይባላል። መጋቢ በገዳሙ ውስጥ ከአበምኔቱ ቀጥሎ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው። ሁሉን የሚመግብ /አይንተ እግዚአብሔር/ እንደሚባለው ሁሉ መጋቢም ስለእግዚአብሔር ፋንታ ለማህበረ መነኮሳቱ ቁርሶ የሚመግብ ቀዶ የሚያለብስ ማለት ነው።

ሦስተኛው ደግሞ ገበዝ ይባላል። ገበዝ የሚባለው ለመንፈሳዊ አገልግሎት (በተለይ በገዳሙ ቤተክርስቲያን አካባቢ) የተመደቡት መነኮሳት ስራቸውን በትክክል ስለመስራታቸው የሚቆጣጠርና በጐደለ የሚሞላ ሹም ነው። እቃቤት የሚባለው አራተኛው ሹም ነው። እቃ ቤት በገዳሙ ውስጥ ያለውን መንፈሳዊና ስጋዊ ሃብቶች/ ቁሶች/ የሚጠብቅ ነው። አምስተኛው ተሿሚ ሊቀረድ ይባላል። ሊቀረድ ማለት የአርድዕት አለቃ ማለት ሲሆን በገዳሙ ውስጥ የሚወጡትን፣ የሚወርዱትን፣ እንጨት የሚቆርጡትን፣ እርሻ የሚያርሱትን መነኮሳት ሁሉ ለሥራ የሚያሰማራ ባለስልጣን ማለት ነው።

ሊቀአበው የሚባለው ደግሞ ስድስተኛው ሹም ሲሆን የአባቶች አገልጋይ ወይም የአበው አለቃ ማለት ነው። ሊቀአበው ማለት በደዌ ዳኛ፣ በአልጋ ቁራኛ በእርጅናና በድካም ያሉትን አባቶች ልብሳቸውን የሚያጥብ፣ ምግባቸውን የሚያዘጋጅ ወጥቶ ወርዶ የሚያገለግላቸው ማለት ነው። ሰባተኛው ደግሞ እኅል መጋቢ ይባላል። እኅል መጋቢ ማለት የመጋቢ ልጅ ወይም የመጋቢው ረዳት ማለት ሲሆን በተግባር ቤት ውስጥ እንጀራ በመጋገር፣ ወጥ በመስራትና ንፍሮ በመቀቀል የሚያገለግል ነው። ከእነዚህ ከሰባቱ ስዩማን ውጭ «አፈ.መምህር» የሚባል ሹም

አለ። አፈ መምህር መምህሩን ወክሎ ከመንግስት፣ ከቤተክህነትና ከምዕመናን ጋር የሚገናኝ ሲሆን በሰባቱ ስዩማን ውስጥ ግን አይካተትም።

እነዚህ ሰባቱ ስዩማን የየራሳቸው የስራ ድርሻ ያላቸው ሲሆን ምንም እንኳን ስራው ተደጋጋፊ ቢሆንም አንዱ የሌላውን ሥራ ተጋፍቶ አይሠራም። በገዳሙ ውስጥ አንዱ ሹም ከሌላው ጋር እንዴት ባለ መንገድ ግንኙነት ፈጥሮ ስምምነት ላይ እንደሚደርስ ለሌላው ሰው ግልጽ ባይሆንም በየእለቱ ጥብቅ የሆነ ግንኙነት አላቸው። ከዚህ ሌላ እነዚህ ስዩማን ጊዜ ወስነው የሚወያዩበት ሁኔታ አለ። እንዲሁም ማህበረ መነኮሳት በጠቅላላ ስለማህበሩ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች እና መፍትሔዎች የሚመክሩበት ጊዜ አላቸው።

ገዳሙን የሚያስተዳድሩት እነዚህ ሰባቱ ስዩማን እንዴት ባለ መንገድ እንደሚመረጡ ቀጥለን እንመልከት። በቅድሚያ የምንመለከተው የአበምኔቱን ምርጫ ይሆናል። ከሰባቱ ስዩማን የስድስቱ ስዩማን ምርጫ ተመሳሳይ በመሆኑ በአንድነት እንመለከተዋለን። የአበምኔቱ ግን የተለየ የምርጫ ሰርአት ያለው በመሆኑ ይህንን ለብቻ ለማየት እንሞክራለን።

### 5.1.3.1 በአበምኔት ምርጫ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች

አበምኔት ጌታ እነሆ በጎቼን፣ ግልገሎቼን፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ (ዮሐ፡21፣15-17) ብሎ ለቅዱስ ጴጥሮስ በተናገረው መሠረት አበምኔትም የገዳሙ የነብስና የሥጋ አባት ሆኖ ገዳሙን ይጠብቃል። መነኮሳቱም ይህንን አበምኔት ባገኙት ሰዓት ሁሉ ጉልበቱን፣ እግሩን ይስማሉ፤ መስቀሉን ይሳለማሉ። ቃሉን አቤት ወዴት ብለው ይሰሙታል። ከእሱ የወጣውን ቃል ሁሉ በተግባር ይፈጽሙለታል።

ከዚህ በፊት አበምኔት የነበሩት በእርጅና ወይም በህመም ምክንያት ማህበረ መነኮሳቱን ወጥተው ወርደው ማስተዳደር፣ ቀድሰው ማቁረብ፣ ሲያቅታቸውና "አባቶቼ የሰጣችሁኝን ኃላፊነት አስተላልፉልኝ" ብለው ማህበሩ ሌላ አበምኔት ሲመርጥ ለቀድሞው አበምኔት ሲደረግለት የነበረው አክብሮት አይጓደልበትም። እንዲያውም አዲሱን አበምኔት የሚሾሙ እሳቸው ሲሆኑ ስማቸውም ሳይወሰድባቸው መምህር፣ አበምኔት እየተባሉ ይጠራሉ። ከአዲሱ አበምኔት ቀጥሎ የራሳቸው ወንበር ያላቸው ሲሆን በክብር ከአዲሱ አበምኔት እኩል ናቸው። ፀሎት ሲደረግ የቀድሞው አበምኔት ካሉ የማሳረጊያ ፀሎቱን እንዲያደርሱ ቅድሚያ ለእሳቸው ይሰጣቸዋል። የቀድሞው አበምኔት ቀዳሚ ልምድ ስላላቸው አዲሱን ተሿሚ አበምኔት በሥራ፣

በፀሎት ያግዟቸዋል። ሥራው ከባድ በመሆኑ በቸገራቸው ጊዜ ይረደቸዋል፤ በድካማቸውም ሰዓት ያበረታቷቸዋል።

በሰባቱ ስዩማን ላይ ሙሉ ስልጣን ያለው ማህበሩ ነው። ማህበሩ ይሾማል፣ ያነሳል፣ ያባርራል፣ ያስራል። ማህበሩ አበምኔቱን ማውረድ ይችላል። ነገር ግን አበምኔቱ ጥፋት ቢገኝባቸው እንኳ እንደሌሎቹ ስድስቱ ስዩማን አያስራቸውም። ለክስም አይቀርቡም፤ ለተግሳጽም አይዳረጉም። አበምኔቱ ቢያጠፉ ከኃላፊነታቸው ሊነሱ ይችላሉ። ይህንንም ለማድረግ ቀስ ብሎ "አባታችን ደክሞዎታል፣ ዳዊት ይድገሙ፣ ማህበሩን በፀሎት ያገልግሉ" ይባላሉ እንጂ ኃይል ያለው ንግግር እንኳ መናገር ክልክል እንደሆነ ገልፀውልኛል።

ገዳሙ አዲስ አበምኔት በሚመርጥበት ጊዜ ጉዳዩን በምስጢር ነው የሚያከናውነው። በቅድሚያ ከሰባቱ ስዩማን ስድስቱ በገዳሙ የሚገኙ አበው መነኮሳትን ጨምረው ገዳሙን የሚያስተዳድሩ እጩ አበምኔት በምስጢር ይመርጣሉ። ምርጫቸውንም ከተመራጩ መነኩሴ ውጭ ለማህበሩ ያሳውቁና በማህበሩ አመኔታ ሲያገኝ እንቅስቃሴው በምስጢር ይቀጥላል። ይሄ ሁሉ ሥራ ሲከናወን በእጩነት የተመረጡት አበምኔት በፍጹም አያውቁም። እንዲህም የሚደረግበት ምክንያት አበምኔትነት ትልቅ ኃላፊነት ከመሆኑ ባሻገር የከፋ ፈተና ስለሚያጋጥም ተሿሚው ሹመቱ አይገባኝም ብለው ገዳሙን ጥለው እንዳይሰደዱ ወይም ራሳቸውን አረጋግተው ለመኖር እንዳይቸገሩ ነው።

ሹመቱ የተያዘለት ጊዜ አንድ እሁድ ብቻ ሲቀረው እጩው አበምኔት ለተልዕኮ /ለሥራ ጉዳይ/ ከገዳሙ ውጭ ይላካሉ። አንድ አበምኔት ሲሾም የክብረ በዓል ያህል ትልቅ ድግስና ዝግጅት ስለሚደረግ እሳቸው በሌሉበት መሰናዶው ይደረጋል። በዚህ የሹመት በዓል ከገዳሙ ውጭ ያሉ የሀገሩ ባላባቶች እንዲገኙ በምስጢር ጥሪ ይደረግላቸዋል። መጋቢውና እጓል መጋቢዎች እንዲሁም የተለያዩ አርድእት የድግሱን መሰናዶ አዘጋጅተው ይጠባበቃሉ።

የአበምኔት ሹመት የሚሰጠው በሰንበት ቀን ነው። እጩው አበምኔት ከተልዕኳቸው ሲመለሱ ቀዳሽ /ሰሞነኛ/ መሆናቸው ይነገራቸውና የዕለቱን ቅዳሴ እንዲቀድሱ ይደረጋል። በዚህም የሰንበት ቀን ሁሉም ገዳማውያን ስለሚገኙ ቤተክርስቲያኑ በማህበረ መነኮሳቱ ይሞላል። ቅዳሴውም እንዳበቃ መነኮሳቱ ሁሉ ወደ ቅድስቱና ቅኔ ማህሌቱ ገብተው ይቆማሉ። በኋላም ቤተክርስቲያኑ ይዘጋል።

በመቀጠል መጋቢው በቅድስቱ መካከል ቆሞ ሦስት ጊዜ ያጨበጭባል። ከዚያም «የመከርነው ምክራችን ምክራችን ነው፤ የመከርነው ምክራችን ምክራችን ነው፤ የመከርነው ምክራችን ምክራችን ነው፤» ሲል መነኮሳቱም መጋቢውን እየተቀበሉ እነሱም ይላሉ። «የሥላሴ ባለተስፋ፣ የሥላሴ ባለተስፋ፣ የሥላሴ ባለተስፋ፣ አባ እገሌ የገዳሙ አበነፍስ ወሥጋ እንዲሆኑልን ማህበር ሙቱልን ብሏል» ብሎ ይናገራል። በዚህ ጊዜ ተሿሚው አበምኔት ወደመቅደሱ ዘለው እንዳይገቡ ካህናቱ መንገዱን ዘግተው ቆመዋል። ወደ ቅድስቱም እንዳይወጡ ማህበረ መነኮሳቱ ሁሉ ከቦ ስለቆመ አማራጭ አይኖራቸውም። አይሆንልኝም እንኳ ቢሉ ማህበር ሙቱልኝ ስላለ ምንም አይነት ምክንያት ማቅረብ አይችሉም።

መቼም በፃድቁ ወንበር ላይ መቀመጥ ስለሚከብዳቸው እምቢ ይላሉ። ፈቃደኛ ከሆኑ በቀጥታ ሄደው በመንበሩ ላይ ይቀመጣሉ። ፈቃደኛ ካልሆኑ ግን ካህናቱ በግዴታ ተሸክመው በመንበሩ ላይ ያስቀምጧቸዋል። አንዴ በመንበሩ ላይ ከተቀመጡ በኋላ ግን መነሳት ክልክል ስለሆነ ቁጭ ይላሉ። በዚህ ጊዜ ወዲያው መነኮሳቱ ካባ አምጥተው ያለብሷቸዋል። የቀድሞው አበምኔት ካሉ/ካላረፉ/ ካባቸውን ያለብሷቸዋል። የእጅ መስቀላቸውንም ይሰጧቸዋል። ጥምጥሙንም ይጠመጥሙላቸዋል። የሚያስፈልገውን ሁሉ ካሟሉላቸው በኋላ ሦስት ዲያቆናት ፊት ለፊት ይቆማሉ። አንዱ ዲያቆን መፆሩን ይዞ "እስመ መምህረ ሕግ ይከውን በረከተ የሐውር እመኃይል ውስተ ኃይል ወይሰተርዕዮ አምላክ አማልክት በፅዮን" ብሎ ይሰብካል። ከዚያም አበምኔቱ ቀዳሽ ከሆኑ ወንጌሉን በዜማ ይሉና የዮሐንስ ወንጌል "እኔ ቸር እረኛ ነኝ፤ ቸር እረኛ ስለበጎቹ ራሱን አሳልፎ ይሰጣል"(ዮሐ.10፣11) የሚለውን ያነባሉ። ይህም ቸር እረኛ እንጂ ምንደኛ/ደመወዝተኛ/ አይደለሁም የሚል ቃል ኪዳን ነው። ጌታ ስለሰው ልጆች በቀራንዮ አደባባይ በመስቀል ተሰቅሎ ሰውን እንዳዳነ ሁሉ አበምኔቱም ስለ ክርስቶስ ፍንታ/አይንተ ክርስቶስ/ ለገዳሙ በሥጋ በነብስ ለመሞት ቃል ገብተው የገዳሙ አበነብስ ወሥጋ ይሆናሉ።

ከዚህ በኋላ ማህበረ መነኮሳቱ ሁሉ ከካህናቱ ጀምሮ በማዕረግ በማዕረጋቸው ተሰልፈው የአበምኔቱን እግር ይስማሉ። መስቀሉንም ይሳለማሉ። ከዚያም በካህናቱ ታጅበው ወደተዘጋጀው የግብር አዳራሽ ይገባሉ። ማህበረ መነኮሳቱም ቀኑን ሙሉ በደስታ ይውላሉ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለአበምኔቱ አንድ ረድ/ረዳት/ ከዲያቆናቱ መካከል ይሰየምላቸዋል።

አንድ አበምኔት አበምኔት ለመሆን በቅድሚያ የክህነት ማዕረግ ሊኖረው ይገባል። ይህም ብቻ በቂ አይደለም። ከዚህ በላይም የቁምስና ማዕረግ ሊኖረው ያስፈልጋል። ምክንያቱም ምንኩስና ለመስጠትና በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ትእዛዝ በገጠር የሚገኙና ብዙ ውጣ ውረድ ያለባቸውን አድባራት የመባረክ ሥራ ለመሥራት የቁምስና ማዕረግ ሊኖረው የግድ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ውጭ ግን ያለው እውቀት ስፋትና የዘር ሁኔታ አበምኔትነት አያስመርጠውም። ሰውን በተግባር ሊያስተምር እና ሊለውጥ የሚችለው ሥነ ምግባር በመሆኑ በገዳም ውስጥ አበምኔት ሆኖ ለመመረጥ የሥነ ምግባር መልካምነት ትልቅ ዋጋ እንደሚሰጠው ነግረውኛል።

አበምኔቶች ብዙ ጊዜ የማህበሩን ፈቃድ መቃወም ስለሚከብዳቸው እንጂ በምርጫው ደስተኛ አይሆኑም። ለዚህም ምክንያቱ የዲያብሎስ ፈተና የገዳምን አስተዳደር ከባድና ውስብስብ ስለሚያደርገው እንደሆነ ገልፀውልኛል። ስለራስ ከማሰብ አልፎ ስለ መቶና መቶ ሃምሳ መናኝ ማህበራዊ፣ መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወት ማሰብ ከባድ ነው። በተጨማሪም ለዘመናት ሲጠበቁ የኖሩ ሃገራዊ ቅርሶችን ለቀጣዩ ትውልድ በጥንቃቄ ለማስተላለፍ ኃላፊነት መሸከም ትልቅ ፈተና ነው። እንዲሁም የገዳማውያን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ማሰብና መሥራት ትልቅ ጭንቀት ይፈጥራል። የገዳሙን አባላት ንስሃ መቀበልና ቀኖና መስጠት እንዲሁም ስለ እነሱ ቀኖና መቀበል ሌላው ተግዳሮት/Challenge/ ነው። በአጠቃላይ በመንፈሳዊ ሕይወት፣ በሥራ ትጋትና ጥራት እንዲሁም ያለምንም ጥቅም ኃላፊነትን የመሸከም አርአያ መሆን ትልቅ መከራ በመሆኑ ሁሉም አባቶች አበምኔትነትን በእጅጉ ይፈሩታል ብለውኛል።

እንግዲህ ቀደም ሲል እንደተገለጸው አበምኔት የገዳሙ የሥጋና የነፍስ አባት ወይም አስተዳዳሪ ናቸው። አበምኔት የእግዚአብሔርን መንጋ የሚጠብቁ(1ኛ ጴጥ 5፥2) እረኛ በመሆናቸው በገዳሙ ትልቅ ክብር ይሰጣቸዋል። እረኝነት የክርስቶስ፣ መንጋ ደግሞ የሕዝብ ተምሳሌት ነው። በመሆኑም የገዳሙ ማህበረሰብ አበምኔቱን እንደ እውነተኛው እረኛ በመቁጠር በፍጹም ትህትና እና አክብሮት ይታዘዙላቸዋል። አበምኔቱ ቢያጠፉና ማስተዳደር ባይችሉ እንኳን ማህበሩ በፍጹም ትህትና ከስልጣናቸው እንዲወርዱ ሊያደርግ ይችላል እንጂ ሊወቅሳቸው እና ሊከሳቸው አይችልም። ፍትሐ ነገስት ከወንድሞች ወገን ለመማታት በአበምኔቱ ላይ እጁን የዘረጋን ሁሉ አርባ ግርፋት ይግረፉት፤ ወደ ሌላ ገዳምም ይሰደድ (ትንሣኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣1990፣119) ይላል። በጎች የእረኛውን ትእዛዝ አክብረው እንደሚንቀሳቀሱ ሁሉ ገዳማውያንም የአበምኔቱን ትእዛዝ በአክብሮት ይፈጽማሉ። የተሻሩት አበምኔትም ማዕረጋቸው ሳይወሰድ፣ አክብሮቱ ሳይጓደልባቸው ተሰሚነታቸው

ሳይቀንስ በገዳሙ ውስጥ እንዲኖሩ ይደረጋሉ። እንዲህ አይነቱ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በገዳሙ ውስጥ ሰላም እንዳይደፈርስ ትልቅ ዋጋ አለው ማለት ይቻላል።

የአበምኔት ክብር ከክርስቶስ ተምሳሌትነት አኳያ የሚመነጭ መሆኑን ተመልክተናል። በእረኝነት የክርስቶስ ተምሳሌት በሆኑት በቀደሙ የአበምኔቶች ወንበር ላይ መቀመጥ ትልቅ ክብር በመሆኑ ይህ ክብር አይገባኝም በሚል ብዙዎች የአበምኔትነትን ሹመት ይፈሩታል። በቤተክርስቲያኑና በፀሎተ ማዕዱ በሚገኙ አበምኔቱ በሚቀመጡባቸው ወንበሮች ላይ እነሱ ባይኖሩ እንኳ ሌላ ሰው አይቀመጥባቸውም። እነዚህ ወንበሮች ታላላቅ የሚሏቸው ቅዱሳን አበምኔቶች እንደተቀመጡባቸው የሚታወቅ በመሆኑ ተመራጩ አበምኔት በነዚህ ወንበሮች ላይ መቀመጥ ይፈራል። በገዳሙ መስራች በአባ ሂሩተ አምላክ ወንበር ላይ መቀመጥ ማንም ገዳማዊ ያስፈራዋል። ማህበሩ መርጦ በእነዚህ ወንበሮች ላይ ካስቀመጠው በኋላ ግን በራሱ ፈቃድ ከወንበሩ /ከስልጣኑ/ መውረድ አይችልም። ፍትሐ ነገስት መናኝ የአበምኔትነት ሹመት መውደድ አይገባውም፤ የሹመት ፍቅር ሰይጣናዊ በሽታ ነው((ትንሣኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣1990፣ 115) ስለሚል ወይም ማስተዳደር ከባድ በመሆኑ አበምኔትነት በፈቃደኛነት አይሾሙም። ለዚህም ይመስላል በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የአበምኔትነት ምርጫ በምስጢር የሚያዘው።

አበምኔቱ የሥጋም የነፍስም አባት በመሆናቸው ሁሉም ገዳማውያን ገና ወደ ገዳሙ ከመግባታቸው በፊት የሰሯቸውን ኃጢአቶች በሙሉ ዘርዝረው ይነግሯቸዋል። በገዳሙ የሚኖሩ አባቶች በሃሳብም፣ በንግግርም፣ በድርጊትም የሰሯቸውን የሥጋም ሆነ የነብስ ጥፋቶች /ኃጢአቶች/ የሚናዘዙት ለገዳሙ አበምኔት ነው። አበምኔቱ የሚያስተዳድሩት ገዳማዊ በሃሳብ፣ በንግግር፣ በድርጊት፣ የፈፀመውን ጥፋት ሁሉ በዝርዝር ማወቅ መቻላቸው አስተዳደራዊ ሥራቸውን ሳያቀልላቸው አይቀርም የሚል ግምት አለኝ። ምክንያቱም የልቡን ሃሳብ ሁሉ በዝርዝር የሚያውቁትን ሰው መምራት ውስብስብነቱን ያቀለዋል። ኃጢአቱንና ጥፋቱን ለአለቃው /ለመሪው/ የሚናገርም መናኝ ፀጥ ለጥ ብሎ ለመገዛት /ለመመራት/ ምቹ ነው። የዘረጉት ሰፊ የደህንነት መዋቅር አልበቃቸው ብሎ በሕዝቡ ልብ ውስጥ የሚታሰበውን ሃሳብ ማጋለጫ መሳሪያ ቢኖር መትከል ለሚያምራቸው የአፍሪካ መሪዎች የዚህን ሃይማኖታዊ ስርአት ቢያውቁ ምን ያደርጉ ይሆን የሚል ጥያቄ ይፈጥራል።

### 5.1.3.2 በስድስቱ ስዩማን ምርጫ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች

የገዳሙ አስተዳዳሪዎች ሰባት ስዩማን መሆናቸውን ቀደም ሲል ገልጫለሁ። ከሰባቱ ስዩማን መካከል የአበምኔቱ የምርጫ ሂደት ከሌሎች ስዩማን ምርጫ የተለየ በመሆኑ ነጥዬ ለማሳየት ሞክሬአለሁ። በመቀጠል የስድስቱ ሹማምንት የምርጫ ሂደት ምን እንደሚመስል እንመልከት።

በዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም ውስጥ ስድስቱ ስዩማን በማንኛውም ቦታና አዳራሽ እንዲሁም በአንድ ግለሰብ ጠቋሚነት አይመረጡም። የስድስቱ ስዩማን ምርጫ በቦታ ደረጃ ከፀሎተ ማዕድ ውጭ አይከናወንም። ምርጫውም የሚከናወነው በማህበር እንጂ በግለሰብ ጠቋሚነት አይደለም። ፀሎተ ማዕድ ከሌሎች ቦታዎች ተመራጭ የሆነበት ምክንያት ማህበሩ በማህበር ፀሎት የሚፀልይበት በመሆኑና ክቡር የሆነው ሕብስት የሚፈተትበትና ጽዋው የሚቀዳበት ቤት በመሆኑ እንደሆነ ይናገራሉ። የእነዚህ ስዩማን የምርጫ ሂደት ምን እንደሚመስል በመቀጠል እንመልከት።

በቅድሚያ የገዳሙ መጋቢ ማህበረ መነኮሳቱ በተሰበሰቡበት ፀሎተ ማዕድ ውስጥ በመካከል ላይ በመቆም የሹመቱን አይነት ገልፆ ዛሬ ባለተስፋ እንመርጣለን ብሎ ያሳውቃል። ሁሉንም ስዩማን የሚያስመርጠው መጋቢው ነው። የሚሾሟቸው ግን አበምኔቱ ናቸው። ቀጥሎም መጋቢው አበምኔቱ በተቀመጡበት መንበር ላይ እንዳሉ ከጎናቸው ሁለት ካህናት ይጨምርላቸውና ሦስት ሆነው እንዲቀመጡ ያደርጋል። ከዚያም በመቅደሱ ያሉ መነኮሳትና በቅድስቱ ያሉ ጥቁር ራሶች ሁሉም ሦስት ሦስት ሆነው መቀመጣቸውን ካረጋገጠ በኋላ አሁን የሚመረጠው ባለተስፋ /አንዱን የሹመት ዓይነት ጠቅሶ/ ምሳሌ «ሊቀ አበው ነው» ይልና «መክራችሁ ጠብቁኝ» ይላል።

በመጀመሪያ መጋቢው ወደ አበምኔቱና ከእሳቸው ጋር ወደተቀመጡት ካህናት ጠጋ ብሎ አባቶቹ ለሊቀ አበውነት የሚሆነው ባለተስፋ ማን ይሁን ብሎ ይጠይቃቸዋል። አበምኔቱም አብረዋቸው ከተቀመጡት ካህናት ጋር መክረው የተስማሙበትን የአንዱን መናኝ ስም ጠቅሰው እሱ ይሁን ብለው ይነግሩታል። በመቀጠልም መጋቢው ሦስት ሦስት አድርጎ ያስቀመጣቸውን እያንዳንዱን መነኮሳት ጠይቆ ሃሳባቸውን ከተቀበለ በኋላ የማን ድምጽ እንደበዛ ያረጋግጥና ለሁለተኛ ጊዜ ይጠይቃቸዋል። በሁለተኛ ጊዜ ጠይቆ አሁንም ከመጀመሪያው ድምጽ ጋር አነፃጽሮ ሲጨርስ ለሦስተኛ ጊዜ እየዞረ ይጠይቃቸዋል። መጋቢው ሦስት ጊዜ እየዞረ መጠየቁ

የሥላሴ የአንድነትና የሦስትነት ምሳሌ እደሆነና አንድ ምክር በሦስት ጊዜ መጽናቱን ለማመልከት መሆኑን ገልፀውልኛል።

ከዚያም መጋቢው ወደ አበምኔቱ ተጠግቶ «ማህበረ መነኮሳቱ ይህን ያህሉ እገሌን፣ ይህን ያህሉ እገሌን፣ ይህን ያህሉ ደግሞ እገሌን መርጠዋል» ብሎ ዝርዝሩን ይነግራቸዋል። አበምኔቱም በብዙ ቁጥር የተመረጠውን አይተው እገሌ ይሁን ብለው ይነግሩታል። መጋቢውም መሐል ቦታ ላይ ይቆምና ሦስት ጊዜ ያጨበጭባል። ቀጥሎም «የመከርነው ምክራችን ምክራችን ነው፤ የመከርነው ምክራችን ምክራችን ነው፤ የመከርነው ምክራችን ምክራችን ነው» ሲል ማህበረ መነኮሳቱ መጋቢው የሚለውን እየተቀበሉ እነሱም ይደግማሉ። ከዚያም «የሥላሴ ባለተስፋ፣ የሥላሴ ባለተስፋ፣ የሥላሴ ባለተስፋ አባ እገሌ ሊቀአበው እንዲሆኑልን ማህበር ሙቱልን ብሏል» ይላል። በኋላ መጋቢው ወደተመረጡት መነኩሴ በመሄድ አባታችን ይነሱ ፀሎት ይቀበሉ ይላቸዋል። እሳቸውም ተነስተው አባቶቼ ያላችሁኝን እቀበላለሁ ካሉ ማህበረ መነኮሳቱ ሁሉ ይነሱና አበምኔቱ ፀሎተ ማርያም፣ አቡነ ዘበሰማያት ደግመውና መርቀው ይሾሟቸዋል። ተመራጩም አባት የአበምኔቱን ጉልበት ከሳሙ በኋላ ዙሪያውን የቆሙትን መነኮሳት ሁሉ ጉልበታቸውን ስመው ሹመታቸውን ይቀበላሉ።

ከዚህ በተለየ ሁኔታ ተመራጩ መነኩሴ በሽታ አለብኝ ወይም አቅም የለኝም ብለው ሹመቱን አልቀበልም ቢሉ ማህበረ መነኮሳቱ «የመረጥንዎት እኛ ብንሆንም የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በመሆኑ ምርጫውን ይቀበሉ» በሚል ያስገድዳቸዋል። «ቀን ተሹሞ ማታ መውረድ ይቻላል፤ ስርዓቱን መቀበል ግን ግዴታ ነው» ይባላሉ። በመጀመሪያ ወደ ገዳሙ አንድነት ሲገባ «ነብሴን ለስላሴ ስጋዬን ለማህበር ሰጥቻለሁ» በሚል ቃል ኪዳን ስለሚገባ ማህበሩ «በቃል ኪዳንህ መሰረት ስጋህን ልጠቀምበት እፈልጋለሁ» ብሎ ሲጠይቅ እምቢ አይባልም። ምንም እንኳ እጅ እንደሌለው እየታወቀ እንዲቆፍር ሊጠየቅ ባይችልም እንዲሰራ ቢመረጥ ግን እምቢ ማለት አይችልም። በዚያ ቦታ የሚሰጠውን ትዕዛዝ አልቀበልም ማለት ቃል ኪዳኑን እንዳፈረሰ ይቆጠራል። ማድረግ የሚችለው ሥራውን ሞክሮት እንዳልቻለ በመግለጽ ማህበረ መነኮሳቱ የሰጡትን ሹመት እንዲያወርዱለት መጠየቅ ብቻ ነው።

ማህበረ መነኮሳቱ በተመረጡበት የሥራ መስክ የግድ መሰማራት ይኖርባቸዋል። አልሰራም ማለት ፍፁም የማይቻል ጉዳይ ነው። አንድ መናኝ ፈቃደኛ አይደለሁም ቢል በራሱ ፈቃድ ከማህበሩ ውጭ ሆነ ማለት ነው። ፍፁም ከአዕምሮዬ በላይ ስለሆነ አልሰራም በሚል ምርጫውን

ቢቃወም ማህበረ መነኮሳቱ «ስርዓት አንሳ» ይሉታል። (ስርአት አንሳ ማለት የማህበሩን ቃል አላከበርክምና ቅጣት ይገባሃል ማለት ነው) እሱም ሥራውን ለመሥራት ካልፈቀደ «ስርዓት አነሳለሁ» ይላል። ማህበረ መነኮሳቱም ፍፁም አያልፉትም። ተገቢ ነው ያሉትን ቅጣት እንደሚወሰኑበት ገልፀውልኛል።

እንግዲህ የስድስቱ ስዩማን ምርጫ የገዳሙ አበምኔት ባሉበት በፀሎተ ማዕድ ውስጥ ይከናወናል። ይህንን ምርጫ በሌላ ቦታ ማከናወን አይቻልም። ምክንያቱም ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ፀሎተ ማዕድ የተቀደሰ ቦታ በመሆኑ ነው። ገዳማዊያን ይህንንም ምርጫ በዚህ በተቀደሰ ቤት ውስጥ ማከናወን የሚፈልጉት ጸሎተ ማዕዱ ክንውኑን ወይም ድርጊቱን መንፈሳዊ ፀጋ ያለው እንዲሆን ያደርገዋል በሚል ስለሚያምኑበት ይመስለኛል። ለዚህ ምርጫ የተቀመጡ ማህበረ መነኮሳት በቦታው ቅድስና እና በሚመገቡት ሕብስት ቅድስና ምክንያት እነሱም የተቀደሱ እደሆኑ አድርገው ሊያምኑ ይችላሉ። ስለሆነም የተቀደሰ ማህበር የሚወሰነው ውሳኔ ሁሉ የተቀደሰ ውሳኔ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። የተቀደሰ ውሳኔም አይጣስም። ምክንያቱም ማህበሩ ቢወስንም ይህንን የውሳኔ ሃሳብ ያቀበላቸው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ስለሚታመን ነው።

ማህበረ መነኮሳቱ አንድ ተሿሚ ለመምረጥ እንደ ማዕረጋቸው ቅደም ተከተል ሦስት ሦስት ሆነው ይቀመጣሉ። ይህም የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ለመግለጽ ሲሆን በምርጫውም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሳተፉበት ለማሳመን ነው። ማህበሩ ሦስት ጊዜ መክሮ መወሰን መቻሉ ውሳኔው የፀናና የማይለወጥ መሆኑን ለማሳየት ነው። ገዳማውያን ተመራጮች ይህንን ጽኑ ውሳኔ "አቅም የለኝም፣ አይሆንልኝም" በሚል ሊቃወሙት አይችሉም። አንድም ይህ ምርጫ በአብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድና ትዕዛዝ የተፈፀመ ነው በሚል ስለሚታመን ይህንን መቃወም አይቻልም። በሌላም መንገድ ማህበሩ የጠየቀው "ለዚህ ማህበር ሲሉ ሙቱልን" የሚል ጥያቄ በመሆኑ "አቅም የለኝም" የሚለው ምላሽ "ከሙቱልኝ" ጋር ሲነፃፀር በጣም የቀላል ነው። ማህበሩ የሰጣቸው ሹመት እስከ ሞት እንኳ የሚያደርስ ቢሆን እሱን አድርጉልን የሚል ጥያቄ እያቀረበ በመሆኑ ለማህበሩ ተገዥ ነኝ የሚል ሁሉ የሚሰጠውን ሹመት ለመቀበል አያንገራግርም። ዋናው ጉዳይ ለማህበሩ ሕግ ተገዥ መሆን ግዴታ በመሆኑና ገዳማውያን ይሄ ስርአት ለአንድነታቸው በእጅጉ ስለሚያስፈልጋቸው ሁሌም ተጠብቆ እንዲኖር ይፈልጋሉ።

በአጠቃላይ የስዩማን ምርጫ የእግዚአብሔር ምርጫ እደሆነ ተደርጎ እዲታመን መደረጉ በገዳሙ ውስጥ የስልጣን ሽኩቻ እንዳይፈጠር የማድረግ ተግባር አለው የሚል እምነት አለኝ። የስዩማኑ ምርጫ በገዳማውያን ምክር የሚፈጸም ቢሆንም በምክሩ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሳተፍበት ያምናሉ። በመንፈስ ቅዱስ የተመረጠ ማንም ገዳማዊ ምርጫውን መቃወም አይችልም። በመንፈስ ቅዱስ የተሾመን ገዳማዊ ቦታውን አይመጥንም በሚል ሊቃወም የሚችል ድፍረት ያለው ገዳማዊም አይኖረውም። የሚሾመውም ሆነ ያልተሾመው ገዳማዊ ሁልጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ስራና ምርጫ እየተገረመ ምረጫውን መቀበል መቻሉ በገደሙ ውስጥ በስልጣን ሽኩቻ ምክንያት የሚከሰት አለመግባበት እዳይፈጠር ማድረግ ይችላል የሚል እምነት ያሳድራል።

## 5.1.4. ጥፋትን በማረም /ኃጢአትን በማንጻት/ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች

በዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም ውስጥ የሚኖሩ መናኞች ጥፋት በሚፈፅሙበት ጊዜ የተለያየ ቅጣት ይቀበላሉ። እንደ ጥፋቱ አይነት ሁሉ የቅጣቱም አይነት የተለያየ ነው። ቀላል የሚባል ጥፋት ያጠፋ መነኩሴ በመጀመሪያ እንዲመከር ይደረጋል። ከጥፋቱ ካለተመለሰ መጋቢው በራሱ ፈቃድ ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ያስረዋል። ከዚህ በኋላ ግን በማህበረ መነኮሳቱ ፊት ቀርቦ ይፈረድበትና ይታሰራል። ከእስራቱ በኋላ ከጥፋቱ ካልተመለሰ ከገዳሙ እንዲሰደድ/እንዲባረር/ ይደረጋል።

በገዳሙ ውስጥ ሌሎች ተጨማሪ የቅጣት ዓይነቶችም አሉ። ከእነዚህም ውስጥ የሥራ ቅጣት አንዱ ነው። ይህም ሸክም፣ እንጨት ፈለጣ፣ ቁፋሮና የተለያዩ ሥራዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ ሌላ የፆም፣ የፀሎት፣ የስግደት ተግሳጽ/ቅጣት/ የሚፈረድባቸው አሉ። የሚፈቀድለትን መቁኑን /ድርጎ/ ቀንሶ መስጠትም ሌላው የቅጣት ዓይነት ነው። ከዚህ ሌላ ቤት ተዘግቶባቸው እንዲጸልዩ የሚፈረድባቸው አሉ። በዚህ ፍርድ አንዳንዶቹ መልካም ትሩፋት አግኝተውበት በዚያው ዘግተው የሚቀሩ አሉ። በገዳሙ ውስጥ እነዚህን ቀላል የሚባሉ የቅጣት አይነቶች ተቀጥቶ ያልተመለሰ ጥፋተኛ ቀጥሎ የሚጠብቀው እስራት ነው። ሁለት የእስራት አይነቶች አሉ። አንደኛው የፈቃድ እስራት ሲባል ሌላው ደግሞ በማህበረ መነኮሳቱ ፍርድ የሚፈፀም እስራት ነው።

የፈቃድ እስራት የሚባለው አንድ መነኩሴ ጥፋት እያጠፋ እያለ ወዲያው መጋቢው ሲደርስበት የሚፈጸም ነው። ይህ ለምሳሌ ዛፍ ላይ ፍራፍሬ ቆርጦ ሲበላ ሲደርስበት ወይም መጋቢው ሥራ እንዲሰራ ሲያዘው ፈቃደኛ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር መጋቢው ራሱ ፈርዶ

የሚፈፅመው የእስራት አይነት ነው። በዚህ የእስራት አይነት ወደ ማሰሪያ ቦታ መውሰድ አያስፈልግም። በቀጥታ መጋቢው ጥፋት እንደተፈፀመ ሲያረጋግጥ የታጨዱ የተወሰኑ ሳሮችን ከጥፋተኛው እግር ላይ በማስቀመጥ ታስረሃል ይለዋል። መነኩሴውም መጋቢው መጥቶ ፈትቼሃለሁ እስካላለው ድረስ ከቆመበት ቦታ በፍፁም አይንቀሳቀስም። ይህም በመሆኑ የፈቃድ እስራት ይባላል።

በማህበረ መነኮሳቱ ፍርድ የሚፈፀመው የእስራት አይነት ደግሞ ከባድ የሚባል ጥፋት በተፈፀመ ጊዜ የሚከናወን ነው። የዚህም እስራት አይነት የራሱ የሆነ የፍርድ ሂደት አለው። በመጀመሪያ ጥፋተኛው በማህበረ መነኮሳቱ ፊት ቀርቦ ይቆማል። ቀጥሎም አበምኔቱ ለጥፋተኛው መነኩሴ የጥፋቱን ዓይነት ይዘረዝሩለትና በራሱ ላይ እንዲፈርድ ይጠይቁታል። መነኩሴውም ጥፋተኛ መሆኑን ከተቀበለ ስርአት አነሳለሁ ይላል። ስርአት አነሳለሁ ማለት ማህበረ መነኮሳቱ የጣለብኝን ፍርድ እቀበላለሁ ማለት ነው። በኋላም አበምኔቱ ስርአት አነሳለሁ ማለቱን አመስግነው ለማህበረ መነኮሳቱ መነኩሴው ያጠፋውን ጥፋት ዘርዝረው «ስርአት አነሳለሁ» በማለቱና በፈቃዱ ስርአት ስለሚቀበል ውሳኔያችሁን ግለፁለት ይላሉ። ማህበረ መነኮሳቱም እንደጥፋቱ ክብደትና ቅለት አመዛዝኖ ይወስንበታል። አበምኔቱም የማህበሩን ውሳኔ አድምጠው በል እንግዲህ ልጄ በፈቃድህ ስርአት አነሳለሁ ስላልክ አንድ ሰንበት ወይ ሁለት ሰንበት ወይም አርባ ቀን እንድትታሰር ፈርደናል ይሉታል።

በመቀጠልም መነኩሴው የፍርዱን ውሳኔ ከሰማ በኋላ የሚታሰርበትን ግንድ ይዞ እንዲመጣ ይታዘዛል። ጥፋተኛው መነኩሴም የሚታሰርበትን ግንድ ተሸክሞ ወደ ማህበረ መነኮሳቱ ይመለሳል። ግንዱን ያስቀምጥና ፀሎተ ማርያም ይቀበላል። ይህንን ፀሎት ከተቀበለ በኋላ ግንዱን ተሸክሞ ወደ መታሰሪያ ቦታው ሄዶ ሁለት እግሩን በግንዱ ሁለት ቀዳዳዎች በማስገባት ሰንሰለት ባለው ቁልፍ ይቆለፍና ይታሰራል።

አዳምም ሆነ ሄዋን ባጠፉት ጥፋት መቀጣታቸው በአንድነት ገዳሙ የሚገኙ መናንያን ባጠፉት ጥፋት የመቀጣታቸው ሃይማኖታዊ መነሻ ነው ይላሉ። በድሎ አልበደልሁም፤ አጥፍቶ አላጠፋሁም፤ የሚል መናኝ ሙሉ በሙሉ ከገዳሙ እንዲሰደድ/እዲባረር/ ይደረጋል። የግል ንብረት አፍርቶ የተገኘ መናኝ ይህን የግል ንብረቱን በማስረከብ ተግሳጽ እንዲቀበል ተጠይቆ ፈቃደኛ ካልሆነ ገዳሙ ከአባልነት ያግደዋል። በገዳሙ ውስጥ ሥራ ለመሥራት እምቢተኛነት ያሳየና የሃይማኖት ልዩነት የታየበት መናኝ ከገዳሙ እንዲሰደድ ይደረጋል።

ከዚህ ገለጻ ላይ መረዳት እንደሚቻለው በዚህ ገዳም ውስጥ ጥፋተኛ የሚቀጣው ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎችን መሠረት በማድረግ ይመስላል። የመጀመሪያው በጥፋተኞች ምክንያት የገዳሙ ማህበራዊ ኑሮ እንዳይናጋና ስርአት አልበኝነት እንዳይነግስ ነው። ማህበረ መነኮሳቱ በስርአት፣ በሕግ፣ በእኩልነትና በነፃነት መኖር እንዲችሉ ጥፋተኞች ይቀጣሉ። የገዳሙ አንድነት እንዳይፋለስ ጥፋት ናቸው የሚባሉ ነገሮች ሁሉ በወቅቱ ይታረማሉ። ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ በጥፋተኛው ላይ የደረሰውን የሰይጣን ፈተና ለማራቅ ጥፋት የፈፀመ መናኝ ይቀጣል። አንድ መነኩሴ ባጠፋው ጥፋት ሲታሰር በላዩ ላይ ያለው ፈተና ይርቅለታል ተብሎ ይታመናል። መናኙ በፈፀመው ጥፋት ሲታሰር ከጥፋቱ ርቆ እንደገና የገዳሙን ህግ የሚያከብር እንዲሆን ለማድረግ እንጂ መቅጣቱ ብቻውን ትርጉም እንደሌለው ይታመናል።

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ፍትህ የሚሰጠው በፀሎተ ማዕድ ውስጥ ነው። ፀሎተ ማዕድ ቅዱስ በመሆኑ በተቀደሰ ሕብስት የሚቀደሰው ማህበር የሚሰጠው ፍርድ የተቀደሰ እንደሆነ ይታመናል። የፍርዱ ውሳኔ ቢበዛም ቢያንስም እግዚአብሔር እንደፈረደው ስለሚታመን ፍርደኛው ውሳኔውን በፀጋ ይቀበላል። ከዚህም ሌላ የቅጣቱ ዋና ዓላማ ጥፋቱን ማረም ብቻ ሳይሆን ጥፋቱን ገፋፍቶ ያስፈፀመውን ርኩስ መንፈስም ጭምር በመቅጣት መናኙ ኃይል አግኝቶ እንዲመጣ ለማድረግ እንደሆነ ይታመናል በዚህም ምክንያት አንዳንዶቹ እባካችሁ እሰሩኝ ብለው የሚጠይቁ እንዳሉ ነግረውኛል።

ስለዚህ የፍርዱ ልክ ቢበዛ ቅጣቱ የሚያርፈው በርኩስ መንፈሱ ላይ በመሆኑ ፍርደኛው ውሳኔውን በፀጥታ ይቀበላል። ማህበሩም ቢሆን በሰጠው ውሳኔ አይሳቀቅም። በመሆኑም በዚህ ገዳም የሚከናወነው ቅጣት ከገዳሙና ከገዳሙ ማሕበረሰብ አንፃር ሲታይ በገዳሙ ውስጥ ስርአት እንዲነግስ አንድነቱ እንዳይፋለስ ያደርጋል። ከፍርደኛው መነኩሴ/መናኝ/ አንፃር ሲታይ ደግሞ በሰማይ ሊያስፈርድበት የሚችለውን ኃጢአት /ጥፋት/ በምድር በሚፈፀምበት ቅጣት እንደሚነጻለት ስለሚያምን ደስታን ያገኛል። ከዚህም በላይ የቀረበው/ገፋፍቶ ኃጢአት ያሰራው/ ርኩስ መንፈስ ተቀጥቶ ከእሱ እንደሚርቅ ማሰቡ በገዳማዊ ሕይወቱ ላይ መረጋጋትን ይፈጥርለታል።

በዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም ውስጥ ጥፋትንም፣ ኃጢአትንም በተመሳሳይ ሁኔታ ለማረም ሲሞከር ይስተዋላል። ወይም በዚህ ገዳም ውስጥ ጥፋትንና ኃጢአትን አንድ አድርጎ በማሰብ ጥፋት ሲታረም ኃጢአትን እንደማስወገድ ይቆጠራል ማለት ይቻላል። ጥፋት የተገኘበት መነኩሴ በማህበር ሲፈረድበት እግዚአብሔር እንደፈረደበት በማመኑ በማህበረ

መነኮሳቱ ላይ ቂም ሊይዝ አይችልም። ማህበረ መነኮሳቱም ፍርዱን የሰጠው እግዚአብሔር ነው ብሎ ስለሚያምን ፍርደኛው መነኩሴ ይቀየመኛል ብሎ አያምንም። ፍርደኛው መነኩሴ በእስራቱ ጊዜ አጥብቆ በመፀፀትና በመፀለይ ጥፋቱንና ኃጢአቱን ሙሉ በሙሉ አርሞ ለመመለስ ይጥራል። ጥፋቱን ማረም ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ እንደሚረዳውም ያምናል። ማህበሩም በእስር ላይ ለሚገኘው መነኩሴ እግዚአብሔር በደሉን ይቅር እንዲለው አጥብቆ ይጸልይለታል።

በገዳሙ ውስጥ ከቅጣት ጋር በተያያዘ የሚፈጸመው አምልኳዊ ስርአት የኢየሱስን የፍርድና የስቅለት ተረክ መነሻ ያደረገ ይመስለኛል። አንድ ጥፋተኛ ጥፋት ፈፅሞ ከተፈረደበት በኋላ የመታሰሪያውን ግንድ ተሸክሞ ይዞ እንዲመጣና ፀሎት ከተቀበለ በኋላ እንደገና ግንዱን ወደሚታሰርበት ቤት ተሸክሞ እንዲሄድ ይደረጋል። ኢየሱስ የሚሰቀልበትን መስቀል ተሸክሞ ወደ ጎልጎታ እንደሄደ ሁሉ ፍርደኛውም የመታሰሪያ ግንዱን ተሸክሞ ወደሚታሰርበት ቤት ይሄዳል። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በከፈለው መከራ የሰውን ልጅ ኃጢአት አስወግዷል ተብሎ እንደሚታመን ሁሉ ፍርደኛውም በግንድ ውስጥ ታስሮ በሚደርስበት መከራ ኃጢአቱን ያስወግዳል ተብሎ ይታመናል። ኢየሱስና ፍርደኛው መነኩሴ በከሳሾቻቸው አንጻር ሲታዩ ሁለቱም በደል እንደፈፀሙ ይታመናል። አጋንንትን/ጠላትን/ በመቅጣት በኩል ሁለቱም የተቀበሉት መከራ ለተመሳሳይ ዓላማ ነበር ማለት ይቻላል። ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ ወደሰማያዊው አባቱ ሄዷል ተብሎ እደሚታመነው ሁሉ ገዳማዊውም በእስራቱ ሀጢአቱን አንጽቶ ቅዱስ እደሆነ ወደሚታመነው ማህበር ይቀላቀላል። ስለዚህ የገዳሙ የቅጣት ስርአት ገዳማውያኑን ገዳሙ ትክክለኛ ወደሚለው መንገድ ከመመለሱ ባሻገር የቀረባቸውን ሰይጣን የመቅጣትና ኃጢአትን የመደምሰስ ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

## *5.2 በግል የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች*

### 5.2.1 አቃቤ ሰዓትና ስውሩ መድኃኔዓለም በተባሉት ስፍራዎች የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች

ቀደም ሲል በነበረው ምዕራፍ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አቃቤ ሰዓት እየተባለ የሚጠራው አባ ሂሩተ አምላክ ወደዚህ ገዳም እንደመጡ ለመጀመሪያ ጊዜ ያረፉበት ቦታ ነው። ይሄ ቦታ በአባ ሂሩተ አምላክ የማዕረግ ስም ተሰይሟል። መናኙ ከጣና ሐይቅ እንደወጡ በዚህ ቦታ ላይ

የተወሰነ ጊዜ እረፍት አድርገውበትና ፀሎት አድርሰውበት ተነስተዋል። እስካሁንም ድረስ ይሄ ቦታ ተለይቶ ጎብኝዎች እንዲመለከቱት ይደረጋል።

ከዚህ በተለየ ሁኔታ ገዳማውያን ለዚህ ቦታ የተለየ ትኩረት ይሰጡታል። በተለይም የመንፈስ አለመረጋጋት ሲያጋጥማቸው ወይም በገዳማውያን አገላለጽ የዲያቢሎስ ፈተና ሲበረታባቸው አቃቤ ሰዓት ወደ ተባለው ቦታ በመሄድ ሱባኤ ይይዛሉ። አጠር ያለ ፀሎት አድርሰውም የሚመለሱ አሉ። በዚህ ቦታ ላይ እጅግ በጣም ትልቅ ዋርካ ይገኛል። በዙሪያውም የተለያዩ የድንጋይ መቀመጫዎች አሉ። የእጣን ማጨሻ ቅርፊቶችም ይታያሉ። ከዚህ ውጭ ቦታው ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የታጠረ ሲሆን ከጀርባ በኩል በትንሽ የእርምጃ ርቀት ላይ የጣና ሃይቅ ይገኛል።

ገዳማውያን ቦታው አባ ሂሩተ አምላክ ለመጀመሪያ ጊዜ ፀሎት ያደረጉበት በመሆኑ በዚህ ቦታ ላይ ሆኖ ፀሎት መፀለይ የእሳቸውን ረድኤትና በረከት ያስገኛል የሚል እምነት አላቸው። በዚህም ምክንያት ብዙ ገዳማውያንና ጎብኝዎች እዚህ ቦታ ላይ መፀለይ ያዘወትራሉ። ምናልባት ጉዳዩን በውል ማረጋገጥ ባይቻልም ሕቡአን መነኮሳት አባ ሂሩተ አምላክን ለመጀመሪያ ጊዜ ያነጋገሯቸው በዚህ ቦታ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት ካለ በዚህ ቦታ ላይ ሆኖ መፀለይ ህቡአንን እንደማግኘት ይቆጠር ይሆናል። ወይም ደግሞ ሕቡአን ለአባ ሂሩተ አምላክ የሰጧቸውን ቃል ኪዳን ለእነሱም እንደሚሰጧቸው ይታመን ይሆናል። ወይም ራሳቸው አባ ሂሩተ አምላክ ይረዱናል የሚል እምነትም ሊኖራቸው ይችላል። ወይም አባ ሂሩተ አምላክ የተገባላቸው ቃል ኪዳን ካለ እሱን እናገኛለን ብለው ያምኑም ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ገዳማውያን ወደዚህ ቦታ በተደጋጋሚ ጊዜ እየሄዱ በመፀለይ የስነልቡና መረጋጋት አግኝተው እንደሚመለሱ ገልፀውልኛል።

ገዳማውያንም ሆኑ ምዕመናን ጎብኝዎች በአንድ ወቅት አንድ አባት በረከት አግኝቶበታል ተብሎ በሚታመንበት ቦታ ላይ መፀለይ ወይም ረዘም ያለ ሱባኤ መያዝ የሚመርጡበት ለምንድን ነው ሲባል አንድም ቦታው ድረስ ሄዶ ለጸለየ ፣ ለተማጸነ ወይም ቦታውን አይቶ ለተመለሰ እንዲህ ይሆንለታል የሚባል ቃል ኪዳን ሲኖር ነው። ወይም ደግሞ በዚያች ክልል ውስጥ ተደጋጋሚ ተዓምራት ተፈፅመው ሲታዩ ነው። አቃቤ ሰዓት በሚል በተሰየመችው በዚህ ቦታ ላይ ቆሞ ለጸለየ፣ ሱባኤ ለያዘባትና በእምነት አየቷት ለተመለሰ ሰው ከስነ ልቡና መረጋጋት ጀምሮ ብዙ በረከት እንደሚያገኝበት በገዳማውያኑ ይታመናል። ይህም በገዳማውያኑም ሆነ በምዕመናን ጎብኝዎች ዘንድ ረቂቅ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አካል

ነስቶና ገዝፎ እንዲታይ ያስችላል። በአንድ በተወሰነ ክልል ላይ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዳለ ማመንም በተጨነቁ ጊዜ፣ በከፋቸው ሰዓት፣ ተስፋ በቆረጡና በአዘኑበት ወቅት ሁሉ እየሄዱ ይህንን ቅዱስ ኃይል ማግኘት እንደሚችሉ እምነት ስለሚያሳድር የገዳማዊ ህይወትን ያጸናላቸዋል። ስለሆነም ገዳማውያን በዚህ ቦታ ያላቸው እምነትና የቦታው ታሪካዊነት እንደተጠበቀ እንዲዘልቅ ማድረግ ከገዳማዊ ህይወት ህልውናቸው ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ትልቅ ዋጋ ይሰጡታል።

ስውሩ መድኃኔዓለም በሚል በሚታወቀው ቦታ ላይም እደዚሁ ገዳማውያን በየጊዜው ሱባኤ ይይዙበታል። ገዳማውያን ይህ ቦታ የመድኃኔዓለም ስውር ሀይል ይገለጽበታል የሚል እምነት ስላላቸው ይመስላል በገዳሙ ውስጥ ፈተና በጸናባቸው ጊዜ ወደዚህ ቦታ በመሄድ ሱባኤ ይገባሉ። ለሱባኤም ሲሄዱ/በመናኙ ፍላጎት የሚወሰን ቢሆንም/ በአብዛኛው መስቀል፣ ስዕል፣ እጣን፣ የሚመገቡት የዳቤ ድርቆሽ ይይዛሉ። ይህ ቦታ ገዳማውያን ከሚኖሩበት አካባቢ ራቅ ያለ በመሆኑና ዙሪያው በጫካ የተከበበ በመሆኑ ሀሳብን ሰብስቦ ለመጸለይ አመቺ መሆኑን ተመልክቻለሁ። ገዳማውያን በእነዚህ ቦታዎች ላይ ሱባኤ ሲይዙ የያዙትን ስዕል እያጠኑ ይጸልያሉ። አካላቸውን ለማድከምም አጥብቀው ይሰግዳሉ፤ ይራባሉ፤ ያለ እረፍት ድጋማቸውን ይደገግማሉ፤ መቁጠሪያቸን ይቆጥራሉ። ጥልቅ በሆነ ጸጥታ ውስጥ መግባትም ይሻሉ።

ገዳማውያን ከተወሰኑ የሱባኤ ቆይታ በኋላ ከሰይጣን ፈተና ተላቀው እንደሚመለሱ ያምናሉ። ይህ ገዳም የእግዚአብሔር ኃይል ስላለበት በጥቅሉ የተቀደሰ ገዳም ነው እየተባለ በቅድስና ውስጥ ሌላ ጠበብ የሆነ ቅድስና መሻት ለምን አስፈለገ የሚል ጥያቄ ይፈጥራል። ይህ ጉዳይ ቀደም ሲል ለመግለጽ እደተሞከረው የፈጣሪን የመንፈስ ኃይል፣ እርዳታና ስጦታ ቅርብና ተጨባጭ አድርጎ ለማሳየት ካለ ፍላጎት የመነጨ ይመስለኛል። ገዳማውያን በገዳሙ ውስጥ የሚታዩና የሚጎበኙ የተለያዩ ቅዱስ ስፍራዎች እዳሉ ማመናቸው ለአምልኳዊ ስርአታቸው አማራጭ ስለሚፈጥርላቸውና ረቂቅ የሆነውን መንፈሳዊነት ተጨባጭ ስለሚያደርግላቸው ገዳማዊ ህይወታቸውን ያጸናላቸዋል የሚል እምነት አለኝ።

### 5.2.2. በጻድቃን ማረፊያ የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች

ምዕራፈ ፃድቃን ማለት የፃድቃን ማረፊያ ማለት ነው። የፃድቃን ማረፊያ የተባለው ቦታ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አጽም ከብዙ ዓመት መንከራተት በኋላ ወደዚህ ገዳም መጥቶ ሲያርፍ «ይህች

የዘለዓለም ማረፊያዬ ናት» የሚል ንግግር በማሰማቱ ምክንያት የተሰጠ ስያሜ እደሆነ ይነገራል። ከዚህም ጊዜ ጀምሮ በዚህች ቦታ ላይ ትንሽ እረፍት ወስዶ ለፀለየና ለተማፀነ ፍላጎቱ ይፈፀምለታል ተብሎ ይታመናል። በዚህም ምክንያት በዚህ ገዳም የሚኖሩ መነኮሳት በማንኛውም አጋጣሚ በዚህ ቦታ ላይ ሲያልፉ ትንሽ አረፍ በማለት ፀሎት አድርሰው የመነሳት ስርአት አላቸው። ይህንን ገዳም ለመጎብኘት የሚመጡ ምእመናንም በዚህ ቦታ ላይ አረፍ በማለት ፀሎት አድርገው ይነሳሉ። በሰዓታት ውስጥ ለተደጋጋሚ ጊዜ በዚህ ቦታ ላይ የማለፍ አጋጣሚ የሚገጥመው መናኝ እረፍት አድርጎና ፀሎት አድርሶ መነሳቱን አይዘነጋውም።

በርግጥ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አጽም «ይህች የዘላለም ማረፊያዬ ናት» በሚል የተናገረው በጥቅል ገዳሙን እንጂ ይህችን ቦታ ብቻ እንዳልሆነ ይነገራል። ከዚህም ሌላ የንጉሱ አጽም ለመጀመሪያ ጊዜ አርፎበታል እየተባለ የሚጠቀስ በገዳሙ ክልል ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች እንዳሉ የገዳሙ አባቶች ነግረውኛል። አሁን አሁን ግን ምዕራፈ ፃድቃን እየተባለች የምትጠራው ይህች ቦታ አጽሙ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳረፈባት ተደርጎ እየተነገረ ይገኛል። የዚህችን ቦታ ታሪካዊነት ለማጽናት ይመስላል የገዳሙ መሥራች እንደሆኑ የሚነገርላቸው አባ ሂሩተ አምላክ ጣና ኃይቅን የተሻገሩባቸውን ድንጋዮች በዚህ ቦታ ላይ አስቀምጠዋቸው ይገኛል። በመሆኑም ይህች ቦታ ከንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ አጽም ማረፊያነት እና ከአባ ሂሩተ አምላክ ተዓምራዊ ድንጋዮች ማረፊያነት ጋር የተያያዘች ሆና ትገኛለች።

በመሆኑም ገዳማውያን በዚህች ቦታ ላይ እረፍት በማድረግ ጸሎት አድርሰው ሲነሱ አንድም የአፄ ዘርዐ ያዕቆብ አጽም ባረፈበት በዚህ ቦታ ላይ ፀሎት ማድረግ "በዚህ ቦታ ላይ ፀሎት ያደረገ ተዓምር ይደረግለታል" የሚለውን ቃል ኪዳን ለመውረስ ነው። አንድም ደግሞ ተዓምር በፈፀሙት በእዚህ ድንጋዮች ማረፊያ ላይ ፀሎት አድርጎ መነሳት ድንጋዮች ሊፈጽሙት የሚችሉት ተዓምር ቢኖር እሱን ለማግኘት ነው። ገዳማውያን እና ጎብኝዎች በዚህ ቦታ ላይ እረፍት አድርገው ሲነሱ የተለያየ ስሜት እንደሚሰማቸው አባ ወ/ሰንበት ነግረውኛል።

በዚህ ገዳም የሚኖሩ መናንያን እነዚህን ድንጋዮች ዘወትር ሲመለከቷቸው መንፈሳዊ ጥንካሬ ይፈጥርላቸዋል ይላሉ። ሐዋርያው ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጋር ሆኖ በባህር ላይ ሲጓዝ በመጠራጠሩ ሊሰምጥ ችሏል። ጴጥሮስ በወቅቱ ፀጋ መንፈስ ቅዱስን ስላልተቀበለ የጥርጣሬ መንፈስ ገጥሞታል። አባ ሂሩተ አምላክ ግን በባህር ላይ በድንጋይ ታንኳ ሲጓዙ ምን ያህል ከፍፁምነት ደረጃ ላይ እንደደረሱ መገንዘብ ይቻላል ብለውኛል። ጌታ በታንኳ በጌር ጌሴኖን ባህር እንደተጓዘ(ሉቃ፡8፣26) ሁሉ እሳቸውም ጌታን መስለው በፍጹምነት በባህር ላይ ሊጓዙ

ችለዋል። ይህንንም ዕለት ዕለት ማስታወስ ለመንፈሳዊ ሕይወት ትልቅ ጉልበት ይፈጥራል። ምክንያቱም ይላሉ አባ ወ/ሰንበት ማንም ጀግና ካላየ ጀግና መሆን ስለማይችል የእሳቸውን የፍፁምነት ተጋድሎ ስንመለከት እኛም በተጋድሎአችን እንበረታለን። በእሳቸው ቃል ኪዳን ስንማፀን ረድኤትና በረከታቸው ይተርፈናል ብለን እናምናለን" ብለውኛል።

ወደዚህ ገዳም የሚመጡ ምዕመናንም ስለምዕራፈ ፃድቃን ምንነትና ተዓምር ስላደረጉት ስለ እነዚህ ድንጋዮች ተረክ ሲነገራቸው የተለያዩ ድርጊቶች እንደሚፈጽሙ ነግረውኛል። አብዛኛዎቹ ምእመናን የቅዱሳኑን ረድኤት ለማግኘት ሲሉ በዚህ ቦታ ላይ አጥብቀው በፀሎት ይማፀናሉ። አንዳንዶች ደግሞ ከድንጋዩ ላይ ለበሽታቸው መድሃኒት እናገኛለን በሚል እምነት ድንጋዩን ይሳለማሉ፤ ድንጋዩን በእጃቸው በማሻሸት የሚያማቸውን ቦታ የሚቀባቡም አሉ፤ ሌሎች ደግሞ እነዚህን ተዓምራዊ ድንጋዮች በውኃ አጥበው እጣቢውን በመውሰድ የሚጠጡ ይገኛሉ። ዓላማቸው በግልጽ ባይታወቅም ከድንጋዮቹ ጋር ፎቶ ተነስተው የሚሄዱም ብዙዎች ናቸው። በአጠቃላይ ስለ እነዚህ ድንጋዮች ታሪክ ሲነገራቸው የሚጠራጠሩ አንዳንድ ጎብኚዎች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ግን በእምነታቸው ተደንቀውና እምነታቸውን አጽንተው የሚሄዱ እንደሚበዙ አስረድተውኛል።

የፃድቃን ማረፊያ በሚል ስያሜ የሚጠራው ይህ ቦታ የፃድቃን ማረፊያ ነው ሲባል በዚህ ቦታና በዚህ ገዳም ብዙ ፃድቃን እረፍት አድርገውበታል /የዘላለሙን እረፍት ጨምሮ ሊሆን ይችላል/ ማለት ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ በዚህ ቦታ ላይ እረፍት የሚያደርጉ ሁሉ ፃድቃን ናቸው ማለት ይሆናል። በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እዚህ ቦታ ላይ እረፍት አድርጎ ፀሎት ላደረሰ ሰው ፀሎቱ እንደሚደርስለት አመላካች ነው። ለዚህም ለአፄ ዘርዐ ያዕቆብ አጽም የተገባለት ቃል ኪዳን ዋና ደጋፊ ማረጋገጫ ነው። እንዲሁም ማርያምና ልጇ ኢየሱስ እንዲሁም ቤተሰቧ ከነጓዛቸው ወራጁን ወንዝ ተራራ ላይ ተነስተው በመጡ ድንጋዮች እንደ ታንኳ ተጠቅመው እንደተሻገሩት (ተስፋ፣ 1988፣ 183) ሁሉ ገዳማውያን አባ ሂሩተ አምላክ የጣናን ሃይቅ የተሻገሩባቸው ድንጋዮች በዚህ ቦታ ተቀምጠው ማየታቸው በቦታው ላይ ፀሎት አድርሶ ለሚነሳው ገዳማዊ ፀሎቱ እንደሚደርስለት፣ እነዚህ ተዓምራዊ ድንጋዮች ማረጋገጫ ሳይሆኑለት አይቀርም።

በመሆኑም ገዳማውያን ይህንን ስርዓት ዘወትር ይፈጽሙታል። ሌሎችም (በተለይ ምዕመናን ጎብኚዎች) ይህንን የእነሱን አምልኳዊ ስርአት በእምነት እንዲፈጽሙ ማስረጃዎችን እያሳዩ ያስተምራሉ። መንፈሳዊ ጎብኚዎች ገዳማትን የሚጎበኙበት የተለያየ ዓላማ ቢኖራቸውም

በየገዳማቱ የተፈፀሙ ተዓምራትን ማየትና ለእኔም ይሆንልኛል ብሎ ማመን ዋና ጉዳያቸው ሳይሆን አይቀርም። ገዳማትም ይህንን የምእመናን ጎብኚዎች ፍላጎት ለማርካትና የጎብኚዎችን ቀልብ ለመግዛት ሊገልጹ የሚችሉት ብዙ ተዓምራት ቢኖሯቸው አይጠሉም ይመስለኛል። ተፈፀሙ የሚባሉትን ተዓምራት ለሰዎች እየገለፁ ለራሳቸውም ይሰሙታል፤ ሁሌም በማየት ይታነፁበታል። በመሆኑም በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኘውን ይህን የፃድቃን ማረፊያ ተብሎ የሚጠራውን ቦታ ገዳማውያን ታሪካዊነቱን ለዘመናት እየተማሩ፣ እያስተማሩና እየጠበቁ የሚኖሩት ለገዳማዊ ሕይወታቸው መሠረት ስለሆነላቸው ሳይሆን አይቀርም በሚል መገመት ይቻላል።

### 5.2.3 በአርምሞ /በጽሞና/ የሚከወን አምልኳዊ ስርዓት

አርምሞ ፍጹም አለመነጋገር ወይም ጥልቅ ፀጥታ ማለት ነው። ፀጥታ በገዳም ውስጥ ራስን የመመርመሪያ ትልቅ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። መነኮሳት ዝም ባሉ ጊዜ የሚያስቡት ስለራሳቸው ኃጢአት ብቻ ነው። ከአስርቱ የፍጹማን ማዕረጋት ውስጥ አንደኛው አርምሞ ነው። እነዚህ አስሩ የፍጹማን ማዕረጋት መንኖ ጥሪት፣ ሁልጊዜ እስከ ሰርክ ጾም፣ ሌሊት መትጋት፣ የሰባቱን ሰዓታት ጸሎት ማድረስ፣ መጽሐፍ ማንበብ፣ የዋህነት፣ ትህትና፣ ወንድምን መውደድ፣ አርምሞ፣ በፍቅረ እግዚአብሔር ሲዘጋጁ መኖር(ዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም፣ የታተመበት ዓ.ም አልተጠቀሰም፣2) የሚሉት ይጠቀሳሉ። እንደበቱን የገታ ሰው የነቢብን /በመናገር የሚፈፀምን/ ኃጢአት እንደማይሠራና የነቢብን ኃጢአት የተቋቋመ ደግሞ ወደ ገቢር የሚወስደውን ኃጢአት እንደሚገታው ይታመናል። አንድ መናኝ በኃልዮ /በሃሳብ/ ቢበድል እንኳን በንግግር ስላላወጣውና በገቢርም ስላልተረጎመው የኃጢአት መንገዱን መዝጋት ችሏል ተብሎ ይታመናል።

የአንደበት ኃጢአት ከባድ በመሆኑ ብዙ አባቶች አርምሞ ውስጥ በመግባታቸው እንደተጠቀሙ ገልፀውልኛል። አርምሞ በረከት የማግኛ መንገድ እንደሆነ ይታመናል። ይሁን እንጂ አርምሞ የፀጋ ስጦታ በመሆኑ ለሁሉም ላይሰጥ ይችላል። አንዳንዶች አርምሞ ውስጥ በመግባታቸው ትልቅ ትሩፋት አግኝተዋል። አንዳንዶች ደግሞ ከፈጣሪ ሳይፈቀድላቸው በራሳቸው ሃሳብ አርምሞ ውስጥ በመግባታቸው ለሰይጣን ፈተና የተጋለጡ አሉ። አባ ተክለዮሐንስ አባ ኃይለስላሴ የሚባሉ አባት ሳያውቁት አንድ ቦታ ላይ እንደቆሙ በአርምሞ ቀኑን ሙሉ ሲጸልዩ ይውሉ እንደነበር አይቻለሁ በማለት ነግረውኛል።

በገዳም ውስጥ ጥልቅ ፀጥታ እንዲሰፍን የተለያዩ ገገር ስርአቶች ተግባራዊ ሆነዋል። ከእነዚህም ውስጥ አንድ መነኩሴ ወደ ሌላው መነኩሴ በዓት/መኖሪያ ቤት/ ያለምንም ተልዕኮ ወይም ያለ ምንም ምክንያት መሄድ አይፈቀድለትም። በዚህም የአንዱን ሰላም ሌላው እንዳይረብሽ ጥረት ይደረጋል። ከዚህ ሌላም ያለሥራ በአንድነት ተሰባስቦ ማውራት ክልክል ነው። አንድ መናኝ የራሱን ኃጢአት መመርመር ባይችል ወይም ጸሎት ለመጸለይ ስንፍና ቢያስቸግረው ወይም ሌላ ስሜት ቢፈጠርበት እንኳ ሁሌም በራሱ በዓት/ቤት/ ተቀምጦ የማሳለፍ ግዴታ አለበት። እንዲሁም የአንዱ መነኩሴ በዓት ከሌላው መነኩሴ በዓት የተራራቀ ሆኖ እዲሰራ መደረጉ ለፀጥታው ትልቅ አስተዋጽኦ አለው በማለት ነግረውኛል።

ገዳማውያን በገዳም ውስጥ የሰፈነውን ፀጥታ ለመጠበቅ ሲሉ አንዱ ሌላውን ከመጥራት ወይም በመጯጯህ መልእክትን ከማስተላለፍ ይልቅ ጭብጨባን /ጽፋትን/ ይጠቀማሉ። በገዳም ውስጥ የሚኖር አባት ቢሞት እንኳን ሊቀ አበው ሰው እንደሞተ የሚገልጸው በጭብጨባ እንጂ በለቅሶ ወይም ጮህ ብሎ በመናገር አይደለም። መነኮሳት በሥራ ላይ ተሰማርተው እያሉ የፀሎት ሰዓት በሚደርስ ጊዜ አሰሪው "የፀሎት ሰዓት ደርሷል" ብሎ አይነግራቸውም። ሰዓቱ እንደደረሰ ያጨበጭባል። ማህበረ መነኮሳቱ ለምን እንዳጨበጨበ ስለሚያውቁ ሥራቸውን አቁመው ጸሎታቸውን አድርሰው ወደ ሥራቸው ይመለሳሉ።

አንድ መነኩሴ ወደሌላው መነኩሴ በዓት ለተልኮ ሲሄድ በቅድሚያ ወደ በዓቱ ከመድረሱ በፊት በጉሮሮው ድምጽ ያሰማል፤ ቀጥሎ በእጁ ያጨበጭባል። ድምፁን ከፍ አድርጎ በጩኸት መጣራት አይፈቀድለትም። ወደ ሌላው በዓት ዘው ተብሎ የማይገባው ምናልባት መነኩሴው በመልካም ትሩፋት ወይም በሥነ ምግባር ጉድለት ላይ ሊኖር ቢችል ከነቀፋ ለመዳን ነው። ለታየውም ሆነ ለሚያየው መነኩሴ መልካም ሁኔታን አይፈጥርም። ሲለዚህ ወደ ሌላው መነኩሴ በዓት መግባት የሚቻለው ፀጥታውን ቀስ በቀስ በመግፈፍ ነው።

አንድ መነኩሴ ወደ ሌላው መነኩሴ በዓት ሄዶ ደጁ ላይ ቆሞ «አውሎግሰን፣ አውሎግሰን፣ አውሎግሰን» ብሎ ያጨበጭባል። አውሎግሰን የአምላክ ስም ሲሆን ይህንን ስም ሰይጣን መጥራት ስለማይችል ያጨበጨበው ሰው እንጂ ሰይጣን አለመሆኑን ለማመልከት ነው። የድሮ አባቶች የበቁ በመሆናቸው ፈተናውም በገሃድ የሚፈፀምባቸው አጋጣሚ ይበዛ ነበር። በመሆኑም የድሮ መናኞችን ሰይጣን እየጠራ በመውሰድ ገደል ውስጥ እየጣላቸውና ሌላም ዓይነት አደጋ እያደረሰባቸው ሲያስቸግራቸው እሱ ሊጠራው የማይችለውን ስመ አምላክ እየጠሩ በጭብጨባ መልእክት ይለዋወጡ እንደነበር ገልጸውልኛል።

ጭብጨባ /ጽፋት/ ሦስት፣ አምስት፣ ሰባት፣ አሥራ ሁለት የተሰኙ ቁጥሮች አሉት። ሦስት ጊዜ ማጨብጨብ የሥላሴን ሦስትነት ለማመልከት ነው። አምስት ጊዜ ማጨብጨብ የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ምሳሌ ነው። ሰባት ጊዜ ሲጨበጨብ ደግሞ ሰባት ቁጥር ፍጹምነትን አመላካች ቁጥር በመሆኗ ፍጽምት የሆነች ስርአትን እየተከተልን ነው የሚለውን ለማመልከት ነው። አሥራ ሁለት ጊዜ ማጨብጨብ ደግሞ የሐዋርያት ምሳሌ ሲሆን መነኮሳት የአርድዕትን ሥራ እየሰራን ነው የሚለውን ለማመልከት ነው። መነኮሳት እነዚህ የጭብጨባ ቁጥሮች እንደየራሳቸው ምርጫ እንጂ ለዚህ ተግባር ይህንን በዚህ ቁጥር ልክ አጨብጭብ የሚል መመሪያ እንደሌለው ነግረውኛው።

ከዚህ ሌላ መነኮሳት የተለያዩ መልእክቶችን ለማስተላለፍ ከድምጽ ይልቅ ደወልን ይጠቀማሉ። በገዳሙ ውስጥ ሁለት ዓይነት ደወሎች አሉ። አንደኛው በቤተክርስቲያን አካባቢ የሚገኘው የነሐስ ደወል ሲሆን ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ብቻ የሚውል ነው። ሁለተኛው ደወል ደግሞ የእንጨት ደወል ሲሆን በተግባር ቤት አካባቢ የሚገኝ ደወል ነው።

የእንጨት ደወሉን የሚደውለው መጋቢው ብቻ ነው። ማንም ቀረብኝ ብሎ ሊደውል አይችልም። የእንጨት ደውሉ ሦስት አይነት አደዋወል አለው። አንደኛው አቢይ ደወል የሚባል ሲሆን መነኮሳቱ ለሥራ ወይም ለመቁኑን/ለምግብ እደላ/ እንዲወጡ የሚደወል ነው። ሁለተኛው ማዕከላዊ የሚባል ሲሆን መነኮሳቱ የፀሎተ ማዕድ ሰዓት እንደደረሰ ለማመልከት የሚደወል ነው። ሦስተኛ ደግሞ የአደጋ ደወል ይባላል። ይህ ደግሞ በማህበረ መነኮሳቱ ላይ አንዳች አደጋ ሲደርስ የሚደወል ሲሆን መነኮሳቱም አደጋው ምን እንደሆነ ለይተው ባያውቁትም መልካም ያልሆነ ነገር እንደተፈጠረ በመገመት ወደ ተግባር ቤቱ ይሰባሰባሉ። ደወሉ የሚለየው በአደዋወሉ የፍጥነት ልዩነት ነው። በአጠቃላይ ደወሉ ምንነቱን የሚጠቁም በመሆኑ ማህበረ መነኮሳቱ ለምንድን ነው የተደወለ እያሉ በመጠያየቅና በመጯጯህ የገዳሙን ፀጥታ አያደፈርሱም። ደወሉ እንደተደወለ ሁሉም በፀጥታና በእርጋታ ወደተፈለጉበት ቦታ እንደሚጓዙ ገልፀውልኛል።

እንግዲህ አርምሞ ወይም ጥልቅ ፀጥታ ኃጢአትን ለማስወገድ ያስችላል ተብሎ እንደሚታመን መረዳት ይቻላል። ይህንንም የሚያደርጉት በገዳም ሕይወት ለሚኖር መናኝ በፀጥታ መጠመድ (ፍትሐ ነገስት፣ 1990፣ 113) እንዳለበት የተደነገገውን መሰረት በማድረግ ሊሆን ይችላል። አርምሞ ፍፁም ከሆነ ደረጃ ለመድረስ የሚያግዝ በመሆኑ ገዳማውያን እለት እለት

የሚለማመዱት ስርአት ነው። አባ ወልደሰንበት እንደነገሩኝ አባ አጋቶን የሚባሉ ግብፃዊ መነኩሴ እንዳይናገሩ በአፋቸው ውስጥ ድንጋይ አስገብተው ይኖሩ ነበር።

አባ አጋቶን ይህንን ለማድረግ የወሰኑት አንድ ቀን በጫካ ውስጥ እየፀለዩ እያሉ አንድ ሰው እየሮጠ በአጠገባቸው ሲያልፍ ይመለከታሉ። ከትንሽ ቆይታም በኋላ ሁለት ሰዎች እየተሯሯጡ ይመጡና አባ አጋቶን ከቆሙበት ደርሰው አባ እንዲህ ዓይነት ሰው በዚህ ሲያልፍ አይተዋል ብለው ይጠይቋቸዋል። አባ አጋቶንም ሰውየው እየሮጠ የሄደበትን መንገድ ጠቁመው አሁን አለፈ ብለው ይነግሯቸዋል። ሰዎቹም አባ አጋቶን የጠቆሟቸውን መንገድ ተከትለው እየተሯሯጡ ይሄዳሉ። ከትንሽ ሰዓት ቆይታም በኋላ እነዚህ ሁለት ሰዎች አባ አጋቶን ወደቆሙበት ቦታ ይመለሳሉ። አባ አጋቶንም ምነው ሰውየውን አጣችሁት እንዴ ብቻችሁን ተመለሳችሁ ብለው ይጠይቋቸዋል። እነዚህ ሰዎችም አይ ሰውየውንማ አግኝተን ገድለነው ተመለስን ብለው ይነግሯቸውና ይሄዳሉ። በዚህ ጊዜ አባ አጋቶን በጣም ይፀፀታሉ። አፌ ባይናገር ኑሮ መች ይህ ሰው ይገደል ነበር ብለው ከዚያን ጊዜ ጀምረው በአፋቸው ድንጋይ ጎርሰው ይኖራሉ። ለቁርባንና ምግብ ለመብላት ካልሆነ በቀር ድንጋዩን ከአፋቸው አያወጡትም ነበር ይባላል ።

ገዳማውያን በዚህ ተረክ ውስጥ አርምሞ ያለውን ዋጋ ለማስተማር ይሞክራሉ። ጽሞና /ተመስጦ/ ከተለመደው የኑሮ ስርአት የወጣ በመሆኑ ገዳማውያን በንግግር ውስጥ ኃጢአት መስራት ስለማይቀር በተቻለ መንገድ ንግግርን መቀነስ አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል። በገዳም ውስጥ ጥልቅ ፀጥታ እየሰፈነ በሄደ ቁጥር ሊፈጠር የሚችለውን ግጭት ሊያስወግድ እንደሚችልም እምነት ይኖራል። በአጠቃላይ ትዕምርታዊ የሆኑ የመልእክት ማስተላለፊያ ጭብጨባዎችን /ፅፋቶችን/ በመለማመድ፣ የገዳሙን የደወል ስርዓት በመገንዘብና ከራስ የመኖሪያ ቤት /በዓት/ በመሰብሰብ አርምሞን መለማመድ እንደሚቻል ይታመናል። ገዳማውያን ከጥልቅ ፀጥታቸው ውስጥ መንፈሳዊ በረከት ማግኘት እንደሚቻልና ሀጢአት ከመስራትም እንደሚቆጥብ በማመናቸው ለዚህ ስርአት በፍቃደኝነት ተገዥ ናቸው። በመሆኑም አርምሞ በገዳሙ ገዳማዊ ስርአት ውስጥ መልካም ስነምግባርን የማነጽ ተግባር አለው ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ ገዳማውን ከስጋዊም ሆነ ከመንፈሳዊ ገዳማዊ ህይወታቸው አኳያ የጀመሩት ገዳማዊ ህይወት ተጠብቆ እንዲዘልቅ ልዩ ልዩ አምልኳዊ ስርአቶችን ይፈጽማሉ። ከሁሉም በላይ በሚያከናውኗቸው ስርአቶች ሁሉ የልዕለ ተፈጥሮ ኃይል እንዳለ ማመን ዋና ጉዳያቸው

ነው። የጸሎተ ማዕድ ስርዓተ አምልኮ የገዳሙ ማህበራዊ አንድነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የማስጠበቅ ተግባር አለው። በተግባር ቤትም የሚከናወነው ስርዓትም ገዳማውያን በህብታቸው እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚያረጋግጥላቸው ነው። ገዳሙ ካስቀመጠው ደንብ ውጭ ለመሆን የሚነሳ ገዳማዊ ቢኖር የማስተማሪያ ተግባራትን በሚፈፅሙ ስርዓቶች ይታረማል። ገዳማውያን የስነልቡና አለመረጋጋት ሲያጋጥማቸው፣ የአምላካቸው መንፈስ እንደራቃቸው ሲያስቡ፣ በገዳሙ ውስጥ እለት እለት የሚነበኟቸውና ስርዓተ አምልኮ የሚፈጽሙባቸው ቦታዎች አሏቸው።

በምዕራፍ ሦስት ውስጥ ገዳማውያን በተረኮቻቸው አማካይነት አሁን ያለው የገዳም ህይወት የት መጣነት በሚገባ አደላድለው እንደሚገልጹ ተመልክተናል። በዚህ ምዕራፍም ይህ የገዳም ህይወት ተጠብቆ እንዲዘልቅ የየራሳቸው ተግባራት ያሏቸውን አምልኳዊ ስርዓቶች እንደሚያከናውኑ አይተናል። እነዚህ ስርዓቶች ገዳማውያን በዚህ ገዳም ውስጥ ለምን እንደሚኖሩ፣ እንዴት እንደሚኖሩ፣ ወይም እንዴት መኖር እንደሌለባቸው፣ መቼና የት ምን እንደሚሰሩ ወይም እንደማይሰሩ፣ ምን ሲገጥማቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው የማጠናከር ተግባር ያከናውናሉ። ገዳማውያን ለህመማቸው ፈውስ፣ ለጭንቀታቸው መረጋጋት፣ ለመንፈሳዊ ተግዳሮታቸው መፍትሔ የማቅረብ ተግባር ያላቸው አምልኳዊ ስርዓቶችን ያከናውናሉ።

## 6.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዓላማ ከዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና በገዳሙ ውስጥ የሚፈጸሙ ስርዓቶች ለገዳማውያን ገዳማዊ ህይወት ያላቸውን ፋይዳ ተንትኖ ማሳየት ነው። በመሆኑም ይህንን አላማ ከግብ ለማደረስ ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ካላቸው የጽሑፍ ሰነዶች፣ በቃለ መጠይቅና በምልከታ መረጃ ተሰብስቧል። መረጃው በጽሑፍ ማስታዎሻ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ግራፍና በመቅረጸ ደምጽ አማካይነት ተቀርጿል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም የተለያዩ ማጣቀሻ መጻሕፍትን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።

ከመረጃዎች ተነስቶ በተሰጠው ትንታኔ መሰረት በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም ከሚነገሩ ተረኮች ውስጥ የተወሰኑት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ከሚገለጽበት ጊዜ ጀምሮ በደሴቱ ላይ ቤተክርስቲያን ተተክሎበት እንደነበርና ይህም ደሴቱ ገና ከጥንት በፈጣሪ የተመረጠ መሆኑ እንደሚታመን የሚያመ ለክት ነው። በዚህ ደሴት ላይ የነበረችው ታቦተ ማርያም ወደደቅ ደሴት እንድትሄድ ሲደረግ የተፈጠረው ተዓምር በውሳኔው ላይ የፈጣሪ ፈቃድ እንዳለበትና ይህንንም የሚያስፈጽሙ አባቶች የተቀደሱና በፈጣሪ የሚደገፉ እንደሆኑ በመረጀ ሰጪዎች ዘንድ ጠንካራ እምነት አሳድሯል። እነዚህ ተረኮች የአሁኑ ገዳማዊ ህይወት መነሻው ምን እንደሚመስልና ገዳማዊው ከሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ በምን እንደሚለይ የሚያሳዩ ናቸው።

በዳጋ ደሴት የሚገኘው የእስጢፋኖስ ታቦት የገዳሙ መስራች ፈጣሪያቸውን በጸሎት በጠየቁት መሰረት በህቡአን አማካይነት ቶራ በተሰኘችው እንስሳ ከእየሩሳሌም ሊመጣላቸው እንደቻለ ይነገራል። ይህ ተረክ ለዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም መመስረት እንደምክንያት የሚጠቀስ ነው። ተረኩ የአስመጭውን፣ የአምጭዎችን፣ የጭነቱንና የመጫኛውን ፍጹም ቅድስና የሚያመላክት ነው። ታቦቱ በዚህ አይነት ተዓምር ከኢየሩሳሌም የመጣ በመሆኑ ከሌሎች ታቦታት የተለየ ነውና በገዳሙ አካባቢ በሚኖሩ ህዝቦች(የክርስትናን መስፋፋት በሚቃወሙ ፈላሻዎችና ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች)፣ በገዳማውያንና ካህናት የሚከበርና የሚፈራ እንዲሆን አስችሎታል። መስራቹም በመነኮሳትና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው እድል ፈጥሮላቸዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የቀረበው ተረክ መስራቹ ለአካባቢው ማህበረሰብ የመንፈሳዊ ህይወት አርአያነት፣ ለገዳማውያኑ ደግሞ የአባትነት ጸጋ

እንደተሰጣቸውና ይህንንም ገዳም ፈጣሪ የዘላለም ርስት አድርጎ እንደሰጣቸው ተረኩ ይገልጻል። ገዳማውያኑም የመስራቹን አርአያ የሚከተሉ በመሆናቸው ለእሳቸው የተገባላቸው ቃል ኪዳን ሁሉ እንደሚፈጸምላቸው ያምናሉ። ይህም እምነት የገዳማውያኑን ገዳማዊ ህይወት የመትከልና የማጠናከር ተግባር አለው።

ቅድስና ባለው ታቦትና በፈጣሪ በሚደገፉ ቅዱስ መናኝ የተመሰረተው ይህ ገዳም ፍጹም ቅድስና ያለው ገዳም እንደሆነ በብዙኃኑ ዘንድ ይታመናል። በሳምንት አንድ ቀን የገነት ነፋስ የሚነፍስበት ገዳም እንደሆነና እንደደብረታቦርና እንደደብረሲና የፈጣሪ መለኮታዊ ኃይል የሚገለጽበት ገዳም መሆኑም ይታመናል። በዚህ ገዳም ላይ በጠላትነት በሚነሱ ወገኖች ላይም መቅሰፍትን የሚያደርስ መለኮታዊ ኃይል እንዳለ ይታሰባል። የደሴቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ የመስቀል፣ የመርከብና የመሶበ ወርቅ ቅርጽ መያዙ እነዚህ ትዕምርቶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተምሳሌታዊ ፍች ያላቸው በመሆኑ የገዳሙ ቅድስና ገና ከጥንት በፈጣሪ የታሰበና የተቀደሰ መሆኑን ያሳያል። የገዳሙን ቅድስና አዕሞች ድምፅ አውጥተው የሚናገሩበት ወይም በራዕይ የሚገልጹበት አጋጣሚ እንዳለና እነዚህ አፅሞች በዚህ ገዳም ማረፋቸው ለገዳሙ የትሩፋት ምንጭ ይሆናሉ የሚል እምነት ያለ መሆኑንም ከቀረቡት ተረኮች መረዳት ይቻላል። እነዚህ ተረኮች በዚህ ገዳም የሚደረገው መንፈሳዊ ተጋድሎ ውጤት እንደሚኖረው የሚያሳዩ በመሆናቸው ገዳማውያን በመንፈሳዊ ተጋድሏቸው እንዲጸኑና እንዲበረቱ የማድረግ ተግባር አለው።

የገዳሙ የፀሎተ ማዕድ ስርዓት የገዳማውያኑ የአንድነት ኑሮ መገለጫ ነው። ገዳማውያን ለዚህ ስርዓት ፍጹም ተገዥ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ጸሎተ ማዕድ ከቤተክርስቲያን ቀጥሎ የተቀደሰና የተባረከ ቤት እንደሆነ ያምናሉ። ጥብቅ የሆነ አምልኳዊ ስርዓት ይፈጸምበታል። ከዚህ አምልኳዊ ስርዓት በኋላም የተቀደሰና የተባረከ ህብስት ይበላበታል፤ ጽዋም ይጠጣበታል። ህብስቱና ጽዋው ከበሽታ ይፈውሳል፤ የስነልቡና መረጋጋትን ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል። ገዳማውያን በዚህ መንፈሳዊ መነሳሳት ውስጥ እንዳሉ የገዳሙ አጠቃላይ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ይተላለፉበታል። በእነዚህ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንደተሳተፈበት ስለሚታመን ሁሉም ገዳማዊ ለውሳኔዎቹ ተገዥ ነው። በመሆኑም ጸሎተ ማዕድ የገዳሙ ማህበራዊ አንድነት እንዳይፋለስና ስርዓት አልበኝነት እንዳይነግስ የመቆጣጠር ተግባር አለው። በተግባር ቤቱም እንዲሁ የሚፈጸመው ጥብቅ የሆነው አምልኳዊ ስርዓት በገዳሙ ውስጥ ፍትሐዊ የሆነ የህብት ክፍፍል መኖሩን የማስረጽ ሙያ አለው።

በጸሎተ ማዕድ የሚደረገው ማንኛውም ውሳኔ የመንፈስ ቅዱስ ውሳኔ እንደሆነ ስለሚታመን በዚህ ቤት የሚሰጠው ሹመት የመንፈስ ቅዱስ ሹመት እንደሆነ ይታሰባል። ይህም እምነት በገዳሙ ውስጥ እምቢተኛነትን ከማስወገዱ በላይ የስልጣን ሽኩቻ እንዳይፈጠር የማድረግ ተግባር አለው። ጥፋት በፈጸሙ ገዳማውያን በዚህ ቤት ውስጥ የሚሰጠው የፍርድ ውሳኔም የመንፈስ ቅዱስ ውሳኔ እንደሆነ ስለሚታመን ፍርደኛው መነኩሴ ፍርዱን በጸጋ እንዲቀበል ያስገድዳል። ከዚህ ሌላ ቅጣቱ የሚያርፈው መነኩሴውን ወንጀል ባስፈጸመው ሰይጣን ላይ በመሆኑና መነኩሴው ቅጣቱን ሲጨርስ ሀጢአቱ ተሰርዮለት፣ የቀረበው ሰይጣን ርቆት ስለሚመለስ በፍርዱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ አይፈጥርም። በዚህ ገዳም ጥፋተኛን ለማረም የሚደረገው ስርዓት መነኮሳት ገዳሙ ትክክለኛ ወደሚለው መስመር እንዲገቡ የመቆጣጠር ተግባር አለው።

በጻጋ እስጢፋኖስ ገዳም የሚገኙ መናንያን የተለያዩ ትዕምርቶችን በመለማመድ አርምሞ ውስጥ የመግባት ስርዓት አላቸው። አርምሞ መንፈሳዊ በረከት ለማግኘት ወይም ከፍ ወዳለ የቅድስና ደረጃ ለመድረስ የሚያግዝ መሳሪያ እንደሆነ ይታመናል። ይህ ስርዓት እምነትን የማስረጽ ተግባር አለው። በዚህ ገዳም የሚገኙ ገዳማውያን ሲያማቸውና የመንፈስ አለመረጋጋት ሲያጋጥማቸው፣ የሰይጣን ፈተና ሲበረታባቸው፣ ወይም የተሻለ ቅድስና ለማግኘት ሲፈልጉ አቃቤ ሰዓትና ስውሩ መድሀኔአለም በሚል ስያሜ የሚጠሩትን ቦታዎች በመጎብኘትና ለተወሰነ ጊዜ ሱባኤ በመያዝ የስነ ልቡና መረጋጋት አግኝተው፣ ከበሽታቸው ተፈውሰው፣ የሰይጣንን ፈተና አራግፈውና ተቀድሰው እንደሚመለሱ ይናገራሉ። ይህም የመንፈስን ረቂቅነት ተጨባጭ የሚያደርግ፣ ሩቅነቱን የሚያቀርብ፣ በቅድስና ውስጥም እንኳን ሌላ ቅድስና ያለ መሆኑን የሚያመለክት ነው። የጻድቃን ማረፊያ በተሰኘውም ቦታ ትንሽ እረፍት በመውሰድ ጸሎት የሚያደርስ ገዳማዊ ለአፄ ዘርዐ ያዕቆብ የተገባለት ቃል ኪዳን እንደሚፈጸምለት ያምናል። እነዚህ ስርዓቶች መኖራቸው ገዳማውያን በመንፈሳዊ ተጋድሏቸው ተስፋ እንዳይቆርጡና በገዳማዊ ህይወታቸው ጽናት እንዲኖራቸው የማድረግ ተግባር አላቸው።

በአጠቃላይ በዚህ ገዳም ውስጥ የሚነገሩ ተረኮች የአሁኑ ገዳማዊ ህይወት ስሩ/ምንጩ/ የት እንደሆነ የሚያመላክቱ ናቸው። ይህም ምንጭ በፈጣሪ በሚደገፉ ቅዱሳን ተረክ ላይ የሚመሰረት ሆኖ እነዚህ ቀደምት ቅዱሳን ያመኑትን እምነት፣ የሄዱበትን መንገድ፣

የተጠቀሙባቸውን እቃዎች፣ ያወጧቸውን መመሪያዎች ሁሉ ቅዱስ አድርጎ የመቁጠር እምነት እንዳለ ያሳያል። እምነትን ከሩቅ ታሪክ ጋር አያይዞ ማመን ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው በመሆኑ የቀደሙት ቅዱሳን እምነት ሲባል የእምነቱን ትልቅነት የሚያሳይ ተደርጎ ተወስዷል። ተረኮቹ እነዚህ ቅዱሳን ሁሉ ለአምለክ የቀረቡ እንደሆኑ አድርገውም ያሳያሉ። እነዚህ ቅዱሳን የረገጧቸውና ያረፉባቸው ቦታዎች ሁሉ ቅዱስ እንደሆኑ አድርገው ያሳያሉ። በተቀደሱ ስፍራዎች የሚከወኑ አምልኳዊ ስርዓቶች ሁሉ የተቀደሱ በመሆናቸው በስፍራው የሚገኙትን ሁሉ የሚቀድሱ መሆናቸውን ያመለክታል። በመሆኑም በዳጋ እስጢፋኖስ የአንድነት ገዳም የሚገኙ ገዳማውያን በዚህ ቅዱስ ገዳም በመገኘታቸው መንፈሳዊ ተጋድሏቸው እንደሚሰምርና ተስፋ ያደረጉትን የቅድስና ደረጃ እንደሚያገኙ እምነት አላቸው። ይህም እምነታቸው ጸንቶ እንዲኖርና ለቀጣዩ ገዳማዊ እንዲተላለፍ የገዳማዊ ህይወቱ ወሳኝ መሰረቶች የሆኑትን ተረኮችና አምልኳዊ ስርዓቶች በጥብቅ ይጠብቋቸዋል።

# ዋቢ ጽሑፎች

Campbell, Anthony. "The Origin of Religion." http://www. Acampbell .org. uk

Danielson, Larry. "Religious Folklore" In Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction. Elliott Oring(Ed.). Logan: Utah State university. Press,1986.

Dorson, Richard M. (Ed.). Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago: The University of Chicago Press,1972.

Goldstein, Kenneth. S. A Guide for Field Works in Folklore. Pennsylvania: Folklore Associates, Inc. Hatboro,1974.

Hailemariam Assefa. "The Addis Ababa Ganata-Iyasus Monastery,1925-1990." Unpublished, Senior Essay, Department of History, Addis Ababa University,1999.

Kottak, P., Conrad. Cultural Anthropology. NewYork:/unknown Publisher/ 2002.

Mezgebu Kassa. "The Mystical Experience of the Monastic Life in the Traditional Context of the Ethiopian Orthodox Tewahido church." Unpublished, Senior Essay, Trinity Theology College, 2001.

Michael Gebru. "Monastic Life and Related Problems in the 20th Century in the Ethiopian Orthodox Church." Unpublished, Senior Essay, Trinity Theology College, 2002.

Ray, C, Benjamin. African Religion: Symbol, Ritual, and Community. New Jersy: prentice Hall, Inc.,1976.

Sims, Martha c. and Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions. Logan, Utah State University press, 2005.

Taddesse Tamrat. Church and State in Ethiopia (1270-1527). London: Oxford University Press, 1972.

Tigab Bezie. "The Ethiopian Claim on the Monastery Deir= Es-Sultan

in Jurusalm, 1850-1994." Unpublished, MA Thesis, Department of History, Addis Ababa University, 1999.

Tsirpanlis, N. Constanitne. Introduction to Eastern Patristic Thought and Orthodox Theology. /Unknown Publisher/ 1991.

Oring, Elliott, /Ed./. Folk Groups and Folklore Genres. Logan: Utah State university Press,1986.

____. Three Function of Folklore: Traditional Functionalizm as Explanation in Folklorestic". The Jornal of American Folklore, vol.89,No.351(Jan.Mar.,1976)pp.6780,http://www.Jstor.org/stable/539547.

Yoder, Don "Towards on the Definition of Folk Religion." Western Folklore, vol.33, No.1, symposium on Folk Religion. Pp 2-15, Western States Folklore Society (Jun.,1974) http://www.Jstor. org/stable/1498248.

ሉሌ መላኩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1997 ዓ.ም።

ልኡል ቃል።የእምነት አደራ። (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፣ 2002 ዓ.ም።

ማህበረ ቅዱሳን። «መላእክት በምድር ላይ» ሐመር። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1987 ዓ.ም።

______። «መላእክት በምድር ላይ» ሐመር። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም።

ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል። የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በምድር ላይ ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ። /አንደኛ መጽሐፍ/ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 2000 ዓ.ም።

ሥርግው ሀብለ ሥላሴ። የአማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1986 ዓ.ም

ሰሎሞን ዮሐንስ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት። አዲስ አበባ፣ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 2001 ዓ.ም።

ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል እና ሌሎች። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንት እና ዛሬ። አዲስ

አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1990 ዓ.ም።

ተስፋ ገብረስላሴ።ተአምረ ማርያም፡ግዕዝና አማርኛ። አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረስላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀ.ሀ.ስላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1951 ዓ.ም።

______ ።የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ። አዲስ አበባ፣ ተስፋ ማተሚያ ቤት፣ 1961 ዓ.ም.።

ታደሰ አይችሉህም። «በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የምንኩስና ስርዓት እና የገዳማውያን የእለት ተእለት ሕይወት ከትዕምርታዊነቱ አንጻር በዝቋላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና በደብረ ሊባኖስ አቡነ ተክለሀይማኖት ገዳማት።» ዲማጽ(MA)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999 ዓ.ም።

ትንሳኤ የመጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት። ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው። አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ መጻሕፍት ማተሚያ ድርጅት፣ 1990 ዓ.ም።

አባ ተከስተ ብርሃን ወልደሳሙኤል። ባህታውያን በዋልድባ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ 1995 ዓ.ም።

አባ ጎርጎሪዎስ ። የቤተክርስቲያን ታሪክ በአለም መድረክ ። አዲስ አበባ፣ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተምያ ቤት፣1978 ዓ.ም።

______ ።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ። አዲስአባባ፣ 1991 ዓ.ም።

አባ ፊሊጶስ። የምንኩስና ሥነሥርዓትና ብያኔ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ሊሚትድ፣1961 ዓ.ም።

ኪዳነወልድ ክፍሌ። መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም።

ወርቁ ከተማ። «በሊሙና ቢልቢሎ ወረዳ፣ የጨፌ መድኃኔለዓም፣ ደብረቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም አመሰራረት ፎክሎራዊ ገጽታ።» ዲማጽ(MA)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999 ዓ.ም።

ደስታ ተክለወልድ። ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1962 ዓ.ም።

ዳንኤል ክብረት። የቤተክርስቲያን መረጃዎች። አዲስ አበባ፣ ማህበረ ቅዱሳን፣ 1999 ዓ.ም።

ዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም። ዳጋ ቅዱስ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም።(የታተመበት ከተማ፣ ዓመተ ምህረትና ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)

ገሰሰ ፋሪስ። ሀመረ ክርስትና በመዋግደ ፍልስፍና። መቀሌ፣ ሚጋ ማተሚያ ቤት፣1998 ዓ.ም።

ጌታቸው ኃይሌ። ደቂቀ እስጢፋኖስ "በሕግ አምላክ"።/ሁለተኛ እትም/ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፣ 2002 ዓ.ም።

ዘመድኩን በቀለ። ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም።

የአማራ ብሔራዊ ክልል ባሕል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ። የአማራ ክልል የቱሪስት መስህብ ሃብቶች /አጭር ቅኝት/። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። መጽሐፍ ቅዱስ። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1980 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። አማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.።

የክልል 3 ቱሪዝም ቢሮ። ክልል 3 ሲጎበኝ። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣1986 ዓ.ም።

የጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማርያም ገዳም። ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ። 1999 ዓ.ም።

ያረጋል አበጋዝ። ፍኖተ ቅዱሳን። /ሁለተኛ እትም /ማተሚያ ቤቱ አልተገለፀም/፣ 1995 ዓ.ም።

ፈቃደ አዘዘ። የሥነቃል መመሪያ። አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጻሕፍት ማዕከል፣ 1991 ዓ.ም።

ፍሬህይወት ባዩ። «በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃተማኖታዊ ገጽታ።» ዲግሪ(MA)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999 ዓ.ም።

## አባሪዎች

## 1. በዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም የተሰበሰቡ የፎቶ ግራፍ መረጃዎች



ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ደሴት



ዳጋ እስጢፋኖስ
ቤተ ክርስቲያን




መስራቹ ሐይቁን
የተሻገሩባቸው ድንጋዮች



ወደ ገዳሙ የማይገቡ ሴቶች
መስተናገጃ ቤት



በገዳሙ የሚገኘው የአፄ
ዳዊት አፅም




በገዳሙ የሚገኘው የአፄ
ሱስንዮስ አፅም



በገዳሙ የሚገኘው የአፄ ዘርዓ
ያዕቆብ አፅም




በገዳሙ የሚገኘው የአፄ
ፋሲል አፅም



አጽሞቹ የተጓጓዙበት ከቆዳና
የቀርቀሃ የተዩረ ሳጥን



በገዳሙ የሚገኙ ነጋሪቶች
መካከል



በገዳሙ ቅርስ ክፍል ውስጥ
የሚገኙ ልዩ ልዩ ቅርሶች



ከግማደ መስቀሉ ላይ በመፌልፌል
እንደተሰራች የሚነረርላት መስቀል



የአፄ ፋሲል ተገጣጣሚ ጠንበር



በገዳሙ የሚገኙ ልዩ ልዩ አልባሳት



የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሰይፍ



ጸሎተ ማዕድ የሚካሔድበት ቤት



ከመቅደሱ በር ላይ የሚገኘው የመስራቹ አጽም



የገዳሙ መስራች የአባ ሂሩተ አምላክ ስዕል



ገዳማውያን በልማት ሥራ
ላይ



የእቃ ቤቱ ኃላፊ አባ ወ/ሃና



ገዳማውያን ሱባኤ የሚይዙበት
ስውሩ መድኃኔዓለም
የተሰኘው ቦታ



የጻድቃን ማረፊያ



አቃቤ ሰዓት በሚል የሚጠራው
ቦታ



አቃቤ ሰዓት በሚል የሚጠራው
ቦታ ላይ ጥናቱን ያካሄደው ተማሪ




የገዳሙ የአትክልት ቦታ






የገዳሙ ሽመና ክፍል



የገዳሙ ወፍጮ ቤት



የገዳሙ የእንጨት ደወል



አበምኔቱ ብቻ የሚቀመጡበት
በጸሎተ ማዕድ የሚገኘው
ወንበር





ዳቤው የሚቆረስበት አውድ

መነኮሳቱ የሚመገቡት ዳቤ





አጥኚው በጀልባ ጉዞ ላይ

የገዳማውያን ድርጎ ሲከፋፈል



ጥፋተኛ ገዳማውያን የሚታሰሩበት ከእንጨት
የተሰራ ግንድ

# 2.የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

## ሀ. ቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | አድራሻ | የሥራ ድርሻ | መረጃ የሰጡበት ቀን | የሰጡት መረጃ አይነት | መረጃ የሰጡበት ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አባ ወልደ ሰንበ ት | ወ | 39 | ዳጋ | መጋቢ | ከ18-21/2002 | ስለገዳሙ አመሰራረት ታሪክ | በመቅረጸ ድምጽና በእጅ ማስታዎሻ |
| | | | | | | | ስለገዳሙ የመመስረቻ ምክንያት ስለገዳ | |
| | | | | | | | ሙ ቅድስና በገዳሙ ስለሚገኙት ልዩ ልዩ | |
| | | | | | | | ስርዓቶችና ቁሶች | |
| 2 | አባ ወልደ ሃና | ወ | 54 | ዳጋ | የእቃ ቤት ኃላፊ | 20/7/2002 | » » » » » » » » » | በመቅረጸ ድምጽና በእጅ ማስታዎሻ |
| 3 | አባ ገብረሀይወት | ወ | 41 | ዳጋ | የእቃ ቤት ጠባቂ | 20/7/2002 | » » » » » » » » » | በመቅረጸ ድምጽና በእጅ ማስታዎሻ |
| 4 | አባ ወልደ ሚካኤል | ወ | 51 | ዳጋ | አበምኔት | 22/7/2002 | » » » » » » » » » | በቪዲዮና በእጅ ማስታዎሻ |
| 5 | አባ ተክለ ዮሐንስ | ወ | 38 | ዳጋ | ረድ | 7/8/2003 | » » » » » » » » » | በመቅረጸ ድምጽና በእጅ ማስታዎሻ |
| 6 | አባ ገብርኤል | ወ | 42 | ዳጋ | ረድ | 8/8/2003 | » » » » » » » » » | በመቅረጸ ድምጽና በእጅ ማስታዎሻ |
| 7 | አባ ሀኃየለ ማርያም | ወ | 46 | ዳጋ | አፈ. መምህር | 23/7/2002 | » » » » » » » » » | በቪዲዮና በእጅ ማስታዎሻ |
| 8 | አባ ወልደ እስጢፋኖስ | ወ | 35 | ዳጋ | እንል መጋቢ | 24/7/2002 | » » » » » » » » » | በቪዲዮና በእጅ ማስታዎሻ |
| | | | | | | | | |

## ለ. ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | እድሜ | አድራሻ | የሥራ ድርሻ | መረጃ የሰጡበት ቀን | የሰጡት መረጃ አይነት | መረጃ የሰጡበት ዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አባ ገብረመድህን | ወ | 27 | ዳጋ | ረድ | 25/7/2002 | ስለገዳሙ ተረኮች ስለገዳሙ ቅድስና | በእጅ ማስታዎሻ |
| | | | | | | | ገዳሙን ስምን እንደሚወዱት | |
| | | | | | | | ስለስውሩ መድኃኒዓለም ስለአቃቢ ሰዓት | በእጅ ማስታዎሻ |
| 2 | አባ ኪሮስ | ወ | 29 | ዳጋ | ረደ | 25/7/2002 | ስለጻድቃን ማረፊያ ስለስውሩ መድኃኒ□ □ □ | በእጅ ማስታዎሻ |
| 3 | አባ ሀይለራጉኤል | ወ | 31 | ዳጋ | እንል መጋቢ | 9/8/2003 | ስለጸሎተ ማዕድ | |
| | | | | | | | ስለቅድመ □ ዳሙ ተረኮች | በእጅ ማስታዎሻ |
| 4 | አባ ተክለሀይማኖት | ወ | 49 | ዳጋ | ረድ | 25/7/2002 | ከገዳሙ ስላገኙት ጥቅም | በእጅ ማስታዎሻ |
| 5 | አባ ወልደ ጊዮርጊስ | ወ | 33 | ዳጋ | ረደ | 9/8/2003 | | |

3.ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በመጀመሪያ ስምዎትን፣ የተውልድ ስፍራዎትን እና እድሜዎትን ቢገልጹልኝ? በገዳሙ ውስጥ ያለዎት የስራ ድርሻ፣ በዚህ ገዳም ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደኖሩ ቢነግሩኝ?
2. ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም በማን፣ መቼና እንዴት ተመሰረተ?
3. የገዳሙ መስራች እግዚአብሔር ምን አመልክቷቸው ነው ይህንን ገዳም ሊመሰርቱ የቻሉት?
4. ገዳሙ በሐይቅ የተከበበ እንደመሆኑ መጠን የገዳሙ መስራች አባ ሂሩተ አምላክ ወደዚህ ደሴት በምን ተሻግረው ሊገቡ ቻሉ?
5. ይህ ገዳም ከመመስረቱ በፊት ገዳሙ ምን ነበረበት?
6. ገዳመ እስጢፋኖስ ከመመስረቱ በፊት በማርያም ስም የታነጸ ቤተክርስቲያን እንደነበረበት ሰምቻለሁ። ስለዚህ ታሪክ የምታውቁትን ብታጫውቱኝ?
7. የማርያምን ቤተክርስቲያን ያሳነጸው ሰው ማን ነው? እንዴትና መቼ ሊመሰርተው ቻለ? ወደደሴቷ በምን እንደተሻገረ ይታወቃል?
8. በመጨረሻ የማርያም ታቦት በዚህች ደሴት ለምን ያህል ጊዜ ኖረች? በኋላስ ወደየት ሄደች? የሄደችበት ምክንያት ምንድን ነው? የታቦት ማርያም ከዚህ ደሴት መነሳት ከደቂቀ እጢፋኖስ ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን? የቀድሞዎቹ ካህናት የት ሄዱ?
9. የማርያም ቤተክርስቲያን ከዚህ ደሴት ተነስቶ ደቅ ወደተሰኘው ደሴት በመሄድ ሲሰራ ማን እንዳመጣቸው ሳይታወቅ ቋሚ እንጨቶች ተገኝተዋል ይባላል። እስኪ ስለዚህ ተዓምር ይንገሩኝ?
10. የገዳሙ መስራች አባ ሂሩተ አምላክ ይህንን ገዳም በማን ዘመነ መንግስት ነው የመሰረቱት የሚባለው? በወቅቱ ከነበረው ንጉስ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል? የአካባቢው ህብረተሰብ አቀባበል ምን ይመስል ነበር?
11. የገዳሙ መስራች ምን ነበሩ? የቤተክህነት ትምህርት ነበራቸው? ከነበራቸው እስከምን ተምረዋል ይባላል? የት ተማሩ ይባላል? ማን ነው ያመነኮሳቸው? በወቅቱ የስንት አመት መነኩሴ ነበሩ?\
12. የገዳሙ መስራች የታየኝ በሚል የጻፉት/ሀገርን፣ መንፈሳዊነትን፣ ምናኔን በሚመለከት/ ነገር አለ ወይ? ወይም ደግሞ እሳቸው የተናገሩት የሚባል ነገር ይኖራል? ከዚህ ጋር በያያዘ መነኩሳት በቃል የሚያስተላልፉት ነገር ካለ ቢገልጹልኝ?

13. መስራቹ ገዳሙን ከመሰረቱ በኋላ በገዳሙ ውስጥ ለሚኖሩ መነኮሳት ያስተላለፉት ትምህርት ወይም ስርዓት ካለ ቢገልጹልኝ? የተናገሩት ወይም የጻፉት ነገር ካለ ለምን ይህንን እንዳሉ የሚታወቅ ነገር አለ?
14. መስራቹ በገዳሙ ውስጥ ካስቀመጡት ስርዓት/ህግ/ ውጭ በተጨማሪነት የታከሉ ጉዳዮች አሉ? ወይስ የቀደመውን ህግና ስርዓት ተከትሎ ነው እየሄደ ያለው?
15. የተጨመረ ህግና ስርዓት ካለ ምን ተጨመረ? በማን ተጨመረ? መቼ ተጨመረ? ለምን ተጨመረ? እንዴት ተጨመረ?
16. በገዳሙ መስራች በአባ ሂሩተ አምላክ ዘመን የተከናዎኑ ጎላ ጎላ ያሉ ክንውኖች ምን ምን እንደነበሩ ቢገልጹልኝ? ስለዚህ ገዳም ሲያስቡ ቀድሞ የሚታወስዎ ጉዳይ ምንድን ነው?
17. በመጨረሻ መስራቹ በማን ዘመነ መንግስት በስንት አመታቸው አረፉ? የትና እንዴት አረፉ? ምን ነበር ያመማቸው? በህመማቸውና በእረፍታቸው ጊዜ የተከሰተ ተአምር አለ? ካለ ተዓምሩን ቢያብራሩልኝ?
18. በህመማቸው ጊዜ እንደሌሎቹ ጻድቃን እግዚአብሔር የገባላቸው ቃል ኪዳን አለ ወይ? ካለ ምን የሚል ቃል ኪዳን ተገባላቸው?
19. ገዳሙ የተመሰረተው በየትኛው እስጢፋኖስ ስም ነው?
20. በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ሲሳደዱ የነበሩ የእስጢፋኖስ ቤተሰቦች ደቅ ደሴት የኖሩ ነበር ይባላል። ስለዚህ ጉዳይ የምታውቁት ነገር ካለ ቢገልጹልኝ?
21. ደቅ ማለት ምን ማለት ነው? ደቂቀ ከሚለው ቃል ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን?
22. የቅኔ ትምህርት የተጀመረው ደቅ ነው ይባላል። እስኪ ስለዚህ ታሪክ ያጫውቱኝ?
23. ደቅ እና ዳጋ ያላቸው መንፈሳዊ ትስስር ምንድን ነው?
24. ዳጋ ማለት ምን ማለት ነው? ስያሜውን የሰጠው ማን ነው? ስያሜው የተሰጠው መቼ ነው? የስያሜው ተምሳሌታዊ ፍች ከላው ምን የሚል ነው?
25. መስራቹ ከተገባላቸው ቃል ኪዳን ጋር ተያይዞ በስማቸው ታቦት ተቀርጾላቸዋል ወይ? መልክ ገድል ተጽፎላቸዋል ወይ? ዜማ ተደርሶላቸዋል ወይ? ቅዳሴ ማህሌት ይደረግላቸዋል? የልደትና የእረፍት ታሪካቸውን መሰረት በማድረግ በስማቸው ዝክር/ማበር/ ይደረጋል?

26. ሂሩት አምላክ የሚለው ስም የተለየ ስም ነው። ለመሆኑ ምን ማለት ነው? ለምን ሂሩት አምለክ እንደተባሉ የሚታወቅ ነገር አለ? በእግዚአብሔር የተመረጡ ስለመሆናቸው በገዳሙ ውስጥ ይህንን የሚያሳይ ነገር አለ?

27. አባ ሂሩተ አምላክ የት ነው የተወለዱት? ከውጭ የመጡ ናቸው ወይስ ኢትዮጵያዊ አባት ናቸው?

28. አፄ ዘርዐ ያዕቆብ አባ እስጢፋኖስንና ተከታዮቹን ሲያሳድዷቸው ጣና ሐይቅ ካሉት ገዳማት በአንዱ ይኖሩ እንደነበር ይነገራል። በየትኛው ገዳም ይኖሩ እንደነበር የሚታወቅ ነገር አለ? የእስጢፋኖስ ተከታዮች በዚህ ገዳም ይኖሩ ነበር እንዴ?

29. በገዳሙ ውስጥ እለት እለት ከሚከወኑ ስርዓቶች ከቀድሞዎቹ የተለዩ ናቸው ወይ? ምን ምን አዳዲስ ስርዓቶች ተጨመሩባቸው? የትኞስ የተቀነሱ ናቸው? ለተጨመሩትም ሆነ ለአዳዲሶቹ የሚጠቀሱ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

30. በዚህ ገዳም  የሚኖሩ ገዳማዊያን ስለዚህ ገዳም ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? በዚህ ገዳም በረከት እናገኝበታለን ብለው ያምናሉ? እርስዎ በዚህ ገዳም ለምን ያህል ጊዜ ኖሩ? ምን ዓይነት መንፈሳዊ በረከት አግኝቸበታለሁ ይላሉ?

31. የዚህ ገዳም ቅዱስ በረከት ለአካባቢው ማህበረሰብ ያበረከተው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? በምሳሌ ሊያብራሩልኝ ይችላሉ? ወይም ደግሞ የደረሰ መቅሰፍት አለ? መቼ? ምን አይነት መቅሰፍት እንደሆነ ቢያብራሩልኝ?

32. የገዳሙ የልማት እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? ወደፊት ምን ለማድረግ የታቀደ ነገር አለ? የአካባቢው ማህበረሰብ ወይም ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ልጆች የገዳሙን የልማት እንቅስቃሴ ለመደገፍ ምን የሚያደርጉት ጥረት አለ?

33. በዚህ ገዳም ውስጥ ምን ምን ቁሳዊ ባህሎች አሉ? በዚህ ገዳም ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ሲጠበቁ እንደኖሩ ሊገልጹልኝ ይችላሉ? እነዚህ ቅርሶች እስካሁን ድረስ የገጠማቸው ችግር ነበር? የገጠማቸው ችግር ካለ ቢያብራሩልኝ?

34. ገዳሙ እነዚህን ቅርሶች ከየት ከየት ነው የሰበሰባቸው? ቅርሶቹ የተሰበሰቡት በስጦታ ነው ወይስ ሌላ መንገድ ነበረው? ገዳሙ በአሁኑ ሰዓት ቅርሶችን የማሰባሰብ አላማ አለው ውይ? በዚህኛው ዘመን ቅርሶችን እየሰበሰበ ከሆነ የአሁኖቹ ቅርሶች ካለፉት ዘመናት ቅርሶች በምን ይለያሉ በምንስ ይመሳሰላሉ?

35. በዚህ ገዳም ከሚገኙት ቅርሶች መካከል የነገስታት አጽሞች እንደሚገኙ ተመልከቻለሁ። ገዳሙ አፅሞቹን ለምን ዓላማ ነው የሚጠብቀው? ነገስታቱ

አጽማቸው በዚህ ገዳም እንዲያርፍ የቀደመ ፍላጎት ነበራቸው? ካላቸው ፍላጎታቸውን እንዴት አሳወቁ? ፍላጎት ካላቸው ለምንድን ነው በዚህ ገዳም ውስጥ ማረፍ የፈለጉት? እነዚህ አጽሞች እዚህ ላለው ገዳማዊ ህይወት ምን አይነት ጠቀሜታ ይሰጣሉ ይላሉ? ከዚህ ሌላ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ አለ? አጽምን እንደቅርስ የመያዝ ልማድ ሀይማኖታዊ መነሻ አለው? አጽሞች ወደዚህ ገዳም እንዴት እንደመጡ የሚታወቅ ነገር ካለ ቢገልጹልኝ? ገዳሙ የነገስታቱን የወግ እቃና የጦር መሳሪያ እንደሀይማኖታዊ ቅርስ የሚጠብቃቸው ለምን ዓላማ ነው?

36. አፄ ሱስንዮስ የካቶሊክን እምነትን ተቀብለው እንደነበርና በዚህም ምክንያት በተፈጠረ ግጭት ብዙ ደም እንደፈሰሰ በታሪክ ድርሳናት ሰፍሮ እናገኛለን። ታዲያ ገዳሙ የእኚህን ንጉስ አጽም በክብር ጠብቆ ማቆየት የፈለገው ለምን ዓላማ ነው? ከነገስታት ስጦታዎችም የእኚህን ንጉስ ስጦታዎች ተመዝግቦ አላየሁም። ምክንያቱ ምንድን ነው?
37. ከአራቱ ነገስታት በተጨማሪ የሌሎች የ10 ነገስታትና የ9 ጳጳሳት አጽም በገዳሙ ውስጥ እንደሚገኝ ይታወቃል። የእነዚህ ጳጳሳትና ነገስታት ስም ማን ማን ይባላል? በመስታወት እንዳይቀመጡ የሆኑት ለምንድን ነው?
38. ዳጋ እስጢፋኖስ በአባ ሂሩተ አምላክ በገዳምነት ከመመስረቱ በፊት ደሴቱ የተቀደሰ ቦታ ነበር ማለት ይቻላል? ቅድስናው በምን ይገለጻል?
39. የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ራሱን የቻለ ስርዓት ይኖረዋል? ካለው ይህንን ስርዓት ማን አመጣው? እንዴት መጣ? አንድ ሰው ከገዳሙ ስርዓት ውጭ ቢሆን ምን ይደረጋል? የሚቀጣ ከሆነ ቅጣቱ መንፈሳዊ መነሻ አለው?
40. የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ስርዓት ሲባል ምኑ ነው ስርዓት የሚያስብለው? የገዳሙን ስርዓት ለአዲሱ ገዳማዊ እንዴት ነው የምታስተዋውቁት? ይህንን ስርዓት ማን ነው የሚነግረው?
41. ስለምንኩና ስርዓት እንዴት ትማራላችሁ? ስለገዳምና ገዳማዊ ህይወት ከአንዱ ወደሌላው እንዴት ነው የሚተላለፈው? መናኒያን በስርዓት እንዲኖሩ የተቀረጸ ስርዓተ ትምህርት አለ? ትምህርቱ ካለ መቼ፣ በማን፣ እንዴት፣ ነው የሚሰጠው?
42. በዚህ ገዳም ውስጥ ምን ያህል መነኮሳት አሉ በገዳሙ ውስጥ ባህታዊ መኖር ይፈቀድለታል?

43. ይህ ገዳም ባለው ቅድስና ወይም ባለው ስርዓት ሊሆን ይችላል ከሌሎች ገዳማት በምን በምን ይለያል? ይህ ለገዳማዊ ህይወታችሁ ምን አስተዋጽኦ አብርክቶላችኋል?

44. ያጠፋውን ለመውቀስና ወደትክክለኛው መስመር ለማምጣት የምትማማሩባቸው ትውፊቶች ይኖራሉ? እስኪ ከአንዱ ወደሌላው በቃል የሚተላለፉ ትውፊቶች ካሉ ይግለጹልኝ? ከገዳሙ ህግና ስርዓት ውጭ በመሆናቸው ምክንያት መቅስፍት የደረሰባቸው መነኮሳት ይኖራሉ? ካሉ ስለነዚህ መነኮሳት ቢያጫውቱኝ?

45. እግዚአብሔር በዚህ ገዳም ስላደረጋቸው ተዓምሮች ቢገልፁልኝ? የገዳሙ ተፈጥሯዊ ቅርጽ የትዕምርተ መስቀል፣ የኖህ መርከብና የመሶበ ወርቅ ቅርጽ አለው ይባላል። በርግጥ ይህ አባባል ትክክል ነው ወይ? ትክክል ከሆነ እነዚህ ቅርጾች ተምሳሌታዊ ፍቻቸው ምንድን ነው? የእነዚህ ቅርጾች ሀይማኖታዊ አንድምታቸው ከገዳማዊ ህይወታችሁ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ምን ይመስላል?

46. አባ ሂሩተ አምላክ በጣና ሐይቅ ላይ የተጓዙባቸው ሁለቱ ድንጋዮች ለዚህ ገዳማዊ ህይወት ምን ፋይዳ አላቸው ይላሉ? ድንጋይ ሰው ጭኖ በውሃ ላይ ሲንሳፈፍ አይተን ስለማናውቅ ይህ ጉዳይ በትክክል ስለመፈጸሙ ያምኑበታል? እነዚህን ድንጋዮች እለት እለት ሲመለከቱ ምን ይሰማዎታል? ለመንፈሳዊ ህይወትዎ ምን ጥቅም አላቸው ይላሉ? እነዚህ ድንጋዮች ከዚያ ጊዜ በኋላ ያበረከቱት ሌላ ተዓምር ይኖር ይሆን? ለጉብኝትም ይሁን ለሱባኤ የሚመጡ ሰዎች ስለእነዚህ ድንጋዮች ያላቸው አስተያየት ምንድን ነው? ድንጋዮችን ሲያዩና ስለሰሩት ተዓምር ሲነገራቸው ምን ያደርጋሉ?/ይሳለሚቸዋል?ይስሚቸዋል? ዳስሰው ሰውነታቸውን ያሻሹባቸዋል?/

47. እነዚህ ድንጋዮች በጣና ሐይቅ ላይ ታቦተ ቅዱስ እስጢፋኖስንና አባ ሂሩተ አምላክን ጭነው በመምጣት እዚህ ደሴት አድርሰዋቸዋል። በዚህ ተዓምር ጎልቶ የሚወጣው የአባ ሂሩተ አምልክ ወይስ የእስጢፋኖስ ገድል ነው? ለምን? ከእነዚህ ድንጋዮች ጋር በተያያዘ ለአባ ሂሩተ አምላክ የተገባላቸው ቃል ኪዳን ይኖር ይሆን?/ድንጋዩን የተመለከተ፣ የነካ ፣ የጸለየ እንዲህ ይደረግለታል ወይም እንዲህ ይሆናል የሚል።/

48. በዚህ ገዳም ውስጥ አባ ሂሩተ አምላክ ለመጀመሪያ ጊዜ ያረፉበት ቦታ አቃቢ ሰዓት እየተባለ ይጠራል። አቃቢ ሰዓት ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ቦታ ለማህበረ መነኮሳቱ ምን ጥቅም ይሰጣል? የጻድቃን ማረፊያ የተባለውስ ቦታ ስያሜውን ያገኘው እንዴት ነው? በዚህ ቦታ ላይ ምን ይደረግባታል? በዚህ ገዳም ውስጥ ስውሩ

መድሀኔአለም የሚባል ቦታ እንዳለ ስመቻለሁ። ይህንን ስያሜ ያገኘው እንዴት ነው? በዚህ ቦታ ላይ የሚፈጸም አምልኳዊ ስርዓት ይኖር ይሆን?

49. ሴቶችና ሴት እንስሳት ጭምር ወደዚህ ገዳም እንዳይገቡ የሚከለከለው ለምንድን ነው? ገዳሙ የእንስሳት እርባታ የለውም? ካለው ሴት አንስሳትን ምን ያደርጋቸዋል?

50. ይህ ገዳም በየሳምንቱ እሁድ ከሰዓት በኋላ «የገነት ነፋስ» ይነፍስበታል ይባላል። የገነት ነፋስ ሲባል ከገነት ወደምድር የሚነፍስ ማለት ነው? ወይስ የገነት ነፋስ አምሳያ ማለት ነው? የገነት ነፋስ በሚነፍስበት ጊዜ ምን ተከስቶ ያውቃል? የእሁድ ከሰዓት በኋላው ነፋስ ከሌሎች ቀናት በምን ይለያል? የገነት የተባለው ለምንድን ነው?

51. ገዳሙ ከተቋቋመ በኋላ የተቋረጠበት ጊዜ ነበር? መቼ? ለምን? በኋላስ እንዴት ሊጠናከር ቻለ? የአፄ ስስንዮስን አጽም እዚህ ገዳም ለማሳረፍ ይዘው ሲመጡ ገዳማዊያን በመቃዎማቸው ገዳማዊያኑ ሲሰደዱ የገዳሙ ገዳማዊ ህይወት እንደተቋረጠ ይነገራል። ይህ ምን ያህል እውነት ነው?

52. በዚህ ገዳም ሁለት የደወል አይነቶች አሉ። እስኪ ስለእንጨት ደወሉ ተግባር ይግለጹልኝ?

53. ገዳሙ በጥብቅ የሚያከብረው የጸሎተ ማዕድ ስርዓት ከመነሻ እስከመድረሻ የሚከወነው ስርዓት ምን እንደሚመስል ይግለጹልኝ? ይህ ህብስትና ጽዋ ከሌላው የተለየ ነው ይባላል። ለምንድን ነው? ሀይማኖታዊ መነሻው ምንድን ነው? ምን ጥቅም አለው ተብሎ ይታሰባል?

54. ተግባር ቤት ስለሚባለው ቤትና በዚህ ቤት ስለሚፈጸመው ስርዓት በዝርዝር ቢገልጹልኝ? የተግባር ቤት ህብስትና ጽዋ ልዩ ልዩ ደዌ ያለባቸውን ይፈውሳል ይባላል። ስለዚህ ጉዳይ ማስረጃዎችን እየጠቀሱ ሊገልጹልኝ ይችላሉ? በተግባር ቤት የሚቆረሰው ህብስት የአቆራረሱ ተምሳሌታዊ ፍች ምንድን ነው?

55. ተግባር ቤትና የጸሎተ ማዕድ ስርዓት አንድነታቸውና ልዩነታቸው ምንድን ነው?

56. በገዳሙ ውስጥ ብዙ ጊዜ ጽጥታ ይበዛል። የገዳሙ ነዋሪዎች እጅግ በጣም ጥልቅ በሆነ ጸጥታ የሚኖሩት ለምንድን ነው?

57. በገዳም ውስጥ በአንድነት መኖር ከመንፈሳዊና ከስጋዊ ጥቅም አኳያ እንዴት ይገለጻል? አንድነት ማለት ምን ማለት ነው?

58. አንድ መነኩሴ ምን አይነት ወንጀል ሲፈጽም ነው ሙሉ በሙሉ ከገዳሙ ሊባረር የሚችለው? መለስተኛ የሚባሉ ቅጣቶችስ ምንድን ናቸው? ለምን አይነት ጥፋት የሚፈረዱ ናቸው?

59. በገዳም ውስጥ የሚያስተዳድሩ ሹማምንት የትና እንዴት ነው የሚመረጡት?

60. በገዳሙ ውስጥ የግል ንብረት ማፍራት ይቻላል? ማፍራት የማይፈቀድ ከሆነ የግል ንብረት አፍርቶ የተገኘ ምን ይደረጋል? ያፈራው ንብረት ቢኖር በንብረቱ ላይ ምን ይወሰንበታል?

ይህ የማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት በማሟያነት የቀረበው ጥናት የእኔ መሆኑንና ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎች በሙሉ በተገቢው ሁኔታ የገለጽኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ።

ስም ሞገስ ጀንበር

ፊርማ ---------------

ቀን ሰኔ 15/ 2003 ዓ.ም